# ወጣትና ልማት በኢትዮጵያ



አርታዒ

ዘሪሁን መሐመድ

# ወጣትና ልማት በኢትዮጵያ


**አርታዒ**

**ዘሪሁን መሐመድ**



ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

© 2007 ዓ.ም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

አዲስ አበባ

ISBN: 978-99944-50-54-1

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል፡ fss@ethionet.et
ድሕረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

ይህ መጽሐፍ የታተመው በሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራም (Civil Society Support Programme-CSSP) የገንዘብ ድጋፍ ነው።

በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣ የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን የሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራምን አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል።

## ማውጫ

ገጽ

መቅድም ........................................................................................ v

መግቢያ ........................................................................................vii

ወጣትነት ከሕግ አንፃር በኢትዮጵያ..........................................................1

አበራ ደገፋ

የወጣቶች የሥራ ፖሊሲዎች በኢትዮጵያ...............................................21

ማርታ ክብሩ

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የህፃናት ጥበቃ፡- የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት ግንዛቤ በኢትዮጵያ ...............................................................51

አሉላ ፓንክረስት

የሥራ ፍልሠትና የሰዎች ዝውውር በኢትዮጵያ፡- ወደ ደቡብ አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ የሚደረጉ የሥራ ፍልሠቶች ምልከታ ..................................105

አስናቀ ከፋለ እና ዘሪሁን መሐመድ

ወጣትና ስፖርት በኢትዮጵያ ...........................................................147

ገነነ መኩሪያ

የአደገኛ ዕፅ ተጠቃሚነት እና ባህሪያዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የጤና ጠንቆቹ........................................................................................169

ጌጤ ፀጋዬ

ወጣቶችና ጫት በኢትዮጵያ.............................................................189

ግርማ ነጋሽ

### ስለፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (Forum for Social Studies) ለትርፍ ያልተቋቋመ በአገራዊ የልማት ጉዳዮች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ሕዝባዊ ውይይቶችን የሚያካሂድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። ድርጅቱ በተወሠኑ የዩኒቨርሲቲ ምሁራንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በሚሠሩ አገር ወዳድ ግለሠቦች በ1990 ዓ.ም የተመሠረተ ነው። የድርጅቱ እንቅስቃሴም በመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች፤ አስፈፃሚዎችና፣ የሲቪል ማኅበረሠቡና በአጠቃላይ በሕብረተሠቡ መካከል በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ጤናማ የውይይት ባህል መዳበር ግልጽና አሳታፊ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገውን ጥረትን ለማጎልበት ያስችላል በሚል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው።

ድርጅቱ ከምስረታው ጀምሮ በተለያዩ የልማት መስኮች አያሌ የፖሊሲ ጥናቶችንና ምርምሮችን ያካሄደ ሲሆን ውጤቶቹንም ለመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈፃሚዎች፣ የሲቪል ማኅበራት፣ የጥናትና ምርምር ተቋማትና እንዲሁም ለሠፊው ሕብረተሠብ አድርሷል። የተለያዩ የፖሊሲ ውይይት መድረኮችን (ወርክሾፕ፣ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች፣ የፓናል ውይይቶች፣ ሴሚናሮች) በማዘጋጀት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተለያዩ ወቅታዊ በሆኑ አገራዊ የልማት አጀንዳዎች ላይ ግልጽና ቀና ውይይትና ክርክር (debates) እንዲያደርጉ ያደርጋል። በተለይ በተመረጡ መሪ ርዕሶች ላይ የሚደረጉት የሕዝባዊ የውይይት መድረኮች ድርጅቱ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ተቀራርበው እንዲነጋገሩና ሁኔታዎች ከተለያዩ ጎኖች (perspectives) እንዲጤኑ የሚያደርግበት አንዱ ዋናው የሥራ መስኩ ነው። ለዚህም *የጾታ ዕኩልነትና ልማት*፣ *ዕውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገር*፣ *ባሕልና ልማት*፤ *የአየር ለውጥና የዘላቂ ልማት ትስስር በኢትዮጵያ* በሚሉት ርዕሶች የተካሄዱት ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች የሚጠቀሱ ናቸው። ድርጅቱ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የሕዝባዊ ውይይት ውጤቶቹን በማሳተም ለሕብረተሠቡ እንዲደርስ ያደርጋል።

ይህ ‹‹***ወጣትና ልማት በኢትዮጵያ***›› የተሠኘው መጽሐፍ የድርጅቱ የሥራ ባህል ውጤት ሲሆን በርዕሱ ለሁለት ዓመታት የዘለቁ 11 የውይይት መድረኮች ተካሂደዋል። በእነዚህ መድረኮች ላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች በውይይቶቹ ዳብረው፣ ተስተካክለውና አርትዖት ተደርጎባቸው እነሆ ለአንባቢያን ቀርበዋል።

## መቅድም

**ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** በ1983 ዓ.ም በአገራችን የተካሄደውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ በአገሪቱ ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በ1990 ዓ.ም የተቋቋመ መንግሥታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ከመነሻው ሲነሳ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ፣ ግልጽና ቀና ምክክር፣ ውይይትና ክርክር የምንመኛትንና የምንጓጓላትን በዕድገት የዳበረች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ ዲሞክራሲ የሠፈነባትና የዜጎች ዕኩልነት የተከበረባት አገር ለመገንባት ያስችላል የሚል ዕሳቤ አንግቦ ነው።

በዚህ መሠረት በተለያዩ አገራዊ ልማታዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት ምርምር በማካሄድ፣ የፖሊሲ ግምገማና አማራጭ በመስጠት፣ የሕዝባዊ ውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈፃሚ የመንግሥት አካላት፣ ምሁራንና ተመራማሪዎች፣ የሲቪል ማኅበራትና ህብረተሠቡ በጥናታዊ መረጃ የተደገፉ ውይይቶች እንዲያካሂዱና አማራጮችን እንዲያቀርቡ ሲያደርግ ቆይቷል። ቀደም ባሉት ዓመታት በከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲና አፈጻጸም፣ በስርዓተ ጾታና ልማት መካከል ስላለው መስተጋብር፣ በአካባቢ ጥበቃና ልማት ላይ ያካሄዳቸው ጥናቶችና ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች ለአብነት ይጠቀሳሉ። በተለይ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ የነበረውና ለረጅም ዓመታት ዘልቆ የቆየው ዕውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ በሚል መሪ ርዕስ ስር በተለያዩ መንግሥታት ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ ቦታና ሚና የነበራቸውን ግለሠቦች የስራ ልምድ፣ ያለፉበትን ውጣ ውረድና በጊዜው የነበረውን ሁኔታ የቃኙበትና ለአሁኑ ትውልድ ልምዳቸውን ያካፈሉበት ሕዝባዊ የውይይት መድረክና ተያይዞ ለንባብ የበቃው መጽሐፍ ከድርጅቱ የቅርብ ጊዜ ሥራዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

ከውይይት መድረኮቹ በተጨማሪ የጥናትና ምርምር ውጤቶች እንዲሁም በየሕዝባዊ ውይይት መድረኮቹ የሚቀርቡትን ጥናታዊ ጽሁፎች በማዳበር በህትመት ለፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚዎች እንዲሁም ለህብረተሠቡ እንዲደርስ ሲያደርግ ቆይቷል፤ ወደፊትም አቅም በፈቀደ መጠን ማድረጉን ይቀጥላል።

**ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** ይህንን ባህል በመከተል ከነሀሴ 2004 ዓ.ም ጀምሮ ‹‹*ወጣትና ልማት በኢትዮጵያ*› በሚል መሪ ርዕስ ስር ለአንድ ዓመት ከ10 ወራት የዘለቀና በየሁለት ወሩ የሚዘጋጅ የህዝባዊ ውይይት መድረክ ሲያካሂድ ቆይቷል። በእነዚህ መድረኮች ላይ በተመረጡ ርዕሶች በመስኩ ባለሙያዎች የመወያያ ጥናታዊ ጽሁፎች እንዲቀርቡ በማድረግ በወጣቱ ህጋዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተግዳሮቶችና መልካም አጋጣሚዎች ላይ ውይይቶችና ክርክሮች ተካሂደዋል። ጉዳዮቹን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከተያያዝነው የዕድገት አቅጣጫና ከወጡት

ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አንጻር በመመልከት የፖሊሲ አማራጮችን ለማሳየትና ግብዓት ለመስጠት ተሞክሯል።

በእነዚህ መድረኮች ላይ ጥናታዊ ጽሁፎችን በማቅረብ፣ በአወያይነት፣ በተቺነት (discussants) እና በተሳታፊነት የተሳተፉትን ምሁራን፣ አግባብነት ያላቸው የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ ተመራማሪዎችና መላውን ተሳታፊ ላመሰግን እወዳለሁ። ይህ መድረክ እንዲካሄድ እንዲሁም በየመድረኮቹ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች በህትመት ለአንባቢያን እንዲደርሱ ለማድረግ እንድንችል የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልን የሲቪል ማኅበራት ድጋፍ ፕሮግራምም (Civil Society Support Programme- CSSP) ምስጋና ይድረሠው።

ምህረት አየነው

ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

መግቢያ

ወጣትነት በሕፃንነትና በጎልማሳነት መካከል የሚገኝ የሕይወት ዘመን ተብሎ ሊተረጎም ይችላል:: ነገር ግን የዚህ የዕድሜ ዘመን ወሰልና ጣራ እንደየአካባቢው፣ ባህሉ፣ የሚተረጎምበት ምክንያትና የተርጓሚው ማንነት ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል:: ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) የወጣትነትን የዕድሜ ክልል ከ15 እስከ 24 ዓመት አድርጎ ሲወስድ፤ የአውሮፓ ህብረትም በተለያዩ ፕሮግራሞቹ ይህንኑ ትርጓሜ ተቀብሎ ይሠራበታል:: በአ.ኤ.አ በ2006 የፀደቀው የአፍሪካ የወጣቶች ቻርተር (African Youth Charter) ወጣትነትን ከ15 እንከ 35 ዓመት ባለ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሲያስቀምጠው (AU, 2006)፤የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት ድርጅት (UNICEF) በበኩሉ በዓለም ዓቀፍ የሕፃናት መብት ስምምነት (The Convention on Rights of the Child) ሠነዱ ላይ ማንኛውም ሰው 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ 'ልጅ' (child) ተደርጎ ይቆጠራል ሲል ይገልፃል::

የተ.መ.ድ የወጣት ትርጓሜን መሠረት አድርገን ብንወስድ እንኳን በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የወጣቱ ብዛት ወደ አንድ ቢሊዮን እንደሚጠጋ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ይህም ማለት ከዓለም ህዝብ አንድ አምስተኛው ከ15-24 ዓመት ባለ የዕድሜ ክልል ይገኛል ማለት ነው:: ከአምስት አመት እስከ 14 ዓመት ያሉ ልጆች ሲጨመሩ ድርሻቸው የዓለም ህዝብ ወደ 38 በመቶ ይደርሳል::

በሌላ በኩል ከኢኮኖሚ መዳበር፣ ከአነስተኛ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የዜጎች ዕድሜ ጣሪያ (life expectancy) መርዘም ጋር ተያይዞ በልማት በአደጉ አገሮች ያለው የወጣት ብዛት በንጽጽር እያነሠ የመጣ ሲሆን፤ በተቃራኒው የዜጎች የዕድሜ መጠን አነስተኛ በሆነባቸው ታዳጊ አገሮች የወጣቱ አንጻራዊ ብዛት ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል:: ለዚህም ነው በአሁኑ ጊዜ ከዓለም ወጣቶች መካከል 85 ከመቶው በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የሚገኙት:: ይህ ቁጥር በ2015 ወደ 89.5 በመቶ እንደሚያድግ ተ.መ.ድ. ይገምታል::

በኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ 'ወጣትነት' ሠፋ ባለ ሁኔታ ተተርጉሞ ከ15 እስከ 29 ዓመት ዕድሜ ያለውን የህብረተሠብ ክፍል ያካትታል:: በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኘው ወጣት ከጠቅላላው የአገሪቱ ህዝብ 30 በመቶ ያህል ይሸፍናል:: ይህ ወጣት በአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሂደቶች ውስጥ ቁልፍ ሚና ሲጫወት ቆይቷል፤ በመጫወትም ላይ ይገኛል:: በልማት፣ የአገርን አንድነትና ዳር ድንበር በማስከበር፣ ሠላም ዲሞክራሲና ዕኩልነት ለማስፈን በተደረጉ የፖለቲካ ትግሎች፣ በስፖርትና ኪነ-ጥበብ ዘርፎች የአገር ስምና ባንዲራ በማስጠራት ያደረገው ተጋድሎ ከፍተኛ ነው:: የቅርብ ጊዜውን ለማንሳት ያህል በ1966 በተቀጣጠለው አብዮትና ተከትሎ በነበረው የፖለቲካ ትርምስ ወጣቱ ከፍተኛ ድርሻ የነበረው ሲሆን የዚያኑ

ያህል የችግሩ ሠለባ ነበር። ነገር ግን በሚገኝበት የዕድሜ ክልልና በሚደርስበት ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖዎች፣ ትኩረት መነፈግና መገለል ሳቢያ በተለያዩ የፖለቲካ ዘመኖች ልዩ ልዩ ችግሮችን ሲጋፈጥ ቆይቷል።

ዛሬም ወጣቱ በህብረተሠቡ ውስጥ በሚገኝበት ልዩ የዕድሜ ሁኔታ ሳቢያ ለልዩ ልዩ ችግሮች ተጋልጦ ይገኛል። በከተማም ሆነ በገጠርም የሚስተዋለው የወጣት ሥራ አጥነት፣ ስደት፣ የአደገኛ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ የኀዳና ተዳዳሪነት፣ በቂና ጥራት ያለው ትምህርት አለማግኘት፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ተጋላጭነት እና የእነዚህ ሁሉ መንስዔና ድምር ውጤት የሆነው የከፋ ድህነት ወጣቱን በመፈታተን ላይ ከሚገኙ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ። እነዚህ ችግሮች አንዳንዶቹ በራሳቸው መፈታት ያለባቸው ሲሆኑ፤ አብዛኛዎቹ ግን የሌሎች መሠረታዊ ችግሮች ውጤቶች ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌ ከፍተኛ የህዝብ ብዛት እድገት፣ የሥራ ገበያ መረጃ እጥረት፣ የሥራ ገበያው ፍላጎትና የሰው ኃይል ክህሎት አለመጣጣም፣ ለሥራ ገበያ ያልተመቻቸ የትምህርትና ስልጠና፣ የሥራ ልምድ ማነስና በሥራ ገበያው ውስጥ ወጣቶች (በተለይ ሴት ወጣቶች) የሚደርስባቸው መድልዎ (discrimination) ወጣቱን አንቆ ለያዘው ሥራ አጥነት በመሠረታዊ ምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

እነዚህን የወጣቱን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ለማቃለል መንግሥት የተለያዩ ፖሊሲዎች ቀርጿል፤ ፕሮግራሞችንም ነድፎ ተግብሯል፤ በመተግበር ላይም ይገኛል። ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲን ከማውጣት ጀምሮ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዝ ልማት መርኃ-ግብር፤ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፖሊሲ፣ የተቀናጀ የመኖሪያ ቤቶች ልማት መርኃ-ግብር፤ ከተማና የገጠር የወጣቶች የልማት ፓኬጆች ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የወጣቱን ችግሮች ለመፍታት የተወሠዱ እርምጃዎች ናቸው። እነዚህ እርምጃዎች በቅርብ ዓመታት በአገሪቱ ከተመዘገበው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ተዳምረው በተለይ የወጣቱ ዋና ችግር የሆነውን ሥራ አጥነትን በመቀነስ ረገድ ውጤት ያመጡ ቢሆንም፤ አሁንም የወጣቱ ፈርጀ-ብዙ ችግሮች በሚገባ ተዳስሰዋል፤ ተቀርፈዋል ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም።

በጥናታዊ ጽሁፎቹ እንደሚታየው የወጣቱ ዘርፈ-ብዙ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች ካሉባቸው ተግዳሮቶች መካከል ግልጽና ሊተገበር የሚችል (practical) ፖሊሲ አለመኖር (ለምሳሌ የጫት ምርትን፣ ንግድና አጠቃቀምን በተመለከተ)፤ ወይም ያለውን ፖሊሲና ስትራቴጂ ከሌሎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ጋር በሚገባ አጣጥሞ በተግባር ላይ አለመዋል (ለምሳሌ የስፖርት ፖሊሲንና የከተማ ልማት ፖሊሲን በተመለከተ) ወይም የሁለቱም ድምር ውጤት ሆነው ይገኛሉ። አሁንም በምሳሌ ለመግለጽ መንግሥት የወጣቱን "የማመዛዘን፣ የመፍጠርና የመመራመር ችሎታን ለማዳበር ችግር ፈቺ" የትምሕርት ፖሊሲ በማውጣትና በመተግበር የትምህርት ሽፋንን በሁሉም እርከኖች ለማስፋፋት ችሏል። ይህ በራሱ መልካም ሆኖ ሳለ፤ የትምህርት ሽፋን መስፋፋት ከትምህርት ጥራት ጋር እኩል

መራመድ ባለመቻሉና በተለይ ከሥራ ገበያው ፍላጎትና አቅም ጋር ባለመጣጣሙ የተነሳ የተማረ ሥራ አጥ መጠን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እጅግ እየጨመረ መምጣቱን ጥናቶች ያሳያሉ (Broussard and Tsegay, 2012; CRDA, 2010; እንዲሁም በዚህ መጽሐፍ የማርታን ጽሁፍ ይመልከቱ)።

በመሆኑም **ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** ከዚህ ቀደም እንደሚያደርገው ሁሉ በአገር ልማትና ግንባታ ሂደት ውስጥ ወጣቱ የሚኖረውን ተሳትፎ ለማሳደግና ከሚገኘው ውጤትም የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት በማሠብ "ወጣትና ልማት በኢትዮጵያ" በሚል ዓቢይ ርዕስ ስር ከሐምሌ 2004 ዓ.ም እስከ ግንቦት 2006 ዓ.ም ድረስ የዘለቀ 11 ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን አካሂዷል። በእነዚህ የውይይት መድረኮች ላይ በተለያዩ የተመረጡ ርዕሠ-ጉዳዮች ላይ በባለሙያዎች ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ከፍተኛ ውይይትና ክርክር ተካሂዶባቸዋል። በውይይቶቹ ላይም የመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚ መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶች፣ የወጣት ማኅበራት ተወካዮች፣ ምሁራን፣ ጋዜጠኞች እንዲሁም ከርዕሠ-ጉዳዮቹ ጋር አግባብ ካላቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመጡ ባለሙያዎች ተካፍለውባቸዋል።

በመድረኮቹ ላይ ከቀረቡት 11 ጥናታዊ ጽሁፎች መካከል ሠባቱ በውይይቶቹ ወቅት ከአወያዮች (discussants) እና ከተሳታፊዎች በተሠጡ ኃሳቦች ዳብረውና አርትዖት ተደርጎባቸው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካተዋል። ቀሪዎቹ አራቱ ጥናታዊ ጽሁፎች በልዩ ልዩ ምክንያቶች አልተካተቱም። ወደፊት ከሌሎች ተመሳሳይ ጥናቶች ጋር ተዳብለው እንዲወጡ ታስቧል።

በዚህ ጥንቅር ውስጥ ከተካተቱት ውስጥ የመጀመሪያው ጥናታዊ ጽሁፍ የ'ወጣትነት' ጽንሠ-ኃሳብንና ወጣቱን በተመለከተ የሚንፀባረቁትን የተለያዩ (አንዳንዴም የሚጣረሱ) አመለካከቶችን (perceptions) መነሻ በማድረግ፤ ሕገ-መንግሥቱንና ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲውን ጨምሮ የተለያዩ የአገሪቱ ሕጎች ለወጣትነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሠጧቸውን ትርጉሞችና የዕድሜ ክልሎች እንዲሁም እነዚህ መለያየቶች የሚኖራቸውን እንድምታ ይፈትሻል። ከዚህ በተጨማሪ ወጣቱ ሠብዕናው የተሟላ ዜጋ እንዲሆን ለማስቻል የወጣውን ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲ ዝርዝር ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፎችን ይመለከታል። በዚህም ፖሊሲውን በሚገባ ለማስፈጸም ከሌሎች ሕጎች ጋር በሚገባ የሚጣጣምበትን ሁኔታ ማመቻቸትና የማስፈጸሚያ ተቋማትን በሚገባ ማደራጀት የግድ መሆኑን ያትታል።

ሁለተኛውና የወጣቱን የሥራ ሁኔታ የሚዳስሰው ጥናታዊ ጽሑፍ የወጣት ሥራ አጥነት ሁኔታንና የተገኙ ለውጦችን በመመልከት፤ በተለይ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ መንግሥት ሥራ አጥነትን ለመቀነስ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የወሠዳቸው የፖሊሲ ለውጦች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ሥራ አጥነትን (በተለይም የወጣት ሥራ

አጥነትን) ለመቀነስ ጉልህ ሚና መጫወታቸውን ባይካድም ሥራ አጥነት አሁንም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረጃዎችን በማጣቀስ ያሳያል። የወጣት ሥራ አጥነት፣ ከአቅም በታች በሆነ ሥራ ላይ መሠማራትና ከፍተኛ ድርሻ ያለው የኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚገባውን ያህል ትኩረት አለማግኘት ዋና ዋና የወጣት ሥራ አጥነትን የሚመለከቱ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ያትታል።

ወጣቶችን (በተለይም ህፃናትንና ሴት ልጆችን) በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት ላይ የሚጥሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሆኑትን ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን የሚመከተው ሶስተኛው ጥናታዊ ጽሁፍ የድርጊቶቹን መጠንና ስፋት፣ የሚፈጸሙባቸውን ቁሳዊና ባህላዊ መሠረቶች፣ እንዲሁም ድርጊቶቹን ለማስወገድ የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች፣ ያስገኙትን ውጤትና ያሉባቸውን ተግዳሮቶች ይተነትናል። ጽሁፉ በተለይ የድርጊቶቹ ሠለባ የሆኑትን ህፃናትና ወጣቶች ለመታደግ ሲባል የወጡት ሕጎችና የሚወሰዱ እርምጃዎች ሌሎች ያልተፈለጉ አሉታዊ ውጤቶችን እንዳያስከትሉ መጠንቀቅ እንደሚገባ ያሠምራል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እጅግ እየተስፋፋ የመጣውንና የወጣቱን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥለውን እንዲሁም የአገር ገጽታን የሚያጎድፈውን ሕገ-ወጥ ፍልሠትና የሠዎች ዝውውርን የሚመለከተው አራተኛው ጽሁፍ ወደ ደቡብ አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ የሚደረገውን የሥራ ፍልሠት መነሻ፣ የፍልሠት ምክንያቶችን፣ የፈላሲዎችን ማንነትና ፍልሠቱ ያስከተላቸውን በጎና ክፉ ጎኖች ይመለከታል። በመደምደሚያውም ፍልሠትን እንደ መልካም የሥራ ዕድል 'በረከት'፤ ወይም ወጣቱን ከአገር የሚስኮበልል 'መርገምት' የመቁጠር ጽንፍ አመለካከቶች መቀየር እንዳለባቸውና አሁን ያለው ቅጥ ያጣ ሁኔታ በአስተማማኝ መረጃ ላይ በተመሠረተ፣ የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ፣ በዕቅድ በሚመራ፣ በተደራጀና በተቀናጀ የውጭ አገር የሥራ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊተካ እንደሚገባ ያሳስባል።

ወጣቱ ጤናው የተጠበቀ፣ አካሉ የደረጀና በመልካም ስነ-ምግባር የታነጸ አምራች ዜጋ እንዲሆን ስፖርት ከፍተኛ ሚና እንዳለው የሚያትተው አምስተኛው ጽሁፍ የወጣቱን በስፖርት የመሳተፍ ፍላጎት፣ ዝንባሌና አቅም ገድበዋል የሚላቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራል። ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል በተለይ ብሔራዊ የስፖርት ፖሊሲው ከሚገልጸው በተቃራኒ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና ወጣቶች በማናቸውም ጊዜ ያለገደብ በቀላሉ ሊጫወቱባቸው የሚችሉባቸው የመጫወቻ ሜዳዎች በአስፈሪ ሁኔታ በፍጥነት ለሌሎች ተግባራት መዋላቸው እንዲሁም በት/ቤቶች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አለመኖር ወጣቱ አጓጉል ስፍራ እንዲውል ከማድረጉ ባሻገር በአካልና በመንፈስ እንዲዳከም አድርጓል በማለት ይከራከራል።

ስድተኛው ጥናታዊ ጽሁፍ የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒቶችን መጠቀም የሚያከትለውን አደጋ የሚመለከት ሲሆን እነዚህ ዕፆች በብዛት ይገኙባቸዋል ተብለው በሚገመቱት በሻሸመኔና ሀዋሳ ከተሞች ካሉ የሁለተኛ ደረጃት/ቤቶች በተወሠዱ

ናሙና ተማሪዎች ላይ በተደረገ ጥናት ችግሩ በተማሪዎች ዘንድ በአሳሳቢ ደረጃ መኖሩን ያሳያል፡፡ አልኮል መጠጥ፣ ጫትና በአፍና በአፍንጫ የሚሳቡ እንደቤንዚል ያሉ ፈሳሾች (inhalants) በከፍተኛ ደረጃ የሚዘወተሩ አደንዛዥ ዕፆች (substances) መሆናቸውን ያሳያል፡፡

የመጨረሻው ጥናታዊ ፅሁፍ ከላይ ከተጠቀሠው የአደንዛዥ ዕፅ ጽሁፍ ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን የጫትን የጤና፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶችን መረጃዎች በማስደገፍ ይተነትናል፡፡ ነገር ግን ጽሁፉ የጫት ዘርፈ-ብዙ ጉዳቶች እንዳሉ ሆነው አሁን ባለው ሁኔታ ጫት በሚመረትባቸው ከፍተኛ የህዝብ ጥግግትና የእርሻ መሬት ጥበት ባለባቸው አካባቢዎች የጫት ምርትና ንግድ ዋና የኑሮ መሠረት እንደሆነ ከመስክ የተሠበሠበ መረጃን ዋቢ በማድረግ ያመለክታል፡፡ ጥናቱ በአሁኑ ጊዜ የጫትን ምርት፣ ግብይትና አጠቃቀምን የሚወስን ፖሊሲ አለመኖሩ ግምት ውስጥ ገብቶ፣ ጫትን በተመለከተ የሚደረጉ ውይይቶችና ክርክሮች (debates) ይህንን በጫት ምርትና ንግድ ህይወቱን የመሠረተውንና በአብዛኛው ወጣት የሆነውን የህብረተሠብ ክፍል ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይገባዋል በማለት በአጽንኦት ያሳስባል፡፡

እነዚህ ጥናታዊ ጽሑፎች ሙሉና ያበቃላቸው፤ እንዲሁም ያነሷቸውን ርዕሠ-ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ የዳሠሡ ናቸው የሚል እምነት የለንም፡፡ በተቃራኒው እጅግ ሠፊና ውስብስብ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተመራማሪዎች በጉዳዮቹ ላይ ሠፊ ቀጣይ ጥናቶችና ምርምሮች እንዲያካሂዱ፤ ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚዎችም ጉዳዮቹን በስፋትና በጥልቀት እንዲመለከቷቸው የሚያሳስቡ የመነሻ ኃሳቦችና የጥናት ውጤቶችን ለማቅረብ የታለሙ ናቸው፡፡

አርታዒው

## ዋቢ መፃህፍት


African Union (2006) *The African Youth Charter*. Adopted By the Seventh Ordinary Session of the Assembly, Held in Banjul, the Gambia, On 2nd July 2006.

Broussard, H. Nzinga and Tsegay Gebrekidan Tekleselassiez (2012) *Youth Unemployment: Ethiopia Country Study.* Working Paper 12/0592. International Growth Centre. London School of Economics and Political Science. London.

CRDA (2010) *Youth unemployment in Ethiopia Youth Unemployment in Ethiopia: The Case of 12 Spots In Four Selected Regions and Two City Administrations.* Addis Ababa May, 2010.

# ወጣትነት ከሕግ አንፃር በኢትዮጵያ

## አበራ ደገፋ

### 1. መግቢያ

በማንኛውም ህብረተሠብ ወጣቱ የአፍላ ጉልበት፣ የብሩህ አዕምሮና ዕምቅ ኃይል ባለቤት በመሆኑ ያለዚህ የህብረተሠብ ክፍል የነቃና የተደራጀ ተሳትፎ የሚታለሙት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታዎችና የልማት እንቅስቃሴዎች ግባቸውን ሊመቱ አይችሉም[1]:: ወጣቱ የዛሬው አገር ገንቢ ብቻ ሳይሆን የነገው የአገር ተረካቢም ጭምር በመሆኑ የአንድ አገር የወደፊት ዕጣ ፈንታም ከወጣቱ ዕድል ጋር የተቆራኘ ነው:: ስለሆነም ለወጣቱ ትኩረት የማይሠጥ ማንኛውም ሥርዓት የወደፊት ሕልውናው ለአደጋ የተጋለጠ ነው[2]:: ወጣቱ የህብረተሠብ አካል ከመሆኑ የተነሳ በወጣቱ ትኩረት መነፈግ የሚጎዳው እርሱ ብቻ ሳይሆን መላው ሕብረተሠብና ከዚያም አልፎ አገር ጭምር ነው::

በአንድ አገር ፈጣንና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኀበራዊ ዕድገት ለማምጣት የሁሉም የህብረተሠብ ክፍሎች ተሳትፎ አስፈላጊ ነው:: ቢሆንም እንደ ኢትዮጵያ ወጣቱ በቁጥር ከአጠቃላይ የአገሪቱ ህዝብ ከ30 በመቶ በላይ ወይም ከ24 ሚሊዮን በላይ በሆነበት አገር ወጣቱ በአገር ግንባታ ሂደት ላይ የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል[3]:: ወጣቱ በቁጥር ብቻ ሳይሆን ያለው ዕምቅ ኃይል ግዙፍ በመሆኑ ለአገር ዕድገት ሊጫወት የሚችለውን የጎላ ሚና ከግምት በማስገባት መንግሥትም ሆነ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለዚህ የህብረተሠብ ክፍል ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል::

ባለፉት ዘመናት በኢትዮጵያ ወጣቱ ጨቋኙን የፊውዳል ሥርዓት ገርስሶ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሥርዓት በቦታው ለመተካት ከ1950ቹ አጋማሽ ጀምሮ አኩሪ ፀረ-ጭቆና ተጋድሎ ከማድረጉም በላይ፤ በተለያዩ የልማት መስኮች በግምባር

---

[1] ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ማብራሪያ ማንዋል 1998::

[2] ይህንን አስመልክቶ በአንድ ወቅት የቀድሞው የ.ተ.መ.ድ ዋና ፀሐፊ ኮፊ አናን "a society that cuts off from its youth severs its lifeline" ብለው ነበር:: በደምሳሳው ሲተረጎም «ከወጣቱ ጋር የተቆራረጠ ህብረተሠብ የህልውናውን ገመድ ይቆርጣል» ልንለው እንችላለን::.

[3] የኢትዮጵያ የከተማ ወጣቶች የዕድገት ፓኬጅ 1998

ቀደምትነት ተሳታፊ በመሆን ጠንካራ የልማት አጋርና አምራች ኃይል መሆኑን አስመስክሯል፡፡ በመጨረሻም የፊውዳሉን አገዛዝና ሥርዓቱን ለመጣል በተደረገው መራራ ትግል ወጣቱ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውቷል[4]፡፡

የንጉሡ ዘውዳዊ አገዛዝ ተወግዶ አምባገነናዊው ወታደራዊው ደርግ በጠመንጃ አፈሙዝ ስልጣን ሲይዝ እልፍ አዕላፍ የኢትዮጵያ ወጣቶች ከመነሻው ወታደራዊውን መንግሥት በመቃወምና በመፋለም ለፍትህ፣ ለነጻነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በቁርጠኝነት የታገሉ የኢትዮጵያ ወጣቶች የደርግ አምባገነናዊ ሥርዓትን ከሥሩ መንግሎ ለመጣል በተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል በግምባር ቀደምትነት በመሠለፍና አስፈላጊውን መስዋዕትነት በመክፈል አምባገነናዊው የደርግ ሥርዓት እንዲወገድ ታሪካዊ ድርሻቸውን አበርክተዋል[5]፡፡ ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ ወጣት አገርን ከውጭ ወራሪዎች ለመከላከልና ሉዓላዊነቷን ለማስከበር በተደረጉት ጦርነቶች ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል የአገር መከታነቱን አስመስክሯል፡፡

በእርግጥ እዚህ ላይ ስለኢትዮጵያ ወጣት ሲወሳ ሊታወቅ የሚገባው አንድ ቁም ነገር የኃይለ ስላሴም ሆነ የደርግ አምባገነናዊ ሥርዓት የአገዛዛቸውንና የሥርዓቶቻቸውን ዕድሜ ለማራዘም የኢትዮጵያን ወጣቶች ለእኩይ ዓላማቸውና ኢ-ፍትሐዊ ለሆኑ ጦርነቶች እንዲማገዱ የማድረጋቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ወጣቱ የህብረተሠብ ክፍል እንደየሁኔታው ለበጎም ሆነ ለእኩይ ተግባር መሣሪያ ሆኖ ሊሰለፍ እንደሚችል አመላካች ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ግን የኢትዮጵያ ወጣቶች የተጫወቷቸው በጎ ጎኖች ሲመዘኑ በአገሪቱ ታሪክ የከፈሉት መስዋዕትነትና ያበረከቷቸው ገንቢ አስተዋፅዖዎች ምንጊዜም የሚረሱ ሳይሆኑ በአርአያነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ[6]፡፡

ወጣቱን በተመለከተ ሌላ ሊታወቅ የሚገባ ጉዳይ ከሚገኝበት የዕድሜ ሁኔታ የተነሳ ማለትም በአካልና በአዕምሮ እየዳበረ የሚሄድበት የሽግግር የሕይወት ምዕራፍ ላይ እንደመገኘቱ ከሁሉም የህብረተሠብ ክፍል በበለጠ ሁኔታ ለተለያዩ ማኅበራዊ፣

[4] Eyob Balcha, *Youth and Politics in post 1974 Ethiopia: Intergenerational Analysis*, (Unpublished Masters Thesis for the Degree of Arts in Development Studies), The Hague: Netherlands, 2009.

[5] Ibid. p. 3.

[6] «በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ፌዴራላዊ ሥርዓት ማዕቀፍ የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት» በፌዴሬሽን ምክር ቤት አስተባባሪነት በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ማኒስቴር ለስድስተኛው የብሔር፣ ብሔረሠቦችና ህዝቦች ቀን በዓል ለውይይት የተዘጋጀ፡፡ ሕዳር 2004 አዲስ አበባ፣ ገፅ 5፡፡

ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ተጋላጭ (vulnerable group) መሆኑ ነው:: ከዚሁ የተነሳ መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሌሎች የህብረተሠብ ክፍሎችና እንዲሁም ወጣቶች ራሳቸው የወጣቱን ለዘርፈ-ብዙ ችግሮች ተጋላጭ መሆንን በመረዳትና የችግሮቹን አድማስ በማወቅ አስፈላጊውን የጋራ የመፍትሔ እርምጃዎች መውሠድ ይጠበቅባቸዋል::

እነዚህም የመፍትሔ እርምጃዎች የሚገለጹት ፖሊሲ በመቅረፅ፣ ሕግና ተቋማትን በማደራጀትና ግልፅ የአፈፃፀም ሥርዓት በመዘርጋት ነው:: ከዚሁ አንፃር የዚህ ፅሑፍ ትኩረት በኢትዮጵያ በቁጥር ግዙፍ፣ ባለብሩህ አዕምሮ፣ ባለዕምቅ አምራች ኃይል፣ አገር ገንቢና ተረካቢ ከመሆን ጎን ለጎን ለተለያዩ ውስብስብና ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ተጋላጭ የሆነውን ወጣት አስመልክቶ በኢትዮጵያ ያለውን የወጣቶች ፖሊሲ፣ የሕግና የተቋማት ማዕቀፍ መዳሰስ ይሆናል:: ምክንያቱም ፖሊሲዎች ያለ ጠንካራ ሕጎችና ተቋማት ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም::

ፅሁፉ በተለይ በኢትዮጵያ ያለው የሕግና የተቋማት ማዕቀፍ ምን ያህል የተቀረፀውን ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚያስችል ይመረምራል:: በዚሁ አቅጣጫ ፅሁፉ በመጀመሪያ ሕገ-መንግሥቱን ጨምሮ በአገሪቱ እየተሠሩባቸው ያሉትን አግባብነት ያላቸው ሕጎችን ይዳስሳል:: ከዚያም የወጣውን ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ለማስፈፀም የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ወጣት-ተኮር ተቋማት መኖራቸውን፤ የነዚህንም ብቃት ለመፈተሽ ይሞክራል::

## 2. የወጣትነት ባሕሪያትና ስለ ወጣቱ ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች (Perceptions)

ኢትዮጵያን ጨምሮ በማንኛውም ህብረተሠብ ወጣቱ የመላው ህብረተሠብ ክፍሎች አካልና ነፀብራቅ ስለሆነ እንደ አንድ የተለየ ክፍል ከሚኖርበት ህብረተሠብ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም:: ከኃብት ክፍፍል፣ ከትምህርት፣ ከጾታ፣ ከኃይማኖት፣ ከብሔረሠብ ከማኅበራዊ አቋም አንፃር ስንመለከት ወጣቱ በራሱ የተለየ ክፍል ያለው ሣይሆን ያለበትን የህብረተሠብ የተለያየ ስብጥር ተጋርቶ የሚገኝ ነው:: በወል ሲታይ ወጣቱ ታዳጊና ለውጥ ፈላጊ የህብረተሠብ ክፍል (source of dynamism and agent of change) ሲሆን ከሌላው የህብረተሠብ ክፍል የሚለየው አንዱ መለያው በአንድ የተወሠነ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ መሆኑ ነው::

ከሚገኝበት የዕድሜ ሁኔታ የተነሳ ወጣቱ ሁሉንም ለማወቅ ጉጉ የመሆንና አንድን ኃሣብ ቶሎ የመቀበል ወይም የመተው፣ ቅብጥብጥ የመሆንና የማመፅ ባህርያት አሉት:: ከዚህም ባሻገር ወጣቱ ያመነበትን ተግባራዊ ከማድረግ ወደኋላ የማይል፣ ተፋላሚና የለውጥ ኃይል በመሆኑ ይህንኑ በመረዳት የተለያዩ ኃይሎች ወጣቱን ከጎናቸው ለማሠለፍ ይጥራሉ:: ወጣቱም በበኩሉ ልምድ ስለሚጎድለው በቀላሉ በተለያዩ ኃይሎች የመታለል ወይም ለተለያዩ ኃይሎች ተፅዕኖዎች የመጋለጥና የእነዚሁ ክፍሎች ዓላማ ማራመጃ የመሆን ዕድሉ የሰፋ ይሆናል:: ይህንን አስመልክቶ አንድ ጸሐፊ የሚከተለውን ብሏል:: “Youth are confronted with confusing and contradictory patterns of protection and pressure, with conflicting perceptions of their abilities and inadequacies, rendering their social presence inconsequential and their social power invisible[7]” በደምሳሳው ሲተረጎም «ህብረተሠቡ ወጣቱን አስመልክቶ በሚያንፀባርቀው የተምታታ አመለካከት የተነሳ ስለራሱና ችሎታዎቹ የሚኖረው ግምት የተዘበራረቀ ይሆንና ማህበራዊ ሚናውም የደበዘዘ ይሆናል» ማለቱ ነው::

ስለ ወጣቱና በህብረተሠቡ ውሰጥ ስላለው ሚና (youth-in-society continuum) የተለያዩ አመለካከቶች ይንፀባረቃሉ[8]:: በአንደኛው ፅንፍ ወጣቱን በጎልማሳ ህብረተሠብ የሚጠቃ (victims of adult society) አድርገው የሚመለከቱ ሲኖሩ፤ በሌላኛው ፅንፍ ደግሞ ወጣቱ ለጎልማሶች አስፈሪ እንደሆነ (threat to adult society) አድርገው የሚመለከቱ አሉ:: በመሃል ደግሞ ወጣቱን የጎልማሶች ተማሪ (learners of adult society) አድርገው የሚያቀርቡ አሉ[9]:: ወጣቱን የነገው ሰው ብቻ (people of tomorrow) አድርገውም የሚመለከቱም አሉ:: እነዚህ አመለካከቶች ወጣቱ በህብረተሠቡ ውስጥ ያለውን ሚና አስመልክቶ የተለያዩ አረዳዶች መኖራቸውን የሚጠቁሙ ቢሆኑም፤ የወጣቱን ገፅታ በመሳል ረገድ ሁሉም የወጣቱን ዕምቅ ችሎታና ለህብረተሠቡ ሊያደርግ የሚችለውን በጎ አስተዋፅዖ የሚሸሽጉ ናቸው[10]:: የእነዚህ የተዛቡ አመለካከቶች ጥቅል ውጤት ወጣቱን ህብረተሠቡ ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ገለልተኛ በማድረግ ህብረተሠቡም ሆነ ወጣቱ ሊገኙ ይችሉ የነበረውን የጋራ ጥቅም ማሳጣት ነው::

[7] Ruthanne Kurth-Schai, The Roles of Youth in Society: A Reconceptualization, *The Education Forum*, Vol. 52, No 2(1988) p. 116.

[8] Ibid. p. 114.

[9] Ibid. pp.114-116.

[10] Ibid. According to the writer, such misconception about the youth has been referred to as “underestimation fallacy” by Goodman. All these approaches are generally marginalizing the youth.

በማንኛውም ህብረተሠብ እንደየሁኔታው ወጣቱ በህብረተሠቡ ውስጥ ሊጫወት የሚችለው ሚና አሉታዊም አዎንታዊም ሊሆን ይችላል:: እንደየህብረተሠቡ የሥርዓት ሁኔታ በወጣቱ ጠንካራ ጎኖች በማተኮርና ይህንኑ በማጎልበት ወጣቱን በተገቢው መንገድ የሚጠቀሙ የመኖራቸውን ያክል፤ የወጣቱን ደካማ ጎኖች አግዝፎ በመመልከት ወጣቱን የማግለል ዝንባሌ የሚያሳዩ ሥርዓቶችም አሉ:: ወጣቱን እንደጥገኛ የመመልከት ሕጋዊ አንድምታ ወጣቱን እንደ መብት የለሽ ዕቃ ወይም ግዑዝ ነገር መመልከት፤ ሙሉ ሠው እንዳልሆነና ህብረተሠብን ሊለውጥ እንደማይችል ዕርዳታ ፈላጊ የህብረተሠብ ክፍል መቁጠር ነው:: ለወጣቱ ዕምቅ ችሎታ ዕውቅና በመንፈግ እንደጥገኛ የመቁጠር ዝንባሌዎች ውጤት የዚያን ህብረተሠብ መፃዒ ህልውና ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው[11]::

የኢትዮጵያ ወጣትም ከሌላው ዓለም የተለየ ሣይሆን ሁሉ-አቀፍ የሆነውን የወጣት ባሕሪያት የሚጋራ ነው:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲ በአቀራረቡ ወጣቱ ያለውን ብሩህ አዕምሮና ዕምቅ ኃይል ከግምት አስገብቶ፤ ወጣቱ በአገር ግንባታ ሊጫወት የሚችለውን በጎና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ዕውቅና የሰጠ ይመስላል[12]:: ወጣቱን አስመልክቶ በፖሊሲው የተንፀባረቀው አመለካከት ወጣቱን እንደ ከፍተኛ የአገር ሀብት የማየት በጎ ዕይታ ነው:: በሌላ ጎኑ ፖሊሲው ወጣቱ ለተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች ተጋላጭ መሆኑን ከግምት ያስገባ ነው[13]:: ከዚህም በመነሳት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 29 ዓመት የሆኑት ወጣቶች ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይገልፃል:: የፖሊሲው መውጣት ከፍተኛ ሥፍራ የሚሠጠው እርምጃ ቢሆንም ከዚሁ ጋር በተጓዳኝነት ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚያስችል ጠንካራና ውጤታማ የሕግና ተቋማዊ ማዕቀፍ ያስፈልጋል::

## 3. የወጣት ትርጉም በኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲና ሕጎች

### 3.1 ወጣትነት በኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲ

በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች አገሮች 'ወጣት' የሚለው ቃል አንድ ወጥ ትርጉም የለውም:: ለወጣት የሚሰጠው ትርጉም በሁሉም አገሮች ዕድሜን መሠረት ያደረገ

[11] Boulding, *Children's Rrights*, as quoted in Ibid. p.116.

[12] ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ማብራሪያ ማንዋል ገፅ 9

[13] Finn Yrjar Denstad, *Youth policy Manual: How to develop a national youth strategy*, Strasbourg: Council of Europe Publishing, 2009. p.17.

ቢሆንም የዕድሜውን ጣራና ወለል በተመለከተ ግን በአገሮች መካከል ልዩነቶች ይታያሉ:: ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት የወጣትነት የዕድሜ ክልል ከ15 እስከ 24 ዓመት ሲሆን በአፍሪካ ህብረት ከ15 እስከ 35 ዓመት ተደርጎ ተቀምጧል[14]::

በኢትዮጵያ የፌዴራል ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲ ዕድሜያቸው በ15 እና 29 መካከል ያለውን የህብረተሠብ ክፍል በሙሉ በወጣትነት ጎራ ይፈረጃል:: በፖሊሲው መሠረት ሠፋ ብሎ አንድ ላይ ተጠቃሎ ወጣት የተሠኘው የህብረተሠብ ጎራ የተወሠኑ ክፍሎች በሌሎች ሕጎች በሕፃንነት ጎራም ተፈርጀው ይታያሉ[15]:: ከዚሁ የብሔራዊ ፖሊሲው የወጣት ዕድሜ አወሳሰንና ስያሜ ጋር በተያያዘ የሚነሳው ዓቢይ የሕግ ጉዳይ በወጣቱ ጎራ ውስጥ የተካተቱት ሕፃናት ለፖሊሲው ዓላማ በወጣትነት የተፈረጁ ቢሆንም፣ በሌሎች ሕጎች በህጻንነታቸው የተነሳ ሊደረግላቸው የሚገባ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ አለ:: ይኸው አስፈላጊ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ በወጣት ማዕቀፍ ውስጥ እንዴት ተፈጻሚ እንደሚሆን በፖሊሲው በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም[16]:: በብሔራዊ የወጣት ፖሊሲው የወጣት ትርጓሜ መሠረት በህፃንነትና በወጣትነት መካከል በተወሰነ ደረጃ መደራረብ (overlapping) የተፈጠረ መሆኑን እናያለን::

በእርግጥ ከመነሻውም ቢሆን ከፖሊሲው አንፃር በወጣትነትና በሕፃንነት መካከል ድንበር መፍጠሩ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል[17]:: ምክንያቱም የወጣቱ የወደፊት ማንነት የሚወሠነው ከ15 ዓመት የዕድሜ ክልል በፊት በነበረው/በሚሆነው የወጣቱ ሁኔታ እንደሆነ ስለሚታወቅ ነው:: እንግዲህ የአንድን ወጣት የወደፊት የሕይወት አቅጣጫና ዕጣ የሚወስኑ ሁኔታዎች በፖሊሲው ከተወሠነው የዕድሜ ወለል በፊት የሚሆኑ ከሆነ የአጠቃላይ የወጣቱ መፃኢ ዕጣ ብሩህና ውጤታማ እንዲሆን እድሜያቸው ከ15 በታች ለሆኑት ሕፃናት ልዩ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ይሆናል:: ከዚሁ አንጻር እነዚህ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆነውና የወጣቱ ምንጭ የሆኑት ሕፃናት ወደ

[14] ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ማብራሪያ ማንዋል፣ ታህሳስ 1998 አዲስ አበባ:: African Youth Charter, 2006.

[15] ለምሳሌ በዓለም አቀፍ የሕፃናት ኮንቬንሽን አንቀፅ 1 መሠረት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት በሙሉ ሕፃን ይባላሉ::

[16] ሆኖም ከሕግ አንጻር ስንመለከተው በሕጻንነታቸው በዓለም አቀፍ የህፃናት ኮንቬንሽንና በሌሎች ሕጎች የተረጋገጠላቸው መብቶችና ጥበቃዎች ይከበሩላቸዋል::

[17] ከዚሁ የወጣት የዕድሜ አወሳሰን ችግር የተነሳ አገሮች የተለያዩ የዕድሜ ወለሎችና ጣሪያዎች ሲጠቀሙ ይታያሉ::

ወጣትነት ሲሸጋገሩ ለሚያደርጉት በጎ አስተዋፅኦ ስኬታማነት ንቁና ሁለንተናዊ ስብዕናው በሚገባ የታነፀ ታዳጊ ወጣት ለመቅረፅ የተለያዩ አካላትና የህብረተሠብ ክፍሎች ልዩ ድጋፍና ትኩረት ያስፈልጋል፡፡

## 3.2 ወጣትነት በኢትዮጵያ ሕጎች

አሁን ያሉትና ያለፉት የኢትዮጵያ ሕጎች ሲፈተሹ ወጣቱን ከሌሎች የህብረተሠብ ክፍሎች የምንለይበት የሕግ መመዘኛ አላስቀመጡም፡፡ ሁለቱ የኃይለ ስላሴ ህግጋተ-መንግስታት ወጣቱን አስመልክቶ በግልፅ ያስቀመጡት ነገር አልነበረም፡፡ በደርግ አገዛዝ የወጣው የ1980ው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ-መንግሥት ግን ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ወጣቱን የሚጠቅሱ ድንጋጌዎች ነበሩት፡፡ ለምሳሌ በአንቀፅ 19 እና በአንቀፅ 20 መንግሥትና ህብረተሠብ ዜጎች የአካል ማሠልጠኛ እንቅስቃሴንና ስፖርትን እንዲያዘወትሩ አስፈላጊው ድጋፍ በመንግሥት እንደሚሰጥና ህፃናት በሳይንሳዊ ኣስተሳሰብ ታንፀው፣ በስነ ምግባር፣ በአዕምሮና በአካል ጠንክረው የአገር ፍቅር ያላቸውና ለሶሻሊዝም የቆሙ ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ልዩ እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ተደንግጎ ነበር[18]፡፡

ዛሬም ባሉት የኢትዮጵያ ሕጎች ‘ወጣት’ የሚለው ፅንሠ-ኃሳብ ሕጋዊ ትርጉም የለውም፡፡ ሕገ-መንግሥቱን ጨምሮ እስከ አሁን በሥራ ላይ ያሉት የኢትዮጵያ ሕጎች ወጣትን እንደ አንድ የህብረተሠብ ክፍል ለይተው ሕጋዊ እውቅና አልሰጡትም፡፡ እነዚህ በብሔራዊ ፖሊሲው በአንድ ጎራ ‘ወጣት’ በመባል የተጠቃለሉት በአገሪቱ የተለያዩ ሕጎች በዕድሜያቸው ወለልና ጣራ ተለያይተው የተፈረጁ ሆነው፤ በሕጎቹ የሚደረጉላቸው ጥበቃዎችና ትኩረቶችም እንደዚያው ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ የፍትሓብሔር ሕግ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሠው እንደ ህፃን ይቆጠራል[19]፡፡ እንግዲህ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲውንና የፍትሓብሔር ሕጉን ስናስተያይ በፖሊሲው ወጣትነት ከ15 ዓመት ስለሚጀምር በፍትሓብሔር ሕጉ በህፃንነት ከሚፈረጁት የተወሠነው ክፍል (በ15 እና 18 መካከል ያለው) በወጣነት ጎራም ይታቀፋል ማለት ነው፡፡

---

[18] የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀፅ 19ና 20 አዋጅ ቁጥር 1/1980 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፡፡

[19] በኢትዮጵያ ሕጎች ለሕፃን የተሰጠ ግልፅ ትርጉም ስለሌለ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ ሕፃናት ኮንቬንሽንና የአፍሪካ የሕፃናት ቻርተር ትርጉም መሠረት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት በሕፃንነት ጎራ ይመደባሉ፡፡

በኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲ መሠረት በወጣቱ የዕድሜ ወለልና ጣራ መካከል ያለውን ልዩነት ስንመለከት የ14 ዓመታት ልዩነት ይታያል:: በዚህም ፖሊሲው ዕድሜያቸው በ15 እና 18 መካከል ያሉትንና በአካልም ሆነ በአዕምሮ በሚገባ ያላደጉትን ከ18 በላይ ካሉትና በአካልም ሆነ በአዕምሮ ሙሉ ሠው ከሚባሉት ጋር ደባልቋቸዋል:: ካላቸው ዕምቅ ኃይልና ብሩህ አዕምሮ የተነሳ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑት ወጣቶች ህብረተሠባዊ ኃላፊነታቸው ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑት ላቅ ያለ ነው[20]:: እንግዲህ ከሕግ አንፃር ስንመለከተው በፖሊሲው 'ወጣት' በመባል በአንድ የተጠቃለለው ወጣት በሁለት ተከፍሎ፤ አንዱ ዕድሜው ከ15 እስከ 18 ዓመት ያለው (በሕጻንነት የሚፈረጅ) ሲሆን ሌላው ደግሞ ከዚያ በላይ እስከ 29 ዓመት ያለው ይሆናል ማለት ነው::

### 3.2.1 ወጣትነት በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት

ወጣቶችን አስመልክቶ አግባብ ያላቸውን የኢትዮጵያ ሕጎች በምንመለከትበት ጊዜ መነሻችን ሁሌም ቢሆን በአገሪቱ የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው:: በእርግጥ ሕገ-መንግሥቱ ለሌሎች የህብረተሠብ ክፍሎች ያረጋገጠውን መብቶችና ነፃነቶች ለወጣቱም እንደማንኛ ውም የህብረተሠብ አባል ያለአድልዎ አረጋግጦላቸዋል[21]:: የእነዚህን መሠረታዊ ሠብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች አፈፃፀምና አተረጓጎም በሚመለከት በህገ-መንግሥቱ አንቀፅ 9/4 እና 13/2ም እንደተደነገገው ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ አካል መሆናቸውን እንዲሁም የሠብዓዊ መብቶቹ አተረጓጎም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሠብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሠብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆች ጋር በተጣጣመ መንገድ መሆን እንደሚገባው ተገልጿል::

ወጣቱን በተለየ ሁኔታ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሕገ-መንግሥቱ በግልፅ የተቀመጡ ባይሆኑም ወጣቱ እንደማንኛውም የህብረተሠብ አባል በህይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት፣ የግል ነፃነት፣ የእኩልነት መብትና ሌሎች መሠረታዊ መብቶቹና ነፃነቶቹ በሕገ-መንግሥቱ ተረጋግጠውለታል:: ከዚህ ውጭ ወጣትን በግልፅና በቀጥታ

[20] ወጣቱ እንደ ወጣት ከፖሊሲው አንፃር በጥቅሉ በሚያደርገው እንቅስቃሴ እነዚህ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት ወጣቶች በወጣቱ እንቅስቃሴ የሚሠጣቸው ኃላፊነቶችና የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ከዕድሜያቸው ጋር የሚመጥን መሆን ይኖርበታል::

[21] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑበሊከ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 25

የሚጠቅሱ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጾች ውስን ናቸው:: ምናልባት በአንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 6 የማንኛውም ሠው ኃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት፤ እንዲሁም በአንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2 የመሠብሠብና ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ መብቶች ለወጣቶች ደህንነት ሲባል ገደቦች ሊጣሉባቸው እንደሚችሉ የሚደነግጉት ሊጠቀሱ ይችሉ ይሆናል::

ወጣትን በጥቅሉ በመመልከት እንደማንኛውም የህብረተሠብ ክፍሎች የመብቶችና ነፃነቶች ባለቤት የሚያደርገው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች በሆኑት ሕፃናት ላይ በልዩነት ተፈፃሚ የሚሆኑ አንቀፆች አሉት:: ስለዚህ አግባብነት ያላቸው ለሕፃናት መብቶች ጥበቃ ተብለው በህገ-መንግሥቱ የተካተቱትና የህፃናት ኮንቬንሽኑ ራሱ ዕድሜያቸው በ15 እና 18 ዓመት መካከል ለሆነው የወጣት ክፍል ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል[22]::

ለሕፃናት አግባብ ወዳላቸው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ስንመለስ የሕፃናት መብቶችን አስመልክቶ በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለው አንቀፅ 36 ነው:: በዚሁ አንቀፅ መሠረት ማንኛውም ሕፃን በሕይወት የመኖር፣ ስምና ዜግነት የማግኘት፣ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሠዎች የማወቅና የእነርሱንም እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው:: ለምሳሌ ከሕግ አንፃር ልናነሳ የምንችለው ጉዳይ በኢትዮጵያ ከልደት ምዝገባ መኖር/አለመኖር ጋር በተያያዘ ያለው ችግር ከሕፃንነት ዕድሜ ባሻገር ከወጣቱ ጋር አብሮት እስከ ውርስ የሚዘልቅ ሆኖ እናገኘዋለን[23]::

በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ማንኛውም ሕፃን ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ መብት ሲኖረው፤ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሠብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን መብቶች አሉት:: ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ

[22] በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 1 መሠረት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነው ማንኛውም ሠው በሕፃንነት ጎራ ይፈረጃል:: *የህፃናት ኮንቬንሽን* የህፃናት፣ወጣቶችና ቤተሠብ ደህንነት ድርጅት፤ 1984፤ አዲስ አበባ:: ኢትዮጵያ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽንን በ1991 ፈርማ ተቀብላለች:: (See also Proclamation No 10 of 1992 by which the legislature has ratified the Convention).

[23] The African Child Policy Forum, *Universal Birth Registration: The Challenge in Africa*, a paper presented for the second Eastern and Southern Africa Conference on Universal Birth registration, Mombassa, Kenya, September 26-30,2005. እንዲሁም በወጣቱ የትምህርት፣ የሥነ ምግባርና ማኅበራዊ ሕይወት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ከ15ኛው ዕድሜ በፊት የሚሆኑ ናቸው::

አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች እንዲሁም ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሠብ እንደሚኖርበት በህገ-መንግሥቱ ተደንግጓል::

ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግሥት ዕርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች፣ በመንግሥት ወይም በግል እጓለ-ማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት ከዐዋቂዎች ተለይተው መያዝ እንዳለባቸው በህገ-መንግሥቱ ተገልጿል:: መንግሥት በተለይ ለእጓለ-ማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸውና በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ እንደሚያበረታታ ሕገ-መንግሥቱ በግልፅ ያስቀምጣል::

እነዚህ የተዘረዘሩት የሕፃናት መብቶችና ነፃነቶች በሕገ-መንግሥቱ ዕውቅና ማግኘ ታቸው ወሳኝ ቢሆንም፤ ለመብቶቹ መከበርና ለውጤታማነታቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎችና ተቋማት አስፈላጊ ይሆናሉ:: ከዚሁ በሕገ-መንግሥቱ ከተሠጠው ሕጋዊ ዋስትና ጋር በተጓዳኝነት ከቤተሠብ ጀምሮ በተለያዩ ደረጃዎች በሕፃናት ላይ የሚደርሱትን የጉልበት ብዝበዛና በአካላቸው ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን ኢ-ሠብዓዊ ቅጣቶች ተከታትሎ መከላከል ወይም ማስቆም የሚያስችል ሥርዓትና ተቋም (institutional and procedural guarantee) ማኖር የግድ አስፈላጊ ይሆናል:: ወጣቱ/ሕፃኑ በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጠለት የትኛውም መብቱ በማንኛውም ወገን ሲጣስበት መብቱ እንዲከበርለት መብቶችን ለማስፈፀም የወጡ ዝርዝር ሕጎችንና የተዋቀሩትን ተቋማት መፈለጉ የሚጠበቅ ይሆናል::

እስከአሁን በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ወጣቱን አስመልክቶ ስላሉት ድንጋጌዎች ለማየት ሞክረናል:: ከዚሁ ቀጥሎ ደግሞ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑት ወጣቶችን የሚመለከቱ የኢትዮጵያ ሕጎችን ለይተን፤ እነዚሁ ሕጎች ደግሞ ምን ያህል በሕገ-መንግሥቱ የተገለጹትን መብቶችና ነፃነቶች እንዲሁም ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲውን ለማስፈፀም ያስችላሉ የሚለውን እንመልከት::

### 3.2.2 ወጣትነት በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች

በኢትዮጵያ እስከ አሁን ባለው ሁኔታ አንድ ወጥ የሆነ ወጣት-አቀፍ ሕግ የለም:: የተለያዩ የኢትዮጵያ ሕጎች ሲፈተሹ በፖሊሲው በወጣትነት የተፈረጁት በሕፃንነት

የሚፈረጁ ሆኖ፤ እነዚህንም የሚመለከቱ ድንጋጌዎችም እንደየሁኔታው በተለያዩ የአገሪቱ ሕጎች ተበታትነው እዚህም እዚያም እናገኛቸዋለን:: በዚህ ሁኔታ በፖሊሲው በወጣትነት የታቀፉትን በተለያዩ የአገሪቱ ሕጎች የዕድሜያቸው ወለልና ጣራ ተለያይቶ እናገኛቸዋለን [24]::

እነዚሁ በፖሊሲው በወጣትነት የተፈረጁት በኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ ያላቸውን አቋም ለመመልከት በዚህ ፅሁፍ በሁለት ከፍለን እናያቸዋለን:: በመጀመሪያ በብዙ የኢትዮጵያ ሕጎች ልዩ ጥበቃ ያሻቸዋል ተብለው በሕፃንነት ክፍል የሚጠቃለሉትን በዕድሜያቸው በ15 እና 18 ዓመት መካከል ያሉት ሕፃናት/ወጣቶች በሕጉ ያላቸውን ሥፍራ ለማየት እንሞክራለን::

### 3.2.2.1 ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ያሉት ወጣቶችና ሕግ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በዕድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ዓመት ያሉት ወጣቶች በአካልና በአዕምሮአቸው በሚገባ ያልዳበሩ ከመሆናቸው የተነሳ ለተለያዩ ጥቃቶች ተጋላጭ ናቸው:: በመሆኑም ሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆነውን ሁሉ በሕፃንነት ጎራ በመፈረጅ ኃላፊነታቸው ያነሰና (persons with lessened capacity, less responsibility and in need of more protection) የበለጠ ህጋዊ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ያሳያሉ[25]:: የተለያዩ የአገሪቱ ሕጎች እነዚህኑ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑትን እንደ አንድ ወጥ ክፍል ሳይሆን እንደየ ዓላማቸው ድንጋጌዎቻቸውም የተለያዩ መሆናቸውን እናያለን:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ኣዋጅ በአንቀፅ 89 ከሌሎች ሕጎች ለየት ባለ ሁኔታ ዕድሜው ከ14 እስከ 18 ዓመት ያለውን ሠራተኛ ለማመልከት 'ወጣት ሠራተኛ' የሚል ፅንሰ ኃሳብ ተጠቅሞ እናገኛለን:: ይህ አዋጅ ዕድሜው 14 ዓመት የሆነ ሕፃን/ወጣት መቀጠር እንደሚችልና ከ14 ዓመት በታች ከሆነ ግን መቀጠር እንደማይችል ይደነግጋል:: አዋጁ በ14 እና 18 የዕድሜ ክልል መካከል ያሉ ተቀጣሪ ወጣት ሠራተኞችን በተመለከተ የሥራ ሠዓታቸውን ልክ፤ የሌሊትና የትርፍ ሠዓት ሥራ ሁኔታዎችንም ይዘረዝራል:: ከዚህ በተጨማሪ ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉትንም

[24] የወጣትነት የዕድሜ ወለልና ጣራ በተለያዩ ሕጎች በተዘበራረቀ መልክ መቀመጣቸው ወጣቱን አስመልክቶ በሚወጣው ወጣት-አቀፍ ሕግ አወጣጥ ላይ በተወሠነ ደረጃ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችል ቢሆንም ወጣት-አቀፍ ሕጉ በሌሎች ሕጎች ዕውቅና የተሰጣቸውን የወጣት መብቶች በሚያስከብር መልክ መውጣት ይኖርበታል::

[25] የ1952 የኢትዮጵያ የፍትሓብሔር ሕግ፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት፤ የተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ፤ የአፍሪካ የሕፃናት ቻርተርና ዓለም አቀፍ የሕፃናት ኮንቬንሽን::

የሥራ ዓይነቶችን በመግለፅ መንግሥት ተጨማሪ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ማውጣት እንደሚችል ይገልፃል[26]::

የ1952ቱን የኢትዮጵያ የፍትሓብሔር ሕግ ስንመለከት በግልፅ ወጣት በሚል ፅንሠ-ኃሳብ ያሠፈረው ነገር ባይኖርም ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ማንኛውም ሠው ፍትሓብሔራዊ መብቶችን በተሟላ መልኩ ለመጠቀም ሕጋዊ ችሎታ እንደሌለው ይገልፃል:: ከዚህም የተነሳ በፍትሓብሔር ሕጉ ቁጥር 313 መሠረት ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሠው የሚፈጽማቸው ፍትሓብሔራዊ ክንዋኔዎች (juridical acts) ዋጋ እንደሌላቸው ያመለክታል[27]:: ሕጉ በዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት የመብቶቻቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሥርዓትም (organs for the protection of minors) ፈጥሯል:: የተሻሻለው የኢትዮጵያ የቤተሠብ ሕግም በተመሳሳይ ሁኔታ ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሠው ሕጋዊ ችሎታ እንደሌለው (incapable) በመግለጽ ሕጋዊ ጋብቻም ሊፈጽም እንደማይችል ይደነግጋል[28]::

በዕድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ዓመት ያሉት ወጣቶች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ከሆኑት ወጣቶች የበለጠ ለጥቃት ተጋላጭ ከመሆናቸውና ከሚሹት ልዩ ጥበቃ አንፃር የወንጀል ሕግ የሚኖረው ፋይዳ በጣም ከፍተኛ ነው:: ከወንጀል ሕግ አንጻር ስንመለከት ወጣቱ ወንጀል የሚፈፀምበት ብቻ ሳይሆን ወንጀል ፈጻሚም ሊሆን ይችላል:: በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት ከወንጀል ነፃ (legal minority) የሚባሉት ዕድሜያቸው ከ9 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ናቸው[29]:: በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የወንጀል ሕግ ቁጥር 53 መሠረት ዕድሜያቸው ከ9 አስከ 15 ዓመት የሆኑ ሠዎች ወጣት አጥፊዎች (young offenders) ተብለው ከዐዋቂዎች በተለየ ሁኔታ የወንጀል ሕጉ ተፈፃሚ ይሆንባቸዋል:: በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 36/2 በተደነገገው መሠረት እነዚህ በወንጀል ሕጉ ወጣት አጥፊዎች የተባሉት ከዐዋቂዎች ተለይተው መጠበቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል:: በዕድሜያቸው ከ15 ዓመት

[26] የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀፅ 89-91::

[27] የፍትሓብሔር ሕግ ቁጥሮች 198-338 የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፍትሓብሔር ሕግ 1952 ነጋሪት ጋዜጣ 1/1952 አዲስ አበባ::

[28] Revised Family Code of Ethiopia, Procl. No. 213/2000. የፍትሓብሃሔር ሕጉና የተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ ከዓለም አቀፍ የሕፃናት ኮንቬንሽን ጋር የተጣጣሙ ናቸው::

[29] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፅ 52 እና 53፤ የወጣቱ የወንጀል ኃላፊነት የዕድሜ ገደብ (age of criminal responsibility) 9 ዓመት ይሆናል ማለት ነው::

በላይ የሆኑት ግን በወንጀል ሕጉ መሠረት እንደዐዋቂዎች ተቆጥረው መደበኛው የሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆንባቸዋል[30]::

በ1954 የወጣውና አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በቁጥር 3 አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት ማለት ዕድሜው ከ9 ዓመት እስከ 15 ዓመት የሆነ ማለት መሆኑን ይደነግጋል:: እነዚህ ዕድሜያቸው ከ9 እስከ 15 ዓመት ያሉት ወጣቶች ወንጀል በመፈፀም በሚከሰሱበት ጊዜ ጉዳያቸው በመደበኛ ፍርድ ቤት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥሮች 171 እስከ 180 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት እንደሚታይ ተገልፃል[31]:: በዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑት ግን ጉዳያቸው እንደ ዐዋቂዎች በመደበኛው የወንጀል ሕግና በመደበኛው ሥነ ሥርዓት ይታያል:: በዚሁ መሠረት አሁን ባለው የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት ዕድሜው በ15 እና በ18 ዓመት መካከል የሆነ ወጣት/ሕፃን የዕድሜ ልክ እሥራት ሁሉ ሊፈረድበት ይችላል ማለት ነው::

አሁንም ዕድሜያቸው በ15 እና 18 መካከል ከሆነው የወጣት ክፍል ሳንወጣ በወንጀል ሕጉ የሠፈሩትን ለዚሁ የወጣት ክፍል አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን ለማየት እንሞክር:: በኢትዮጵያ ዕድሜያቸው በ15 እና 18 ዓመት መካከል የሆኑትን ሕፃናት/ወጣቶች ከተለያዩ ጥቃቶችና ብዝበዛ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በወንጀል ሕጉ በስፋት ተዘርዝረዋል:: ለምሳሌ ዕድሜዋ ከ13 እስከ 18 የሆነች ሴት ልጅ ከተደፈረች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 620 መሠረት የጥቃቱ ፈፃሚ እስከ 20 ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እስራት እንደሚቀጣ ተደንግጓል[32]:: በአንቀፅ 589ም እንዲሁ ጠለፋ እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል:: ዕድሜው ከ18 ሸ በታች ከሆነ/ች ወጣት ጋር ጋብቻ መፈፀም የሚያስቀጣ መሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 648 ሰፍሯል:: በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 635 ደግሞ ሴቶችንና ሕፃናትን ማዘዋወር በወንጀል ያስቀጣል[33]:: በአጠቃላይ ዕድሜያቸው በ15 እና 18 ዓመት መካከል የሆኑት ሕፃናት/ወጣቶችን ከወሲብ ጥቃትና ብዝበዛ፣

---

[30] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፅ 157-175. አንቀፅ 56 በቅጣት አወሳሰን ላይ ፍርድ ቤቱ ሊመለከታቸው የሚችላቸውን ሁኔታዎች ያስቀምጣል:: ከመነሻው ግን ከወንጀል ኃላፊነት አንፃር የ9 ዓመት ሕፃንና የ15 ዓመት ወጣትን በተመሳሳይ ደረጃ ማስቀመጡ የሚያከራክር ነው::

[31] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት 1954::

[32] በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 626ም ተመሳሳይ ድንጋጌ ተቀምጧል::

[33] በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 636 መሠረት ማንኛውም በሕፃናትና ሴቶች ላይ ወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት ያደረሰ ሠው በወንጀል እንደሚቀጣ ተገልፃል::

ከሌሎችም ጎጂና ልማዳዊ ጥቃቶች ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሌሎች ድንጋጌዎች በወንጀል ሕጉ ውስጥ ተካተዋል[34]::

የእነዚህ ሕጎች መኖር ጠቀሜታው ከፍተኛ ቢሆንም ከዚሁ ባልተናነሰ ሁኔታ ከፍተኛ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በወጣቱ ላይ ሊፈፀሙ የሚችሉትን የመብት መጣሶች እንዳይደርሱ ለመከላከል፣ መብቶቹም ሲጣሱ ፍትህ ለማግኘት የኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ተደራሽና ውጤታማ አሠራሮች (child-friendly, flexible, cheaper, efficient and accessible criminal procedures) እንዲኖሩ ማድረግ ነው[35]:: ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ ሥነ ሥርዓት ሕግ ዕድሜያቸው ከ9 እስከ 15 ዓመት ላሉት ሕፃናት በተወሰነ ደረጃ ከዐዋቂዎች የተለየ ሥነ ሥርዓት ተግባራዊ እንደሚሆን ይደነግጋል:: ዕድሜያቸው በ15 እና 18 ዓመት መካከል ላሉት ግን በተዋረድ ቀላልና ተደራሽ የሆነ የተለየ የወንጀል (child-friendly) ሥነ ሥርዓት አላስቀመጠም[36]:: የዚህን የወጣት ክፍል ዕድሜ ከግምት ሳያስገባ እንደማንኛውም ሠው ጉዳያቸው በመደበኛ ፍርድ ቤት በመደበኛ የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት እንዲታይ የመደረጉ ሁኔታ ትንሽ ሊያከራክር ይችላል:: በማረሚያ ቤቶችም ቢሆን ከዐዋቂዎች ተለይተው የሚጠበቁበት ሁኔታ በሕጉ አለመቀመጡ የሥርዓቱን ለዚሁ የወጣት ክፍል የተመቻቸ አለመሆን ያመለክታል[37]:: እነዚህን በሚመለከት የወንጀል ፍትህ ፍልስፍናዊ መሠረቱ ቅጣትን መሠረት ያደረገ (retributive) ሣይሆን ዕርቅን (restorative) የሚያመጣና ትምህርታዊ መሆን አለበት::

እንግዲህ እስካሁን ባጭሩ በኢትዮጵያ ባሉት ሕጎች ዕድሜያቸው በ15 እና 18 ዓመት መካከል ያሉት ወጣቶች/ሕፃናትን አስመልክቶ የተደነገጉትን ለማየት ሞክረናል:: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 29 ዓመት ያሉት ወጣቶችን በሚመለከት አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች የተደነገጉትን ለማየት እንሞክራለን::

---

[34] የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 551፣ 561 እና 565ን ማየት ይቻላል::

[35] But there seems to be lack of effective complaint mechanism that is accessible to children at the grass root/local level.

[36] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 171-180::

[37]ለእነዚህ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ የሆነ ልዩ ሥርዓት (out of court and fully child friendly) ቢበጅላቸው የተሻለ ይሆን ነበር::

### 3.2.2.2 ዕድሜያቸው ከ18 በላይ የሆኑ ወጣቶችና ሕግ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት ወጣቶች በአዕምሮም ሆነ በአካልም በሚገባ ያልዳበሩ በመሆናቸው ለተለያዩ ጥቃቶች በቀላሉ ስለሚጋለጡ በሕጉ ልዩ ጥበቃ የተሰጣቸው መሆኑን ተመልክተናል:: ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች ግን በዐዋቂዎች (persons with full legal responsibility) ጎራ ስለሚመደቡ በሕጉ የሚደረግላቸው ልዩ ጥበቃ የለም:: እነዚህ እንደ ዐዋቂ የሚቆጠሩትና በዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች የሚፈለጉት ካላቸው ብሩህ አዕምሮና ዕምቅ ኃይል አንፃር ጉልበታቸውንና ብሩህ አዕምሮአቸውን ለአገር ብልፅግናና ዕድገት ለማዋል ነው:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲም ዓላማው ወጣቱን እንደ ግዙፍ የልማት ኃይል በመቁጠር ይህን ኃይል አንቀሳቅሶ ለአገር ግንባታ ማሰለፍ ነው[38]::

ያም ሆኖ ግን አሁን ያሉት የኢትዮጵያ ሕጎች (ሕገ-መንግሥቱን ጨምሮ) ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ ለሆነው ወጣት በወጣትነቱ ምንም የተለየ የሕግ ስፍራ (legal status) አልሰጡትም:: አሁን ከወጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ በተጓዳኝ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 29 ዓመት የሆነውን በሙሉ በአንድ ጥላ ሥር የሚያስተናግድ የሕግ ማዕቀፍ በተሟላ መልኩ የለም ማለት ይቻላል:: ማንኛውም ፖሊሲ በባሕሪው አንድን ሕዝባዊ/ብሔራዊ ጉዳይ አስመልክቶ በመንግሥት ሊወሰዱ የታቀዱትን የተግባር መመሪያና አቅጣጫ ከማመልከት በስተቀር ሕጋዊ ኃይል (legal force) ያላቸው መብቶችና ግዴታዎችን ማስቀመጥ አይችልም[39]:: ስለዚህ ለብሔራዊ ፖሊሲው ውጤታማነት ፖሊሲውን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ የማስፈፀሚያ ዝርዝር ሕጎችና ተቋማት መኖራቸው ግድ ይሆናል::

### 4. የብሔራዊ የወጣት ፖሊሲው የሕግና የተቋማት ማዕቀፍ

በኢትዮጵያ የወጣቶች ብሔራዊ ፖሊሲ ወጣት የሚል ትርጉም የተሰጣቸውና በዕድሜያቸው በ15 እና በ29 ዓመት መካከል ያሉት ወጣቶች በፖሊሲውና በፓኬጆቹ እንደተገለፀው ዘርፈ-ብዙ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች አሉባቸው::

[38] Finn Yrjar Denstad, *Youth policy manual: How to develop a national youth strategy*, Strasbourg: Council of Europe Publishing, 2009. p.17.

[39] ለምሳሌ ፖሊሲው ተግባራዊ ባለመሆኑ ተጎጂ ነኝ ባይ በፍርድ ቤት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ሕጋዊ መብት ሊኖረው አይችልም::

በአገሪቱ ካለው የሥራ ስምሪት ውስንነት የተነሳ ሥራ አጥነት፣ የወጣቱ ለአልኮልና ዕፅ ሱሰኝነት መጋለጥ፣ ከሚገኝበት አካላዊና ስነ ልቦናዊ የዕድገት ደረጃ የተነሳ ለኤድስና ሌሎች የግብረ-ስጋ በሽታዎች ተጋላጭ መሆንና ከአገር መሠደድ በግልፅ የሚታዩ የወጣቱ ችግሮች ናቸው:: የብሔራዊ ፖሊሲው ዓላማ እነዚህን የወጣቱን ችግሮች ለመቅረፍና ወጣቱን አንቀሳቅሶ ባሉት የልማት ዘርፎች በማሳተፍ ወጣቱ አገሩንም ራሱንም እንዲጠቅም ለማድረግ ነው[40]::

ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲውን ለማስፈፀም ስለሚያስችሉ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ መኖርና አለመኖርን አስመልክቶ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ዓመት መካከል ያሉትን ወጣቶች በሚመለከት በተለያዩ የአገሪቱ ሕጎች በተበታተነ መልክም ቢሆን የተለያዩ ሕጎች እንዳሉ አይተናል:: ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑትን አስመልክቶ ግን እስከ አሁን ምንም ሕግ እንደሌለ ተመልክተናል:: በጥቅሉ ፖሊሲውን ማዕቀፍ አድርጎ ወጣቱን እንደ አንድ ክፍል የሚያስተናግድ የተለየ ወጣት-ተኮር ሕግ (Youth specific law) እስከአሁን የለም:: እንዲሁም የወጣቶችን ጉዳይ አቀናጅቶ ለመምራት (mainstreaming)፣ ለማስተባበርና ለመቆጣጠር የሚያስችል የሕግና የተቋማት ማዕቀፍ (legal and institutional framework) በአግባቡ የተደራጁ አይመስሉም::

የኢትዮጵያን ወጣቶች አስመልክቶ በብሔራዊ የወጣት ፖሊሲውም ሆነ በፓኬጆቹ በዝርዝር የተመለከቱት ተግባራዊ ቢደረጉ ለአገሪቱም ሆነ ለራሱ ለወጣቱ ሊያስገኙ የሚችሉት ጥቅም ከፍተኛ መሆኑ ግልፅ ነው:: ያም ሆኖ ግን ለአንድ ፖሊሲ ውጤታማ መሆን ወሳኙ ፖሊሲው የሚዘረዝራቸው ጉዳዮች ብቻ ሳይሆኑ በፖሊሲው አወጣጥ ሂደት ላይ የባለድርሻ አካላት ሙሉ ተሳትፎ መኖር ነው:: ማንኛውም ፖሊሲ በይዘቱ ምንም ያክል ጥሩ ቢሆን ያለ ባለድርሻ አካላት ሙሉ ተሳትፎ ውጤታማ ሊሆን አይችልም::

በዚህ የባለድርሻ አካላት ቁልፍ ሚና የሚጫወተው ወጣቱ ራሱ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: በመሆኑም የወጣቱን ተሳትፎ የሚያበረታታና ውጤት መስጠት የሚያስችል የተመቻቸ ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች መመቻቸት ይኖርባቸዋል:: ወጣቱ ከቤተሠብ ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ባሉት ደረጃዎች በተዋረድ በነፃነት

[40] የኢትዮጵያ የከተማ ወጣቶች የእድገት ፓኬጅና የኢትዮጵያ የገጠር ወጣቶች የእድገት ፓኬጅ ሰኔ *1998.*

ተደራጅቶ ለራሱም ሆነ ለአገር የሚበጀውን የሚወስንበት መዋቅራዊ አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል:: አሁን በየቦታው የተቋቋሙት የወጣት ማዕከላትና የወጣት ፎረሞች ሙሉ በሙሉ በወጣቱ ተነሳሽነት ስለመመስረታቸውና በወጣቱ ውስጥ ሊንፀባረቁ የሚችሉትን የተለያዩ አስተሳሰቦች ለማስተናገድ ምቹ ስለመሆናቸው ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ:: ከዚህም የተነሳ የወጣት ማዕከላቱና ፎረሞቹ የተፈለገውን ያክል ውጤት አላመጡም ይሆናል[41]::

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሠቦችና ሕዝቦች ካሏቸው ባህሎችና ልማዶች ጠቃሚ የሆኑት ቦታ እንዲኖራቸው ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲው ሲቀረፅ በሚፈለገው ደረጃ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሠቦችና ሕዝቦች ተሳትፎ ለመኖሩ ብዙም የተገለፀ ነገር የለም:: ስለዚህ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሠቦችና ሕዝቦች ከወጣቱ አንፃር ያላቸው መልካም ዕሴቶች፣ ልማዶችና አሠራሮች ምን ቦታ እንደሚኖራቸው በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም:: በእርግጥ አግባብነት ካላቸው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች አንፃር ስንመለከተው በተሠጣቸው የስልጣን ክልል የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሠቦችና ሕዝቦች የፌዴራሉን ሕገ-መንግሥትና ሌሎች ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችና ኮንቬንሽኖች መሠረት በማድረግ ልማዶቻቸውን ተፈፃሚ ከማድረግ የሚከለክላቸው የለም::

በፖሊሲው በሚገባ ያልተንፀባረቀው ሌላው ጉዳይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሁኔታ ነው:: ለምሳሌ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲውን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የህብረተሠቡና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚና የሚፈለገውን ያህል ጎልቶ የወጣ አይመስልም:: አሁን ኢትዮጵያ ባለችበት የዕድገት ደረጃ ግን የኢትዮጵያ ወጣቶችን ችግሮች ለመቅረፍ የሲቪል ማሕበረሠብና ህብረተሠብ ድርሻ ወሳኝ መሆኑ አሌ የማይባል ነው:: በተለይ ወጣቱ ላይ የሚደርሱ የወሲብ ጥቃቶች የሚፈፀሙትና ወጣቶች ተጋላጭ የሚሆኑባቸው አካባቢዎች (settings) የሚገኙት በህብረተሠቡ ውስጥ ነው:: ከዚህም የተነሳ በወጣቱ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን ጥቃቶች ለመከላከልና ጥቃቶች ሲደርሱም ጥቃት አድራሾችን ለፍርድ ለማቅረብ የህብረተሠቡ ተሳትፎ እጅግ ወሳኝ ነው:: አሁን ባለው ሁኔታ ግን ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ የተደራጀና ህብረተሠብ አሳታፊ የሆነ መዋቅር የለም::

[41] ወጣቱ የመላው ህብረተሠብ አካል እንደመሆኑ ህበረተሠቡ ኃሳብን በነፃ የመግለፅና የመደራጀት መብቶች ካሉት እርሱም የዚሁ ተጠቃሚ ሲሆን ህብረተሠቡ እነዚህ መብቶች ከሌሉት ወጣቱም ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም::

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣት ፖሊሲ ዓቢይ ዓላማ ወጣቱን የህብረተሠብ ክፍል እንደ ግዙፍና ወሳኝ የልማት ኃይል ተቀብሎ ለውጤታማ የአገር ልማት ማሠለፍ ነው:: በፖሊሲው ውስጥ ተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማስፈፀም ግን አግባብነት ያላቸው ሕጎች፣ ተቋማትና የአፈፃፀም ክትትል ሥርዓት ያስፈልጋሉ:: ወጣቱን ሊያሳትፉ የሚችሉ በሕግ የተቋቋሙ ተቋማት በተዋረድና በተቀናጀ መልክ መዋቀር ለፖሊሲው አፈፃፀም የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል:: አሁን ባለው ሁኔታ በሕግ የወጣውን ፖሊሲ ተፈፃሚነት ለመከታተልና ለማስተባበር የሚያስችሉ ተለይተው የታወቁ ተቋማት ውስን ናቸው[42]::ለምሳሌ የወጣው ፖሊሲ በማንኛውም ክፍል በማንኛውም ምክንያት ተግባራዊ የማይደረግ ከሆነ የተጠያቂነቱ ሁኔታ እንዴት እንደሚሆንና ጠያቂውም በምን ሕጋዊ መሠረት ሊጠይቅ እንደሚችል የተገለጸ ነገር ስለሌለ ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚያስችል ግልፅ የሆነ የቁጥጥር ሥልትና አሠራር (a clear and transparent reporting, monitoring and evaluating system has to be put in place) ሊኖር ይገባል[43]:: እስከ አሁን ወጣቱ በሕግ የተቋቋመ ማኅበር ወይም ድርጅት ስለሌለው ወጣት-ነክ በሆኑ ፌዴራላዊም ሆኑ ክልላዊ ጉዳዮች ላይ ድምጹን በቋሚነት የሚያሠማበት ነፃ ምክር ቤቶች (independent youth organization) በየደረጃው ሊኖሩ ይገባል[44]::

ይህ በፌዴራል ደረጃ የወጣው ፖሊሲ ከፌዴራል ሥርዓቱ አንፃር የኢትዮጵያን የተለያዩ ስብጥሮች በሚያስተናግድ መልክ እንዴት ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚችልና ክልሎች በዚህ ረገድ ያላቸው ሥልጣንና ሊስተናገዱ የሚችሉ ልዩነቶች ምን ያህል እንደሆኑ በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል:: ሌላው በፖሊሲው በሚገባ ያልተንፀባረቀው ጉዳይ ወጣቱ ከአባቶች ሊተላላፉለት የሚገቡትን ጥሩ ጥሩ ልማዶች ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ (intergenerational knowledge transfer) ነው:: በአባቶችና በወጣቱ

---

[42] በእርግጥ የወጣቶች ጉዳይ በሚኒስትር ደረጃ መቋቋምና በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የወጣቶችና የሴቶች ጉዳይ ቢሮዎች መኖራቸው አበረታች ቢሆንም፤ በአፈፃፀም ረገድ ያለው ቅንጅት ዝቅተኛ ይመስላል::

[43] After all, policy obligations are not legal obligations! ሌላው የወጣት ፖሊሲውን ለማስፈፀም ብዙ መስሪያ ቤቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑ የታወቀ ቢሆንም በባለቤትነት ሥልጣን የሚሰጠው አካል ኖሮ የዚህ አካል ሥልጣንና ኃላፊነት በሕግ መገለፅ ይኖርበታል::

[44] እስከ አሁን በነበረው የኢትዮጵያ ሁኔታ ነፃ የወጣት ማህበራት ተቋቁመው በተፈለገው ደረጃ መንቀሳቀስ የቻሉበት ሁኔታ አልነበረም:: በአመዛኙ ሥልጣን ላይ የነበሩ የፖለቲካ ኃይሎች ወጣቱን በማደራጀት ለየራሳቸው ዓላማ ሲያሰልፉ የነበረ መሆኑ ይታወቃል::

ትውልድ መካከል የሚኖረው መቀራረብና መተሳሰር ዕውቀትና ልምድ ከአንዱ ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ መሸጋገሪያ ዐይነተኛ መንገድ ሲሆን ወጣቱ ትውልድም ከአባቶች ጠቃሚ ልምዶች የሚቀስምበት ሥርዓት ይፈጥራል[45]።

ወደ ወንጀል ሥርዓቱ ስንመጣ በአገሪቱ የወንጀል ፍትህ አሠጣጥ በተለይ ዕድሜያቸው በ15 እና 18 ዓመት መካከል ያሉ ወጣቶች ወይም ህፃናት ጉዳዮች በተለየ ለልጆች በተመቻቸ ቀልጣፋና ተደራሽ ፍርድ ቤት ሊታይ ይገባል። እነዚህን ወጣቶች/ሕፃናት የሚመለከቱ ጉዳዮች ከፍርድ ቤት ውጪ (out of court) መፍትሔ የሚያገኙበት አሠራር ሊኖር ይገባል። ወጣቶቹ በመደበኛ ፍርድ ቤትና በመደበኛ ሥነ ሥርዓት መዳኘት የለባቸውም። በማረሚያ ቤቶችም ከዐዋቂች መለየት ይኖርባቸዋል። ሕግን በመተላለፍ በወጣቱ ላይ ጥቃቶች ሲደርሱ የወጣቱን አቤቱታ በፍጥነት ተቀብሎ ሊያስተናግድ የሚችል ውጤታማና ተደራሽ የፍትህ አካላት በተዋረድ ያስፈልጋሉ። ከህብረተሠቡ ጋር በቅርበት የሚሠራ በወጣቶች ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ልዩ ስልጠና ያለው የፖሊስ ግብረ-ኃይል ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ወጣቱን የሚመለከት አንድ ወጥ ሕግ (Youth - specific comprehensive law) መውጣት ይኖርበታል[46]። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለፖሊሲው አፈጻፀም የሚረዱ በወጣቱ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩና ስለአፈጻፀሙ ክትትል የሚያደርጉ ተቋማት በህግ መቋቋም ይኖርባቸዋል። ከብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲው ጋር ይህ ያልተሟላውና አስፈላጊ የሆነ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ ከተሟላ የኢትዮጵያ ወጣቶች ፖሊሲው እንዲጫወቱ የሚፈልገውን በጎ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ[47]።

---

[45] ይህ ከወጣቱ ማንነት ጋር የሚያያዝ ከመሆኑም ባሻገር እንደ አገርም ያለንን ታሪካዊና ባህላዊ ዕሴቶች ለመጪው ትውልድ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው።

[46] በእርግጥ የወጣትም ሆነ የማንኛውም የህብረተሠብ ክፍል እንቅስቃሴ ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት በአባላት ሙሉ ነፃነትና ተሳትፎ የሚደራጅና የሚንቀሳቀስ ሲሆን ነው።

[47] የወጣት ተኮር ሕግና ተቋማት መኖርም ፋይዳ የሚኖረው ወጣቱን ሙሉ በሙሉ በነፃነት ሊያንቀሳቅሱ የሚችሉ ሲሆኑ ብቻ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

# የወጣቶች የሥራ ፖሊሲዎች በኢትዮጵያ

## ማርታ ክብሩ

### 1 መግቢያ

ባለፉት ሁለት አስርተ-አመታት የወጣቶች ድርሻ ከጠቅላላው የኢትዮጵያ የህዝብ ብዛት አኳያ ቁጥሩ ጨምሯል። በአሁኑ ጊዜ ከአገሪቱ ሕዝብ 30 ከመቶ የሚሆነው በወጣትነት የዕድሜ ክልል የሚገኝ ነው። በኢትዮጵያ እየተባባሰ የመጣው ወደ የሰው ኃይል ገበያው የመግባት አስቸጋሪነትም በዋናነት የሚያጠቃው ወጣቱን ነው። በተለይም በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ከ35 ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ዜጎች የሥራ አጥነት ችግር ዋነኛ ተጠቂዎች ናቸው። በከተማ የሚኖረውን ህዝብ አንድ አራተኛ የሚወክለው ወጣት ክፍል የሥራ አጥነት መጠን ከፍተኛ ነው። ሆኖም ግን ሥራ አጥ የሆነው ወጣት ቁጥር ከ2004 - 2011[1] ባለው ጊዜ ውስጥ ከ 31.5 በመቶ ወደ 23.7 በመቶ ዝቅ ብሏል።

የሥራ አጥነት መጠን ብቻውን የወጣቱን ችግር ሁሉ አይገልጽም። በተጨማሪም ወጣቱ የተሠማራበትን የሥራ አይነትና ደረጃን ማጤንም ያስፈልጋል። ወጣቱ አጥጋቢ ሥራ የማግኘት ችግር አለበት። አብዛኞቹ ወጣቶች ወደሰው ኃይል ገበያው የሚቀላቀሉት ደረጃቸው ዝቅተኛ በሆኑ ሥራዎች ወይም በሥራ አጥነት ነው። እንዲሁም በሥራ ላይ ከሚገኙ ወጣቶች 80 በመቶ የሚሆኑት የተሰማሩት ኢ-መደበኛ በሆነ የሥራ ዘርፍ ሲሆን አብዛኛዎቹም በቤተሠብ ሥራ ላይ የተሠማሩና ያለምንም ክፍያ የሚሰሩ ናቸው።

ሌላው የወጣቱ ዋነኛ ችግር የሠለጠኑበት የሙያ ዘርፍና የተሠማሩበት የሥራ ዘርፍ አለመመሳሰል ነው። ምንም እንኳን አሁን ያለው ትውልድ በኢትዮጵያ ታሪክ የላቀ የትምህርት ደረጃ ያለው ቢሆንም፤ ወጣቱ በሠለጠነበት የሙያ ዘርፍ ተሰማርቶ ሙያውን ሥራ ላይ ካላዋለ መንግሥት በትምህርት ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰሱን ተከትሎ አገሪቱ በግለሠብና በማኅበረሠብ ደረጃ ልታገኝ ትችላለች ተብሎ የሚታሠበውን ተጠቃሚነት ያሳጣል። በተጨማሪም ይህ ሁኔታ ከቀጠለ ቁጥሩ በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የተማረ የከተማ ወጣት ወደተስፋ መቁረጥ ሊመራው ይችላል። ከዚህ አኳያ ከ1999-2005 የነበረው ሁኔታ አበረታች ነበር።

---

[1]በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ቀናትና ዓመታት በሙሉ እንደ አውሮፓውን የዘመን አቆጣጠር ናቸው።

ሥራ አጥነት ባሉት ዘርፈ-ሠፊ ተፅዕኖች ምክንያት በብዙ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የፖሊሲ አውጪ አካላትን ትኩረት በከፍተኛ ደረጃ ይስባል። በቅርቡ በተወሰኑ የሠሜን አፍሪካ አገራት የታዩት በዋናነት ወጣቶች የተሳተፉባቸው ህዝባዊ አመጾች በግልጽ ከሚያሳዩት ነገር አንዱ አገራት የወጣቶችን ሥራ አጥነት ችግር ለመፍታት ብሎም ወጣቶች ወደ ሰው ኃይል ገበያው እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችሉ አስቸኳይ ችግር ፈቺ እርምጃዎችን መውሠድ እንዳለባቸው ነው። እንዲሁም ይህ የወጣቶች ሥራ አጥነት ባለበት የሚቀጥል ከሆነ እያደገ የሚሄድ የዕኩልነት አለመኖር፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አለመረጋጋት አደጋን ማስከተሉ አይቀርም።

በኢትዮጵያ የወጣቱን ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። ለዚህም ማሳያ የሚሆኑ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተነድፈዋል። ከነዚህም ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ የተባሉት የትምህርት ፖሊሲውና ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን በተመለከተ የተዘጋጁት የፖሊሲ ማዕቀፎች ናቸው። ይሁን እንጂ ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ የተዘጋጁት ፕሮጀክቶች እጅግ በጣም ውስን ሲሆኑ በሚገባም አልተገመገሙም።

የዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ ያለውን የወጣቶች የሰው ኃይል ገበያን መዳሰስ ሲሆን ጥናቱ በኢትዮጵያ ያለውን የሥራ አጥነት ሁኔታ ለማሳየትና የሰው ኃይል ገበያውን ለማሻሻል በመንግሥት ለሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች የሚያገለግሉ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ የሚረዱ የፖሊሲ ግብዓቶችን ለማቅረብ ይሞክራል። ይህ ጥናት ገላጭ የሆነ የትንተና መንገድንና በአገር አቀፍ ደረጃ ወካይ ሊባል የሚችለውን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን የ1984፣ 1999 እና 2005 አገር አቀፍ የሰው ኃይል ጥናት መረጃዎችን፣ እንዲሁም የ2004፣ 2009፣ 2010 እና 2011 የከተሞች የሰው ኃይል ጥናት መረጃዎችን በመጠቀም በኢትዮጵያ የሰው ኃይል ገበያ ውስጥ ያሉትን ተሳታፊዎች ይዳስሳል።

# 2 የወጣቶች ሥራ አጥነት ዳሰሳ በኢትዮጵያ


## 2.1 የኢትዮጵያ ወጣቶች ገፅታ - ከአጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር አንፃር

ምንም እንኳን ላለፉት ሦስት አስርተ-ዓመታት የመቀነስ አዝማሚያ ቢያሳይም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት የዕድገት መጠን አሁንም ከፍተኛ ሊባል የሚችል ነው። በግንቦት 2007 በተደረገው አጠቃላይ የህዝብ ቆጠራ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 79.3 ሚሊዮን እንደሆነ ሲገመት ይህ ቁጥር በ2010 ወደ 79.8 ሚሊዮን እንዲሁም በ2030 129.1 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል (World Bank, 2007)።

ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ውስጥ የወጣቶች ቁጥር በአጠቃላይና በመቶኛ ጭማሪ አሳይቷል። ይህ ጭማሪ የተባበሩት መንግስታት ወጣት ብሎ የሚገልጻቸው ከ15-24 ዕድሜ ክልል የሚገኙትንም ሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ወጣት ብሎ የሚፈርጃቸውን ከ15-29 ዕድሜ ክልል የሚገኙትን ይወክላል። በሥራ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ቁጥር ከአጠቃላይ በሥራ ላይ ከሚገኘው ህብረተሠብ አንጻር ሲታይ ግን ከላይ ከተገለፀው በተቃራኒ ቅናሽ አሳይቷል። በ1999 ከአጠቃላይ የሥራ ላይ ተሳታፊ ወጣቶች ውስጥ 35 በመቶ የሚሆኑት ከ15-24 ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሲሆን ይህ ቁጥር በ2011 ግን ወደ 28 በመቶ ወርዷል። ለዚህ ሁኔታ ዋነኛው ምክንያት የወጣቶች የትምህርት ተሳትፎ መጨመሩ መሆኑም ታውቋል።

የወጣቱ የሰው ኃይል ገበያ አሳሳቢና ትኩረትን የሚፈልግ ጉዳይ ነው። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት እንደኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች የህዝብ ስብጥር እንደሚያሳየው አብዛኛው ሕዝብ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ጥቂት ብቻ በሽምግልና ዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ። ይህም የህዝብ ስብጥር የፒራሚድ ቅርፅ ይዞ ይታያል (ምስል 1)።

**ምስል 1፡** <u>የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት ስብጥር በዕድሜ ክልሎች</u>



በኢትዮጵያ የሰው ኃይል ገበያን በተመለከተ ያለው አስደናቂ እውነታ ወደ ገበያው የሚገባው የሰው ኃይል ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሔድ ነው። በአገሪቱ ያለው የወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ የሥራ ኃይል ቁጥር ዕድገቱ ከጠቅላላው የአገሪቱ ህዝብ ብዛት ዕድገት መጠን የላቀ ነው። ከጠቅላላው ህዝብ ውስጥ የወጣቶች የቁጥር ድርሻ ከፍ ያለ መሆኑ በሰው ኃይል ገበያው ላይ የራሱ ጫና እንደሚኖረውና እንዲሁም እያደገ የመጣው የወጣቶች ቁጥር በሥራ አጥነት ችግር ላይም የራሱ የሆነ ተፅእኖ እንደሚኖረው ይታመናል።

## 2.2 የወጣቶች ሥራ አጥነት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ወጣቶች በሥራ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ሲሆን የወጣቶች የሥራ አጥነት መጠንም ከፍተኛ የሚባል ነው። እንዲሁም ወጣቶች ኢ-መደበኛ በሆነው የሥራ መስክ ያላቸው ተሳትፎ ከጠቅላላው የአገሪቱ አማካይ መጠን ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ሊባል የሚችል ነው። ይህም የአገሪቱ ከተሞችም ሆነ ገጠራማ አካባቢዎች መገለጫ ነው።

በ2005 ዕድሜያቸው ከ15-24 ካሉ ወጣቶቸ መካከል 79 በመቶ የሚሆኑት በሥራ ገበያው ውስጥ ተሳታፊ ሲሆኑ፤ ከ15-29 ዓመት ያሉት ወጣቶች የተሳትፎ መጠን ደግሞ ወደ 82 በመቶ ይጠጋል። ይህም የወጣቶች የሥራ ገበያ ላይ ተሳትፎ ከዕድሜ ጋር አብሮ እንደሚጨምር ያመላክታል። ዝቅተኛው የሥራ ገበያ ተሳትፎ መጠን ደግሞ ዕድሜያቸው ከ15-19 ባሉት ታዳጊ ወጣቶች የተመዘገበው (33 በመቶ) ሲሆን፤ ከፍተኛው ተሳትፎ ደግሞ ዕድሜያቸው ከ25-29 ባሉ ወጣት ወንዶችና (93 በመቶ) በተመሳሳይ ዕድሜ (25-29) ክልል ባሉ ወጣት ሴቶች (76 በመቶ) የተመዘገበው ነው (CSA, 2011)።

ከታች በምስሉ እንደተመለከተው ከ15-24 ዓመት ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የሥራ አጥነት መጠን ከአገር አቀፍ አማካይ የሥራ አጥነት መጠን በ7.4 በመቶ ከፍ የሚል ሲሆን፤ እንዲሁም ዕድሜአቸው ከ15-29 ላሉት ደግሞ የሥራ አጥነት መጠን ከአገር አቀፍ አማካይ በ7 በመቶ ከፍ ይላል። ከችሎታ ወይም ከአቅም በታች በሆኑ ሥራዎች ውስጥ በመሠማራት በኩል ዕድሜያቸው ከ15-24 ላሉት ከአገር አቀፍ አማካዩ በ25 በመቶ ዝቅ የሚል ሲሆን፤ ከ15-29 ዓመት ላሉት ደግሞ ከአገር አቀፍ አማካይ ጋር ሲነፃፀር በ27 በመቶ ዝቅ ይላል።

በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወጣቶች ከዐዋቂዎች ጋር ሲነጻጸሩ የሚኖራቸው የሥራ ልምድ አነስተኛ ስለሚሆን፤ ከሁለት-ሦስት እጥፍ ከዐዋቂዎች በላቀ ሥራ አጥ የመሆን ዕድል አላቸው። በተጨማሪም ወጣቶች መደበኛ በሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ ለመሠማራት በርካታ እንቅፋቶች ይገጥሟቸዋል።

በኢትዮጵያ ሥራ አጥነት ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል በላቀ ወጣቶችን ያጠቃል:: ለበርካታ አስርተ-ዓመታት በአገሪቱ የነበረው የወጣቶች የሥራ አጥነት መጠን ከጠቅላላው ህዝብ የሥራ አጥነት መጠን ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ ነበር:: በዕድሜ መደብ ሲነፃፀር፤ በ1984 በአብዛኛው ታዳጊ ወጣቶች ሥራ አጥ የነበሩ ሲሆን በ1994 እና በ1999 ግን በአብዛኛው ዕድሜያቸው ከፍ ያሉ ወጣቶች ሥራ አጥ ሆነዋል:: በ1984 ከ15-29 ዓመት ያሉ ወጣት ሥራ አጦች ከአጠቃላዩ ሥራ አጥ ቁጥር የ52 በመቶ ድርሻ የነበራቸው ሲሆን፤ በ1994 የ67 በመቶ፣ በ1999 ደግሞ የ57 በመቶ ድርሻ ይዘዋል::

ለወጣት ወንዶች የሥራ አጥነት መጠኑ ዕድሜ ሲጨምር የሚቀንስ ሲሆን በ2011 የታዳጊ ወንድ ወጣቶች የሥራ አጥነት መጠን 23 በመቶ ነበር:: ዕድሜያቸው ከ25-29 ላሉት ወንድ ወጣቶች ግን መጠኑ ወደ 11 በመቶ ይወርዳል:: ለሴት ወጣቶች ግን በዕድሜና በሥራ አጥነት መካከል ግልፅ የሆነ ግንኙነት አይታይም::

በኢትዮጵያ ውስጥ ለአጭር ጊዜ የሚቆይና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሥራ አጥነት ችግር አለ:: ለአጭር ጊዜ የሚቆየው የሥራ አጥነት ችግር በተለይ ታዳጊዎችን ያጠቃል:: ነገር ግን ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ካላቸው ዐዋቂዎች ጋር ሲነጻጸር ታዳጊዎች ሥራ አጥ ሆነው የሚቆዩት አጠር ላለ ጊዜ ነው::

ወጣቶች በሥራ አጥነት የቆዩበት ጊዜ መርዘም የወጣቶችን የሥራ ገበያ ውድቀት ያመላክታል:: ከዚህ አንፃር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ከሁለት ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ በሥራ አጥነት የሚቆዩ ሲሆን ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ደግሞ በ6 ወራት ውስጥ ሥራ ያገኛሉ:: ከ1999-2004 በነበረው ጊዜ ውስጥ ሥራ አጥ ከነበሩት ወጣቶች መካከል 49.2-64.6 በመቶ የሚሆኑት ከ12 ወራት ለበለጠ ጊዜ በሥራ አጥነት ቆይተዋል::

በአማካይ በኢትዮጵያ በከተሞች አካባቢ ያለው የሥራ አጥነት ጊዜ ከአንድ ዓመት የላቀ ነው (Serneels, 2007):: 38 በመቶ ገደማ የሚሆነው በከተሞች አካባቢ ያለው ሥራ አጥ ከ1-6 ወራት ሥራ አጥ ሆኖ የሚቆይ ሲሆን፤ 25 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ከአንድ ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ በሥራ አጥነት ይቆያል (CSA, 2005)::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወጣቶች በሥራ አጥነት ረጅም ጊዜ በቆዩ ቁጥር እንደ ወጣት ጥፋተኝነት፣ የዕፅ ሱሰኝነት፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ ልመና፣ ጎዳና ተዳዳሪነትና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጠቂነት ወደ መሳሰሉት ማኅበራዊ ቀውሶች ውስጥ የመዘፈቅ ዕድላቸው ይጨምራል:: ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ የረጅም ጊዜ ሥራ አጥነት መኖር እንዲሁም ረጅምና አድካሚ የሆነው የሥራ ፍለጋ ሂደት ወጣቶች በህይወታቸው ደስተኛ እንዳይሆኑና ሞራላቸው እንዲወድቅ ምክንያት ይሆናል::

እንዲሁም በሥራ አጥነት የሚዎዩበት ጊዜ በረዘመ ቁጥር የወጣቶችን በራስ መተማመን ከመሸርሸሩ ባሻገር ችሎታንና አቅምን የማሳጣት ተፅዕኖ ይኖረዋል ።

## 2.3 የወጣቶች ሥራ አጥነት ገፅታዎች

በወጣቶች ሥራ አጥነት ላይ የቀረቡ ጥቅል አኃዞች በመኖሪያ አካባቢ፣ በጾታ እንዲሁም በትምህርት ደረጃ ሲነጻጸሩ በወጣቶች መካከል ያለውን ከፍተኛ የሥራ አጥነት ልዩነት በግልጽ አያሳዩም። ነገር ግን የተለያዩ መረጃዎችን በማመሳከር የወጣት ሥራ አጥነትን በነዚህ መስፈርቶ አንፃር ምን እንደሚመስል ቀጥሎ ለመመልከት እንሞክራለን።

### ሀ) ሥራ አጥነት በከተማና በገጠር

እንደጠቅላላው ህዝብ ሁሉ አብዛኛው ወጣት የህብረተሠብ ክፍል የሚኖረው በገጠር አካባቢ ነው። በገጠር አካባቢ የሚኖረው ወጣት ከጠቅላላው የገጠር ነዋሪ 77 በመቶ የሚሆነውን ክፍል ይሸፍናል። ነገር ግን አብዛኛው ወጣት አሁንም በገጠር አካባቢ ቢኖርም፣ በከተማ ያለው የወጣት ቁጥር ባለፉት ሁለት አስርተ-አመታት ጨምሯል። በዚህ መሠረት በ1984 በከተማ ያለው ወጣት ቁጥር 14 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2007 ግን ወደ 23 በመቶ ከፍ ብሏል።

የከተማና የገጠሩን ሁኔታ ነጣጥለን ስንመለከት በገጠርና በከተማ በሚኖሩ ወጣቶች መካከል እንዲሁም በወጣቶች በዐዋቂዎች መካከል ከፍተኛ ልዩነቶች ይስተዋላሉ። በገጠር ያሉ ወጣቶች በሰው ኃይል ገበያው ላይ ያላቸው የተሳትፎ ድርሻ ከከተማው ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ የሚባል ነበር። 2005 ዓ.ም 84 በመቶ የሚሆኑ ከ15-24 የዕድሜ ክልል የሚገኙ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ሥራዎች ውስጥ ሲሳተፉ፤ በተመሳሳይ ወቅት በከተማ የሚኖሩ ወጣቶች ተሳትፎ 57 በመቶ ብቻ ነበር። በከተማና በገጠር መካከል ለሚታየው ከፍተኛ የሥራ ተሳትፎ ልዩነት ዋነኛ ምክንያት በከተማና በገጠር መካከል ያለው የወጣቶች የትምህርት ተሳትፎ ድርሻ ልዩነት ነው። በገጠር አካባቢዎች ያለው ውስን የትምህርት ዕድል እና ከፍተኛ የድህነት መጠን በገጠር የሚኖሩ ወጣቶች በሥራ ኃይል ውስጥ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው አስገድዷቸዋል (Denu et.al., 2005)።

በሁለተኛ ደረጃ በከተማና በገጠር የሚስተዋለው ልዩነት፤ በገጠር ያሉ ወጣቶች የሥራ (የሰው ኃይል) ገበያ ተሳትፎ ከዐዋቂዎች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፤ በከተማ የሚኖሩ ወጣቶች ግን በከተማ ካለው ዐዋቂ ህብረተሠብ ጋር ተመሳሳይ የሰው ኃይል ገበያ ተሳትፎ የላቸውም። በከተማ ያሉ ወጣቶች አነስተኛ የሥራ ኃይል ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን፤ በሥራ ላይ የተሠማራው ወጣት ከጠቅላላው የወጣት ቁጥር ጋር ሲነፃፀር

ድርሻው አነስተኛ ነው። 2011 ዕድሜያቸው ከ15-24 የሆኑ ወጣቶች በሥራ ኃይል ውስጥ የነበራቸው የተሳትፎ መጠን ከጠቅላላው በከተማ ካለው አማካይ የተሳትፎ መጠን በ20 በመቶ ያነሰ ሲሆን; ዕድሜያቸው ከ25-29 ያሉትን በተመለከተ ግን የተሳትፎው መጠን ከጠቅላላው በከተማ ካለው የተሳትፎ መጠን ጋር ሲነፃፀር የሚያንሰው በ9 በመቶ ብቻ ነው። በተመሳሳይ ወቅት በከተማ የነበረው የወጣቶች የሥራ ስምሪት ከጠቅላላው የከተማ አማካይ የሥራ ስምሪት ከ11-21 በመቶ ያነሰ ነበር።

የከተማ ወጣቶች የሥራ አጥነት መጠን ከጠቅላላው የከተማ ነዋሪ የሥራ አጥነት መጠን ጋር ሲነፃፀር ከ6-10 በመቶ ከፍ ያለ ነበር። በኢትዮጵያ ከገጠር ወደ ከተማ ባለው የሰው ኃይል ፍልሠት የተነሳ በከተማ ውስጥ ያለው የሥራ አጥነት መጠን እጅግ አስከፊ ነው። ወቅት እየተጠበቀ ብቻ የሚሠማሩበት የግብርና ሥራ ዋነኛ መተዳደሪያ በሆነባቸው በኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢ የሚኖሩ በርካታ ሰዎች የተሻለ የሥራ ዕድልን ፍለጋ ወደ ከተማ ይፈልሳሉ። በተጨማሪም በገጠር አካባቢዎች ለተመዘገበው አነስተኛ የሥራ አጥነት መጠን ሌላው ምክንያት በገጠር ያሉ ወጣቶች ከአቅማቸው ወይም ከችሎታቸው በታች በሆኑ የሥራ ዘርፎች ላይ መሠማራታቸውና በዚህም እንደባለሥራ መቆጠራቸው ነው።

### ለ) ሥራ አጥነት ከሥነ-ጾታ አንፃር

በኢትዮጵያ ያለው የሰው ኃይል ገበያ በሴትና ወንድ ወጣቶች መካከል ልዩነትን ያሳያል። በሥራ ኃይል ውስጥም በሴትና ወንድ መካከል ያለው ልዩነት በወጣቶችና በዐዋቂዎች መካከል ካለው ልዩነትም በጣም የሰፋ ነው። በጥቅሉ በሥራ ኃይል ውስጥ የወንዶች ተሳትፎ ከሴቶች ተሳትፎ የላቀ ሲሆን በ2005 የሚሆኑ ዕድሜያቸው ከ15-29 የሆኑ ሴቶች በሥራ ኃይል ውስጥ የ79 በመቶ ተሳትፎ የነበራቸው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ወቅት የወንድ አቻዎቻቸው የተሳትፎ መጠን ግን 86 በመቶ ነበር። ይህ መጠን በወንዶች በኩል በ1999 ከነበረበት የ87 በመቶ መጠነኛ ቅናሽ (2 በመቶ) ያሳየ ሲሆን፤ በሴቶች በኩል ግን በተመሳሳይ ወቅት ከነበረበት የ75 በመቶ የ4 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ከላይ የተጠቀሱት በወጣት ወንዶች እና በወጣት ሴቶች መካከል ያሉት ልዩነቶች በሥራ ላይ ከመሠማራትና ከሥራ አጥነት አኳያ ሲታዩ ልዩነታቸው የበለጠ ይጎላል። በ1999 የነበረውን የሥራ አጥነት መጠን ስንመለከት በወቅቱ የነበረው የወጣት ሴቶች የሥራ አጥነት መጠን 17.3 በመቶ ሲሆን፤ የወንድ አቻዎቻቸው ግን 6.9 በመቶ ብቻ ነበር። በዚህ ወቅት በከተማ የሚኖሩ ሴት ወጣቶች የሥራ አጥነት መጠን 27.2 በመቶ የነበረ ሲሆን፤ የወንድ አቻዎቻቸው ደግሞ 13.7 በመቶ ነበር። ይህም ምን ያህል በከተማ የሚኖሩ ሴት ወጣቶች ከወንድ አቻዎቻቸው በላቀ ለሥራ አጥነት

ችግር ተጋላጭ እንደሆኑ ያመለክታል። ከላይ የተመለከተው ልዩነት ከሌሎች ምክንያቶች በተጨማሪ የሴቶችን በቂ የትምህርት ዕድል ያለማግኘትና ተሳትፏቸው በአብዛኛው ኢ-መደበኛ በሆኑ የሥራ ዘርፎች ላይ መሆኑን ያሳያል።

የወንድና ሴት ወጣቶችን የትምህርት ሁኔታ ስንመለከት 71 በመቶ የሚሆኑት ሴት ወጣቶች ያልተማሩ ሲሆኑ የወንድ አቻዎቻቸው መጠን ግን 51 በመቶ ብቻ ነው። ሴቶች ከወንዶች ቀድመው ወደትዳር መግባታቸው በተቃራኒ ፆታዎች መካከል እኩል ተጠቃሚነት ያለመኖሩን ያንጸባርቃል። ከዚህ አንጻር በመጀመሪያ ደረጃ ሴቶች ሲያገቡ ከሰው ኃይል ገበያው እንደሚወጡና በርካታ የሆኑ ያለምንም ክፍያ የቤት ሥራ የሚሠሩትን ሴቶች የሚገልጽ ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሴቶች በጊዜ እናገባለን ብለው ማሰባቸው ወደትምህርት እንዳያዘነብሉ ያደርጋቸዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚከሰተው የሴቶች ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ደግሞ ለሴቶች ከፍተኛ ሥራ አጥነት ችግርና በአብዛኛው መደበኛ ባልሆነው (ኢ-መደበኛ) የሥራ ዘርፍ እንዲሣተፉ ምክንያት ሊሆን ይችላል። በኢ-መደበኛው የሥራ ዘርፍ ከተሠማራው የሰው ኃይል ውስጥ 70 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ወጣት ሴቶች ከኢ-መደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ የቤት ውስጥ ሥራ ይሠራሉ።

ከ1999 ጀምሮ በገጠርና በከተማ ያሉ ወጣት ሴቶችና ወንዶች በሰው ኃይል የሥራ ገበያ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ እየተሻሻለ መጥቷል። በ2005 በሥራ ላይ ያሉ ወጣት ወንዶች መጠን 83 በመቶ ሲሆን የሥራ አጦቹ መጠን ደግሞ 4 በመቶ ብቻ ነበር። ለሴቶቹ ደግሞ 71 በመቶ የሚሆኑት በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን 11 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ሥራ አጥ ነበሩ።

የገጠሩ ሠራተኛ ከገጠሩ ነዋሪ ጋር ሲነፃፀር ቁጥሩ የጨመረ ሲሆን የሥራ ፈቱ ቁጥር ደግሞ ቀንሷል። በገጠር አካባቢ ለሚኖሩ ወጣት ወንዶች ዋነኛው ችግራቸው ከአቅም በታች መሥራት ሲሆን በዚህም ረገድም ቢሆን ከ1999-2005 ባሉት ዓመታት ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል። በ1999 ዓ.ም 56 በመቶ የሚሆኑ በሥራ ላይ ያሉ ወጣት ወንዶች ከሚፈልጉትና ከሚችሉት የሥራ ሠዓት በታች ይሠሩ የነበር ሲሆን በ2005 ግን ይህ ቁጥር ወደ 30 በመቶ ዝቅ ብሏል።

በከተማ ለሚኖሩ ወጣት ወንዶች የሰው ኃይል ተሳትፎ መጠን የቀነሰ ሲሆን ይህም የሆነው በኢትዮጵያ የትምህርት ተሳትፎ በመጨመሩና ወጣቶችም ክህሎታቸውን ለማዳበር ሲሉ ወደ ሰው ኃይል ገበያው ዘግይተው መግባት በመጀመራቸው ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በሥራ ላይ ባለው ሕዝብ መጠን ላይ ግን ያን ያህል መቀነስ አልታየም። ሆኖም ግን ሥራ አጥነት በሚገባ ቀንሷል። በከተሞች አካባቢ በሥራ ላይ ያሉ ወጣት ወንዶችም በኢ-መደበኛው የሥራ ዘርፍ ላይ ያላቸው ተሳትፎ ቀንሷል። በ2011 ዓ.ም 29 በመቶ ብቻ የሚሆኑ በከተሞች አካባቢ ያሉ ወጣት ወንዶች በኢ-

መደበኛው የሥራ ዘርፍ ላይ የተሠማሩ ሲሆን ይህም ቁጥር በ1999 ከነበረው ጋር ሲነጻጸር በ22 በመቶ ቀንሷል።

ለሴቶችም ተመሳሳይ ሁኔታ የታየ ሲሆን የገጠሩንና የከተማውን ሁኔታ ተለይቶ ሲታይ ግን በጾታ ልዩነቱ ጉልህ ይሆናል። ምንም እንኳን የሥራ አጥነት ችግር በገጠሩ አካባቢ ዝቅተኛ ቢሆንም በ2005 የወጣት ሴት ሥራ አጦች መጠን ስድስት በመቶ ሲሆን የወንዶቹ ግን አንድ በመቶ ብቻ ነበር። በከተሞች አካባቢ ደግሞ የወጣት ሴቶች ሁኔታ የከፋ ነው። በ2011 የከተሞች አማካኝ ሥራ አጥ መጠን 18 በመቶ የነበረ ሲሆን የወጣት ሴት ሥራ አጦች መጠን 30 በመቶ ሲሆን ከወንዶቹ በ14 በመቶ ይበልጥ ነበር። በተጨማሪም ሴቶች በአብዛኛው በኢ-መደበኛው የሥራ ዘርፍ ላይ የሚሳተፉ ሲሆን በ2011 ዓ.ም 41 በመቶ የሚሆኑ በሥራ ላይ ያሉ ሴቶች መደበኛ ያልሆነ (ኢ-መደበኛ) ሥራ ይሰሩ ነበር።

### ሐ) ሥራ አጥነትና ትምህርት

በኢትዮጵያ የተማሩ ወጣቶች ቁጥር (literacy rate) ዝቅተኛ ሲሆን በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ልዩነትም ሰፊ ነው። ወንድ ወጣቶች ከሴት አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀሩ የተሻለ የትምህርት ደረጃ አላቸው። አብዛኛዎቹ ሴቶች ያልተማሩ የመሆን ዕድላቸው እጅግ ሰፊ ሲሆን መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ወይም ከፍተኛ ትምህርት የማጠናቀቅ ዕድላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው። በርካታ በከተማ የሚኖሩ ሴቶች መደበኛ ትምህርት የመማር ዕድል ሳያገኙ ሊቀሩ የሚችሉ ሲሆን፤ ከአንደኛ ደረጃ የዘለለ ትምህርት የሚኖራቸውም ውስን ናቸው። ይህም ሆኖ የአንደኛ ደረጃና ጠቅላላ ትምህርትን የማጠናቀቅ ሁኔታ መጠን በወጣት ወንዶችና ሴቶች መካከል ሲታይ ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን። በከተማና በገጠር ያለውን የትምህርት ሁኔታ ስናነፃፅር ደግሞ በከተማ አካባቢ ያሉ ወጣቶች በገጠር አካባቢ ካሉት የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሲሆን በከተማ ወጣት ወንድና ሴት ወጣቶች መካከል የሚታየው የትምህርት ደረጃ ልዩነት በገጠርም በተመሳሳይ ሁኔታ ይንፀባረቃል።

ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ያለው የትምህርት ሽፋን መጠን በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል። ተማሪዎች ቅበላ መጠን በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች በከፍተኛ ቁጥር ያደገ ሲሆን በአገሪቱ የሚገኘው አጠቃላይ የተማረ የሰው ኃይል ቁጥርም ጨምሯል። በተለይም በቅርብ አመታት ውስጥ የወጣቶች የተማረ የሰው ኃይል መጠን በከፍተኛ ቁጥር አድጓል። በተለያየ የትምህርት ገበታ ላይ የሚገኘው ወጣት ቁጥር ድርሻ ከ1999-2011 ባለው ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል።

በ1999 ዕድሜአቸው ከ15-29 የሆኑ ኢትዮጵያዊያን መካከል 61 በመቶ የሚሆኑት ከመጀመሪያ ደረጃ ያልዘለለ የትምህርት ደረጃ የነበራቸው ሲሆን የመለስተኛ ሁለተኛ

ደረጃ ያጠናቀቁት ብዛት ደግሞ 18 በመቶ ብቻ ነበር፡፡ በ2011 ከመጀመሪያ ደረጃ ያልዘለለ ትምህርት ያላቸው ወጣቶች ድርሻ ወደ 51 በመቶ የወረደ ሲሆን ቢያንስ ሁለተኛ ደረጃን ያጠናቀቁ ወጣቶች ድርሻ ደግሞ ወደ 37 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ ከሁሉም በላይ አስደናቂ ለውጥ የተመዘገበው ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የሚተሳተፉትን ሰዎች በተመለከተ ነው፡፡ በ1999 ዓ.ም 4 በመቶ ብቻ የሚደርሱ ወጣቶች ከፍተኛ ትምህርት የቀሰሙ ሲሆን ይህ ቁጥር ግን በ2011 ወደ 20 በመቶ አድጓል፡፡

እንደ ከተማ ባይሆንም በገጠርም የትምህርት ተሳትፎ መሻሻል የተመዘገበ ሲሆን ከ1999-2005 ባሉት ዓመታት በገጠር የመፃፍና የማንበብ መጠን (literacy rates) እና የመጀመሪያ ደረጃን የሚከታተሉ ወጣቶች ቁጥር ጨምሯል፡፡ ነገር ግን ከመጀመሪያ ደረጃ በላይ ያለው ተሳትፎ መጠን ግን እምብዛም አልጨመረም፡፡ ይህ በትምህርት ተሳትፎ በኩል የታየው መሻሻል ቀደም ሲል ወጣቶች ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸው ሲጨምር በሥራ ገበያው ውስጥ ያላቸው የተሳትፎ መጠን ይቀንሳል የሚለውን መደምደሚያ የሚደግፍ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ብዛት ያላቸው ሰዎች ያለምንም ወይም ጥቂት መደበኛ ትምህርት ብቻ ይዘው የሥራ ገበያውን ይቀላቀላሉ፡፡ ያለመማር ከአቅም በታች እና በኢ-መደበኛ የሥራ ዘርፍ ለመሠማራት ዋናው ምክንያት ነው፡፡ ትምህርት ሰዎች የሚሠማሩበትን የሥራ ዘርፍ ስለሚወስን የሰው ኃይሉን ወደ ሥራ መሠማራት ለማረጋገጥና ምርታማነቱን ለመጨመር አይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡ ሰዎች ብዙ በተማሩ ቁጥር ገቢ በማያስገኙ ሥራዎች ላይ የመሠማራት ዕድላቸው ዝቅተኛ ሲሆን፤ ካልተማሩት አቻዎቻቸው ጋር በንፅፅር ከፍ ያለ ክፍያ ባላቸው ሥራዎች ላይ የመሠማራት ዕድላቸውም ይጨምራል፡፡

በሥራ ገበያው ሁኔታና በትምህርት መካከል ያለው ግንኙነት አስደናቂ ነው፡፡ ከ1999-2011 ያለውን የትምህርት ተሳትፎ እና የሥራ አጥነት መረጃን ስንመለከት ከትምህርት ደረጃ መጨመር ጋር ተያይዞ የሥራ አጥነት መጨመርን መታዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ዓይነት ከትምህርት ደረጃ ጋር አብሮ የሚከሰት የሥራ አጥነት ችግር "የተማረ የሰው ኃይል የሥራ አጥነት ችግር" (educated unemployment) በመባል ይታወቃል፡፡ ይህም የሚሆነው የገበያው የሰው ኃይል ፍላጎት ከተማረውና ከሠለጠነው የሰው ኃይል ጋር ሳይመጣጠን ሲቀር ነው፡፡ ከትምህርት ደረጃ መጨመር ጋር አብሮ የሚጨምረው የሥራ አጥነት ችግር በብዙ ታዳጊ አገሮች ጎልቶ ይታያል፡፡

ከትምህርት ደረጃ መጨመር ጋር አብሮ የሚጨምረው የሥራ አጥነት ችግር በተለይ ከ15-19 ዕድሜ ክልል የሚገኙ ታዳጊዎችን ያጠቃል፡፡ በዚህ የዕድሜ ክልል ያሉ ታዳጊ ወጣቶች የትምህርት ደረጃቸው እየጨመረ ሲሄድ በሰው ኃይል ገበያው ላይ

ያላቸው ተሳትፎ ይቀንሳል። ይህም የሚያሳየው ብዙዎቹ ትምህርታቸውን አለመጨረሳቸውን ነው። ታዳጊ ወንድ ልጆች የትምህርት ደረጃቸው ከፍ ሲል ሥራ አጥ ሆነው የሚቆዩበት ጊዜ ይቀንሳል። ነገር ግን ይህ ሁኔታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያልጨረሱትን አይገልጽም።

ከትምህርት ደረጃ መጨመር ጋር አብሮ የሚጨምረው የሥራ አጥነት ችግር በሴቶች ላይ በብዛት አይታይም። የሴቶች ትምህርት ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ የሥራ አጥነት መጠናቸውም ይቀንሳል። ይህ ችግር በዕድሜ ተከፋፍሎ ሲታይ ከ20-25 ዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣት ሴቶች የትምህርት ደረጃቸው እየጨመረ ሲሄድ ሥራ አጥ ሆነው የሚቆዩበት ጊዜ የሚቀንስ ሲሆን ከ25-29 ዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣት ሴቶች ግን የትምህርት ደረጃቸው ሲጨምር ሥራ አጥ ሆነው የሚቆዩበት ጊዜ አብሮ ይጨምራል።

በአጠቃላይ ከ1999-2011 ባለው ጊዜ ውስጥ የሥራ አጥነት ሁኔታ ለውጥ አሳይቷል። በ1999 የነበሩት ወጣቶች በ2011 ከነበሩት ወጣቶች ጋር ሲነጻጸሩ ሥራ አጥ የመሆን ዕድላቸው አነስተኛ ነበር። ይህም የሚያመ|ክተው ያለው የሥራ ገበያ ፍላጎት (በተለይም ከፍተኛ ትምህርትና የሥልጠና ደረጃ የሚጠይቅ የሥራ ገበያ ፍላጎት) እየጨመረ ካለው የትምህርት መስፋፋት ጋር እኩል መራመድ አለመቻሉን ነው።

እንደሚታወቀው ትምህርት የሥራ ሁኔታን ይወስናል። ቀደም ባሉት ዓመታት በአብዛኛው ሥራ አጥ ያልተማረው ሕዝብ የነበረ ሲሆን ከጊዜ በኋላ ግን አብዛኛው ሥራ አጥ የተማረው የህብረተሠብ ክፍል ሆኗል። ለምሳሌ በ1980ዎቹ እና 1990ዎቹ አስርተ-ዓመታት ከ7-8 በመቶ የሚሆነው ሥራ አጥ ያልተማረ ነበር። ነገር ግን የ2005 መረጃ እንደሚያሳየው 7.8 በመቶ የሚሆነው ሥራ አጥ የተማረ ሲሆን፤ ያልተማረው ሥራ አጥ ቁጥር ወደ 3.5 በመቶ ወርዷል። የተማረ ከሚባለው ህብረተሠብ ውስጥ ቁጥሩ የሚበዛው ሥራ አጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያልጨረሱ፣ የጨረሱና የመሠናዶ ትምህርት ብቻ ያላቸው ናቸው።

ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የጨረሱ ሥራ አጦች ቁጥር መብዛት ነው። በ1984 20 በመቶ የነበረው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጨረሱ ሥራ አጦች ቁጥር በ1994 ወደ 28.3 በመቶ ያደገ ሲሆን፤ በ2005 ደግሞ ወደ 28.8 በመቶ ከፍ ብሏል። በተጨማሪም ከፍተኛ የሥራ አጥ ቁጥር የተመዘገበው መካከለኛ የትምህርት ደረጃ ባላቸው ሰዎች ላይ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በጨረሱና ከ9-10ኛ ክፍል የተማሩ ወጣቶች የሥራ አጥነት ችግር ዋናው ሠለባ ሲሆኑ፤ ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ወጣቶች ግን ብዙ ጊዜ የችግሩ ሠለባ ሲሆኑ አይስተዋልም። ይህም የሚያሳየው ምንም እንኳን

ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም ትምህርት የሥራ ሁኔታ ላይ አመርቂ ውጤት እንዳለው ነው፡፡

መካከለኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሰዎች (የአንደኛ ደረጃ ትምህርተ የጨረሱ ነገር ግን ከ10ኛ ክፍል በላይ ያልተማሩ) የሥራ አጥነት ችግር ዋና ሠለባ መሆናቸው አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የሚያመላክተው በትምህርት ሥርዓቱና የሥራ ገበያው በሚፈልገው የሙያ (ክህሎት) መካከል መጣጣም አለመኖሩን ነው፡፡

## 2.4 የወጣቶች የሥራ ሁኔታ በኢትዮጵያ

ከ1974-1991 በነበረው የደርግ የሶሻሊስት ሥርዓት ዘመን የሥራ ዕድገት ይወሰን የነበረው ሠፊ በነበረው የመንግሥት ክፍል ነበር፡፡ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በጥቃቅንና መደበኛ ባልሆኑ ሥራዎች የተወሰነ ሲሆን መደበኛ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ረገድ የነበረው ሚናም ውስን ነበር፡፡ በ1991 ከደርግ መንግሥት መውደቅ ጋር ተያይዞ በሠፈነው የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ መርህ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ሊስፋፋና አያሌ መደበኛ የሥራ ዕድሎችንም ሊፈጥር ችሏል፡፡

ነገር ግን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አሁንም በግብርን ላይ የተመሠረተ፣ አብዛኛው ህብረተሠብ በገጠር አካባቢ የሚኖርና በግብርናና በከብት እርባታ የሚተዳደር ነዉ፡፡ በመሆኑም ልክ እንደሌላው የህብረተሠብ ክፍል ሁሉ ከሶስት-አራተኛ በላይ የሚሆነው ወጣት በዚሁ አነስተኛ ውጤትና ገቢ ባለው የግብርና ሥራ ይተዳደራል፡፡ እንዲሁም ቀላል ቁጥር የሌለው ሰው የመንግሥት ተቀጣሪ ሲሆን በተለይም በኢንዱስትሪና በመንግሥት የሲቪል አስተዳደር ሥራ ላይ ተሠማርቶ ይገኛል፡፡ የኢንዱስትሪው ክፍል የማዕድንና ድንጋይ ማምረት፣ የማምረቻ (ማኑፋክቸሪንግ)፣ መብራት፣ ጋዝ፣ ውኃና የመሳሰሉት የሥራ አይነቶች ያካትታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አብዛኛውን ሠራተኛ ያቀፈው ማኑፋክቸሪንግ ነው፡፡ ኢንዱስትሪ መደበኛና በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ዘርፍ ስለሆነ የተሻለ የሥራ ሁኔታ አለው፡፡ እንደ ቱሪዝም፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛ (ኮሙኒኬሽን)፣ ጤና፣ ትምህርት፣ የመንግሥት አስተዳደር (የሲቪል አገልግሎት) የመሳሰሉትን የሚያካትተው የአገልግሎት ሠጪ ዘርፍ ሌላው አያሌ ሠራተኛ ያቀፈ የሥራ መስክ ነው፡፡ በማደግ ላይ ካለው አገልግሎት ሠጪ ዘርፍ ውስጥ የመንግሥት አስተዳደር (የሲቪል አገልግሎት) ብዛት ያለውን ሠራተኛ በማቀፍ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የሆነው በአዲሱ የፌዴራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ምክንያት በተለያዩ የክልል አስተዳደራዊ እርከኖች የተለያዩ የመንግሥት ጽ/ቤቶች በመመስረታቸው ሳቢያ ነው፡፡

የወጣቱ የሥራ ሁኔታ ከአጠቃላዩ የሕዝብ የሥራ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በንጽጽርም 1999 ከጠቅላላው ህዝብ ጋር ሲነጻጸር በግብርናና ኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ

ዘርፎች የተሠማራው ወጣት አንፃራዊ ቁጥር በመቶኛ ትንሽ ዝቅ ያለ ሲሆን በአገልግሎቱ ዘርፍ የተሰማራው ግን ከጠቅላላው መቶኛ ትንሽ ከፍ ያለ ነበር። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው ዋና ምክንያት በአንጻራዊ ብዛት ያለው ወጣት በከተማ አካባቢ ስለሚኖር ሲሆን በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች ከሌላው የህብረተሠብ ክፍል ጋር ሲነጻጸሩ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፉ ሥራ ፍለጋ በብዛት ወደከተሞች የመሰደድ ዕድላቸው ሠፊ ስለሆነ ነው።

የሥራ ሁኔታን ከግል ሁኔታ አንፃር ስንመለከተው በ2004 ከጠቅላላው የሠራተኛ ብዛት ጋር ሲነፃፀር ወጣቶች ይበልጥ ደሞዝ በማይከፈልበት የቤተሠብ ሥራና በግል ሥራ ላይ የተሠማሩ ሲሆን፤ በተቃራኒው በመንግሥትና በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ያላቸው ድርሻ አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ከ1990ዎቹ በፊት መንግሥት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው ለሚወጡ ወጣት ምሩቃን የሥራ ዕድል የሚያመቻችበት ሁኔታ ከቀረ በኋላ የወጣት ሥራ አጡ ቁጥር በ60 በመቶ ካሻቀበበት ሁኔታ ጋር ይገጣጠማል። ይህም ወጣቱ ወደ መደበኛ የሥራ ገበያ ዘልቆ የመግባት ችግር እንዳለበት ያመለክታል። ሌላው አስገራሚ ሁኔታ ከ1994-2004 ባሉት ዓመታት ደሞዝ በማይከፈልበት የቤተሠብ ሥራ ላይ ተሠማርቶ የነበረው የሰው ኃይል በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ነው። ከዚህ የሰው ኃይል ውስጥ አብዛኛው ጎልማሳ በመንግሥትና በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የታቀፈ ሲሆን አብዛኛው ወጣት ግን ከ17 በመቶ ወደ 31 በመቶ ባደገው የግል ሥራ ውስጥ ተካትቷል። ይህ ከፍተኛ ለውጥ ከመንግሥት መቀየርና ተያይዞ ከመጣው የፖሊሲ ለውጥ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ያታሠባል። ሌላው ለለውጡ ምክንያት ይሆናል ተብሎ የሚገመተው ቀደም ሲል ያለክፍያ ከቤተሠብ ጋር የሚሠሩ ሰዎች ምናልባት በኢ-መደበኛ ዘርፍ ተሠማርተው የነበሩና አሁን የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ሥራ ሲያገኙ ወደ ሌላ ዘርፍ የገቡ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ነው።

### ሀ) የውጭ አገር ሥራ ስምሪት

የኢትዮጵያውያን ዋና የውጭ አገር የሥራ ዕድል ወደሩቅ ምሥራቅ አገራት በመፍለስ የሚሠማሩበት የቤት ሠራተኛነት የሥራ ዘርፍ ነው። በውጭ አገር የሚሠሩ ዜጎች መብታቸው የሚከበር ከሆነ ወደአገር ውስጥ የሚልኩት የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት አንጻር ለአገሪቷ ዕድገት ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ የሚታወቅ ነው። የ2000 መረጃ እንደሚያሳየው ወደ ውጭ አገር በብዛት የሚሠደዱት በ20ዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገኙ፣ ወጣትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ሴቶች ነበሩ። ይህ መረጃ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በንጽጽር ሲታይ ግን አሁን በአብዛኛው የሚሠደዱት ታዳጊና አነስተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሴት ልጆች ሆነው ይገኛሉ።

## ለ) መደበኛ ያልሆነ (ኢ-መደበኛ) ሥራ

የአንድን ሥራ መልካምነት ከሚያሳዩ መመዘኛዎች አንዱ ሥራው መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ መሆኑ ሲሆን፣ ኢ-መደበኛ ሥራ ዝቅተኛ ውጤትና ገቢ ያለው እንደሆነ ይታሠባል:: መደበኛ ሥራ የተሻለ ጥራት ያለው እንደሆነ ቢገመትም በኢትዮጵያ ግን እስካሁን የፈጠረው የሥራ ዕድል ውስን ነው ። በመሆኑም ወደሰው ኃይል ገበያው የሚቀላቀሉ አዲስ ገቢዎች በብዛት ወደ ኢ-መደበኛው የሥራ ዘርፍ ለመግባት ይገደዳሉ:: በ1999 በግብርናና በቤት ሠራተኛነት ከተሠማራው ዜጋ ውጪ አንድ-አራተኛ የሚሆነው በሥራ ላይ ያለው ሕዝብ ብቻ በመደበኛው የሥራ ዘርፍ ላይ የተሠማራ ሲሆን ቀሪው ሦስት-አራተኛ የሚሆነው ግን መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ የተሠማራ ነበር:: በዚህ መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ ከተሠማራው ህብረተሠብ ውስጥ 32 በመቶ የሚሆኑት ወጣቶች ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ 31 በመቶ የሚሆኑት በከተማ የሚኖሩ ሲሆን፤ 69 በመቶ የሚሆኑት በገጠር አካባቢዎች ይኖራሉ::

መደበኛ ያልሆነው የሥራ ዘርፍ በተለይም በገጠሩ አካባቢ በሠፊው የተስፋፋ ሲሆን፤ በ1990 ዓ.ም. 90 በመቶ የሚሆነው በገጠር የሚገኘው ወጣት ሠራተኛ መደበኛ ባልሆነ ሥራ ተሠማርቶ ነበር:: ይህም የሆነው ለመደበኛ ሥራ አስፈላጊ የሆኑት እንደ የሥራ ዕድል፣ ትምህርትና የመሳሰሉት አገልግሎቶች በብዛት የሚገኙት በከተሞች አካባቢ ስለሆነ እንደሆነ ይታመናል::

በከተሞች አካባቢ በአብዛኛው መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የሚሠማሩት ታዳጊዎች ናቸው:: በንጽጽር 68 በመቶ የሚሆኑ ታዳጊዎች መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የተሠማሩ ሲሆን፤ 48 በመቶ ብቻ የሚሆኑ ወጣቶች መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ ተሠማርተዋል:: ይህም የሚያሳየው ታዳጊዎች መጀመሪያ ሥራ የሚያገኙት መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ ሲሆን ከጊዜ በኋላ ግን ወደ መደበኛ ሥራ እንደሚሸጋገሩ ነው::

መደበኛ ያልሆነውን የሥራ መስክ ከጾታ አንጻር ስንመለከት በኢትዮጵያ በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች በብዛት መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ ተሸማርተው እንደሚገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ:: ከ15-19 ዓመት ያሉ ታዳጊ ሴት ልጆች በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ከሚገኙ ታዳጊ ወንድ ልጆች ባነሰ መልኩ መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የተሸማሩ ሲሆን፤ ከ20-24 ዓመት ያሉ ወጣት ሴቶች ግን በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ከሚገኙ ወጣት ወንዶች በላይ መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ ተሰማርተዋል:: ይህም የሚያሳየው ታዳጊ ሴት ልጆች መደበኛ ሥራ የሚያገኙ ሲሆን ዕድሜያቸው ከፍ እያለ ሲሄድ ግን ወደ መደበኛ ወደአልሆነው የሥራ ዘርፍ እንደሚገቡ ነው::

# 3 በኢትዮጵያ ያሉ የወጣቶች የሥራ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች

የአገር ወስጥ የሠራተኛ ፍላጎትና አቅርቦት በወጣቶች ሥራ አጥነትም ሆነ ከአቅም በታች መሥራት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። ከሠራተኛ አቅርቦት አንፃር የሰው ኃይል መስተጋብር (demographic factors)፣ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች የራሳቸው የሆነ ተጽዕኖና አስተዋጽኦ አላቸው። ከሠራተኛ ፍላጎት አንፃር ሲታይ የኢኮኖሚው ሁኔታና ወደ ገበያ የሚገቡ ሠራተኞችን የመቀበል አቅሙ እንዲሁም የተቋማት ማደግና አዳዲስ የሥራ ዕድል ፈጣሪዎች የሠራተኛ ፍላጎት ላይ አስተዋፅኦ አላቸው። የሰው ኃይል ወይም የሠራተኛ ግብይትን እና ተቋማትን በተመለከተ የሚወጡ ፖሊሲዎች በሠራተኛ አቅርቦትና ፍላጎት መካከል የማሳለጥ ሥራ ይሠራሉ።

ይህም ክፍል የወጣቶች ሥራ ሁኔታን በተመለከተ በፌዴራል ደረጃ በአሁኑ ጊዜ በትግበራ ላይ ያሉ ፖሊሲዎችን ወይም እየተካሄዱ ያሉ ተግባራትን የሚገመግም ሳይሆን በወጣቱ ሥራ ላይ ያላቸውን ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተፅዕኖዎች መዳሰስ ብቻ ይሆናል።

## 3.1 የወጣት ሠራተኛ ግብይት ፖሊሲዎችና ተቋማት

ካለፈው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ ጀምሮ የተማረው ኃይል በኢትዮጵያ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ተሳትፎ ንቁና ከፍተኛ ሊባል የሚችል ነው። ሆኖም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የወጣቱን ጉዳይ በተመለከተ የተቀመጠ ፖሊሲ አልነበረም። የወጣቶች ጉዳይ በከፍተኛ የስልጣን እርከን ደረጃ ውስጥ የተዋቀረ ወይም በሚኒስቴር ደረጃ ራሱን የቻለ ጉዳይ ሆኖ አይታይም ነበር። ከዚያ ይልቅ በተበጣጠሰ ሁኔታ በተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ደረጃ የሚከናወን ጉዳይ ነበር።

ከ1990ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ የወጣቱን ጉዳዮች የሚያጎሉ አበረታች ክንውኖች እየተካሄዱ ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በ2001 የወጣቶች ጉዳይ በሚኒስቴር ደረጃ ትኩረት ተሠጥቶት በወጣቶች ስፖርትና ባሕል ሚኒስቴር ስር መካተቱ ነው። ይህም አካል የሚከተሉትን ጉዳዮች በተመለከተ ኃላፊነትና ስልጣን ተሰጥቶታል።

- የወጣቶችን ጉዳይ በተመለከተ የሚያስፈልጉ ረቂቅ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀትና ፖሊሲዎቹ ሲቀረፁ ተፈፃሚነታቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፤
- ጤናማና ኃላፊነት የሚሠማው ወጣት እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤
- ወጣቱ መንግሥትን መሠረት ያደረገ የዴሞክራሲያዊ ማኅበረሠብ ግንባታ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያስችሉ ድጋፎችን ማድረግ፤

- ወጣቱ በአገር ውስጥ ያሉ ዕሴቶችንና ባህሎችን እንዲያከብርና እንዲያስተዋውቅ ማበረታታት፡፡

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ይህ በሚኒስቴር ደረጃ የተቋቋመው ተቋምና በክልሎች ያሉት ጽህፈት ቤቶች የማስተባበር፣ የማቀናጀትና የፖሊሲዎችን ተፈፃሚነት የመገምገም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 3.2 ከወጣቶች የሥራ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የመንግሥት ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች

ኢትዮጵያ ከሠሀራ በታች ከፍተኛ የወጣቶች ቁጥር ካላቸው አገሮች ውስጥ አንዷ በመሆኗ እና አብዛኛዎቹ ወደ ሥራ የሚሠማሩት ወጣቶች ዝቅተኛ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው በመሆኑ ምክንያት የወጣት ሥራ አጥነት ከፍተኛ ትኩረት እየተሰጠው ይገኛል (Guarcello *et al.*, 2008)፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ መንግሥት ለወጣቶች ፖሊሲና ስትራቴጂ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቷል፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች በተለያዩ የመንግሥት ሠነዶች ውስጥ እንዲካተቱም ተደርጓል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋና ሠነዶች የፈጣንና ዘላቂ ልማት ድህነትን የማጥፋት ዕቅድ (2005/06-2009/10)፣ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ (2004)፣ የሠራተኞች ድንጋጌ (377/2003)፣ የ1994 የትምህርት ፖሊሲ፣ የወጣቶች ዕድገት ፓኬጅ (2006)፣ የኢንዱስትሪ ዕድገት አቅጣጫ ሠነድ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የማሳደግ አቅጣጫ ሠነድ፣ እና የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖሊሲ ይገኙበታል፡፡

### ሀ) በአምስት ዓመት የዕድገት ዕቅድ ውስጥ ያለ የወጣቶች ቅጥር (2005/06 - 2009/10)

የአምስት ዓመቱ የዕድገት ዕቅድ የኢትዮጵያ መንግሥት ያለውን ፖሊሲ ለማስፈፀም የሚጠቀምበት ዋነኛ መመሪያ ነው፡፡ ይህም ዕቅድ መንግሥት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እና ተያያዥ ፖሊሲዎችን ያካትታል፡፡ የአገሪቱ የዕድገት ዕቅድ የሚያተኩረው የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ እና በዘመናዊው፣ መደበኛ ባልሆነው እና በግብርናው ክፍል ኢኮኖሚ ውስጥ ገቢ ማስገኛ መንገዶች መፍጠር ላይ ነው፡፡ በዕቅዱ ሥራ አጥነትና ከአቅም በታች መሥራትን ከሴቶችና ከወጣቶች አንፃር አፅንኦት ተሠጥቶት የሚሰራበት ጉዳይ ነው፡፡

ከ2005/06-2009/10 ሲሠራበት የቆየው ‹‹የፈጣንና ዘላቂ ልማት ድህነትን የማጥፋት ዕቅድ›› ለሥራ አጥነት በተለይ ለወጣት ሥራ አጥነት ትኩረት የሠጠና ይህንንም በ2004 በወጣው ብሔራዊው የወጣቶች ፖሊሲ ውስጥ የወጣቶችን የትምህርት፣ ስልጠና እና የሥራ ሁኔታን የተመለከተ ክፍል በማካተት አሳይቷል (FDRE, 2004)፡፡ በዚህ ዕቅድ መሠረት ለወጣቱ የሥራ ዕድል መፍጠር ከስምንቱ ድህነትን

ለማጥፋት ከተቀመጡ የዕድገት ዕቅድ ምሶሶዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ከሚረዱ ነገሮች ውስጥ አንዱ የሰው ኃይል በብዛት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ነው፡፡ በተጨማሪም ሥራ አጥነት እና ከአቅም በታች መሥራት የሚያስከትሉትን ችግሮች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የህዝብ ቁጥር ዕድገትን መቆጣጠር ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

የፈጣንና ዘላቂ ልማት ድህነትን የማጥፋት እቅዱ የሥራ ዕድልን ከመፍጠር አንፃር ለግሉ የኢኮኖሚ ክፍል በተለይ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ትኩረት ይሠጣል፡፡ ይህም የሆነው እነዚህ ኢንተርፕራይዞች ሠፊ የሥራ ዕድልን ስለሚፈጥሩ ነው፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው በከተማ አካባቢ ለሚገኝ ሥራ አጥነት ችግር እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚታዩትን የትምህርት ጥራት ችግር እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ከኢኮኖሚው ፍላጎት ጋር ያለመጣጣም ችግርና መፍትሔዎች በዕቅዱ ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም ለሥራ አጥ ወጣቶች የክህሎት ሥልጠና መስጠትና በተለያዩ ህዝባዊ ሥራዎች ውስጥ ማሳተፍ በዕቅዱ ውስጥ እንደመፍትሔ ከተካተቱት ውስጥ ይገኙበታል (MoFED, 2006)፡፡

የአሁኑ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2010/11-2014/15) የወጣቱን የሥራ አጥነት ችግርን በቀጥታ ባያካትትም በተዘዋዋሪ ግን ይህን ችግር ለመፍታት ይረዳ ዘንድ የተለያዩ የኢኮኖሚውን ክፍሎች ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ይገልጻል፡፡ እንዲሁም ለግሉ የኢኮኖሚ ክፍል በተለይ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ትኩረት ይሰጣል፡፡ የእነዚህ ተቋማት ዕድገት ዋነኛው የድህነት መቀነሻና የሥራ ዕድል መፍጠሪያ መንገድ እንደሆነም ያምናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት የሥራ ገበያውን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዕድገትን ከፍ ሊያደርግ የሚችል የሰው ኃይል እንዲያመርቱ ያበረታታል፡፡ በተጨማሪም ዕቅዱ ሴቶችና ወጣቶች የሚደርሱባቸውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ይዳስሳል (MoFED, 2010)፡፡

### ለ) ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ

ኢትዮጵያ በ2004 ለመጀመሪያ ጊዜ ወጣቶችን የተመለከተ ብሔራዊ ፖሊሲ ነድፋለች፡፡ በዚህም መሠረት ወጣትነትን በ15-24 ዓመት የዕድሜ ክልል ከሚወስነው የተ.መ.ድ ትርጓሜ ሠፋ በማድረግ የኢትዮጵያ የወጣቶች ፖሊሲ ወጣት የሚባለው ከ15-29 ዓመት ያለ ግለሠብ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ብሔራዊ ፖሊሲው እንደ ሥራ ፈጠራ፣ ትምህርት፣ ማኅበራዊ አገልግሎት፣ ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስና የመሳሰሉትን ከወጣቶች ጋር የተያያዙ አንኳር ጉዳዮችን ይዳስሳል፡፡

ፖሊሲው ኢ-መደበኛው ዘርፍ ሠፊ የሥራ ዕድልን እንደሚፈጥር ጠቀሜ የሥራ አጥነትንና ከአቅም በታች የመሥራትን ችግሮች ለመፍታት የሚረዱ የመፍትሔ ኃሳቦችን ያቀርባል፡፡ ፖሊሲውን በተጠናከረ መልኩ በፍጥነት ሥራ ላይ ለማዋል የወጣቶች ልማት ፓኬጅ በ2006 ተቀርጿል፡፡

ፖሊሲው የወጣቱን የሥራ ፈጣሪነት ጉዳይ የሚዳስስ ሲሆን በተጨማሪም የግሉ ኢኮኖሚን የሥራ ዕድል የመፍጠር ዓቅምን የማሳደግና የወጣቱ የሥራ ዕድል መዳረሻ የመሆን ጉዳይን ይዳስሳል፡፡ ፖሊሲው የሥራ ዕድልን በራስ የመፍጠር እና የመደበኛና ኢ-መደበኛ የሥራ ዕድል ፈጠራን ያመቻቻል፡፡ በማኅበረሠቡ እና በተለይ ደግሞ በወጣቱ ዘንድ መንግሥትን እንደ ብቸኛ የሥራ አጥነት ችግር ፈቺ አካል አድርጎ የማየት አመለካከትን መቀየር ሌላው በፖሊሲው አፅንኦት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ፖሊሲው ወጣቶችን ሥራ ከመጠበቅ ይልቅ ሥራ ፈጠራ ላይ እንዲሠማሩ የሚያስችላቸውን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ላይ ያተኩራል፡፡ እንዲሁም የግል ክፍለ-ኢኮኖሚውን የሥራ ዕድል ፈጠራ ማበረታታትንና የወጣቱን በዚህ ዕድል የመሳተፍ ወይም ተጠቃሚ የመሆን ጉዳይ ማረጋገጥ ላይ ያተኩራል፡፡ ፖሊሲው በተለይም በክልሎችና ከተማዎች ዋነኛ የወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠርያ መንገድ ተደርገው የተወሰዱትን የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን የማሳደግ ጉዳይ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው፡፡

ፖሊሲው ከትምህርት ውጪ ያሉ፣ ትምህርታቸውን ያቋረጡ፣ ልዩ ክትትል የሚያስፈልጋቸውና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ወጣቶችን ‹‹ልዩ ትኩረት የሚሠጣቸው ክፍሎች›› በሚል ለይቶ ያስቀምጣቸዋል፡፡ ከትምህርት ውጪ ላሉ ወጣቶች የመፃፍና የማንበብ ችሎታቸውን፣ የስነ ዜጋና የስነ-ምግባር ዕውቀታቸውን የሚያሻሽል የትምህርት አገልግሎት እንዲዳብር የተመቻቸ መንገድ ለመፍጠር ያልማል፡፡ በተጨማሪም ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ወጣቶች የሚረዱበትን መንገድና ልዩ ክትትል ለሚያስፈልጋቸውንና ልዩ ችሎታ ላላቸው ወጣቶች ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ወይም መርኃ-ግብሮች እንዲኖሩ ያቅዳል፡፡

ፖሊሲው በገጠር ለሚኖሩ ወጣቶች አፅንዖት የሚሰጥ ሲሆን አላማውም ወጣቶቹ ለእርሻና ለግጦሽ ከሚሆን መሬት ተጠቃሚ እንዲሆኑና ምርታማነታቸው እንዲጨምር ማድረግ ነው፡፡ ፖሊሲው በተለይ ከግብርና ውጪ ያሉ ተግባራትን ያበረታታል፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ከግብርና ውጪ ያሉ ሥራዎች ለወጣቱ ሠፊ የሥራ ዕድል የመፍጠር ዓቅም አላቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

በአጠቃላይ ብሔራዊ ፖሊሲው ባለፈው መንግሥት የትምህርት ሥርዓት ላይ የነበሩ ችግሮችንና ለሥራ አጥነት መባባስ የነበራቸውን አስተዋፅኦ ለይቶ ያስቀመጠ ሲሆን፤

የፖሊሲውም ራዕይ ወጣቱን ከትምህርትና ስልጠናዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና ከትምህርት ውጪ ላሉ ወጣቶች ደግሞ የመፃፍና የማንበብ ችሎታቸውን የሚያሻሽል የትምህርት አገልግሎት እንዲዳብር የሚረዳ አመቺ ሁኔታ መፍጠር ነው። ብሔራዊ ፖሊሲው በከተማና በገጠር፣ በወንድና በሴት እንዲሁም በተለያዩ ክልሎች መካከል ያለውን የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ልዩነቶቹን ለማጥበብ የሚረዱ የመፍትሔ ኃሳቦችን ያቀርባል። በተጨማሪም ሴቶችና ወጣቶች የሥራ አጥነት ችግር ዋነኛ ተጠቂ እንደሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው።

የወጣቱ ፖሊሲ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያለው፣ በዕውቀት፣ በክህሎት እና በስነ-ምግባር የታነፀ ወጣትን የማፍራት ራዕይ አለው። ይህም ወጣቱ በመልካም አስተዳደር እና በዴሞክራሲያዊ ማኅበረሠብ ግንባታ፣ እንዲሁም በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖረው ያስችላል። የፖሊሲው መሠረታዊ መርሆችም በአገሪቷ ዴሞክራሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ የወጣቱን ንቁ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የወጣቱን አንድነት ማበረታታት፣ እንዲሁም ወጣቱ ተደራጅቶ መብቱንና ፍላጎቱን እንዲያስከብርና በተለያዩ ሥልጠናዎች አቅሙን መገንባት ማስቻል ናቸው።

## ሐ) የትምህርት ፖሊሲ

ከ1994 በፊት የነበረው የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ለንድፈ-ኃሣብ ልዩ ትኩረት የሰጠና ለሙያና ቴክኒክ ትምህርት ላይ ትኩረት ያላደረገ በመሆኑ የተማሪዎችን የአስተሳሰብ አድማስ ለማስፋትና ተነሳሽነታቸውን በመጨመር የሚፈልገውን ውጤት ለማምጣት ሳያስችል ቀርቷል (MOE, 2002)። በጊዜው በነበረው የትምህርት ሥርዓት መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ የሚያካትተው ከ1-6ኛ ክፍል ሲሆን፣ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 7 እና 8ኛ ክፍልን ሲይዝ፣ ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከ9-12ኛ ክፍልን ያጠቃልላል። 12ኛ ክፍል ላይ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለመግባት የሚያበቃቸውን ፈተና ይወስዳሉ። ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሰው እንዳለ ቢሆንም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚገቡት ተማሪዎች ቁጥር በጣም ጥቂት ነበር። ይህን ዕድል ያላገኙ ተማሪዎች ደግሞ ገበያው የሚፈልገውን ሙያና ሥልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ አልነበረም።

በ1994 የተቀረጸው አዲሱ የትምህርት ሥርዓት ከላይ የተጠቀሱትን የቀድሞውን የትምህርት ሥርዓት ደካማ ጎኖች ግምት ውስጥ በማስገባት በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ አካሂዷል። አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ትኩረት የሚሠጠው አገሪቱና ገበያው የሚፈልጉትን ክህሎት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት ላይ ነው። በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ከ1-8ኛ ክፍል ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሲባል፣ ከ9-10ኛ ክፍል ያለው ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት

ተብሏል፡፡ በእነዚህ ሁለቱም ደረጃዎች መሠረታዊ የአካዳሚ ትምህርት የሚሠጥ ሲሆን ተማሪዎች የ10ኛ ክፍል ትምህርት ሲያጠናቅቁ ብሔራዊ የመልቀቂያ ፈተና በመውሠድ ያለፉት ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት (11-12 ክፍል) ወይም የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ይገባሉ፡፡ ወደዚህ የትምህርት ደረጃ መዛወር ያልቻሉት ደግሞ የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ዕድል ሲኖራቸው ተማሪዎቹም ትምህርታቸውን ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ይከታተላሉ፡፡

አዲሱ የትምህርት ሥርዓት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ትኩረት የሠጠ ሲሆን በ2000 ዘርፉን እንደገና ለማዋቀር ያለመ ሠፊ ፕሮግራም ተጀምሯል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ውጤታማነት ለመጨመር የትምህርት ሚኒስቴር በ2004 አዋጅ አውጥቷል፡፡ አዋጁም የትምህርት ማስረጃ እውቅና፣ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት፣ እንዲሁም የትምህርት ተቋማት ቦርድና ካውንስል አመሠራረትና አመራር ላይ መመሪያ ይሠጣል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ወጣቱን ማበረታታትና በቂ የሆነ ክህሎት እንዲጨብጥ በማድረግ የራሱን የሥራ ዕድል እንዲፈጥር በማስቻል የወጣት የሥራ አጥ ቁጥርን መቀነስ ይቻላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና የሥራ ዕድል ከመፍጠር አንፃር ያለውን ሚና የሚያሳይ በሚገባ የተጠና ጥናት የለም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አሁን ያሉት መረጃዎች ያለውን ተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ለማሳየት በቂ ስላልሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን የጉዳዩን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለመነሻ የሚሆኑ ጥቂት ግምታዊ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ከነዚህም ጥናቶች ውስጥ አንዱ እንደሚያሳየው በጥናቱ ከተካተቱት ወጣቶች ውስጥ 2 በመቶ የሚሆኑት ብቻ የሙያ ስልጠና ነበራቸው (Guarcello and Rosati 2007)፡፡ ጥናቱ እንዳሳየው በስልጠና ላይ የተሳተፉ ሰዎች በከተማ አካባቢ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው በ25 በመቶ ሲጨምር በገጠር አካባቢ ደግሞ በ13 በመቶ አድጓል፡፡

**መ) ከኢንዱስትሪና ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዕድገት ጋር የተያያዙ አቅጣጫዎች**

**፩) የኢንዱስትሪ ዕድገት አቅጣጫ**

በ2001 የተቀረፀው የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፤

- የግል ክፍለ-ኢኮኖሚውን ተሳትፎ መጨመርና ሙሉ አቅሙን እንዲጠቀም ማድረግ፣

- ከፍተኛ የሰው ኃይልና በአገር ውስጥ የሚገኙ ግብዓቶችን የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም፣
- ኢንዱስትሪው ለጥቅል የአገር ውስጥ ምርት፣ ለቅጥርና ለውጭ ምንዛሪ ያለውን አስተዋጽኦ መጨመር።

በተጨማሪም ስትራቴጂው ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከሚፈልጉት አነስተኛ የመነሻ ካፒታልና ለወጣቱ ካላቸው የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም አንፃር ያላቸውን ጥቅም እውቅናና አጽንኦት የሠጠ ከመሆኑ በላይ ኢንቨስትመንትና ቁጠባን ለማሳደግ ያላቸውን ጠቀሜታ ያገናዘበ ነው። ይህን ለማሳካት ስትራቴጂው አመቺ የንግድ ሁኔታን መፍጠርና ኢላማ የሆኑ እንደጨርቃጨርቅ፣ የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ የግንባታ ኢንዱስትሪ፣ እንዲሁም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች አፅንዖትና ድጋፍ ይሰጣል (PASDEP, 2006)።

**፪) የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የዕድገት አቅጣጫ**

መንግሥት የሥራ አጥነት ችግርን ለመፍታት የሚረዱ፣ የሥራ ዕድልን በፍጥነት ሊያመጡ የሚችሉና ለሥራ አጦች በተለይም ለወጣቶች የገንዘብ፣ የምርት እና የሽያጭ ቦታ አቅርቦት ድጋፍ ሊያመጡ የሚችሉ መርኃ-ግብሮችን በመለየት ላይ ይገኛል። ከነዚህም ፕሮግራሞች ውስጥ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መርኃ-ግብር በኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ ትኩረት ተሰጥቶት የሥራ አጥነት ችግርን ለመዋጋትና የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማምጣት እየተሠራበት የሚገኝ ፕሮግራም ነው።

ሥራ በመፍጠር አቅም ከግብርና ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ሥራ አጥነትን በመቀነስና በአገሪቷ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ተቋማት በአገሪቷ ካሉት ጠቅላላ ተቋማት ውስጥ 99 በመቶ የሚሆነውን የያዙ ሲሆን፤ ከግል ተቋማት ከሚመነጨው የሥራ ዕድል ውስጥም 60 በመቶ የሚሆነውን የሚፈጥሩት እነዚሁ ተቋማት ናቸው (Demeke, *et. al.*, 2006)።

ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በግብርና ዘርፉ ውስጥ ከአቅም በታች ለሚሠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ ሲሆን፤ በግብርና ለሚተዳደሩ ቤተሠቦች ደግሞ አማራጭ የገቢ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ። በተጨማሪም ለመካከለኛና ከፍተኛ ተቋማት የዕድገት መሠረት ሆነው ያገለግላሉ።

የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ከሥራ ፈጠራና ገቢ ማመንጨት አንፃር ያላቸውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ በመገንዘብ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ2004 የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ስትራቴጂ ቀርጿል። ይህ ስትራቴጂ ለሴቶች፣

ትምህርት ላቋረጡ፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ እንዲሁም ሥራ አጥ ለሆኑት ወጣቶች ልዩ ትኩረት ይሠጣል። የዚህ ስትራቴጂ አብይ አላማ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን ማጠናከር፣ የኢኮኖሚውን ዕድገት ማፋጠንና ፍትሐዊ የሆነ ልማት እንዲኖር ማድረግና የሥራ ዕድልን መፍጠር ነው። ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ሕጋዊና ተቋማዊ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የሚደረገውም ድጋፍ የብድር አገልግሎት፣ የሥራ ፈጠራና የንግድ አስተዳደር ሥልጠና፣ የተስማሚ ቴክኖሎጂና ገበያ ምርምር፣ መረጃና ማማከር፣ መሠረተ-ልማት ማመቻቸት (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ መንገድና የመስሪያ ቦታ መስጠትን) ያካትታል ። ከዚህም በተጨማሪም ለጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ድጋፍ የሚያደርጉ አካላትን ለማጠናከርና ለማደራጀት የሚረዳ የፌዴራል ጥቃቅን አነስተኛ ተቋማት ዕድገት ኤጀንሲ ተቋቁሟል። ይህም ኤጀንሲ የጥቃቅን አነስተኛ ተቋማት ተፎካካሪነትን የሚያሻሽሉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። ከነዚህም ውስጥ የማምረቻ ቦታን ማመቻቸት፣ አዳዲስ ድርጅቶችን ማቋቋምና የገበያ ዕድል ለመፍጠር ይገኙበታል።

ይህንንም ተከትሎ በአሁኑ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች በተለያዩ የአገራችን ከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተጠቃሚ ሆነዋል። በመሆኑም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በከተማ ውስጥ የሚገኘውን የሥራ አጥ ቁጥር ከመቀነስ አንጻር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

በአገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በአምስት ዓመት ውስጥ (ከ2010/11-2014/15) 3.05 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታስቧል። ከፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በ2011/12 ብቻ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት 1.15 ሚሊዮን ሥራ ፈጥረዋል። እነዚህ የሥራ ዕድሎች በግልና የመንግሥት ዘርፍ የተፈጠሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በግንባታ፣ በአገልግሎት ሠጪ፣ በንግድ፣ በማምረቻ እና በከተማ ግብርና ዘርፍ የተፈጠሩት የሥራ ዕድሎች ይጠቀሳሉ። በተጨማሪም ከቤት፣ ከመንገድ፣ ከባቡር፣ ከመብራት፣ ከመስኖ እና ከስኳር ማምረቻ ጋር የተያያዙና በመንግስት እጅ ያሉ ታላላቅ ፕሮጀክቶች ሠፊ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል። ከነዚህም ውስጥ የአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሥራ ዕድል ፈጥሯል።

በሌሎች ታዳጊ አገሮች እንደሚታየው ሁሉ በኢትዮጵያም ውስጥ የግል ዘርፍ በተለይም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዕድገታቸውን ለሚፈታተኑ እንቅፋቶች ይጋለጣሉ። ከመሠረተ-ልማት፣ ከብድር አቅርቦት፣ ከመስሪያ ቦታ፣ ከምክር፣ ከመረጃና ከመሳሰሉት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ችግሮች በስፋት ያጋጥሟቸዋል።

የግሉን ዘርፍ ዕድገት ከማፋጠንና የሥራ ዕድሎችን ከመፍጠር አንጻር አበረታች የሆኑ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ታይተዋል። ነገር ግን የሥራ ሁኔታን ለማሻሻልና

ቢሮክራሲያዊ እንቅፋቶችን ለማስወገድ የሚረዱ ተጨማሪ ለውጦች አሁንም ያስፈልጋሉ፡፡

## 3.3 የሥራ ዕድል ፈጠራ እንቅስቃሴ በክልል ከተሞች

ሁለቱ አንኳር የክልል ከተሞች ችግር የሆኑት ድህነትና ሥራ አጥነትን ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመቅረፍ ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ መንግሥት ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን እንደ ስትራቴጂ ተጠቅሞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

በፈጣንና ዘላቂ ልማት ድህነትን ለማጥፋት ዕቅድ መሠረት የከተማ ሥራ አጥነት ችግርን ለመቀነስ መንግሥት በተለያየ መንገድ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ድጋፍ በመስጠት፣ የተለያዩ የሙያ ሥልጠና በመስጠት፣ አካባቢን መሠረት ያደረጉና ብዙ የሰው ኃይል የሚጠይቁ የከተማ አካባቢ ሥራዎችን ማስፋፋት፣ ጥቃቅን የብድርና ቁጠባ ተቋማትን ማስፋፋት ይጠቀሳሉ፡፡

ይህም እንቅስቃሴ በአገር አቀፍ ደረጃ የከተማ ልማት ማዕቀፍ እና የከተማ መልካም አስተዳደር ማዕቀፍ በሚሉ ሁለት መሠረታዊ የከተማ ልማት ፖሊሲዎች ውስጥ ተካቷል፡፡ የከተማ ልማት ፖሊሲ አላማዎች ሥራ አጥነትና ድህነትን መቅረፍ፣ የግንባታ ኢንዱስትሪውን አቅም ማዳበር፣ ያለውን የቤት ችግር መቅረፍ፣ ከተሞችን እንደ የዕድገት ሞተር በመጠቀም የህብረተሠቡን በተለይም የወጣቱን የከተማ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ-ልማት ማሻሻል ያካትታል፡፡

የፖሊሲው ማዕቀፍ ካካተታቸው አምስት ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ የጥቃቅንና አነስተኛ ፕሮግራም ዋነኛው ነው፡፡ ጥቃቅንና አነስተኛ ሥራዎች እንደ ዋና የድህነት መቅረፍያና ለብዙ የሙያ ማሠልጠኛ ተቋቋም ምሩቃን የሥራ ዕድል መፍጠርያ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህንን በመረዳት መንግሥት ብዙ መዋለ-ንዋይ መድቦ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በተለያዩ ክልሎች ለማስፋፋት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የከተማ ድህነትና ሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ ከሚደጉ ጥረቶች አንጻር ይህ ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈታተኑ ግቦችን የያዘ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ከ2006/07-09/10 ባለው ጊዜ ውስጥ በ825 የክልል ከተሞች ውስጥ ለ1.5 ሚሊዮን ነዋሪዎች የሥራ ዕድልን ለመፍጠር የተነደፈው ዕቅድ ይጠቀሳል፡፡ በዚህ ፕሮግራም መሠረት 50 በመቶ የሚሆኑት ተጠቃሚዎች ሴቶች ይሆናሉ ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን፣ መንግሥትም ወደ 6.2 ቢሊዮን ብር ኢንቨስት የማድረግና ለጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ዕድገት ይረዳ ዘንድ 4,900 ሄክታር መሬት ለመስጠት ዕቅድ ይዞ ነበር፡፡

የመንግሥት ፍላጎትና ፖሊሲዎች ትክክል ቢሆኑም ፖሊሲዎቹ በምን ያህል ደረጃ የሥራ ዕድል እንደፈጠሩ፣ ድህነትን በምን ያህል እንደቀነሱና የተረጋጋ የንግድ ዕድገትን በማምጣት ረገድ የነበራቸውን ሚና መገምገም ተገቢ ነው። በዚህ ዙርያ መረጃ ማግኘት ከባድ ነው። እስከ አሁን በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዕድገት ስትራቴጂ ድህነትን በመቀነስ የሥራ ዕድልን በመፍጠር እና ለንግድ ዕድገት ያደረገውን አስተዋፅኦ በተመለከተ በገለልተኛ አካል የተደረገ ግምገማ የለም። ሆኖም የነዚህን ፕሮግራሞች ውጤታማነት በተመለከተ መነሻ የሆነ ግምት ማስቀመጥ ይቻላል።

## 3.4 በከተማ አካባቢ ያሉ ፕሮጀክቶች

### ሀ) የተቀናጀ የመኖሪያ ቤቶች ልማት መርኃ-ግብር

የመኖሪያ ቤት እጥረትና ሥራ አጥነት በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ያሉ ነዋሪዎችን የሚፈታተኑ ሁለት ዋነኛ ችግሮች ናቸው። በኢትዮጵያ የመኖሪያ ቤቶች ልማት ፕሮግራም (The Integrated Housing Development Program) የቤት አቅርቦትን ችግርን ለመፍታት ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በመደገፍ ወጪ ቆጣቢ ቤቶች እንዲሠሩ ይረዳል። በግንባታ ዘርፍ ላይ የተሠማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትብዙ የሰው ኃይል የሚጠቀሙና ዝቅተኛ ክህሎት ያላቸው ግለሠቦችን የሚቀጥሩ በመሆኑ ፕሮግራሙ ደሀ ሥራ አጦችን ያለመ ነው።

በዚህ ፕሮግራም የሚሳተፉ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በአብዛኛው የተቋቋሙት ወጣት በሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሠልጠኛ ተቋማት ምሩቃን ወይም በግንባታው ዘርፍ ልምድ ባላቸው ወጣቶች ነው። የክልል የቤት ልማት ቢሮዎች በዚህ ፕሮግራም ለሚሳተፉ ተቋማት እንደ የሥራ ቦታን በቅናሽ ዋጋ ወይም በነፃ መስጠት፣ የሥልጠና እና አስፈላጊ የሆኑ ማሽኖች በድጎማ ማቅረብ የመሳሰሉትን ድጋፎች ያደርጋሉ ይሰጣሉ።

በ2004 ፕሮግራሙ ሥራ ላይ ሲውል ከ2005-2010 ባሉት ዓመታት ውስጥ 400,000 የሚሆኑ በዝቅተኛ ወጪ የሚሠሩ የጋራ መኖርያ ቤቶችን ለመገንባት፣ ለ200,000 ግለሰቦች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና ከ10,000 የሚበልጡ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ለማስተዋወቅ ያለመ ነበር። በ2010 ፕሮግራሙ 171,000 ቤቶች የገነባ ሲሆን፣ 176,000 አዳዲስ ሥራዎችንም ፈጥሯል። በተጨማሪም በግንባታው ዘርፍ ያለውን የቴክኒክ አቅም ከማሳደጉ በላይ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ቁጥርና አቅምን ጨምሯል።

**ለ)የኮብልስቶን ፕሮጀክት**

በኢትዮጵያ የኮብልስቶን ፕሮጀክት የተጀመረው የጀርመን መንግስት በሚረዳው የመንግሥት የምንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም ነው:: የመንግሥት የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም ከ2007 ጀምሮ የተለያዩ ስልጠናዎችን (በተለይም ለወጣቶች ከኮብልስቶን መጥረብና መደልደል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥልጠናዎች) ሲሰጥ ቆይቷል:: ፕሮጀክቱ ሁለት ዓላማዎች ያሉት ሲሆን፤ አንደኛው ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ሲሆን ሌላው ደግሞ በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ለዓይን የሚማርኩ መንገዶችን መገንባት ነው:: ይህ ፕሮግራም በአቅራቢያ የሚገኙ ግብዓቶችን የሚጠቀም ሲሆን ከፍተኛ የሰው ኃይልን ተጠቅሞ ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መልኩ መንገዶችንና የህዝብ ቦታዎችን ለመገንባት ይረዳል:: በከተማ አካባቢ የሚሠሩ መንገዶች ግብዓቶች በቀላሉ ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ:: በዚህም ፕሮግራም ከተፈጠሩት ሥራዎች ውስጥ ቁፋሮ፣ ድንጋይ መጥረብና መደልደል፣ እንዲሁም መሣሪያዎችን ማምረት ይጠቀሳሉ:: ፕሮጀክቱ በ140 ከተሞች ውስጥ ከ2,000 በላይ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን የፈጠረ ሲሆን ከ90,000 በላይ ሠራተኞችን ቀጥሯል::

## 3.5 ከወጣቶች የሥራ ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች

የኢትዮጵያ የሠራተኞች ሕግ (Labour Proclamation 377/2003) የተደነገገው በ2003 ሲሆን ዓላማውም የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ሕጋዊ መሆኑን ማረጋገጥ ነው:: ይህም የሠራተኛና አሠሪ ማኅበሮችን የማቋቋም መብትንና የሥራ አመራር ማጠናከሪያ መርሆዎችን ያካትታል::

የኢትዮጵያ የሠራተኞች ሕግ ለጠቅላላው ሠራተኛ የሚሠራ ሲሆን የተወሠኑ የህጉ ክፍሎች ግን በተለይ ወጣቱን የሚመለከቱ ናቸው:: በተጨማሪም ሴቶችንና ከ14-18 ዓመት ዕድሜ ያሉ ታዳጊዎችን የሚመለከቱ ሕጎችንም ያካትታል:: በሕጉ መሠረት አነስተኛው የሠራተኛ ዕድሜ 14 ዓመት ሲሆን የሥራ ላይ ልምምዶች ወይም ቅጥሮች ከ14 ዓመት በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር እንዲፈጸም ይፈቅዳል (አንቀጽ 48):: በተጨማሪም ከ14-18 ዕድሜ ያሉ ታዳጊዎች ለሕይወታቸውና ለጤናቸው አስጊ የሆኑ ለምሳሌ እንደ ትራንስፖርት፣ ከፍተኛ ጉልበት በሚጠይቁ፣ አደገኛና ለጤና አስጊ በሆኑ እንደ ማዕድን ማውጣት ያሉ ሥራዎች ላይ እንዳይሳተፉ ያግዳል:: ነገር ግን ከሙያ ሥልጠና ጋር በተያያዘ የሚሠሩ ሥራዎች ግን በዚህ እገዳ ውስጥ አይካተቱም:: የኢትዮጵያ የሠራተኞች ሕግ አንቀጽ 90 ሠራተኞች በመደበኛ የሥራ ቀናት ከሠባት ሠዓት በላይ እንዳይሠሩ፤ በተጨማሪም በምሽት፣ በዕረፍትና በበዓል ቀናት በሚሰሩ የትርፍ ሠዓት ሥራዎች ውስጥ ወጣት ሠራተኞች እንዳይሳተፉ ያግዳል::

የኢትዮጵያ የሠራተኞች ሕግ አንቀጽ 29 እንደሚገልጸው በመሥሪያ ቤቶች የሠራተኞች ቅነሳ አስፈላጊ ሲሆን አሠሪው ከሠራተኛ ማኅበራት ጋር በመነጋገር የተሻለ ክህሎት ላላቸውና ምርታማ ለሆኑ ሠራተኞች ቅድሚያ ይሠጣል። ይህም ወጣቱን በተሻለ መልኩ ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ይታሰባል። በሌላ በኩል ተመሳሳይ ክህሎትና ምርታማነት በሚኖርበት ጊዜ የመጀመሪያ ተቀናሽ የሚሆኑት አነስተኛ የአገልግሎት ዘመንና ጥቂት ጥገኛ ቤተሠብ ያላቸው ይሆናሉ። ከዚህ አንፃር በአብዛኛው ጊዜ ወጣቶች የአገልግሎት ዘመናቸው በንጽጽር አጠር ያለ ስለሚሆንና በአብዛኛው አነስተኛ ጥገኛ ቤተሠብ ስለሚኖራቸው የቅነሳው ሰለባ ይሆናሉ።

በቅርቡ የተካሄዱት ተቋማዊና የሰው ኃይል ገበያ ፖሊሲ ማሻሻያዎች የአገሪቱ የሥራ አጥ ችግር ላይ በጎ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ተብሎ ይገመታል። በደርግ ጊዜ በሥራ ላይ የነበረው የሠራተኛ ሕግና የደሞዝ ፖሊሲ በአመዛኙ የሠራተኛውን መብት መጠበቅ ላይ ያተኮረ ነበር። በጊዜው የነበሩት ሕጎች ሠራተኞችን ከመቅጠርና ከማሠናበት ጋር በተያያዘ ግትርነት የሚጠቃቸው የነበሩ ሲሆን፤ የሥራ ኃይል ገበያውን ያላገናዘበ አነስተኛ ክፍያም ይደነግጉ ነበር። የሠራተኛ ማኅበራት መቋቋምን (በተለይ በመንግሥት ሠራተኞች መካከል) የሚያበረታታ ከመሆኑ በላይ ማዕከላዊ የሠራተኞችን ምልመላ እና የሥራ ገበያ መደብ የፈጠረ ነበር።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በደርግ ሥርዓት ጊዜ የነበረው የሥራ አጥነት ችግር አንዱ ዋነኛው ምክንያት የተሻለ የትምህርት ደረጃ የነበራቸው ወጣቶች በንጽጽር የተሻለ ክፍያ የሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ መፈለጋቸው ነበር። መንግሥት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው ለሚወጡ ምሩቃን በሙሉ የመንግሥት ሥራ መስጠቱ ሁኔታውን አባብሶት ቆይቷል። ነገር ግን ይህ ሁኔታ በኢ-መደበኛው ኢኮኖሚ ሠፊነትና በዘርፉ ውስጥ የተደነገገውን ዝቅተኛ የደሞዝ ክፍያ ለማስከበር አስቸጋሪ ስለነበር ሁኔታው በአጠቃላይ የሥራ ገበያው ላይ የነበረው ተጽዕኖ አነስተኛ ነበር ማለት ይቻላል።

ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ በሥራ ገበያ ተቋማት እና ተያያዥ በሆኑ ፖሊሲዎች ላይ የተካሄዱ ማሻሻያዎች ወይም ተሃድሶዎች የራሳቸው የሆነ ሥነ-ልቦናዊ (psychologica) ተፅዕኖ አሳድረዋል። በተማረው የሰው ኃይል ዘንድ ሠፍኖ የነበረው መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን እንደብቸኛ የሥራ ዕድል ፈጣሪና እንደ ከፍተኛ የሥራ ደረጃና የደሞዝ ምንጭ አድርጎ የማሠብ አመለካከት ተቀይሯል።

ነገር ግን ምንም እንኳ የሥራ ገበያውን ሁኔታ ለማሻሻል ተቋማዊና የሠራተኛ ገበያ ፖሊሲዎች ላይ ማሻሻያ ቢካሄድም አሁንም በዘርፉ የሚታዩ ክፍተቶች አሉ። አሁን በሥራ ላይ ያሉ ተቋማትንና የሕግ አካላት በመደበኛ ሥራና በደሞዝ በሚሠሩ ሠራተኞች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ምንም እንኳን ኢ-መደበኛውና የግል ሥራው ዘርፍ

ለአብዛኛው ወጣት የሥራ ዕድል የፈጠሩ ቢሆንም፣ ተገቢውን ትኩረት ግን ተነፍጓቸዋል:: በ1993 የወጣውና በ2003 የተሻሻለው የሠራተኞች አዋጅ ለኢ-መደበኛውና ለግል ሥራው ዘርፍ ምንም ዓይነት ትኩረት አልሰጠም::

ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው የሠራተኛ ማኅበራት (unionization) ያላት አገር ነች (MoLSA, 2009):: በአገሪቱ ካለው አጠቃላይ የሰው ኃይል ውስጥ በብሔራዊ የሠራተኛ ማኅበር ኮንፌዴሬሽን (Confederation of Ethiopian Trade Unions) የታቀፈው ከ10 በመቶ በታች ነው:: ለዚህም እንደ ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሠደው የአገሪቱ ኢኮኖሚ በአብዛኛው በግብርና እና በኢ-መደበኛ የአሠራር ሥርዓት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው:: ዝቅተኛ ለሆነው የማኅበራት ሁኔታ (በተለይም በመደበኛው የግል ዘርፍ) ሌላው ምክንያት በአገሪቱ ውስጥ ያለው ከፍተኛ የሥራ አጥነትና የገቢ ዝቅተኛ መሆን ለቀጣሪዎች የተሻለ የመደራደርያ አቅም (bargaining power) ስለሰጣቸው ነው:: በተጨማሪም የሠራተኛ ድንጋጌው ትግበራ ወይም የአፈጻጸም ደረጃ በተለይም በግል ክፍለ-ኢኮኖሚው ውስጥ ዝቅተኛ መሆን ለሠራተኛ ማኅበራት አለመስፋፋት ሌላው ምክንያት ነው (WB, 2007)::

በአሁኑ ጊዜ ያለውን የሰው ኃይል ገበያ ሥርዓት ድክመት ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ሥርዓቱን ከኢኮኖሚ ዕድገትና ድህነት ቅነሳ አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች ጋር ለማዛመድ እንዲቻል መንግሥት በ2009 ብሔራዊ የቅጥር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ (National Employment Policy and Strategy) አውጥቷል:: ይህ ሠነድ ድህነት እና ሥራ አጥነት ለመቀነስ የሚደረጉ ተግባራትን በተመለከተ አቅጣጫዎችን ይጠቁማል (MoLSA, 2009):: ሠነዱ ሥራ አጥነትን፣ ከአቅም በታች መሥራትን፣ መጥፎ የሆኑ የሥራ ሁኔታዎችን፣ በተለይም ኢ-መደበኛ በሆነው የሥራ ዘርፍ ውስጥ ያለውን አነስተኛ የመብት ጥበቃ እና የመሳሰሉትን ችግሮች በተቀናጀ የቅጥር ፖሊሲና ደንብ ለመፍታት ያልማል:: እንዲሁም ፖሊሲው የተረጋጋ የሰው ኃይል አቅርቦት፣ ፍላጎትና የሥራ ገበያ ተቋማት መኖራቸውን ያረጋግጣል::

## 4 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የቅጥር ሁኔታ በጥልቀት ለመቃኘት ሞክሯል:: ጥናቱ እንዳሳየው ከ1999 ጀምሮ አጠቃላይ የአገሪቱ የሥራ አጥ ቁጥር (በተለይም የወጣት የሥራ አጥ ቁጥር) በከፍተኛ ሁኔታ ቢቀንስም ሥራ አጥነት አሁንም በአገሪቱ በሠፊው ተንሰራፍቶ ይገኛል::

ጥናቱ ወጣት-ተኮር የሆኑትንና ለሥራ ፈጠራ ከፍተኛ ዕድል የሚፈጥሩትን ብሔራዊ ፕሮግራሞችንና ፖሊሲዎችን የፈተሸ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሥራ ዕድልን በመፍጠር ጉልህ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኙትን የጥቃቅንና አነስተኛ

ኢንተርፕራይዞችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። እንዲሁም ከፍተኛ የሆነውን የህዝብ ቁጥር ለመቆጣጠር የተወሰዱ እርምጃዎችም በሥራ ገበያው ላይ ተፅዕኖ መፍጠር ችለዋል። በ2004 የተቀረፀው የወጣቶች ፖሊሲም ወጣት-ተኮር የሆኑ እርምጃዎች መወሠድ እንዳለባቸው ያስገነዘበ ሲሆን በቀጣይነትም ለሚቀረፁ ፖሊሲዎችም እንደጥሩ መነሻ ሊወሰድ ይችላል።

የስራ አጥነትን ችግር በመቅረፍ ረገድ ከ1999 ጀምሮ ከፍተኛ የሆኑ መሻሻሎች ቢታዩም ጥናቱ ወደፊት መሻሻል ያለባቸውን ሁኔታዎችን ለማሳየት ሞክሯል። ለምሳሌ ለሴቶች የሥራ ዕድልን መፍጠር (ከተቻለ መደበኛው የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ)፣ ለተማሩና ለሠለጠኑ ወጣቶች የሥራ ዕድልን መፍጠር፣ እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋውን ከአቅም በታች የመሥራት ሁኔታን ማሻሻል እንደሚገባ ተጠቅሷል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በመንግሥት ተቀርጸው የሚወጡ ፖሊሲዎች በጣም ደካማ የሆነውን የሴቶችንና በአጠቃላይ የወጣቱን የቅጥር ሁኔታ ታሳቢ ሊያደርጉ ይገባል። በተጨማሪም በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ያለውን የተማረ ሥራ አጥ ቁጥርን ያገናዘቡ ስትራጂዎች መቀረጽና መተግበር ይኖርባቸዋል።

የወጣቶች ሥራ አጥነት በጣም የተወሳሰበ ጉዳይ ሲሆን መፍትሔውም የመንግሥትን፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፣ የሲቪል ህብረተሠቡን፣ እንዲሁም የግል ዘርፉን ተሳትፎ ይጠይቃል። በጥናቱ እንደተገለፀው የግሉ ዘርፍ በተለያዩ የዕድሜ ደረጃ ለሚገኙ ሰዎች መደበኛና ኢ-መደበኛ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር ችሏል። መደበኛ ያልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ ከመንገድ ላይ ንግድ ጀምሮ እስከ ጥቃቅንና አነስተኛ እንዲሁም ትልቅ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ብዙ ሰዎች ይገኙበታል። የግሉ ዘርፍ ከዚህ በተጨማሪ ወጣት ሥራ አጥነትን የመቀነስ ሚና ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ የግሉ ዘርፍ ለወጣቶች ከትምህርት ወደ ሥራ መሸጋገሪያ ድልድይ ሊሆን ይችላል። አጠር ያሉ የሥራ ላይ ልምምዶችን በማዘጋጀት ወጣቶች የሥራ ልምድ እንዲያገኙ ሊረዱ ከመቻላቸው በላይ፣ ከቴክኒክና የሙያ ኮሌጆች ጋር በመተባበር ለተማሪዎች ተግባራዊ የሥራ ሙከራዎችን በማዘጋጀት ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላሉ። የትምህርት አሰጣጡም የግል ዘርፉን ፍላጎት ያማከለ ይሆን ዘንድ የግሉ ዘርፍ ድርጅቶች በካሪኩለም ቀረፃ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል። መንግሥት በበኩሉ የሥራ ፈጠራን የሚያበረታቱ እርምጃዎችን መውሠድ ይገባዋል። በተጨማሪም ሥራ ለመጀመር የሚረዳ መነሻ ብር ዋስትና በመስጠት ከጥቃቅንና አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ድርጅቶች ብድር ማመቻቸት ይችላል። እነዚህና መሠል እርምጃዎች የወጣት ሥራ አጥ ቁጥርን ለመቀነስና የወጣቶችን የመቀጠር ዕድልን ለመጨመር ይረዳሉ።

## ዋቢ መጽሐፍት

CSA (1984, 1994, 2007) „Population and Housing Census Report", A.A., Ethiopia.

CSA (1999, 2005) „National Labour Force Survey". A.A., Ethiopia.

CSA (2004, 2009, 2010, 2011) „Urban Employment Unemployment Survey". A.A., Ethiopia.

Denu, Berhanu; Abraham Tekeste and Hannah van der Deijl (2005) *Characteristics and determinants of youth unemployment, underemployment and inadequate employment in Ethiopia* (Employment Strategy Papers).

FDRE (1993).Labour Proclamation no. 42/1993, A.A., Ethiopia.

FDRE (2004) Labour Proclamation no.377/2003, A.A., Ethiopia.

FDRE (2004).National Youth Policy.Policy report, Addis Ababa, Ethiopia.

FDRE (2009). Employment Exchange Services.Proclamation no. 632/2009, A.A., Ethiopia.

FDRE and ILO (2009).Decent Work County Programme (DWCP) Ethiopia (2009-2012), A.A., Ethiopia.

Guarcello, L. and Rosati, F.(2007). Child Labor and Youth Employment: Ethiopia Country Study. SP Discussion Paper No.0704.The World Bank.

MOE (2002).The Education and Training Policy and its Implementation. Policy report Ministry of Education, Addis Ababa, Ethiopia.

MOE (2008).National Technical and Vocational Education and Training Strategy.2nd edition Ministry of Education, Addis Ababa, Ethiopia.

MoFED (2010).Growth and Transformation Plan (2010/11-2014/15). Volume i: Main text Ministry of Finance and Economic Development (MoFED), Addis Ababa, Ethiopia.

MoFED (2006). Ethiopia: Building on Progress A Plan for Accelerated and Sustained Development to End Poverty (PASDEP)(2005/06-2009/10). Volume i: Main text Ministry of Finance and Economic Development (MoFED), Addis Ababa, Ethiopia.

MoLSA (2009).National Employment Policy and Strategy of Ethiopia. Policy report Ministry of Labour and Social Affairs, Addis Ababa, Ethiopia

Mulat Demeke, Fantu Guta and Tadele Ferede (2006). Towards a more Employment-Intensive and Pro-Poor Economic Growth in Ethiopia: Issues

and Policies. Employment Strategy Department, International Labor Office, Geneva.

Serneels, P. (2004). The Nature of Unemployment in Ethiopia.CSAE WPS/2004-01.

Tassew Woldehanna, Fantu Guta and Tadele Ferede (2005) „Labour market flexibility and employment security in Ethiopia: economic part", Employment Strategy Department, ILO. (Unpublished).

World Bank (2007). Ethiopia: Urban Labour Markets in Ethiopian: Challenges and Prospects. Synthesis Report.Vol I & II.

World Bank (2009). Ethiopia: The Employment Creation Effects of the Addis Ababa Integrated Housing Program.

World Bank (2012) "World Development Indicators."

# ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የህፃናት ጥበቃ፡- የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት ግንዛቤ በኢትዮጵያ


## አሉላ ፓንክረስት


### መግቢያ

ይህ የጥናት ወረቀት በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ያለውን አመለካከት ይዳስሳል፡፡ ሁለቱም ልማዳዊ ድርጊቶች በአገሪቱ በጥልቅ የተንሰራፋውንና የሴቶችን የመውለድ አቅምና በጋብቻ ምክንያት የሚመጣውን ኃብት የሚቆጣጠሩበትን የአባቶችና ታላላቆች የበላይነትን (patriarchal and gerontocratic values) ያንፀባርቃሉ፡፡ በዚህ ጥናት "የልጆች ጋብቻ" ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የልጅነት ጣራ፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕግ ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ ተደርጎ ከሚወሰደው 18 ዓመት በታች በሆኑ ግለሠቦች የሚፈፀም ጋብቻ ነው፡፡

ጥናቱ የተከናወነው እነዚህን የሴት ልጆችን ደህንነትና መብቶች የሚጥሱ ድርጊቶችን ለማስወገድ ዓለም አቀፍና ብሔራዊ ፖሊሲ አውጭዎችና የሠብዓዊ መብት ተሟጋቾች የተባበረ ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ነው፡፡ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘት በኢትዮጵያ መንግሥት "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች" ተብለው ተፈርጀዋል፤ ድርጊቶቹን መፈጸምም በሕግ ያስቀጣል፡፡ ይህ የመንግሥት ዕርምጃ የህፃናትን ጤናና ደህንነት ጉዳት ላይ የሚጥሉ ልማዳዊ ድርጊቶችን ከሚከለክለው የተ.መ.ድ የህፃናት መብት ስምምነት (United Nations Convention on the Rights of the Child) አንቀጽ 24 ጋር ይጣጣማል፡፡ ሁለቱም ድርጊቶች "ጎጂ" ተብለው ከመፈረጃቸውና ሁለቱም በሴት ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ከመሆናቸው ባሻገር የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዛት አብረው እንዲጠኑ ያስፈለገበት ሌላው ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛት ብዙውን ጊዜ ለጋብቻ ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ ስለሚፈጸም ነው፡፡

ጥናቱ ድርጊቶቹ የሚፈጸምባቸውን ባህላዊ ምክንያቶችና ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት የደረሱበትን ሁኔታ ይፈትሻል፡፡ በዚህም በአመለካከትና ድርጊት መካከል ያለውን ውስብስብ ሁኔታና ድርጊቶቹን በተመለከተ በብሔረሠብ፣ በኃይማኖትና በጾታ ያለውን ልዩነትም ያሳያል፡፡ የመንግሥትና የማኅበረሠብ አመራሮች ድርጊቶቹን ለማስወገድ የሚያደርጉት ጥረትም ምንም እንኳን ከክልል ክልል ቢለያይም እንዲሁም

አሁንም ተቃውሞና መከላከል የሚታይበት ቢሆንም የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘት እንዲቀንሱ ወይም መልካቸውን እንዲቀይሩ ማድረጉን ያሳያል፡፡ የለውጡን ሂደት በማሳየት ከጋብቻ በፊት ስለሚኖር የግብረ-ስጋ

ግንኙነት፣ የድብቅ ግርዘትና ሌሎች ልጆችን ለመታደግ በወጣው ሕግ ሳቢያ የሚደርሱትን ያልተጠበቁ ውጤቶችንም ይዳስሳል፡፡ በዚህም ሴት ልጆችን ለረጅም ጊዜ ከተንሰራፉት ልማዳዊ ድርጊቶች ለመታደግ የሚወሰዱት እርምጃዎች ያሉባቸውን ተግዳሮቶች ላይ አፅንዖት ያደርጋል፡፡

የጥናቱ ትንተናም *ያንግ ላይቭስ* የተባለው ግብረ-ሠናይ ድርጅት ለ15 ዓመታት በኢትዮጵያ፣ ሕንድ (አንድራ ፓርዲሽ)፣ ፔሩ እና ቬትናም በህፃናት ድህነት ላይ ባሰባሰበው ኢ-አኃዛዊ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የዚህ ፕሮጀክት አካል የሆኑ 20 የጥናት ሳይቶች (research sites) ያሉ ሲሆን ፕሮጀክቱ 3,000 ልጆችን በሁለት ዕድሜ ደረጃ በመከፋፈል በየጊዜው ሠርቬይ በማካሄድና፤ 100 ልጆችን፣ ቤተሠቦቻቸውንና ማኅበረሠቦቻቸውን ደግሞ በልዩ ልዩ ክፍሎች በናሙናነት በመከፋፈል ኢ-አኃዛዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥናት ያካሂዳል፡፡ ይህ ጥናት በ2007፣ 2008፣ እና 2011 በሶስት ዙር ከ25 ከፍ ያሉ ልጆች ንዑስ ቡድን አባላትን፣ የዕድሜ ዕኩዮቻቸውን፣ ቤተሠቦቻቸውንና ዐዋቂ ሰዎችን በመጠየቅ በተሠበሠበ ኢ-አኃዛዊ መረጃዎች(qualitative data) ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እነዚሁ ንዑስ ናሙና ቡድኖች በሶስቱም ሠርቬዮች ውስጥ የተሳተፉ ሲሆን በተጨማሪም በእያንዳንዱ የጥናት አካባቢ አራት አራት የቡድን ውይይቶች (focusgroup discussions) እና ወደ 12 የሚጠጉ የግል ቃለ-መጠይቆች (interviews) ተደርገዋል፡፡ በቡድን ውይይቶቹ የማሕበረሠብ ተወካዮች (የአገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ የሴቶች ማኅበራት መሪዎች፣ አግልግሎት ሠጪዎች)፣ ወላጆችና ልጆች ተካፍለውባቸዋል፡፡ የግል ቃለ-መጠይቆች ከልጆችና ወላጆቻቸው፣ መምህራንንና ጉዳዩን በሚገባ ይረዳሉ ከሚባሉ ሰዎች (key informants) ማለትም የጤና አገልግሎች ሠጪዎች፣ የሴት ማኅበራት መሪዎች፣ የቀበሌ መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት መሪዎችና የግብረ-ሠናይ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ተካሂደዋል፡፡

## 1 የጥናቱ አሠራር

የያንግ ላይቭስ አምስቱ ኢ-አኃዛዊ የጥናት አካባቢዎች ከእያንዳንዱ ትልቅ ክልላዊ መንግሥትና ከአዲስ አበባ የከተማ አስተዳደር አንድ አንድ በመውሠድ የተውጣጣ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ትልቁ 20 ‹‹ሳይት›› ናሙና እንዲውጣጣ ተደርጓል፡፡ ሁለቱ ኢ-አኃዛዊ የጥናት አካባቢዎች ከከተማ (አዲስ አበባና ሐዋሳ) የተመረጡ ናቸው፡፡ የከተማና የገጠር ልዩነቶች ከሴቶች የመጀመሪያ ጋብቻ ዕድሜና ከሴት ልጆች ግርዘት

ስፋት (prevalence) ጋር በስታቲስቲክስ እንዲመጣጠን ተደርጓል፡፡ ሁለቱም የከተማ የጥናት አካባቢዎች የኑሮ ሁኔታን፣ በወላጆች የትዳር ሁኔታንና (marital status) የልጆች ዕድልን መስፈርት በማድረግ ከደሀ መንደሮች የተመረጡ ሲሆኑ፤ የተቀሩት አምስት የጥናት አካባቢዎች ሁሉም ለከተማ ቀረብ ካሉ የገጠር አካባቢዎች የተመረጡ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ለ‹‹ዘመናዊነት›› አስተሳሰብና መንግሥት ለሚያካሂደው ‹‹ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን›› የማስወገድ ዘመቻ ኃሳብ ከሌሎች ራቅ ካሉ የገጠር አካባቢዎች የበለጠ ዕውቀት ሊሰጣቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች የትምህርት አቅርቦትና የጤና አገልግሎቶች መሻሻል፤ ትምህርት ሴት ልጆች ያለዕድሜ ጋብቻን የሚከላከሉበት የለውጥ መሣሪያ የመሆኑ ግንዛቤ መዳበር፤ እንዲሁም የስነ-ተዋልዶ ጉዳዮችን የሚያስተምሩ በየቀበሌዎቹ የተመደቡ የጤና ኤክስቴሽን ሠራተኞች የሴት ልጆችን ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘት ለመከላከል በሚሰሩት ሥራ ስለጉዳዮቹ ያለው አመለካከት እንዲለወጥ አስችሏል፡፡

የገጠር የጥናቱ አካባቢዎች ያለው ህብረተሠብ በአብዛኛው በእርሻና በከብት ማርባት ኑሮውን የሚገፋ ሲሆን በሐይቅ አቅራቢያ በሚገኘው የኦሮሚያ የጥናት አካባቢ አሳ ማስገር ሌላው ዋና የሥራ ተግባር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቀሩት ሶስቱ ሳይቶች የማኅበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ለብዙ ደሀ ቤተሠቦች የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ የግል ኢንቨስትመንቶችም በአካባቢዎቹ ኢኮኖሚ ላይ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ በኦሮሚያ ሳይት አቅራቢያ የሚገኘው የአበባ እርሻ ለወጣት ሴቶች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፤ በትግራይ ሳይት ለክልሉ ዋና ከተማ መንገድ ሥራ የሚሆን ኮብል ስቶን የማምረት የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በአማራ ወጣቶች በመኸር ወቅት በሀብታም ሰዎች እርሻና በቦሎቄ ንግድ በሠራተኛነት ተቀጥረው ከመሥራታቸው ባሻገር አንዳንዶቹ ከተማ ሱቅ ተከራይተው ምግብና መጠጥ ይነግዳሉ፡፡ ለወጣቶች (በተለይ ለወጣት ሴት ልጆች) የተሻለ የሥራ ዕድል መፈጠር ከቤተሠብ ቁጥጥር የተወሠነ ነፃነት ያጎናጸፋቸው ሲሆን፤ ስለጋብቻ፣ ከጋብቻ በፊት ስለሚፈጸም የግብረ-ስጋ ግንኙነት፣ የትዳር ጓደኛን ስለመምረጥና መቼ ትዳር መመስረት እንዳለባቸው በመወሠን ረገድ ያላቸው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

ሁለቱ የከተማ የጥናቱ ሳይቶች በከተሞቹ መሐል ገበያ አካባቢ የሚገኙ ሲሆን በዚህም በጥናቱ የታቀፉት ቤተሠቦች በቅጥርና በጥቃቅን ንግድ ሥራ ላይ በመሠማራት ኑሯቸውን የመግፋት ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ የአዲስ አበባው ሳይት በከተማው በሚገኘው ትልቁ የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አቅራቢያ ሲሆን፤ በጥናቱ የተካተቱት ልጆች ወላጆች ቤታቸውን ለመጋዘንነት በማከራየት፣ በተሸካሚነትና በጥቃቅን ንግድ ሥራ የተሠማሩ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሀዋሳ በገበያ አካባቢ በሚገኘው የጥናት ሳይት የጥቃቅን ንግድ ሥራ፣ የቀን ሠራተኛነት፣ የመንገድ ላይ ንግድና ሌሎች ተመሣሣይ የግል ሥራዎች ዋና ዋና መደበኛ ያልሆኑ የሥራ መስኮች

ናቸው:: በአዲስ አበባው ሳይት የሴተኛ አዳሪነት ሥራ በስፋት የሚሠራበት ሲሆን በጥናቱ የተካተቱ አንዳንድ ወላጆችም በዚህ መስክ የተሰማሩ ናቸው:: በእናቶች ብቻ የሚመራ ቤተሠብም (female-headed households) በብዛት ይገኛል:: በዚህ አካባቢ የሚታየው የተፋፈነ የአኗኗር ሁኔታና በስፋት የሚስተዋለው ሴተኛ አዳሪነት፣ ዕፅና ቁማር ልጆች ገና በትንሽነታቸው ለግብረ-ስጋ ግንኙነት፣ ለአስገድዶ መደፈርና ዕፅ ተጠቃሚነት በከፍተኛ ደረጃ ሊጋልጣቸው እንደሚችል ኢ-አኃዛዊ መረጃዎች ያሳያሉ:: ይህም ልል የግብረ-ስጋ ግንኙነት ባህልን (norms) በማስፈን ወጣቶች በባህላዊው ወግ ትዳር ከመመስረት ይልቅ ገና በልጅነታቸው የፍቅርና የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንዲጀምሩ ሊያደርግ ይችላል የሚል ግምት አሳድሯል::

የብሔረሠብና ኃይማኖች ስብጥርን በተመለከተ በሠሜን የአገሪቱ ክፍል የሚገኙት አማራና የትግራይ ሳይቶች ተመሳሳይነት አላቸው:: በአማራ ሳይት ነዋሪዎቹ ሙሉ በሙሉ የአማራ ብሔር አባላት ሲሆኑ በትግራይ ደግሞ የትግራይ ብሔር አባሎች ናቸው:: በሁለቱም ሳይቶች ያሉ ነዋሪዎች የኦርቶዶክስ ክርስትና ዕምነት ተከታዮች ናቸው:: በተቃራኒው በሁለቱ የከተማ ሳይቶች በእያንዳንዳቸው ሶስትና አራት የሚደርሱ ብሔረሠቦችና የሁለት ሁለት ዋና ኃይማኖቶች ተከታዮች ይገኙባቸዋል[1]:: የአማራ፣ ትግራይና ኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት በየክልላቸው ባሉት ሳይቶች ከፍተኛውን ብዛት የያዙ ሲሆን (በአማራና በትግራይ ሙሉ በሙሉ)፤ በተቀሩት የከተማ ሳይቶችም በአንደኛነት ደረጃ ባይቀመጡም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: በጥናቱ ከተሳተፉት መካከል ወደከተማ በመፍለስ በንግድ ሥራ በመሰማራት የሚታወቁት የጉራጌ ብሔረሠብ አባላት በሁለቱም የከተማ ሳይቶች ከፍተኛ ብዛት ያላቸው አናሳ (minority) ብሔረሠብ ሆነው ተገኝተዋል:: የወላይታ ብሔረሠብ በሐዋሳ የጥናቱ ከታቀፉት ቤተሠቦች ግማሽ ያህሉን ይሸፍናሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በሁለቱም የከተማ ሳይቶች የሌሎች የደቡብ ብሔረሠብ አባላት ይገኛሉ:: በኃይማኖት ረገድ በ2007ቱ ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ መሠረት 43% የአገሪቱን ሕዝብ የሚሸፍነው የኦርቶዶክስ ኃይማኖት በሁሉም ሳይቶች ዋናው ኃይማኖት ሲሆን፤ በሁለቱ የሠሜን ሳይቶች ሙሉ በሙሉ ይሸፍናል:: ከአገሪቱ 34% የሚይዘው እስልምና በአዲስ አበባ ሳይት ሲሶውን ያህል፣ በኦሮሚያ ደግሞ ሩብ ያህሉን ይይዛል:: ከአገሪቱ ሕዝብ 19% የሚሸፍነውና በደቡብ ክልል በስፋት የሚታየው የፕሮቴስታንት ክርስትና በሐዋሳ ሳይት 40% ይይዛል:: በኋላ በስፋት እንደምንመለከተው በየጥናት ሳይቱ ያለው

[1]በአዲስ አበባ ሳይት የአማራ ተወላጆች ሲሶውን ይሸፍናሉ:: ጉራጌ 1/5ኛውን ሲይዝ የትግራይና ኦሮሞ ተወላጆች ጥቂት ናቸው:: በሐዋሳ የወላይታ ብሔረሠብ ተወላጆች ከፍተኛውን ድርሻ (45%) ሲይዙ፤ አማራ 25%፣ የኦሮሞ ተወላጆች ደግሞ 15% ይሸፍናሉ:: የትግራይና ጉራጌ ብሔረሠብ አባላት ደግሞ በጥቂቱ ይገኙበታል:: ኃይማኖትን በተመለከተ ኦርቶዶክስ ክርስትና ከፍተኛውን ቦታ (በአዲስ አበባ 63% እና በሐዋሳ 54%) የያዘ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ እስልምና 36% በመሸፈን በሁለተኛነት ተቀምጧል:: በሐዋሳ ግን የፕሮቴስታንት ክርስትና በ40% ሁለተኛ ነው::

የብሔረሠብና የኃይማኖት ስብጥር በጋብቻ ዓይነትና ዕድሜ፣ የሴት ልጅ ግርዘት ዓይነትና ዕድሜ፣ በድርጊቶቹ ላይ ባለው አመለካከትና በሁለቱ ድርጊቶች መካከል ባለው ቁርኝት ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አላቸው።

# 2 ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጆች ግርዛት መጠንና ስፋት

## 2.1 የሴት ልጆች ያለዕድሜ ጋብቻ

ያለዕድሜ ጋብቻ በዓለም ላይ የሴት ልጆች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አማራጮች ውስን በሆኑባቸውና በልማት እምብዛም ባልገፉ አገራት በስፋት የሚታይ ችግር እንደሆነ በመስኩ የተደረጉ አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ። ሲንግና ሳማራ የተባሉ ባለሙያዎች በ40 አገራት የተሠበሠቡ የሥነ-ሕዝብና የጤና መረጃዎችን በመመርኮዝ ባደረጉት ጥናት የሥራ ተሳትፎ ደረጃ፣ መደበኛ ትምህርት የማግኘት ዕድልና የሚኖሩበት አካባቢ የከተሜነት ደረጃ የሴት ልጆችን የመጀመሪያ የጋብቻ ዕድሜ የሚወስኑ ሶስት አቢይ ምክንያቶች እንደሆኑ አመልክተዋል[2] (Singh and Samara, 1996)።

ያለዕድሜ ጋብቻ በብዙ መንገድ አሳሳቢ ነው። ባለሙያዎች ችግሩን በተለይ በጤና ላይ ከሚያስከትለው ጉዳትና በትምህርት ላይ ካለው አሉታዊ ተፅዕኖ አንጻር ይመለከቱታል። ድህነትና በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘው የእናቶችና የህፃናት የጤና አገልግሎቶች አደጋውን ይበልጥ አባብሰውታል። ያለዕድሜ ጋብቻ በጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት በልጅነት ዕድሜ ከማርገዝና ከመውለድ ጋር በቀጥታ ይያያዛል። ሌሎች ጥናቶችም ያለዕድሜያቸው የሚወልዱ እናቶች በወሊድ ወቅት ከሚያጋጥማቸው የጤና አደጋና ተያያዥ የፊስቱላ ችግር በተጨማሪ ለሌሎች ለበሽታዎች ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ መሆኑን ያሳያሉ። ካለዕድሜያቸው ከሚወልዱ እናቶች የሚወለዱ ህጻናትም አምስት ዓመት እስከሚሞላቸው ድረስ እንኳን ይበልጥ ለሞት የተጋለጡ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ያለዕድሜ መውለድ ለሴት ልጆች ከትምህርት ገበታ መስተጓጎል አይነተኛ ምክንያት ነው።


ሴት ልጆች በዕድሜ በብዙ የሚበልጧቸውን ወንዶች እንዲያገቡ ሲደረግ በዕድሜ አለመመጣጠን የተነሳ በባልና ሚስት መካከል የውሳኔ ሠጪነትና የማኅበራዊ ደረጃ አለመጣጣም ችግሮችም ይከሠታሉ። ይህም የሚሆነው በአብዛኛው ሴቷ ልጅ በአካል፣

[2]እንደ ሲንግና ሳማራ (1996) ጥናት ሥራ መሥራት ወላጆች ልጆቻቸው ትዳር እንዳይመሠርቱ ከሚመርጡባቸው ምክንያቶች አንዱ ነው። ትምህርት በበኩሉ ስለወሊድ መቆጣጠሪያ ከሚኖር ዕውቀትና ከሴት ልጅ ከፍተኛ የውሳኔ ሠጭነት አቅም መዳበር ጋር አዎንታዊ ቁርኝት እንዳለው ያሳያል። እንዲሁም ከተሜነት ሴት ልጆች በለጋነታቸው ትዳር እንዳይዙ የሚያስችል አስተሳሰብ ከማላበሱ በተጨማሪ በቤተሠቦቻቸውና ቤተዘመዶቻቸው ከሚደርስባቸው ግፊትና ቁጥጥር ያርቃቸዋል።

በአእምሮና በስሜት በሚገባ ሳትበስል ትዳር እንድትመሠረት በመደረጉና ራሷን በሚገባ ለመግለጽ ባለመቻሏ የተነሳ ነው፡፡ በሕንድ አገር የተደረገ ሌላ ጥናት እንዳመለከተው 18 ዓመት ሳይሞላቸው ትዳር የመሠረቱ ሴቶች 18 ዓመት ሞልቷቸው ካገቡ ሴቶች ሁለት ጊዜ እጥፍ የቤት ውስጥ ጥቃት፤ እንዲሁም ሶስት ጊዜ እጥፍ ጾታዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው አመልክቷል (Jain and Kurz, 2007)፡፡

ካለዕድሜ ጋብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚታይ ሲሆን ችግሩን ከወንድና ሴት ልጆች የጋብቻ መመስረቻ ዕድሜ ልዩነት አንፃር ስንመለከተው መነሻ ጉዳዩ ሥነ-ጾታዊ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህንን በሚመለከት በእጃችን የሚገኘው የቅርብ ጊዜ መረጃ እ.ኤ.አ በግንቦት 2012 ይፋ የሆነው የ2011ዱ አገራዊ የሥነ-ሕዝብና ጤና ዳሠሣ (Demographic and Health Survey) ነው፡፡ በአገራችን የሴት ልጆች አማካይ የመጀመሪያ ትዳር መመስረቻ ዕድሜ 17.1 ዓመት ሲሆን የወንድ ልጆች ግን 23.1 መሆኑን መረጃው ይጠቁማል፡፡ ይህም ሴት ልጆች በአማካይ ትዳር የሚመሠርቱት በሕግ ከተቀመጠው ዝቅተኛ የትዳር መመስረቻ ዕድሜ (18 ዓመት) በአማካይ በአንድ ዓመት ቀድመው መሆኑን ያሳያል፡፡

**ምስል 1፡** በ2011 የመጀመሪያ ትዳር መያዣ ዕድሜ በጾታ፣ ክልል፣ ከተማና ገጠር




(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፡ 2012)

ከላይ በምስሉ እንደምንረዳው የሴት ልጆች የመጀመሪያ ጋብቻ ዕድሜ በከተሞችና በገጠር እንዲሁም በክልሎች መካከል ልዩነቶች እንዳሉት ይታያል፡፡ የሴት ልጆች አማካይ የጋብቻ ዕድሜ በከተሞች ከህጋዊው ዝቅተኛ የጋብቻ ዕድሜ መጠን ከፍ ያለ ሲሆን፤ በክልል ደረጃ ደግሞ የሴት ልጆች ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ በሠሜናዊ


የአገሪቱ ክፍሎች በሚገኙት የአማራና ትግራይ ክልሎች ከደቡባዊዎቹ የኦሮሚያና የደቡብ ሕዝቦች ክልሎች ዝቅ ያለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም ዳሠሣው የሴት ልጆች የትምህርት ደረጃ በጨመረ መጠን ትዳር የሚመሠርቱበት ዕድሜም ከፍ እንደሚል ይጠቁማል፡፡ከ25-49 ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉና እስከ 2ኛ ደረጃ ድረስ የተማሩ ሴቶች የትዳር መመስረቻ ዕድሜያቸው በአማካይ 22.8 ዓመት ድረስ ከፍ እንደሚል ታውቋል፡፡ የሀብት (የኑሮ) ደረጃም ተመሳሳይ ልዩነት ያሳያል፡፡ በናሙናነት የተያዙት ሴቶች በሀብት ደረጃ በአምስት ቅደም ተከተል እርከኖች ተከፍለው የመጨረሻው የሀብት እርከን ላይ ያሉት የጋብቻ ዕድሜ 16.4% ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ላሉት ግን 19.1 (ህጋዊው ዝቅተኛ የጋብቻ መመስረቻ ዕድሜ ከሆነው 18 ዓመት በታች) ሆኗል፡፡ በተቃራኒው ለወንዶች የትምህርትና የሀብት ደረጃ የትዳር መመስረቻ ዕድሜ ላይ ተፅዕኖ እንደሌላቸው ያሳያል (CSAE 2012a: ገጽ 66፣ ሠንጠረዥ 4.4) ፡፡

የ2011ዱ ዳሠሣ አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ መመስረቻ ዕድሜን እና ከ15-25 ባሉት የዕድሜ ክልሎች ውስጥ ሴት ልጆች ትዳር የመሠረቱበትን አማካይ ዕድሜ ያሳያል፡፡ በዚህ መሠረት ከ25-49 ዓመት ያላቸው ሴቶች ናሙና ውስጥ የመጀመሪያ ትዳር የመሠረቱበት አማካይ ዕድሜ 16.5 ዓመት ሲሆን የወንድ አቻዎቻቸው ግን 23.1 ዓመት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምስል 2 ከ20-25 እስከ 40-49 ዓመት ባሉት የዕድሜ ክልሎች ያሉ ሴቶች የመጀመሪያ ትዳር የመሠረቱበትን አማካይ ዕድሜና ከ15-19 እስከ 45-49 ባሉት የዕድሜ ክልሎች በ15 ዓመታቸው ትዳር የመሠረቱ ሴት ልጆችን አማካይ ዕድሜ አኃዝ ያሳያል፡፡

**ምስል 2**፡ <u>የመጀመሪያ ትዳር ሲይዙ የነበረ አማካይ ዕድሜ (በዕድሜ ክልል) እና በ15 ዓመታቸው ያገቡ ብዛት በመቶኛ</u>




(ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን 2012a)

ምስል 2 የዕድሜ ክልሎቹ በቀነሱ ቁጥር ትዳር የሚመሠርቱበት ዕድሜም ከፍ እንደሚል ያሳያል። ከ20-24 ዓመት ክልል ላሉ ናሙናዎች ይህ አኃዝ ዝቅተኛ ትዳር መመስረቻ ዕድሜ ከሆነው 18 ዓመት በላይ ሆኖ ተገኝቷል።

ጥናቶች የሴት ልጆች የጋብቻ ዕድሜን በተመለከተ ከወንዶች ቀድመው እንደሚያገቡ ቢጠቅሱም ብዙ ጊዜ ዕድሜ በጋብቻ ውስጥ እንደዋና መለያ ነገር (diacritical factor) ተደርጎ ስለማይወሰድ ጥናቶቹ ቁርጥ ያለ ነገር አያሳዩም። ነገር ግን በቅድመ-አብዮት ዘመን የሴት ልጆች ያለዕድሜ ጋብቻ በአማራና በተወሰነ መልኩ በትግራይ አካባቢዎች በስፋት ይታይ እንደነበር ግልጽ ነው። ልጆችን በህጻንነታቸው የማስተጫጨትና ልጅቷ በወደፊት ባለቤቷ ቤተሠቦች ዘንድ እንድታድግ የማድረግና እንዲሁም ወንዱ ወደፊት ለሚያገባት ባለቤቱ ወላጆች በጉልበት የሚያገለግልበት ልማዳዊ ወጎች በስፋት ይተገበሩ ነበሩ። አንዳንዴም ልጆቹ ገና ሳይወለዱ ወይም ገና ጭቅላ ህፃን እያሉ ወላጆች "ልጅህን ለልጄ" በመባባል ጋብቻ የሚመሠረትበት ወግ በስፋት ነበር (Ambatchew, 1956; Shack, 1974; Bauer, 1977)። የዚህ አይነቱ ጋብቻ በአብዛኛው በተጋቢዎቹ ቤተሠቦች መካከል በዘርና ኃብት ላይ የተመሠረተ ዘላቂ

ትስስር ለመፍጠር የታቀደና ደሀ ወንድ ልጆች ሚስት ለማግኘት የጉልበት አግልግሎት የሚሠጡበትን ስትራቴጂ የያዘ ነበር።


በትግራይ ከልጅቷ ቤተሠቦች ለአግቢው የሚሠጠው *ገዝሚ* የተባለ ጥሎሽ ከአስር እስከ አሥራ አምስት የሚደርስ የቀንድ ከብትና ፈረስ ወይም በቅሎ የሚያካትት ሲሆን፤ ሠጪው ሀብት ያለው ከሆነ መሬትና የጦር መሣሪያም ሊጨምር ይችላል (Shack 1994, Bawer, 1997)። በአማራ ጎጆ መውጫ በመርህ ደረጃ ከሁለቱም ወገን የሚሰጥ ሲሆን ይህ ስጦታ አብዛኛውን ጊዜ የቀንድ ከብት የመሳሰሉ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የሚያካትትና በፍቺ ወቅት እያንዳንዱ ወገን የራሱን ድርሻ የሚከፋፈልበት ሥርዓት ነው (Wodajo 1953; Ambatchew 1956; Hoben 1973)። እነዚህ ጎጆ መውጫ ስጦታዎችና በቤተሠብ የሚዘጋጁ ጋብቻዎች በአብዛኛው የሚፈጸሙት በመካከላቸው ቁርኝትን (ዝምድናን) ለመፍጠር በሚሹ ባለፀጋና የፖለቲካ ስልጣን ባላቸው ቤተሠቦች መካከል ሲሆን፤ ድሀ ቤተሠቦች ግን ልጆቻቸውን ለአቅመ-አዳምና አቅመ-ሔዋን እስኪደርሱ ድረስ ያዘገይዋቸዋል። እጅግ ደሀ የሆኑት ደግሞ የዚህ አይነት የጋብቻ ሁኔታን እስከነአካቴው አይሞክሩትም (Reminick 1973; Amera 2004)። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ የጋብቻ ስጦታ እየቀነሠ የመጣ ሲሆን አግቢው ለልጅቷ የሚሠጠውን ልብስና ጌጣጌጥ፤ ለወላጆቿ የሚበረከት ሌሎች የተወሠኑ ስጦታዎችን ብቻ ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪ የጎጆ መውጫ ስጦታ በመደብና የኃብት ደረጃ፣ እንዲሁም የ1966ቱን አብዮት ተከትሎ በተደረገው የመሬት ክፍፍልና እየተስፋፋ በመጣው ድህነት፣ ድርቅ፣ የህዝብ ብዛት መጨመርና የመሬት ጥበት ሳቢያ እየቀነሰ መጥቷል።

ከሠሜኑ የአገሪቱ ክልል በተለየ በኦሮሞና ሌሎች በደቡብ የአገሪቱ ክፍል በሚገኙ አያሌ ብሔረሠቦች ዘንድ ጥሎሽ የተለመደ ሥርዓት ነው። ይህ ጥሎሽ ጥንት በባህል በከብትና መጥረቢያ ይከፈል የነበረ ሲሆን ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው ከገባ በኋላ ግን በጥሬ ገንዘብ መከፈል ተጀምሯል (Huntingford 1955; Ambatchew et al. 1957; Cerulli 1956; Hamer 1987; Baxter 1996)። በእነዚህ ብሔረሠቦች አባላት ዘንድ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት በባህል የተለመደ ቢሆንም ድርጊቱ በጥቂት የተደላደለ ኑሮ ባላቸው ትልልቅ ሰዎች መካከል የተገደበ ነበር። ጠለፋና የ"ውዴታ ጠለፋ" (ተዋድዶ መኮብለል) ለጥሎሽ የሚጠየቀውን ከፍተኛ ክፍያ ለመፈጸም አቅማቸው በማይችል ደሀ ሰዎች የሚዘወተሩ፣ የተለመዱና ተቀባይነት ያላቸው የጋብቻ ዓይነቶች ናቸው (Cerulli 1956; Ambatchew et al. 1957; Holcomb 1973; Wadillo 1985)። በደቡቡ የአገሪቱ ክፍል ባሉ ብሔረሠቦች ዘንድ የጋብቻ ዕድሜን በተመለከተ የኢትኖግራፊያዊ ጥናቶች እምብዛም የተሟላ መረጃ አይሠጡም። ነገር ግን አንድ የኢትኖግራፊ ጥናት እንደሚያሳየው በኦሮሞ ብሔር ሴት ልጅ በ16 ዓመቷ እንድታገባ ሲጠበቅ፤ ወንድ ልጅ ደግሞ ከ20 ዓመት በፊት ትዳር እንዲመሠርት

አይጠበቅም ነበር። እነዚህ ኢትኖግራፊያዊ ጥናቶች በአብዛኛው በየብሔረሠቦቹ ለጋብቻ በማይፈለጉ (ለምሳሌ የቅርብ ዘመድን ያለማግባት) እና በሚመረጡ (ለምሳሌ በአፋር የአጎትማማች ልጆች ጋብቻ) ክፍሎች ላይ ያተኩራሉ (Huntingford 1955)።

በጥሎሽ ክፍያ ሥርዓትና ጠለፋን በባህል ተቀባይነት ያለው ጋብቻ አድረጎ በመውሠድ መካከል ጠንካራ ቁርኝት ያለ ይመስላል። የ2005ቱ የEDHS መረጃ እንደሚያሳየው በደቡብ (12.9%) እና በኦሮሚያ (10.8%) በጠለፋ ያገቡ ሴት ልጆች አማካይ ብዛት ከአገራዊው አማካይ (7.8%) ከፍ ያለ ሆኖ ተግኝቷል። ይህ ቁጥር በአማራ 2.4% እና በትግራይ 1.4% ብቻ ሲሆን፤ ይህም በከተሞች ከተመዘገበው የ4.7% እና የገጠር 8.5% እጅግ ዝቅ ያለ ሆኖ ተገኝቷል (ምስል 3)። በተመሳሳይ ሁኔታ ቢያንስ አንዲት ልጃቸው በጠለፋ ያገባች እንዳለች ለቤተሠቦች በቀረበው ጥያቄ በተሠጠው ምላሽ በከተማና በገጠር እንዲሁም በክልሎች መካከል ልዩነቶች ተስተውለዋል።

**ምስል 3፡** <u>በጠለፋ ያገቡ ሴቶችና ቢያንስ አንዲት ልጅ ተጠለፋ ያገባችባቸው ቤተሠቦች ስብጥር (በከተማ-ገጠርና በክልል)</u>




(ምንጭ፡የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን 2006)

## 2.2 የሴት ልጅ ግርዛት


የተለያዩ የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች ያሉ ሲሆን ከባዱ የግርዘት ዓይነት ከፍተኛ የጤና ቀውስ ያስከትላል:: እንደ የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ በዓለም ላይ ከ100-140 ሚሊዮን ሴቶች ግርዘት ተፈጽሞባቸዋል:: በየዓመቱም ሁለት ሚሊዮን ያህል ሴት ልጆች ይገረዛሉ (WHO 2010):: የሴት ልጅ ግርዛት በሠብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ በሴት ልጅ መብት ተከራካሪዎችና በአንትሮፖሎጂስቶች መካከል ከፍተኛ ክርክር ሲያስነሳ የኖረ ጉዳይ ነው:: ምንም እንኳን ብዛት ያላቸው የጤና ጥናቶች የሴት ልጅ ግርዛት በደፈናው ከብዙ የሥነ-ተዋልዶና ሌሎች የጤና እክሎች ጋር ቁርኝት እንዳለው ቢገልጹም፤ በተጨባጭ ግን የሴት ልጅ ግርዘት የሚያስከትለው የጤና ችግር እንደ ግርዘቱ ዓይነት ይለያያል:: በዚህ ረገድ ቂንጥርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የማስወገድ የግርዘት ኣይነት (Clitorodectomy) እና ቂንጥርንና የብልትን ትንሹን ከንፈር የመቁረጥ የግርዘት ዓይነት (Excision) የሚያስከትሉት የጤና እክሎች ላይ የተሠሩ በቂ የጥናት ውጤቶች የሉም:: በተቃራኒው ብልት መስፋትን የሚያካትተው የግርዘት ዓይነት (Infibulation) ዘላቂ ከሆነ የማህፀን እና የሽንት ቱቦ ችግር፣ በወር አበባና በግብረ-ስጋ ግንኙነት ወቅት ከሚፈጠር ከባድ ሕመም፣ ከወር አበባ መጠን መብዛት፣ ከመሀንነትና በወሊድ ወቅት ከሚፈጠር ችግር ጋር ይያያዛል:: የሴቶች መብት ተከራካሪዎችና የሠብዓዊ (እንዲሁም የሕፃናት) መብት ተሟጋቾች ድርጊቱ ጾታዊ መድልዎ ያለበት፣ አካላዊ ሙሉነትን የሚገስስ፣ የግብረ-ስጋ አካላትን የሚያጎድል ከዚህም በላይ ፈቃደኝነታቸውን ለመግለጽ በማይችሉ ሕጻናት ላይ የሚፈጸም ድርጊት መሆኑን በመጥቀስ ይኮንናሉ::

ነገር ግን በጣም ውስን የሆኑ የሴት ልጅ ግርዛት ተቃዎሚዎችን የሚተቹ ሌሎች ተማራማሪዎችም ይገኛሉ:: አንዳንዶቹ (ለምሳሌ Morison et al. 2001; Obermeyer 1999, 2005) የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትለውን የጤና ችግር የሚያሳዩ ጥናቶችን ጥልቀትና ትክክለኛነት ጥርጣሬ ውስጥ ሲያስገቡ፤ ሌሎቹ ደግሞ (ለምሳሌ Shell-Duncan, 2008) ድርጊቱ ግልጽ የሕፃናት መብት ረገጣ ነው የሚለውን ኃሳብ ጥያቄ ውስጥ ያስገባሉ:: ሌሎች ደግሞ ድርጊቱን ለማስቆም የሚደረገው ዘመቻ ሊያስነሳ የሚችለውን ማኅበራዊ ግጭትና በመካከሉ ሴት ልጆች ሊደርስባቸው በሚችለው ችግር ላይ ትኩረት ያደርጋሉ (e.g. Ahmadu and Shweder, 2009; Boddy 1998; Boyden, Pankhurst and Tafere 2012; Sabatello 2009)::

የሴት ልጅ ግርዛትን መጠንን በተመለከተ ያለው የቅርብ ጊዜ መረጃ ማጠቃለያው (summary) በሚያዝያ 2012 የተለቀቀው የ2011ዱ የደህንነት ግምገማ ሰርቬይ (Welfare Monitoring Survey) ነው:: መረጃው እንደሚያመለክተው ምንም እንኳን

በከተማና በገጠር እንዲሁም በክልሎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ቢኖርም በአሁኑ ጊዜ በአገር አቀፍ ደረጃ ድርጊቱ ከአራት ሴት በአንዷ ላይ እንደሚፈጸም ታውቋል።

**ምስል 4፡** <u>በ2011 ግርዘት የተፈጸመባቸው ሴቶች ስብጥር (በከተማና በገጠር በክልሎች)</u>




(ምንጭ፡ CSAE 2012b: 25, Figure 12.)

ከላይ በምስሉ ላይ እንደተመለከተው የከተማው 15% የግርዘት መጠን ከገጠሩ 24 ከመቶ እጅግ ያነሠ መሆኑ ይታያል። በክልሎች መካከል ደግሞ 15% ብቻ ከሆነባቸው የአዲስ አበባ፣ ደ/ብ/ብ/ህ/ እና የጋምቤላ ህዝቦች ክልሎች እስከ 40 ከመቶ ገደማ የሆነበት የአፋር ክልል ድረስ ይለያያል። *ያንግ ላይቭስ* ከሚሰራባቸው ክልሎች መካከል ከሁለት ሴቶች አንዷ የተገረዘች የሆነበት የአማራ ክልል ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ሲሆን፤ ከአራት ሴቶች አንዷ የምትገረዝበት ትግራይ በሁለተኝነት ይከተላል። ኦሮሚያ (ከአምስት አንድ)፣ እና ከ10% በታች የሚገረዙባቸው የደቡብና የአዲስ አበባ ክልሎች በመቀጠል ተቀምጠዋል።

በ1997 የተካሄደ አንድ ጥናት በኢትዮጵያ ከአካባቢ አካባቢ የሚለያዩ ውስብስብ የግርዘት ዓይነቶች እንዳሉ ይጠቁማል። በአጠቃላይ ስንመለከት ግን ሶስት ዓይነት የሴት ልጅ የግርዘት አይነቶች ይገኛሉ። እነዚህም ቂንጥርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የማስወገድ (Clitorodectomy)፣ ቂንጥርንና የብልትን ትንሹን ከንፈር የመቁረጥ (Excision) እና ቂንጥርና የብልትን ከንፈር በመቁረጥ ብልትን የመስፋት

(Infibulation) ናቸው:: እጅግ ዘግናኙ የግርዘት ዓይነት የሴት ልጅ ብልትን በመስፋት የሚከናወነው (Infibulation) ሲሆን የዚህ ዓይነቱ አገራረዝ በምሥራቁ የአገሪቱ ክፍል በሚገኙት የሱማሌና የአፋር ብሔረሠቦች የሚከናወን፤ በሌላ በየትም የአገሪቱ ክፍል የማይደረግ ነው:: ይህ የግርዘት ዓይነት በአፋር በተወሰነ መጠን ቂንጥርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የማስወገድ የግርዘት ዓይነት ጋርም ይያያዛል:: የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የግርዘት ዓይነቶች በአማራ በስፋት የሚዘወተሩ ሲሆን በትግራይ በመጠኑ፤ በደቡብ ደግሞ በጥቂቱ ይታይሉ:: በኦሮሚያ cliterodectomy በጣም የተለመደ የግርዘት ዓይነት ሲሆን excision ግን እምብዛም አይዘወተርም:: ምንም አይነት የሴት ልጅ ግርዘት የማይደረግበት ብቸኛው ክልል የጋምቤላ ህዝቦች ክልል ብቻ ነው::

ሴት ልጆች የሚገረዙበት ዕድሜን በተመለከተ በሠሜንና በደቡብ ክልሎች መካከል ልዩነቶች ይስተዋላሉ:: በሠሜን ኢትዮጵያ ልጆች ገና እንደተወለዱ ወይም በተወለዱ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ሲከናወን፤ በደቡብ ግን ድርጊቱ ከጋብቻ ጋር ተያይዞ ይፈጸማል:: በሠሜን cliterodectomy እና/ወይም labiadectomy የተለመደ የገርዘት ዓይነት ሲሆን፤ በትግራይ ህጻኗ በተወለደች በሠባተኛው ቀን፤ በአማራ ደግሞ በአምስተኛው፣ በሠባተኛው ወይም በአሥራ አምስተኛው ቀን ይፈጸማል:: በመሆኑም በዚህ ክፍል የሴት ልጅ ግርዛት ልጅቷ ገና ስም እንኳን ሳይወጣላት በአራስነት ቤት የሚፈጸም ነው::

በኦሮሞና ሌሎች የደቡብ ብሔረሠቦች ግን ግርዘት የተለየ ማኅበራዊ ቦታ አለው:: የአማራ ባህልና የእስልምና ኃይማኖት ተፅዕኖዎች ጎልተው በሚታዩባቸው የደቡብ ኦሮሞ አካባቢዎች ብቻ ሴት ልጆች በአራስነታቸው ግርዘት ሲያከናውኑ፤ በአንዳንድ የምዕራብ ኦሮሞ አካባቢዎች ሴት ልጆች ከ10 ዓመታቸው በፊት ይገረዛሉ:: በምሥራቅ ከ9-12 ዓመት ዕድሜ፤ በመካከለኛው የአርሲ ኦሮሞ ክፍል (*የያንግ ላይብሽ አንዱ የጥናት ቦታ በሚገኝበት*) ደግሞ ግርዘት ከጋብቻ በፊት ይከናወናል (Tippet 1970: 9—12; Slikerveer 1990; Terefe 2000; EGLDAM 2008a: 95—6)::


የሴት ልጆች ግርዘት ከወንድ ልጆች ግርዘት ጋር በአንድ ላይ ይከናወን እንደሆነ፤ እንዲሁም ግርዘት ከአንድ የሰውነት ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የመሸጋገሪያ ሥርዓት (rite of passage) መሆንና አለመሆኑ፣ የማኅበረሠቡ የወል ጉዳይ ወይንም የቤተሠብ ብቻ ጣጣ መሆኑ እንዲሁም ግርዘቱን የሚፈጽመው ሰው ማንነት ላይም ልዩነቶች ይስተዋላሉ:: በደቡብ ባሉ ብሔረሠቦች የወል ግርዘት በጣም የተለመደ ሲሆን ገራዦችም በአብዛኛው የዕደ-ጥበብ ባለሙያዎች ናቸው:: በወላይታ ብሔረሠብ አባላት ልጃገረዶች ከሠርጋቸው በፊት በcliterodectomy የግርዘት አይነት በሸክላ ሠሪዎች ይገረዛሉ (Berhane Selassie 1993):: በከምባታና ሀዲያ የጋራ ግርዘት ከፍተኛ

ስፍራ ያለው ሲሆን በአንድ ላይ የተገረዙ ልጃገረዶች የገበያ ቀን ለህዝብ ተሠልፈው እንዲታዩ ያደረጋል (Braukämper 1983)፡፡ በሲዳማ ደግሞ ሴት ልጅ በስምንት ዓመቷ ገደማ ወይም ከማግባትዋ ቀደም ብሎ፤ ወይም ልክ እንዳገባች (ክብረ-ንፅህና እንዳላት በሚረጋገጥበት ወቅት) እንድትገረዝ ይደረግና ለሁለት ወር ገደማ ከሰው ተለይታ በባልዋ ቤተሠብ ቅቤ፤ ወተትና ስጋ እየተመገበች እንድትቆይ ይደረጋል (Hamer 1987: 68, Elfmann 2005; EGLDAM 2008a: 95)፡፡ በጉራጌ ብሔረሠብ ልጆች ከ8 እስከ 10 ዓመት ሲሆናቸው በዓል ተደርጎ የሚገረዙ ሲሆን ገራዦችም ቀደም ሲል ኑሯቸውን በአደን ይገፉ የነበሩ የተለዩ ጎሣ አባላት ናቸው፡፡ በአንድ ላይ የተገረዙ ሴት ልጆች በሌላ የተለየ ጎሣ አለቃ "የውሸት" ተጠልፈው በጫካ ውስጥ ለአንድ ወር ያህል ከወንዶች ተደብቀው የritual ቋንቋ እየተማሩ ይቆያሉ፡፡ እነዚህ በአንድ ላይ የተገረዙ ሴት ልጆች ባል እስከሚያገቡ ድረስ የዚህ ቡድን አባላት ይሆናሉ (Huntingford 1955; Cerulli 1956; Shack 1966: 131—4)፡፡ በተለያዩ የደቡብ ብሔሠቦች ውስጥ ወንድንና ሴት ልጆችን የመግረዝ ኃላፊነት በወላይታ "ጭኔሳ" በመባል የሚታወቁትን ለመሳሰሉ በሸክላ ሥራ፣ በአንጥረኝነትና በቆዳ ማልፋት ሥራ ለተሰማሩ ልዩ ጎሣ አባላት የተሠጠ ተግባር ነው፡፡ የእነዚህ ጎሣ አባላት ከግርዘት በተጨማሪ በማዋለድና ቀብር ሥርዓቶች ላይም ይሳተፋሉ (Pankhurst 2003)፡፡

## 3 የሴት ልጆች ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘት ባህላዊና ቁሳዊ መሠረቶች

በዚህ ክፍል በአምስቱ የጥናት አካባቢዎች ለሴት ልጆች ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘት ባህላዊና ቁሳዊ መሠረቶች የሆኑ ነገሮችን እንመለከታለን፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ያላት ሠፊ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ልዩነቶች በእነዚህ ጉዳዮች ላይም በሠፊው የሚጸባረቁ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህ መሠረት ለምሳሌ በአማራና በትግራይ የጥናቱ አካባቢዎች ያለው አንፃራዊ የባህልና የብሔረሠብ መመሳሰል የሴት ልጅን ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘትን በተመለከተ ተመሳሳይ አመለካከትና ድርጊት ይታያል፡፡ እነዚህን ሁለቱንም ድርጊቶች በተመለከተ ያለው ለውጥና መሻሻል በአዲስ አበባና ሌሎች የከተማ አካባቢዎች በአጠቃላይ ፈጣን ቢሆንም ከ1997 እስከ 2007 የተካሄደ ዳሠሣ እንደሚያሳየው ለውጡ ከኦርቶዶክስና ሌሎች የክርስትና ዕምነቶች ተከታዮች ጋር ሲነፃፀር ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሲሶውን በሚሸፍኑት የእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል ግን አዝጋሚ መሆኑ ታይቷል (ምስል 5ን ተመልከት)፡፡

**ምስል 5፡** <u>ከ1997-2007 የሴት ልጅ ግርዛት በተመለከተ የታየ ለውጥና መሻሻል (በየኃይማኖቱ ዘርፍ)</u>




(ምንጭ፡ የቀድሞው የጎጂ ባህሎች አስወጋጅ ብሔራዊ ኮሚቴ (1998) እና EGLDAM (2008a))

የ"ዘመናዊነት" (modernity) መስፋፋትና እነዚህን 'ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን' ለማስወገድ መንግሥት፤ ዓለም አቀፍና አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያደርጓቸው ጥረቶች በከተሞች አካባቢ የበለጠ ለውጥ እንዳመጡ ጥናቱ አመልክቷል። ነገር ግን ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሱ ሰዎች ይህንን ልማድ ይዘው በመምጣት በከተሞችም መተግበር እንደሚቀጥሉ ታውቋል። ለምሳሌ በደቡብ የሴት ልጅ ግርዛት ከማንኛውም አካባቢ የበለጠ በወላይታ የተስፋፋ መሆኑ ይታወቃል (ሀዋሳ ሁለተኛው ትልቁ የከተማ ናሙና ሲሆን የወላይታ ብሔረሠብ አባላት ከከተማው ካለው ጠቅላላው የያንግ ላይቭስ ናሙና ልጆች መካከል ሲሶውን ያህሉን ይሸፍናሉ)። ይህ አይነት ልዩነት የብሔረሠብ ስብጥራቸው ከፍተኛ በሆነባቸው የከተማ አካባቢዎች የሚጠበቅ ቢሆንም፣ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘትን በተመለከተ በአንጻራዊ ብሔረሠባዊ ስብጥራቸው አነስተኛ በሆነባቸው የገጠር አካባቢዎች ሳይቀር በህብረተሠቡ መካከል ባለው የኑሮ ደረጃ፣ ዕድሜና ማኅበራዊ ደረጃ ልዩነቶች ሳቢያ የድርጊቱ ደረጃ ልዩነቶች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል።

በአብዛኛው ህብረተሠብ ውስጥ (ምንም እንኳን በሁሉም ባይሆንም) ሁለቱ ልምዶች ጠንካራ ባህላዊ መሠረቶችና አመንክዮሽ (cultural logic) ያላቸውና እንዲህ በቀላሉ ሊለወጡ የሚችሉ እንዳልሆኑ አበክሮ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም ሁለት አበይት ጉዳዮችን የያዘ ነው። በመጀመሪያ የሴቷ ቤተሠቦችና ቤተዘመዶች በሴቷ ጉልበትና ልጅ የመውለድ (እና ዘርን የመተካት) ችሎታ ላይ ከፍተኛ ስልጣን ያላቸውና ይህም የሴቷን ልጅ የወሲብ ባህሪን እስከመቆጣጠር ድረስ የሚሄድ ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ

የሴት ልጅ ግርዛትና ጋብቻ ሴት ልጆች ወደ ማኅበረሠቡ የሚዋሀዱበት፤ የግብረ-ገብ ደረጃቸው የሚልቅበትና ማኅበረሠቡም እነርሱን ከጉዳት የሚከላከልበት መንገድ ተደርጎ በመቆጠሩ ነው:: በመሆኑም ብዙ መላሾች እነዚህን ሁለቱንም ድርጊቶች በሴቶች ልጆች ላይ የሚደረጉ ጥቃቶች አድርገው አይቆጥሯቸውም:: እንዲያውም ከብሔራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ፖሊሲ ተንታኞች በተፃራሪ ድርጊቶቹን ለሴቶቹ ልጆች ማንነት መሠረት አድርገው ይመለከቷቸዋል:: የዚህ አመለካከት ማኀበራዊ ኃይል የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ክፍሎች ድርጊቶቹን ለማስቀነስና ብሎም ለማስቆም በከፍተኛ ደረጃ በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ሳይቀር ዕንቅፋት ሲሆን ይስተዋላል::

ከላይ እንደተገለጸው ሁለቱ ልምዶች ብዙ ጊዜ እርስ በርስ የተቆራኙ ሲሆን የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ጋብቻ ቅድመ-ሁኔታ ተደርጎ ይታያል:: ጋብቻ ደግሞ ወደ ሙሉ ሰውነት የመተላለፍ ሽግግር ተደርጎ ይወሰዳል:: በዚያው መጠን ሁለቱም ልማዶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ ቁጥጥር የማድረግ ባህላዊ ወግ ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: ሁለቱም ድርጊቶች ሴቶች ልቅ ግንኙነትን እንዳያዳብሩና ወሲባዊ 'አደጋ' እንዳይደርስባቸው ወሲባዊ ፍላጎታቸውን ለመገደብ፣ ያለወቅቱ የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንዳይጀምሩና ዝሙት ከመፈጸም ታቅበው በጊዜያቸው በወግ በማዕረግ ትዳር እንዲመሠርቱ ያስችላሉ በሚል ዕምነት የሚተገበሩ ናቸው::

## 3.1 የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ

የባህላዊው የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ዋና ዋና ገጽታዎች መካከል አንዱ ጋብቻው በዋናነት በተጋቢዎቹ ወላጆች የሚመቻችና አግቢዋ ማንንና መቼ ማግባት እንዳለባት፤ እንዲሁም የተጋቢዎቹ ቤተሠቦች ከጋብቻው ምን ሊያገኙ እንደሚችሉ በወላጆች የሚወሠን መሆኑ ነው:: በዚህ ረገድ የማኅበራዊ ዋስትና ፈጽሞ በሌለበት ወይም ባልዳበረበትና ለተደጋጋሚ የተፈጥሮ አደጋ በተጋለጠ በዝናብ ላይ የተመሠረተ የእርሻ ኢኮኖሚ ላይ ጥገኛ በሆነው የኢትዮጵያ ህብረተሠብ ውስጥ በወላጆች መልካም ፈቃድ የሚመቻች ጋብቻ በስነ-ህዝብና ማቴሪያል ረገድ ጠቀሜታ ሊኖረው እንደሚችል የአዝጋሚ ለውጥ ንድፈ-ኃሳብ (evolutionary throey) ለማስረዳት ይሞክራል:: የአንድ ቤተሠብ የሀብት መጠንና የኑሮ ደረጃ ቤተሠቡ ውስጥ ባሉት ሴት አባላት የመውለድ አቅም ጋር በቅርብ እንደተገናኘ ሲታሰብ ብዙ ልጆች ያለው ቤተሠብ የቤተሠቡን የሥራ አቅም/ጉልበት ያጎለብታል:: የእናቶችና ሕጻናት ሞት ከፍተኛ በሆነበት ሁኔታ ሴት ልጆችን በለጋ ዕድሜያቸው መዳር በአጠቃላይ የልጆቹን ብዙ ልጅ የመውለድ እድል በማስፋት የቤተሠብ የሥራ ኃይል ዋስትናን ማስተማመን ይሆናል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ሴት ልጆችን ትዳር ማስያዝ ችግር በጣም ለሚጠናባቸው ቤተሠቦች የቤተሠብ ቁጥርን መቀነሻ ዘዴ ይሆናል:: በዓለም አቀፍ

ደረጃ የተደረጉ አንዳንድ ጥናቶች የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ለልጅቷ ቤተሠቦች ከሚሠጠው ጥሎሽ ጋር እንደሚያያዝ ያመለክታሉ። ጥሎሹም የሴቷን ልጅ የግብረ-ስጋ ፈቃድና ልጅ ወልዶ የማሳደግ አቅም ለማግኘት የአግቢው ወገን ለልጅቷ ቤተሠብ የሚከፍለው ክፍያ ተደርጎ ይወሰዳል። እነዚህም ነገሮች በልጅነት የዕድሜ ክልል የተሻለ ዋጋ ያወጣሉ ተብሎም ይታመናል።

በኢትዮጵያ የተደረጉ ጥናቶች ግን ይህንን በማቴሪያል ላይ የተመሠረተ ትንተና ጥርጣሬ ላይ የሚጥል ውጤት ያሳያሉ። በመጀመሪያ የልጅነት ጋብቻ ፍቃድ የሚፈፀመው ለልጆቻቸው መልካም የትዳር ጓደኛ በሚሹ ሀብታምና ቀደም ሲል ደግሞ ጠንካራ የፖለቲካ መሠረት በነበራቸው ቤተሠቦች፤ ከዚያም ገፋ ሲል ደግሞ ከደሀ ቤተሠብ የወጣ ትዳር ፈላጊ ወጣት ለሀብታም ቤተሠብ አድሮ በማገልገል በመጨረሻ ልጃቸውን በሚያገባበት ሁኔታ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ያለዕድሜ ጋብቻ በብዛት የሚተገበረው የሴት ቤተሠቦች ጥሎሽ በሚሠጡበት ሳይሆን በተቃራኒው የሴት ልጅ ቤተሠቦች ለወንዱ በሚሰጡበት የሠሜኑ የአገሪቱ ክፍል ነው። ይህም የሴቷ ቤተሠቦች አቻችን የሚሉትን የልጅ ባል እስከሚያገኙ ድረስ ትዳር የሚዘገይበት ሳይሆን እንዲያውም ልጆች ገና በጨቅላነታቸው የሚተጫጩበት ሥርዓት ነው። የዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚታየው በባለፀጋ ቤተሠቦች መካከል ሲሆን የድህነት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመጣ ቁጥር የሚሠጠው የጥሎሽ መጠንም እየቀነሠ መጥቷል። በሶስተኛነት የጥሎሽ ሥርዓት ጠንካራ በሆነበት የደቡቡ የአገሪቱ ክፍል ያለዕድሜ ጋብቻ እምብዛም የተለመደ አይደለም። ይህም የሚሆነው ምናልባትም ወጣት ወንድ ልጆችና ቤተሠቦቻቸው ይህንን ከፍ ያለ የጥሎሽ ገንዘብ ለማጠራቀም ጊዜ ስለሚወስድባቸው ትዳር እንዲዘገይ ምክንያት ይሆናል። እንዲሁም የጥሎሽ መጠን ከፍ ማለት ከአንድ በላይ ሚስት የማግባትን መጠን ገድቦታል።

ያንግ ላይብስ ጥናት ባካሄደባቸው አካባቢዎች የተሠበሠቡት መረጃዎች የተደባለቀ ምስል የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል። በአማራ ክልል የጥናት አካባቢ አንድ የቀበሌ ተመራጭ ሴት ልጅን በትንሽነቷ መዳር የልጅቷን የመውለድ ዕድሜ በማራዘም ብዙ ልጅ እንድትወልድ ያስችላታል ብለዋል። በትግራይና አማራ ክልል የጥናቱ አካባቢዎች ቤተሠብ ጋብቻን የሚያደራጅበትና ሴት ልጆች የትዳር አጋራቸውንም ሆነ የትዳር ዕድሜያቸውን ለመወሠን የማይችሉበት የትዳር አደረጃጀት ዋና ዓላማ አዲስ የሚመሠረተውን ቤተሠብ የኢኮኖሚ ዓቅም ለማደራጀት እንደሆነ ገልጸዋል። ለምሳሌ በትግራይ የጥናቱ አካባቢ አንድ አሳዳጊ ቤተሠቦች የልጃቸው የወደፊት ሚስት ከሀብታም ቤተሠብ የወጣች እንድትሆን በፅኑ ይሻሉ ሲሉ ተናግረዋል። በአካባቢው ባህል መሠረት የልጅቷ ቤተሠቦች የሚሠጡት ጥሎሽ ወንዱ ከሚሠጠው ዕጥፍ ነው። ዛሬ ዛሬ ግን ይህ ባህል እየተዳከመ መጥቷል። በአማራ ክልል የጥናቱ አካባቢ ደግሞ ደሀና አቅመ-ቢስ ወላጆች ደህና ድጋፍ ሊሠጥ የሚችል የልጅ ባል እንደሚሹ

ተደርሶበታል። ነገር ግን በዚህ ላይ አንድ የአካባቢው ባለስልጣን የተለየ አስተያየት ሠጥተዋል። እንደርሳቸው አስተያየት በቀድሞ ጊዜ ሀብታም ወላጆች ከደሀ ወላጆች ይበልጥ ልጆቻቸውን በልጅነታቸው ትዳር ያስይዙ ነበር። ለዚህ ዋና ምክንያቱ ልጅን በልጅነቱ ትዳር ማስያዝ "የባለፀጋነት አንዱ መለኪያ ተደርጎ ስለሚቆጠር" እና እንዲሁም እነዚህ ሀብታም ወላጆች ብዙ መሬት ስለሚኖራቸው ከሌሎች ሀብታም ቤተሠቦች ጋር በጋብቻ መተሳሰር ስለሚፈልጉ ነበር። የልጅቷና የልጁ ወላጆች ለአዲስ ተጋቢዎቹ ከሁለቱም ወገን ተመጣጣኝ የሆነ የእርሻ መሬትና የቁም ከብት ስጦታ መስጠትም የተለመደ ባህል ነበር። ዛሬ ግን የእርሻ መሬትና የቁም ከብት ብዛት እያነሠ በመምጣቱ ለአዲስ ተጋቢዎች የሚሠጠው የመሬት ስጦታ እጅግ አነስተኛ ሲሆን፤ የቁም ከብት ስጦታው ደግሞ ከ500 እስከ አንድ ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ ስጦታ ተተክቷል።

በኦሮሚያ የጥናቱ አካባቢ የአገር ሽማግሌዎች እንደገለፁት ቤተሠብ ከሚያደራጀው ጋብቻ የልጅቷ ቤተሠቦች የሚያገኙት ዋና ጥቅም ጥሎሽ (በአካባቢው "*ገበራ*") ሲሆን ይህም ሁለት ሺ ብርና አያሌ የቁም ከብቶች ያካትታል። እንዲያውም አንዳንድ የአካባቢው ሰዎች እንደሚገልጹት በቤተሠብ የሚደረግ ጋብቻ ሴት ልጅን በገንዘብ እንደመቀየር (እንደመሸጥ) ሊቆጠር ይችላል ይላሉ። ነገር ግን ይህንን ከፍተኛ የ"*ገበራ*" ገንዘብ ማጠራቀም ለአብዛኛው ትዳር ፈላጊ ወጣት አዳጋች በመሆኑ አንዳንድ ወጣቶች በቤተሠብ ከሚደረግ ጋብቻ ይልቅ ከወደዷት ወጣት ጋር "የውዴታ ጠለፋ" በመፈጸም ትዳር ይመሠርታሉ። ከዚህ በተጨማሪ የገበራ ከፍተኛ መሆን ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን ከባድ አድርጎታል።

የጥናቱ የተሳታፊዎች ለሴት ልጆች ያለዕድሜ ጋብቻ አንዱ ዋና ምክንያት ነው ብለው ያስቀመጡት ከጋብቻ በፊት ሴት ልጆች የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሊጀምሩ ይችላሉ የሚለው ስጋት ነው። ሴት ልጆች ለአቅመ-ሔዋን ከመድረሳቸው በፊት ወይም ገና እንደደረሱ ጋብቻ ማስያዝ ለግብረ-ስጋ ግንኙነት በሚደርሱበት ጊዜ ጨዋነታቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል ተብሎ ይታመናል። የሴት ልጅ ያለዕድሜ (በልጅነት) ጋብቻ ሲነሳ ከጋብቻ በፊት ወሲብ የመፈፀም "አደጋ" እና ስጋት በስፋት የሚነሳ ሲሆን ይህም ሊከሰት ከሚችል ከስነ-ተዋልዶ ጤንነት ችግር አንስቶ የቤተሠብ ክብር መነካት፤ ያልፈለገ እርግዝና መከሠትና ከቤተሠብ፤ ጎሣና ጎረቤት መገለልን ያካትታል። በዚህ ሳቢያ በኦሮሚያ ወላጆች ሴት ልጅን በጊዜ ትዳር ማስያዝ ልጅቷን ከዝሙትና ተላላፊ የአባለዘር በሽታዎች (በተለይ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ) አይነተኛ መከላከያ ዘዴ አድርገው ይመለከቱታል። ከዚህ በተጨማሪ ከጋብቻ በፊት ወሲብ የጀመሩ ልጃገረዶች በፍቅር ጓደኞቻቸው የኂላ ኂላ እንዴት ሊከዱ እንደሚችሉ፣ ይህም ወደፊት ሌላ የትዳር ጓደኛ እንዳያገኙ እንደሚያደርጋቸውና እንዲሁም ከጋብቻ

በፊት ወሲብ በመፈፀም የወለደች ልጃገረድ ከነልጇ ከቤተሠብና ከጎሣ እንደምትገለል ያስረዳሉ።

## 3.2 የሴትልጅ ግርዛት

የሴት ልጅ ግርዛት ምክንያት ተደርገው የሚቀርቡ ሠበቦች ከሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ሠበቦች ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይ ሲሆኑ ግርዘት የሴትዋን ከልክ ያለፈ የወሲብ ፍላጎትን በመቆጣጠር ጨዋና ትዳርዋን አክባሪ የሆነች ልጅ እንድትሆን ያስችላታል የሚል ነው። የሴት ልጅ ግርዘት ከትዳር ባለፈ ልጅቷን ከ"ቆሻሻ" በማንፃት መልካም ባህሪ ያላብሳታል የሚል አስተሳሰብም ይንፀባረቃል። በዚህ ረገድ የሴት ልጅ ግርዛት እንደማኅበራዊ አካልና መንፈሳዊ ሕንፀት ሊቆጠር ይችላል። ሴት ልጅ በምትገረዝበት ማኅበረሠብ ውስጥ እያንዳንዷ ሴት ለሙሉ አካል የደረሠች፣ ለትዳር የምትመጥን፣ "ቆንጆ"፣ ንፁህና "ፅዱ" ለመሆን መገረዝ የግድ ነው በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው (Boddy 1998: 86).

ይህ አመለካከት ጥናቱ በተካሄደባቸውና አሁንም የሴት ልጅ ግርዛት በሚፈፀምባቸው (ከትግራይ በስተቀር) በአራቱም የጥናት አካባቢዎች ለጥናቱ በተመረጡ ናሙናዎች ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ሁኔታ ተንፀባርቋል። ሆኖም ይህ አመለካከት በተለይ በኦሮሚያ የጥናቱ አካባቢ የበለጠ የተጠናከረ ሲሆን፤ በዚያ አካባቢ የሴት ልጅ ግርዛት ከ“ህንፀት”፤ አለመገረዝ ደግሞ ከቆሻሻ አለመወገድ ጋር ያያይዙታል። የሴት ልጅን መገረዝን በመደገፍ በአንድ የወጣት ወንዶች የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ያልገረዙ ሴቶች በተገረዙ ሴቶች “ልምቡጣም” ተብለው ይሠደባሉ ሲሉ ገልፀዋል።

ሌላ አንድ አሳዳጊ ሲያብራራ “ያልተገረዘች ሴት ልጅ በገላዋ ላይ ቆሻሻ እንደተሸከመች ተቆጠራለች። በዚህም ሳቢያ በጓደኞቿ፣ በዕድሜ እኩዮቿና በጎረቤት ትነቀፋለች” ብሏል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በሀዋሳ አንድ አዛውንት ያልተገረዘች ሴት ልጅ ባል የማታገኝ ሲሆን በመጨረሻም “ቆማ ቀር” ትሆናለች ብለዋል። አንዳንድ መላሾች የሴት ልጅ ግርዛትን ምክንያት ሲያብራሩ “ካልተገረዘች ቆማ ትቀራለች” የሚለውንና ያልተገረዘች ሴት ልጅን ከወንድ የሚያመሳስለውን የአማርኛ አባባል ይጠቅሳሉ።

በአዲስ አበባ በቡድን ውይይት ላይ የተሳተፉ ሙስሊም ወጣት ሴቶች በእነርሱ ማኅበረሠብ የተገረዘች ሴት ልጅ ንፁህ፣ “የተረጋጋች” እና ከወንድ ጋር ለመቅበጥ የማትሻ እንደሆነች ተደርጎ እንደሚታይ ይገልፃሉ። በእነርሱ አመለካከት ግርዘት “የአንዲት ልጅ አስፈላጊ የህይወት አካል ሲሆን እንደ ቀበጥባጣነት፣ ከቁጥጥር ውጭ መሆን፣ እረፍት የለሽነትና ካለዕድሜ ወሲብን መመፈለግን ከመሳሰሉ “መጥፎ”

ባህሪያት ለመከላከል ይረዳል። አንዲት ተሳታፊ ያልተገረዙ ሴት ልጆች "ለፍላፊዎች" እንደሚሆኑ ስትገልጽ፤ ሌሎቹ ደግሞ ሴሰኞችና ካለዕድሜያቸው የጾታ ግንኙነት የሚጀምሩ እንደሚሆኑ አመልክተዋል። በአማራ ክልል አንድ አሳዳጊ ሲገልጹ ያልተገረዘች ሴት ልጅ የወሲብ ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ ስለሚሆን ከባሏ ጋር ተስማምታ ለመኖር ያዳግታታል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ግርዘት ሴቶች በቤት ውስጥ ሥራ እንዳይሠንፉ ይረዳል የሚል አስተያየትም ይታያል። ይህ አስተሳሰብ በአዋሳ "ያልተገረዘች ልጅ ቅል ትሠብራለች□" በሚል አባባል ተደግፎ በስፋት ተንፀባርቋል። ይህም ማለት ያልተገረዘች ልጅ በቤት ውስጥ ባልትና ትሠንፋለች የሚል አመለካከትን መሠረት ያደረገ ነው። በዚሁ በአዋሳ ከተማ ያሉ አንድ የወላይታ ብሔረሠብ አባል የሆኑ አዛውንት ካለመገረዝ የሚኖር አለመጽዳትና ስንፍና ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸው ሲያስረዱ "ሴት ልጅ ካልተገረዘች ዕቃ ትሠብራለች ይባላል። ግንኮ ያልተገረዘች ልጅ ያዘጋጀችውን ምግብ ማን ይበላል? እሷ እኮ አልፀዳችም!" በማለት ገልፀዋል። የህንፅት ጉዳይ የኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ ብሔረሠቦች አባላት ዘንድ ትልቅ ቦታ አለው (ለዚህ የወላይታ ብሔረሠብ ዋና ምሳሌ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል)። "ያልፀዳች ልጅ ምግብ ማብሰል አትችልም" የሚለው አመለካከት አለመገረዝ የሴት ልጅ ዋና የቤት ውስጥ ተግባር/ሚና ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ያሳድራል። ነገር ግን እንደሌላው ባህላዊ አመለካከት ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም የህብረተሠብ ክፍል አንድ አይነት አቋም የለውም። በተለይ በሥልጣን ላይ ያሉ ክፍሎች በሴት ልጅ ግርዛት አይስማሙም። አንዲት የቀበሌ ሴቶች ማኅበር መሪ "የ14 ዓመት ሴት ልጅ አለችኝ። አላስገረዝኳትም። ነገር ግን እስከ ዛሬ በቤት ውስጥ ምንም ዕቃ አልሰበረችም። ቀደም ሲል የሴት ልጅ ግርዛት አስፈላጊ ነው ብዬ አስብ ነበር። አሁን ግን አልቀበለውም" ብላለች።

አብዛኛው የሴት ልጅ ግርዛት ተቃውሞና እንዲወገድ የሚደረገው ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ውትወታ ድርጊቱ የሚያደርሰውን የጤና ችግር በማስመልከት ነው። ነገር ግን ተግባሩን የሚደግፉ ክፍሎች ግርዘት የጤና ጠቀሜታም አለው በማለት ይከራከራሉ። ተግባሩን በሚመለከት ያለውን ኦፊሴላዊ ፖሊሲ የሚገነዘቡ ቢሆንም ድርጊቱን ግን ይፈፅማሉ። ለምሳሌ በኦሮሚያ ያሉ ያገር ሽማግሌዎች (elders) መንግሥት በደም መፍሰስና በመሳሰሉት የጤና አደጋዎች ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛትን እንደከለከለ ቢያውቁም በክልከላው ግን አይስማሙም። ላለመስማማታቸው ዋና ምክንያት ደግሞ በግርዛት "ተቆርጦ የሚጣለው የሰውነት ክፍል ነው፣ የሚቀረውም የሰውነት ክፍል ነው። የሴት ልጅ ግርዛት ምንም ጉዳት የለውም፣ በምትገረዘው ልጅ ጤንነት ላይም ምንም ችግር አያደርስም□□" በማለት ይከራከራሉ። በግርዛት ጊዜ የደም መፍሠስን እንደጤና አደጋ ከመቁጠር ይልቅ "በግርዛት ጊዜ የሚፈሰው ደም በሰውነት ውስጥ ያሉ አንዳንድ በሽታዎች አጥቦ ያወጣል። እንዲያውም ለአንዳንድ የበሽታ ዓይነቶች

ግርዛት በጣም ጠቃሚ ነው" ይላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ በአማራ የጥናት አካባቢ ያሉ አንዲት አዛውንት ገጠመኝ ባሉት ታሪክ አንዲት ያልተገረዘች ሴት አርግዛ ቤት ውስጥ በሠላም ለመገላገል ስላልቻለች ወደ ሆስፒታል እንደተወሰደችና ዶክተሩ ከማዋለዱ በፊት በሠላም ለመውለድ እንዲረዳት እንደገረዛት ገልፀዋል። ይህ ገጠመኝ እንደሚያሳየው የሴት ልጅ ግርዛት ልጅ ለመውለድ አስፈላጊና ቁልፍ ጉዳይ አድርገው መቁጠራቸው ነው።

አንዳንዶች ድርጊቱ በዕምነታቸው የተደነገገ አድርገው ቢቆጥሩትም በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛትን የሚደግፍ ኃይማኖታዊ መሠረት የለም። በመሆኑም ምንም እንኳን አንዳንድ የሙስሊም ህብረተሰብ ክፍሎች የሴት ልጅ ግርዛት በኃይማኖቱ የታዘዘ ነው በሚል ዕምነት ቢፈፅሙትም ድርጊቱ የኃይማኖቱ አስተምሮት አለመሆኑ እንዲያውም በቅድመ-እስልምና የነበረ ልማድ እንደሆነ ይታወቃል። በአዲስ አበባ የጥናቱ አካባቢ ያሉ አንዳንድ የሙስሊም ማኅበረሠብ አባላት የሸሪአ ሕግን እንደ ዋቢ ያቀርባሉ። አንድ አሳዳጊ እንዳስረዱት "አንዲት ሴት ልጅ ሳትገረዝ መሄድ ሀራም (ኃጢያት) በመሆኑ ሰዎች አሁንም የሴት ልጅ ብልትን በትንሹ ይቆርጣሉ" ብለዋል።

የሴት ልጅ ግርዛት አነስ ባለ ደረጃ ቢሆንም በኦርቶዶክስ፣ ፕሮቴስታንትና ካቶሊክ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድም ይፈፀማል። በአማራ ክልል በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ለሴት ልጅ ግርዛት ከሚሠጡት ምክንያቶች አንዱ አንዳንድ ሴት ልጆች በተፈጥሮ ተገርዘው የሚወለዱ ("የማርያም ግርዝ") መሆናቸው ሲሆን (Pankhurst 1992: 135)፤ የሴት ልጅ ግርዛት ሔዋን ላደረሠችው ጥፋት የተጣለባት ክርስቲያናዊ ቅጣት እንደሆነ ለማስረዳት በኦሮሚያ አንድ አዛውንት የሚከተለውን አፈ-ታሪክ ተርከዋል።

> ሔዋን ከአዳም የቀኝ የጎድን አጥንት ተፈጠረች። ሠይጣን አዳም ሌላ ሚስት አገባ ብሎ ለሔዋን ዋሽቶ ነገራት። በዚህም ጊዜ በጣም ተበሳጨች። ለአዳም እንድታበላው ሠይጣን የመርዝ ፍሬ ሠጣት። እርሷ ግን ፍሬውን መጀመሪያ ቀመሠችው። ፍሬው ከጉሮሮዋ ወደ ሆዷ፣ ከዚያም ወደ ብልቷ ወረደ። አሁን የሚገረዘው ያ የመርዝ ፍሬ ያለበት ክፍል ነው። በዚህ የተነሳ ነው ሰዎች እንስሳትን ሲያርዱ ደሙ ሰውነቱ ውስጥ እንዳይቀር የሚጠነቀቁት። የወር አበባም ተመሳሳይ ነው። ሔዋን በሠራችው ጥፋት ደሟ እንዲፈስ ተፈረደባት። እድለኛ ለሆኑት ወደ ሽልነት ያድጋል። አዳምና ሔዋን በዚያን ቀን ከገነት ተባረሩ። በዚህ ኃጢያት የተነሳ ነው ሴት ልጆች የሚገረዙት። ነገር ግን መንግሥት ይህንን እንዳንናገር ይከለክላል። በመሆኑም የሴት ልጅ ግርዛት ምንም ጉዳት የለውም።

ይህ አፈ-ታሪክ የሴት ልጅ ግርዛትን ከወር አበባ እና እንስሳት ሲታረዱ ደሙ ወደ ውጭ እንዲፈስ ከሚደረገው ልማድ ጋር ለማያያዝ ይሞክራል። በዚህም ድርጊቱን ከደም እና ከሴት ልጅ ታዛዥነት ጋር በምሳሌ ሊያገናኝ ይጥራል። በደቡብ አንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ያልተገረዙ ሴቶች በቤተ-ክርስቲያን መካነ-መቃብር ውስጥ እንዳይቀበሩ ይታገዳሉ (Freeman and Pankhurst 2003) ።

በማጠቃለያ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዛት ሠበቦች በሴት ልጅ ታዛዥነት፣ ወሲባዊ ቁጥብነትና ልጅ የመውለድ አቅም ዙሪያ ያጠነጥናሉ። ነገር ግን የድርጊቶቹ አፈፃፀምና ደረጃ ያንግ ሳይቭስ ጥናት በሚያደርግባቸው የደቡብና የሠሜን የአገሪቱ ክፍሎች በእጅጉ ይለያያል። በሠሜን (በተለይ በአማራ) የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ባህላዊ ስፍራና ሚና የጎላ ሲሆን የሴት ልጅ ግርዛት ግን እምብዛም ትኩረት አይሠጠውም። በተቃራኒው በደቡብ ግርዛት ወደ ጋብቻ ለመሸጋገር አስፈላጊ፣ ቁልፍ እና ደማቅ ባህላዊ ክንውን ሲሆን ያለዕድሜ ጋብቻ ግን ብዙም አይተኮርበትም። ከዚህ በተጨማሪ በደቡብ የሴት ልጅ ግርዛት ከጋብቻ ወቅት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው።

## 4 የለውጥ ኃይሎች

የኢትዮጵያ መንግሥት የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ሴቶችንና ልጆችን የሚበድሉ ከፍተኛ ኂላ ቀር ባህላዊ ድርጊቶች ናቸው በማለት ጠንካራ አቋም ይዟል። ኢትዮጵያ በ1979 የተፈረመው "ሴቶችን የሚያገልሉ ሁሉን አይነት ድርጊቶችን አስወጋጅ ዓለም አቀፍ ስምምነት" (Convention on the Elimination of All Forms of Discrimination Against Women [CEDAW])፣ የ1989ኙ የተ.መ.ድ የህፃናት መብት ሕግ (Convention on the Rights of the Child)፣ የአፍሪካ የህፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር (the African Charter on the Rights and Welfare of the Child)፣ የ1998ቱ የአፍሪካ አንድነት የሴቶች ጥቃት ተቃውሞ መግለጫ (the Addis Ababa Declaration on Violence Against Women)፣ እና የ2008ቱ የተ.መ.ድ የሴት ልጅ ግርዛት ማስወገጃ ስምምነት (United Nations Interagency Statement on Elimination of FGM) ፈራሚ አገር ነች። ከዚህ በተጨማሪ በ2008 ዓ.ም. የተ.መ.ድ እና ዩኒሴፍ በጋራ ባዘጋጁት የ17 አገራት የፀረ-ሴት ልጅ ግርዛት "ኢኒሼቲቭ" አባል አገር ነች። እንዲሁም የአፍረካ ሕብረት በ2011 በአዲስ አበባ ባደረገው ስብሰባ የተ.መ.ድ በ66ኛ ጠቅላላ ጉባኤው የሴት ልጅ ግርዛት በመቃወም መግለጫ እንዲያወጣ ጠይቋል።

በአገር አቀፍ ደረጃም የ1995ቱ የፌደራል ህገ-መንግሥት አንቀጽ 35 ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሯቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጐች፣ ወጐችና ልማዶችን ይከለክላል። የ1997ቱ የፌዴራል የባህል ፖሊሲ ጉዳ ባህላዊ ድርጊቶችን ደረጃ በደረጃ የማስወገድ አስፈላጊነትን ይጠቅሳል። በ2005

የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በበኩሉ በዚህ ረገድ የተቀመጡ ቅጣቶችን ይዟል። የ2011 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በአምስት ዓመታት ውስጥ የሴት ልጅ ያለ ዕድሜ ጋብቻን በ2010/11 ከነበረበት 21.4% በ2014/15 ወደ 10.4% ለማውረድና፤ የሴት ልጅ ግርዛትን ደግሞ በ2010/11 ከነበረበት 37.7% በ2014/14 ወደ 0.7% በመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ዕቅድ አስቀምጧል።

ጉጂ ባህላዊ ድርጊቶችን በማስወገድ ረገድ በከተሞች ውስጥ መንግሥት፣ መገናኛ ብዙሀንና ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በሐዋሳ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ሕዝባዊ ንቅናቄው በመምራት ረገድ ጉልህ ሚና እንዳላቸው በዚህ ጥናት መረዳት ተችሏል። ነገር ግን ድርጊቶቹን ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት መጠንና ደረጃ ከክልል ክልል ይለያያል። የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻን ለማስቀረት የሚደረገው ጥረት በሠሜን ክልሎች (በተለይ በአማራ) ጠንካራ ሆኖ ሲታይ፤ የሴት ልጅ ግርዛትን በመዋጋት ረገድ ደግሞ ደቡባዊ ክልሎች (በተለይ በኦሮሚያ) የተሻሉ ሆነው ይገኛሉ።

ለዚህ ጥናት ያነጋገርናቸው የመንግሥት ኃላፊዎች ምንም እንኳ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዛት የሚፈፀሙባቸውን ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ "ምክንያቶች" ቢረዱም ድርጊቶቹን በፅኑ እንደሚቃወሙ መረዳት ተችሏል። ከዚህ በመነሳት በመስኩ የተደረጉት የአድቮካሲና ሕግ የማስከበር (law enforcement) ጥረቶች በየተዋረዱ ባሉት የስልጣን አካላት ላይ ተጨባጭ የአመለካከት ለውጥ ማምጣታቸውን መገንዘብ ይቻላል።

## 4.1 የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ

በ2000 ዓ.ም የወጣው የተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ አንቀጽ 7 ዝቅተኛው የጋብቻ የዕድሜ ገደብ 18 ዓመት መሆኑን ይደነግጋል። የፌዴራል የቤተሠብ ህጉ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በክልሎች በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፤ በ2008 ዓ.ም ከዘጠኙ ክልላዊ መንግስታት ስድስቱ የየራሳቸውን የቤተሠብ ሕግ አውጥተዋል። በተለይ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ በስፋት በሚታይበት የአማራ ክልል ዘመቻው በሠፊው ተካሂዷል። በመጨረሻም በ2004 ዓ.ም ዕድሜያቸው ያልደረሠ ልጆችን በሚድሩ ቤተሠቦች ላይ የብር 200 ቅጣት ሲደነገግ የዚህ አይነት ዝግጅት የሚያደርጉ ቤተሠቦችን የትምህርት ቤት ክበቦች ሪፖርት በማድረግ ያሳወቃሉ። በዚህም ያለዕድሜ ጋብቻ ከ1990ዎቹ ጀምሮ በአማራ የጥናቱ አካባቢ እየቀነሰ መምጣቱ ታውቋል።

መንግሥት የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻን ለማስወገድ በሚያካሂደው በአማራ ክልል ላይ ያተኮረ ከፍተኛ ዘመቻ መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶችና በለጋሾች የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ጉልህ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው። ጥናቱ በተካሄደባቸው

አካባቢዎች ድርጊቱ በእጅጉ እንደቀነሠ ኢ-አኃዛዊ መረጃዎች ያሳያሉ። ዛሬ ዛሬ ተጋቢዎች በፈቃዳቸው የሚተጫጩበት ሥርዓት እየተስፋፋና በቤተሠብ የሚወሠን ጋብቻ እየቀረ መጥቷል። የእርሻ መሬት ጥበትና የኑሮ ውድነት በአማራ ሰዎች ብዙ ልጅ ስለመውለድ ያላቸውን አስተሳሰብ እየቀየረው መጥቷል። የሠፊ ቤተሠብ ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ እየቀረ በመምጣቱ ሴት ልጆችን በለጋ ዕድሜያቸው ለመዳር ሠበብ የነበረው አንዱ ምክንያት ተወግዷል ሲል አንድ የቀበሌ ተመራጭ ገልጿል።

## 4.2 የሴት ልጅ ግርዛት

የ2005ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ልዩ ልዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መፈፀም እስርን ጨምሮ በተለያዩ የቅጣት ዓይነቶች እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል[3]። የሴት ልጅ ግርዛትን በመላ አገሪቱ ለማስቀረት በተለይ ድርጊቱ በከፍተኛ ደረጃ በሚፈጸምባቸው ክልሎች (በተለይ በምሥራቅና ደቡብ የአገሪቱ ክፍሎች በሚኖሩ ከፊል አርብቶ አደሮች) ላይ ትኩረት በማድረግ በመንግሥትና ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች የታገዘ ከፍተኛ ዘመቻ ተካሂዷል።

በ2002 ዓ.ም. የብሔራዊ የሴት ልጅ ግርዛት አስወጋጅ ኔትወርክ በኖርዌጂያን ቸርች ኤድ (Norwegian Church Aid) ድጋፍ ሠጭነትና በቀድሞው የብሔራዊ ልማዳዊ ድርጊቶች ኮሚቴ (አሁን የኢትዮጵያ ጎጂ ላማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ማኅበር (EGLDAM) ተብሎ በተሠየመው) አስተባባሪነት ተቋቋመ። ኔትወርኩ በኅዳር 2010 በኦፊሴል ሥራውን የጀመረ ሲሆን በታህሳስ 2011 በብሔራዊ ደረጃ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን ጨምሮ መንግስታዊ ድርጅቶች፣ የእምነት ተቋማት፣ የሲቪል ሶሳይቲ ድርጅቶች፣ የተ.መ.ድ መ/ቤቶች (በተለይ UNFPA, UNICEF and WHO) እንዲሁም የመገናኛ ብዙኃንን ያካተተ 46 አባላት ያሉት ፎረም አቋቁሟል። የክልል ደረጃ ኔትወርኮችም በደቡብ በጥር 2010፣ በሶማሌ ክልል በታህሳስ 2010 የተመሠረቱ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በትግራይ ክልል በ2012 በመመስረት ላይ ይገኛል። ፎረሙ መልካም ተሞክሮዎችን የሚያስተዋውቅበት በየአራት ወሩ የሚወጣ ጋዜጣ የሚያሳትም ሲሆን የልምድ መለዋወጫ ዓመታዊ ጉባኤም ያካሂዳል።

ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው የኃይማኖት ተቋማትና አገር-በቀልና ዓለም አቀፍ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች (በተለይም የኖርዌጅያን ቸርች ኤድ) ጠቃሚ እርምጃዎችን

---

[3] አንቀጽ 565 የሴት ልጅ ግርዛትን መፈፀም ከሶስት ወር ያላነሠ የእስር ቅጣት ወይም ከአምስት መቶ ብር ያላነሰ የገንዘብ መቀጮ ይደነግጋል። እንዲሁም የሴት ልጅ ብልትን መስፋት ከሶስት እስከ አምስት ዓመት የእስር ቅጣት ያስቀጣል። አንቀጽ 587 ደግሞ የጠለፋ ወንጀል ከሶስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ቅጣት ያስቀጣል ከማለቱ በላይ ተጠላፊዋ 13 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነች እስከ ሶስት ዓመት፤ ከ13 ዓመት በታች ከሆነች ደግሞ የ7 ዓመት እስራት ይደነግጋል።

በመውሰድ ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ኢቫንጀሊካን ቤተ-ክርስቲያን ፌሎሺፕ በጥር 26 ቀን 2010 ባወጣችው ባለ5 ነጥብ የአቋም መግለጫ የሴት ልጅ ግርዛት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮት ውጭ የሆነና ለሴት ልጅ ሰውነት ከተሠጠው ኃይማኖታዊ ክብር የሚቃረን የጭካኔ ተግባር ነው ስትል ከመኮነኗ በላይ የሴት ልጅን ሠብዓዊ መብት የሚፃረር፣ አካላዊ፣ መንፈሳዊና ስሜታዊ ጉዳትን የሚያስከትል ኢ-ፍትሀዊ ድርጊት ነው ስትል አውግዛለች። የሴት ልጅ ግርዛት ወላጆች ለልጆቻቸው ሊሠጡት ከሚገባው ፍቅርና እንክብካቤ በተቃራኒ የሚፈጸም፤ የሴት ልጅን ጾታዊ ስሜት የሚያኮስስ፣ ጋብቻን የሚያሰናክልና በወሊድና ድህረ-ወሊድ ወቅቶች ለከፍተኛ ህመምና ስቃይ የሚዳርግ ድርጊት ነውም ብላለች (ECFE, 2010)። የአቋም መግለጫው በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ምንም ድርድር ሊኖር እንደማይገባም አስምሮበታል። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያንም በኦክቶበር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሴት ልጅ ግርዛትንና ጾታዊ ፀብን በተመለከተ ባወጣችው ተመሣሣይ የአቋም መግለጫ የሴት ልጅ ግርዛት ፈጣሪ ሙሉ አድርጎ የፈጠረውን የሴት ልጅ ሰውነት የሚያጎድል፣ የሴት ልጅን ሠብዓዊና ህገ-መንግስታዊ መብቶች የሚጥስ የተሣሣተ ድርጊት ነው ስትል ኮንናለች። መግለጫው የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ የኃይማኖት አባቶችና ወንዶች ጠንካራ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግና የቤተ-ክርስቲያኒቷና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ትብብርን እንደሚጠይቅ ይጠቅሳል። መግለጫውን ተከትሎ “Theological Reflection on Female Genital Mutilation” በሚል ርዕስ መቅድሙ በፓትሪያርኩ የተፃፈ መጽሐፍ ታትሞ ወጥቷል (EOC, 2010 NCAA 2011)።

በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች እንቅስቃሴዎች የነበሩ ሲሆን በተለይ የአፍሪካ የሴቶችና ህጻናት ጤንነትን የሚያውኩ ልማዳዊ ድርጊቶች ኮሚቴ (Inter-African Committee on Traditional Practices Affecting the Health of Women and Children) ጥር 6 2003 ባዘጋጀውና በኋላም መግለጫውን የተባበሩት መንግታት የሠብዓዊ መብት ኮሚሽን ባፀደቀው ጉባኤ ላይ የናይጀሪያዋ ቀዳማዊ ዕመቤት ስቴላ ኦባሳንጆ “*ድርድር አልባው የሴት ልጅ ግርዛት*” (“zero tolerance to FGM”) በሚል ባቀረቡት መግለጫ ላይ ተንተርሶ ዕለቱ የዓለም አቀፍ የሴት ልጅ ግርዛት የግንዛቤ ቀን ሆኖ እንዲከበር የፀረ-የሴት ልጅ ግርዛት ኔትወርክ (FGM Network) ጥረት በማድረግ ላይ ነው።

መንግሥት ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች (በተለይም ከተ.መ.ድ የህፃናት ድርጅት) እና ሌሎች ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር “zero tolerance” አካባቢዎችን ለመከለል ጥረቶች አድርጓል። ይህም በአፋር፣ በደቡብና በአዲስ አበባ ክልሎች የተደረገ ሲሆን፤ በመጀመሪያ በአፋር ክልል በ2007 አንድ ወረዳ፣ በ2010 ሁለት ወረዳዎች እንዲሁም በ2012 ተጨማሪ ሁለት ወረዳዎችን በ“zero tolerance” ክልልነት እንዲታቀፉ ተደርጓል። በቅርቡ ይህ መግለጫ በአፋር፣ በቤኒሻንጉል

ጉሙዝ፣ በደቡብና በአዲስ አበባ ክልሎች ያሳየውን ውጤት በተመለከተ የተካሄደ ጥናት ከአዲስ አበባ በስተቀር በሁሉም ክልሎች የሴቶች ግርዛት አሁንም በከፍተኛ ደረጃ ያለ መሆኑን ( ከ80-100%) ሲያሳይ ድርጊቱ በለጋ ወጣት ሴቶች ዘንድ ግን አነስተኛ (ከ64-28%) መሆኑን አመልክቷል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የሴት ልጅ ግርዛት በተለያዩ ምክንያቶች እየቀነሠ የመጣ ቢሆንም የመግለጫውን ሙሉ ውጤት ለመናገር ግን ጊዜው ገና መሆኑን መረዳት ያሻል። በአዲስ አበባ ባሉ ሁለት የጥናቱ አካባቢዎች የግርዘት መጠን በዐዋቂ ሴቶች ዘንድ ከ30-38% ሲሆን በለጋ ወጣት ሴቶች ዘንድ ግን ከ5% በታች ሆኖ ተገኝቷል። ነገር ግን በአዲስ አበባ ያሉ ብዛት ያላቸው ሴቶች እንዲሁም በሌሎቹ ሁሉም የጥናቱ አካባቢዎች ያሉ ለጋ ወጣት ሴት ልጆች (በተለይም በአዲስ አበባ) ስለመገረዝ አለመገረዛቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ "አላውቅም" የሚል ምላሽ የሠጡ መሆናቸው መዘንጋት የለብንም። ይህም ጥያቄውን በቀጥታ ላለመመለስ ሲሉ የሠጡት ምላሽ ይሆናል የሚል ግምት አሳድሯል። ወደፊት ሴት ልጆቻውን ያስገርዙ እንደሆን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሁሉም የጥናቱ አካባቢዎች ያሉ አብዛኛዎቹ መላሾች "አላስገርዝም" የሚል ምላሽ ቢሠጡም፤ በአፋር በአንድ የጥናት አካባቢ እንዲሁም በደቡብ ሌላ የጥናት አካባቢ ከ30% በላይ መላሾች እንደሚያስገርዙ መግለፃቸው አሁንም የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት የሚደረገው ጥረት አያሌ ተግዳሮቶች እንዳሉበትና ለለውጥ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ አለመሆኑን ያመላክታል።

ከያንግ ላይቭስ የጥናት አካባቢዎች መካከል በሀዋሳና በኦሮሚያ መንግሥትና ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት በሠፊው ይንቀሳቀሳሉ። በትግራይ ቀደም ሲል በትጥቅ ትግሉ ወቅት በትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር (ህወሀት) በኩል ስነ-ጾታን በተመለከተ የተሠራው ሥራ ውጤት በማሳየቱ ሴት ልጅን የመግረዝ ልማድን በእጅጉ ቀንሶታል። በዚህ ረገድ ምንም እንኳን የተለያዩ የህብረተሠብ አካላት ለተለያዩ የፖሊሲው ክፍሎች በሚሰጡት ምላሽ ቢለያዩም (ለምሳሌ በአዲስ አበባ ያሉ ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት በወሊድ ወቅት ችግር ስለሚያስከትልና እንዲሁም የወሲብ ፍላጎትን ስለሚቀንስ መንግሥት ጎጂ ልማድ አድርጎ እንደመደበው ይረዳሉ)፤ በአጠቃላይ የመንግሥት ፖሊሲ በጉዳዩ ላይ በ5ቱም ክልሎች ለውጥ ለማምጣት ማስቻሉን መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል በአማራ ክልል ያለች አንዲት ሴት የመንግሥትን አቋም የሕዝብ ቁጥርን ለመቀነስ ከሚያደርገው ጥረት ጋር አያይዛዋለች። በእርሷ አመለካከት የተገረዙ ሴቶች በልጅነታቸው ስለሚወልዱ ብዙ ልጅ ይኖራቸዋል። በመሆኑም መንግሥት ግርዘትን የሚከለክለው የሕዝብ ቁጥር ለመቀነስ ነው ብላ ታምናለች።

የሴት ልጅ ግርዛትን የማስወገድ ፍላጎትና ግፊት (pressure) በአንዳንድ አካባቢዎች በሠፊው ይስተዋላል። ለምሳሌ በሆሳዕና አንዲት የቀበሌ የሴቶች ማኅበር መሪ

መንግሥት ድርጊቱን ለማስቆም ፖሊሲውን በመገናኛ ብዙሀን፣ ኤፍ. ኤም ራዲዮና በሴሚናሮች ማስተዋወቅና ማስፋፋት እንዳለበት ገልጻለች። በሆሳዕና በዐዋቂዎችም ሆነ በልጆች ዘንድ የሴት ልጅ ግርዛትን ተቃውሞ በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል። ይህም የሆነው ህጉ በሚገባ በተግባር ላይ በመዋሉ እንደሆነ አንዲት የአካባቢ ዕድር መሪ ትገልጻለች። በመቀጠልም "ድርጊቱ አሁንም በአካባቢው የሚፈፀም ቢሆንም በመቀነስ ላይ ይገኛል። ህጉን ተላልፈው ድርጊቱን በሚፈጽሙት ላይ የእስራት ወይም የገንዘብ መቀጮ ይጣልባቸዋል። በት/ቤቶችም ስለ ኤች.አይ.ቪና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ትምህርት ያገኛሉ" ብላለች። በቡድን ውይይት ላይ የተካፈሉ በአዋሳ ከተማ ያሉ ወላጆችም ሜሪ ጆይ የተባለ አገር-በቀል ግብረ-ሠናይ ድርጅት በ"ቡና ጠጡ!" ፕሮግራሙ ጎጂ ልማዱን ለማስቀረት የሚሰጠው ትምህርት ያመጣውን አዎንታዊ ተጽዕኖ አስረግጠው ገልጸዋል። ይህ ፕሮግራም ህብረተሠቡ ስለሴት ልጅ ግርዛትና ያለዕድሜ ጋብቻ ያለውን አስተሳሰብ እንዲያሳድግ ረድቶታልም ተብሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ የአካባቢው የመንግሥት አካላት አያሌ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ለሴቶች ማኅበራት፣ ለወጣቶች፣ ለት/ቤት ክበባት በመስጠት ስለሴት ልጅ ግርዛት አስከፊነት ብቻ ሳይሆን ስለቤተሠብ ምጣኔ አስፈላጊነት፣ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ተጓዳኝ ጉዳዮች በማስተማር ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ።

በአንዳንድ አካባቢዎች ልጆች የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትለውን አካላዊ ጉዳት ጠንቅቀው መረዳታቸውን ለማወቅ ተችሏል። ይህም ምናልባት በየአካባቢዎቹ በተሠራው ሠፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሳቢያ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አሳድሯል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ በተካሄደ የቡድን ውይይት ላይ የተሳተፉ ሴት ልጆች አለመገረዝ ከባህሪ ጋር በምንም አይነት ሁኔታ እንደማይያያዝ፤ እንዲሁም የሴት ልጅ ግርዛት ጉዳትን በተለይም የመግረዣ ቁሳቁሶች ንፅህና በሚገባ ባለመጠበቁ የሚደርሰውን የጤና ችግር በሚገባ እንደሚረዱ ለመገንዘብ ተችሏል።

## 5 የለውጥ አዝማሚያዎች (Trends)

የሴት ልጅ ግርዛትንና ካለዕድሜ ጋብቻን በተመለከተ በጊዜ ሂደት ውስጥ የተፈጠረውን ለውጥ ለመመልከት ሁለት መሠረታዊ የመረጃ ምንጮችን ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ብሔራዊ ጎጂ ልማዶች አስወጋጅ ኮሚቴ (NCTPE) በ1997 ያካሄደው የዳሠሣ ጥናት (survey)፤ እንዲሁም ይኸው ኮሚቴ በኋላ ስሙ ወደ የኢትዮጵያ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ማኅበር (ኢገልድአማ) ከተቀየረ በኋላ በ2007 ያካሄደው ሁለተኛ ዙር ሠርቬይ ነው። ሁለተኛው የመረጃ ምንጭ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በተመረጡ የናሙና አካባቢዎች በ2000፣ 2005 እና 2011 ያካሄዳቸው የኢትዮጵያ የስነ-ሕዝብና ጤና ሰርቬይ (Ethiopian Demographic and

Heath Survey) እንዲሁም በ2011 የተካሄደው የሴት ልጅ ግርዘትን የሚዳስሰው የደህንነት ግምገማ ሰርቬይ (Welfare Monitoring Survey) ነው።

ሁሉም መረጃዎች ሲነፃፀሩ ሁለቱም አይነት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች (ካለዕድሜ ጋብቻም ሆነ የሴት ልጅ ግርዛት) በአጠቃላይ የመቀነስ አዝማሚያ ያሳዩ ሲሆን፤ ለውጡ በከተሞች በከፍተኛ ደረጃ ተስተውሏል። ነገር ግን ይህ ለውጥ በክልሎች መካከል የመበላለጥ ሁኔታ ይስተዋልበታል። ሁለቱን ጎጂ ድርጊቶች እርስ በርሳቸው በቀጥታ ማወዳደር አስቸጋሪ ቢሆንም የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ በለጋነታቸው የሚያገቡ ሴት ልጆች ብዛትን በማየትና ትዳር የሚመሠርቱ ሴት ልጆች ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት ያላቸውን አማካይ ዕድሜ በመመልከት ለውጡን መረዳት ይቻላል። እንዲሁም የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ የተገረዙና ያልተገረዙ ዐዋቂና ልጅ-አግር ሴት ልጆችን ቁጥር በማወዳደር ለማወቅ ተችሏል። በዚህ መሠረት የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የሴት ልጅ ግርዛትን በማስወገድ ረገድ የተገኘው ውጤት ካለዕድሜ ጋብቻን ለማስቀረት በተደረገው ጥረት ከተገኘው ውጤት እጅግ ልቆ ተገኝቷል።

የአሁኑ ህፃናት ትውልድ ከቀድሞው ህፃናት ትውልድ ጋር ሲነፃፀሩ ካለዕድሜ ጋብቻም ሆነ የሴት ልጅ ግርዛት መቀነሳቸውን አሀዛዊ መረጃዎች ያሳያሉ። ነገር ግን በኋላ እንደምንመለከተው ድርጊቶቹን በተመለከተ አሁንም ተቃርኖዎች መኖራቸውን፤ በዘመናዊና ባህላዊ ድርጊቶችና ልማዶች መካከል ፉክክርና ፍትጊያ መኖሩን፤ የድርጊቶቹ መጠንና ስፋት በክልል፣ በኃይማኖትና በብሔረሠብ እንደሚለያይ፤ እንዲሁም ስልጣን ባላቸው የመንግሥት ሹማምንት፣ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ እና የአካባቢና የአገር ሽማግሌዎችና መሪዎች እንዲሁም በወላጆችና ልጆች መካከል የአመለካከት ልዩነቶች አሁንም እንዳሉ መረዳት ተችሏል።


ለጥናቱ የተጠየቁ መላሾች በጎ ለውጥ እንዲመጣ ያስቻሉ ያሏቸውን የተለያዩ ምክንያቶችም ዘርዝረዋል። ምላሾቹ በአብዛኛው የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በተሠሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች፣ ለጤና ችግር የመጋለጥ ስጋትን (በተለይ ግርዘትን በተመለከተ)፣ እና ልጆችንና ልጅነትን በተመለከተ የተፈጠሩ የአመለካከትና አስተሳሰብ ለውጦች ላይ ያተኩራሉ። ይህን በሚመለከት የደረስንበት ድምዳሜ ምንም እንኳን የመንግሥት እንቅስቃሴና ዕርምጃዎች በጎ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋፅዖ ማበርከታቸው ባይካድም ከ"ዘመናዊነት" ጋር የተያያዘው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሻሻል (በተለይ የትምህርት ዕድል መስፋፋትና የሴት ልጆች የመሥራት ዕድል መፈጠር) ለተገኘው ውጤት ከፍተኛ ድርሻ ማበርከቱ ሊሠመርበት ይገባል።

## 5.1 የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ዓመት

የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ላይ የታየውን ለውጥ ለመረዳት የሚያስችሉ ሁለት የስታቲስቲክስ ሰርቬይ የመረጃ ምንጮች መመልከት ይቻላል:: የመጀመሪያው 1997 እና 2007 የተካሄዱት የNCTPE/EGLDAM ሰርቬዮች ሲሆኑ ሁለተኛው በሶስት ዙሮች የተካሄደው (2000፣ 2005 እና 2011) የኢትዮጵያ ስነ-ሕዝብና ጤና ሰርቬይ ነው::

የNCTPE/EGLDAM መረጃ በ1997 እና በ2007 ዓ.ም. ከ15 ዓመት በታች ያገቡ ሴት ልጆችን አንፃራዊ ቁጥር የሚሰጥ ሲሆን በዚህም ከተጠቀሰው ዓመት በታች በማግባት ረገድ ድርጊቱ ከአንድ ሶስተኛ ወደ አንድ አምስተኛ ዝቅ ብሎ ተገኝቷል:: ይህ ለውጥ ግን ከክልል ክልል ልዩነት እንዳለውም መረዳት ተችሏል::

**ምስል6፡** ከ1997 እስከ 2007 ድረስ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ክልላዊ





(ምንጭ፡- NCTPE፣ 1997፣ EGLDAM 2008a እና 2008b)

በዚህ መሠረት የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ በሠሜን ክልሎች ከፍተኛ የነበረ ሲሆን በአማራ 68% በትግራይ ደግሞ 53% ነበር:: በተመሣሣይ ሁኔታ በአዲስ አበባና በበኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 50% ገደማ ነበር:: የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ በሶማሌ ክልል 4% ብቻ የነበረ ሲሆን በተመሣሣይ በደቡብ፣ በጋምቤላ ሕዝቦች፣ በሐረሪ እና በኦሮሚያ ክልሎችም ዝቅተኛ እንደነበር መረጃው ያሳያል:: የሴት ልጅ ያለዕድሜ

ጋብቻን በመቀነስ ረገድ በ10 ዓመታት ውስጥ የታየው ለውጥ ከክልል ክልል ይለያያል:: በትግራይና በአዲስ አበባ ከፍተኛ ለውጥ (19% ነጥብ) የተመዘገበ ሲሆን በበኒሻንጉልና በአማራም የ18% እና የ17% ነጥብ ለውጥ ታይቷል:: በአጠቃላይ አገራዊው ለውጥ በመቶኛ ሲታይ ድርጊቱ በአንድ ሶስተኛ ዝቅ ሲል በክልሎች መካከል ባለው ንፅፅር የደቡብ ክልል የ47.1% ለውጥ በማሳየት ቀዳሚ ሲሆን አዲስ አበባ በ36.5%፣ ትግራይ በ35.6% በሁለተኛነትና በሶስተኛነት ይከተላሉ:: ነገር ግን በአማራ (27.5%) እና በኦሮሚያ (26.9%) የተመዘገበው ለውጥ ከአገራዊው አማካይ ለውጥ በታች ሲሆን በሶማሌ ክልል ደግሞ አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል (EGLDAM 2008ለ ሠንጠረዥ 3.6.2)::

**ምስል 7፡** <u>የሴት ልጅ ጋብቻ መጠን ከ2000-2011 በክልልና[4] በከተማ-ገጠር ንጽጽር</u>




(ምንጭ፡ CSAE 2001; CSAE 2006; CSAE 2012a)

የEDHS መረጃ ከ2000 እስከ 2005 ባሉት ዓመታት የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ የተወሠነ መሻሻል ማሳየቱን ያመለክታል:: በዚህም የሴት ልጅ የጋብቻ መያዣ አማካይ ዕድሜ በ2000 ዓ.ም. ከነበረበት 16.4 ዓመት በ2011 ዓ.ም. ወደ 17.1 ዓመት አድጓል:: ለውጡ ከ2005 እስከ 2011 ባሉት ዓመታት ፈጣን እንደነበረ ያመለክታል:: ምስል 7 አማካይ የጋብቻ መያዣ ዕድሜ ከገጠር ይልቅ በከተማ ከፍ ያለ እንደሆነም ያሳያል:: የጋብቻ መያዣ ዕድሜ መሻሻል በከተሞች ከ2000 እስከ

[4]ያንግ ላይቭስ የሚሠራባቸው ክልሎች ብቻ ናቸው የተነጻጸሩት::

2005 ባሉት የመጀመሪያ አምስት ዓመታት በጉልህ የታየ ሲሆን፣ በገጠር ግን በ2005 እስከ 2011 ባለው ሁለተኛ አምስት ዓመታት ውስጥ ተስተውሏል። ይህም ለውጡ በገጠር ከቅርብ ጊዜ ወዲስ እየተስፋፋ መምጣቱን ያመለክታል። በክልሎች ደረጃ ስንመለከት ደግሞ በ2000 ዓ.ም. አማካይ የጋብቻ ዕድሜ ከአገራዊው አማካይ የጋብቻ ዕድሜ በታች በነበረባቸው በሠሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች (በተለይ በአማራና ትግራይ ክልሎች) እና የደቡብና ኦሮሚያ ክልሎች መካከል ልዩነቶች ተስተውለዋል[5]። በከተሞች አካባቢ ለውጡ 15% ነጥብ በማስመዝገብ ፈጣን ሲሆን በአንፃሩ የገጠሩ 0.4% ነጥብ ብቻ ሆኖ ተገኝቷል። ከፍተኛ ለውጥ የተመዘገበው በትግራይ ክልል ሲሆን (1.4% ነጥብ) ይህም ከአገራዊው አማካይ ለውጥ እጥፍ ሆኖ ተገኝቷል። በአማራ 0.6% ነጥብ፣ ኦሮሚያ 0.5% ነጥብ ሆነዋል። ዝቅተኛው ለውጥ የተመዘገበው በደቡብ ክልል ሲሆን ከ2000 እስከ 2005 ባሉት ዓመታት ውስጥ ዝቅ ማለት የተስተዋለ ሲሆን ከ2001 እስከ 2011 ባሉት ዓመታት የተመዘገበው ለውጥ 0.1% ነጥብ ብቻ ሆኗል። የተለያዩ የዕድሜ ክልሎችን (20-49 እና 25-49) ስናወዳድር በ2000 ዓ.ም. እና በ2005 ዓ.ም. መካከል ምንም እንኳን ጥልቅ ንፅፅር ለማድረግ የሚያስችል ከ15-19 እና ከ20-24 ዓመት የዕድሜ ክልሎች አማካይ ዕድሜ መረጃ ባይሠጥም በአጠቃላይ ሲታይ ለውጡ በአነስተኛ የዕድሜ ክልል ባሉት ላይ የበለጠ እንደሆነ ይታያል።

የያንግ ላይቭስ ኢ-አኃዛዊ መረጃዎች (qualitative data) የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ መጠን በአገሪቱ መቀነሱን ያሳያሉ። ነገር ግን በድርጅቱ ጥናት ናሙና ውስጥ ካሉት ንዑስ ክፍሎች መካከል ከ25 ሴቶች (የ16 ዓመት ሴቶችና ልጃገረዶች) መካከል ሁለቱ ትዳር የያዙ ሆነው ተገኝተዋል። በኦሮሚያም ቀጥሎ እንደተመለከተው ምንም እንኳን ከልጁ (ከባሏ) ጋር ቀደም ብሎ የሚተዋወቁና አብረው ይወጡ የነበረ ቢሆንም ጋብቻው በመጨረሻ በጠለፋ የተፈጸመ ነው።

**ጉዳይ 1 (Case 1)፦ <u>በኦሮሚያ በ “ጠለፋ” ተፈጸመ የተባለ ጋብቻ</u>**

በመጀመሪያ ሽማግሌ ወደወላጆቼ በመላክ እኔን ለማግባት ጠየቀ። ወላጆቼ ጥያቄውን ለመቀበል ፈቃደኛ ቢሆኑም እኔ ግን ትምህርቴን እማራለሁ ብዬ እንቢ አልኩኝ። እርሱም ጓደኛውን በመላክ እንዳገባው ጠየቀኝ። እኔ አሁንም እምቢ አልኩኝ።.... አንድ ቀን ወደ ከተማ አብረን እንድንወጣ ጋብዞኝ ሻይ ስንጠጣ ስለጋብቻ አነሳብኝ። ከሁለት ወር በኋላ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ወደ ገበያ ስሄድ ጠልፈው ወደዚህ ከተማ አመጡኝ። ወላጆቼ ምንም አላሉም። እኔም ሌላ የምነግረው ሰው የለኝም። .... ከወላጆቼ ጋር ዕርቅ ለማውረድ ረጅም ጊዜ ወስዶብናል። በቅርቡ ባለቤቴ ለወላጆቼ 2,200 ብር በካሳ ከፍሏል።

[5]ንፅፅሩ የተካሄደው ያንግ ላይቭስ በሚሠራባቸው ክልሎች መካከል ብቻ ነው።

ከዚያም ከሁለት ወር በኋላ [በመጋቢት 2001] ጠጅ፣ ብርድ ልብስና ገንዘብ ይዘን ወደ ወላጆቼ ቤት ሄደን ዕርቅ አደረግን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወላጆቼን እንደበፊቱ እጠይቃለሁ። በዚህም ደስተኛ ነኝ። ነገር ግን እኔ ልጅ እስክወልድ ድረስ በባለቤቴ ጎሣ ባህል መሠረት ወላጆቼ እኛ ቤት መምጣት አይችሉም ። ከውጭ ነው የማገኛቸው። ወንድሞቼና እህቶቼ ግን ቤቴ መግባት ይችላሉ። ባለቤቴ ገና ጥሎሽ ስላልከፈለ ጋብቻችን ገና በባህሉ መሠረት አልፀናም። ጥሎሹ አምስት የቀንድ ከብት ሲሆን ይህንን ገንዘብ አጠራቅመን በመክፈል ጋብቻችንን ማጽናት ይጠበቅብናል።

በኦሮሚያ ክልል በ15 ዓመቷ ያገባች ልጅ

ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌ በጠለፋ የተፈፀመውን ጋብቻ ህጋዊ ለማድረግና ከልጅቷ ቤተሠብ ጋር ዕርቅ ለመፍጠር ካሣ መከፈል ያለበት መሆኑንና በተጨማሪም ጥሎሽ ተከትሎ የሚከፈል መሆኑን ያሳያል።

በትግራይ ክልል በልጅቷ ፈቃደኝነትና በወላጆች ስምምነት የተፈጸመ ጋብቻ ቀጥሎ ይመለከታል።

**ጉዳይ 2፡ በትግራይ በወላጆቿ በታቀደ ጋብቻ በፈቃደኝነት ያገባች ወጣት**

ባለፈው ጥር [2001] ነበር ትዳር የመሠረትኩት። ከባለቤቴ ጋር ጎረቤታሞች ነበርን። ማንም ሳያስገድደኝ በፈቃዴ ነው ያገባሁት....። በቤተሠቦቼ (በእናቴ) ፈቃድ የተፈጸመ በመሆኑ በጋብቻዬ ደስተኛ ነኝ። ከነበረብኝ ከፍተኛ የጉልበት ሥራም ገላግሎኛል። ቀደም ሲል እንዲህ በልጅነቴ አገባለሁ የሚል ኃሳብ አልነበረኝም። ነገር ግን ትምህርቴን አቋርጬ በከባድ ሥራ ስጠመድ ትዳር ይገፔ መገላገል ፈለግኩ.....። ለሠርጌ ጎረቤቶቻችን 600 ብር በስጦታ ሲሰጡ እናቴም ለድግሱ ተጨማ ወጪ አውጥታለች። የባለቤቴ ቤተሠቦች የተሻለ አቅም ስላላቸው ለሠርጉ የበለጠ ወጪ አውጥተዋል። በባህላችን ገዝሚ የተለመደ ቢሆንም ያለው ብቻ ነው የሚሠጠው። እናቴም የሠርጌ ዕለት 1,300 ብር ገዝሚ ሠጥታለች። ገንዘቡን ከተማ ከምትሠራው ታላቅ እህቴ ነው ያገኘችው። እናቴ ገዝሚ በገንዘብ የከፈለችው ልትሠጥ የምትችለው የቁም ከብት ስለሌላት ነው።

(በትግራይ ክልል በ16 ዓመቷ ያገባች ልጅ)


ከላይ የተጠቀሰው ታሪክ ጋብቻው በስምምነት የተፈጸመ፣ የልጅቷ ፈቃደኝነት የነበረበት፣ ገዝሚውን እናትየው ከትልቅ ልጅዋ አምጥታ እንደከፈለችና የሠርጉ ወጪም በአግቢው ቤተሠብና በተጋባዥ እንግዶች እንደተሸፈነ ያሳያል።

## 5.2 የሴት ልጅ ግርዛት

ሶስት የተጠናቀሩ መረጃዎች ማለትም የ1997ቱ የNTCPE ሰርቬይ እና ተከታዩ የEGLDAM ሠርቬይ፣ የEDHS 2000 እና 2005 ሰርቬዮችና እና 20011ዱ “Welfare Monitoring Survey (WMS)” የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊት መሻሻሉን ይጠቁማሉ:: የEGLDAM ሰርቬይ ሁሉንም ሴቶች የሚመለከት መረጃ የሚሠጥ ሲሆን የEDHS ግን ከ15-49 ዓመት ክልል ያሉ ሴቶችን ቢያንስ አንድ የተገረዘች ልጅ ያለቻቸው እንደሆነ በመጠየቅ የተጠናቀረ መረጃ ይሠጣል:: የWMS መረጃ በበኩሉ ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሴት ልጆችን በመጠየቅ የሠበሠበ መረጃ ነው::

የNTCPE/EGLDAM መረጃ የሴት ልጅ ግርዛት በአጠቃላይ ሲታይ በ1997 ከነበረበት የ61% በ2007 ወደ 46% እንደወረደ ያመለክታል:: ይህ ለውጥ ግን በክልሎች መካከል ልዩነት ይታይበታል::

**ምስል 8፡** <u>የሴት ልጅ ግርዛት ለውጥ በክልል (ከ1997-2007)</u>




+

(ምንጭ፡NCTPE 1998, EGLDAM 2008a)

በክልሎች መካከል ንጽጽር ስናደርግ ከፍተኛው ለውጥ የተመዘገበው በትግራይ ሲሆን (27% ነጥብ) ይህም የሴት ልጅ ግርዛት ቀደም ሲል ከነበረበት በግማሽ ያህል መቀነሱን ያሳይል:: አማራና አዲስ አበባ በ18% ነጥብ በሁለተኛነት ተመዝግበዋል:: ምንም ለውጥ ያልታየበት ክልል ደግሞ ሶማሌ ሆኖ ተገኝቷል::

የEDHS መረጃ በበኩሉ በከተማና ገጠር ልዩነት በሌለበት ሁኔታ በ2000 ዓ.ም. የሴት ልጅ ግርዛት 80% እንደነበር ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ይህ አሀዝ በ2005 ዓ.ም. በአጠቃላይ ወደ 2/3ኛ ዝቅ ሲል በከተሞች ደግሞ (ምስል 9 እንደሚያሳየው) ወደ 1/3ኛ አሽቆልቁሏል፡፡

**ምስል 9፡** <u>የሴት ልጅ ግርዛት ለውጥ በክልል፣ ከተማና ገጠር (2000-2005)</u>




(ምንጭ፡CSAE 2001, CSAE 2006)


የ2000 ዓ.ም. መረጃ እንደሚያመለክተው የሴት ልጅ ግርዛት በስፋት የሚተገበርባቸው ሁለቱ አርብቶ-አደር ምሥራቃዊ ክልሎች (አፋርና ሶማሌ) ሲሆኑ፤ ድርጊቱ በአነስተኛነት የሚታይበት ደግሞ ሲሶ ያህሉ ሴቶች ብቻ ግርዘት ተፈጽሞባቸው የነበረው የትግራይ ክልል ነበር፡፡ ያንግ ላይቭስ የሚሰራባቸውን የጥናት አካባቢዎችን ለይተን ስንመለከት ኦሮሚያ ከፍተኛውን ስፍራ ሲይዝ (90%)፣ አማራና አዲስ አበባ በሁለተኛነት ይከተላሉ (እያንዳንዳቸው 80%)፡፡ ደቡብ በ37% በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ለውጡን በክልሎች መካከል ስናነፃጽር ከ2000 -2005 ዓ.ም. ባሉት አምስት ዓመታት ከፍተኛ ለውጥ የተመዘገበው በአዲስ አበባ ሲሆን (14% ነጥብ)፤ አማራ (11% ነጥብ) እና ትግራይ (6% ነጥብ) በሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ኦሮሚያና ደቡብ እያንዳንዳቸው 2% ነጥብ በማስመዝገብ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ

ተቀምጠዋል፡፡ የ2005ቱ የEDHS መረጃ ትምህርት የሴት ልጅን ግርዛት በማስቀረት ድርሻ እንዳለው ያመለክታል፡፡ በዚህም ምንም መደበኛ ትምህርት በሌላቸው መካከል የግርዘት መጠን 77% ሲሆን ሁለተኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ባሉት መካከል ግን የግርዘት መጠን 64% መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የተሻለ ኑሮ ደረጃና የሀብት መጠን በሴት ልጅ ግርዘት ላይ ለውጥ እንዳላሳየ መረጃው ይጠቁማል

ነገር ግን እናቶች ቢያንስ አንዲት የተገረዘች ልጅ እንዳላቸውና እንደሌላቸው የሚጠይቁት በ2000 እና በ2005 የተካሄዱት የEDHS ሰርቬይና ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሴት ልጆችን መገረዝና አለመገረዛቸውን የሚጠይቀው የ2011ዱ Welfare Monitoring Survey የሴት ልጅ ግርዛት ላይ መሻሻል መመዝገቡን የበለጠ አሳማኝ መረጃዎች ይሠጣሉ፡፡ ምንም እንኳን ጥያቄዎቹ የተለያዩ ቢሆኑም ከ2005 እስከ 2011 ላሉት ዓመታት የሴት ልጅ ግርዛትን በተመከተ የለውጥ ማስረጃዎች ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

የEDHS መረጃ እንደሚያሳየው በ2000 ዓ.ም. ቢያንስ አንዲት የተገረዘች ልጅ ያላቸው እናቶች መጠን ከግማሽ ከፍ ያለ የነበረ ሲሆን ይህ መጠን ከተጠያቂዎቹ እናቶች መካከል ከተገረዙት በጣም ያነሠ ሆኖ ተገኝቷል (ከተጠያቂዎቹ እናቶች መካከል ሶስት አራተኛዎቹ የተገረዙ ናቸው)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2000-2005 ቢያንስ አንዲት የተገረዘች ልጅ ያላቸው እናቶች መጠን ከ52% ወደ 38% ወርዷል፡፡ ይህ አሀዝ በከተማ ይበልጥ በመቀነስ 30% ድረስ የወረደ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ምስል 10፡** ከ15 ዓመት በታች ባሉ ልጆች የሴት ልጅ ግርዘት ለውጥ በከተማና በገጠር 2000-2011




(ምንጭ፡ CSAE 2006; CSAE 2012a; WMS 2011)

ምስል 10 እንደሚያመለክተው የተመዘገበው ለውጥ ከክልል ክልል ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሲሆን ከፍተኛው የለውጥ መጠን (rate) የተመዘገበው በአፋር ክልል (97%) ሲሆን አማራ (78%) በሁለተኛነት ተመዝግቧል። ዝቅተኛው ደግሞ ደቡብ (37%)፣ ትግራይና (39%) እና አዲስ አበባ (40%) ሆነዋል። ከፍተኛው ለውጥ የተመዘገበው በጋምቤላ ሕዝቦች ክልል (32% ነጥብ) ሲሆን ሶማሌ (30% ነጥብ) እና አማራ (22% ነጥብ) ይከተላሉ። አነስተኛው ለውጥ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል የተመዘገበ ሲሆን (8% ነጥብ) ትግራይ (9% ነጥብ) በሁለተኛነት ይከተላል። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰው ውጤት ቢመዘገብም *ያንግ ላይቭስ* ከሚሠራባቸው ክልልች መካከል የአማራ ክልል በሴት ልጅ ግርዛት በ57% በማስመዝገብ ከፍተኛውን ደረጃ ሲይዝ፤ ኦሮሚያና (35%) እና ትግራይ (30%) በሁለተኛነትና ሶስተኛነት ተቀምጠዋል። ይህ አሀዝ በአዲስ አበባ 25% በደቡብ ደግሞ 23% ሆኖ ተገኝቷል። መረጃው የትምህርት ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ የግርዘት መጠን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስም ይጠቁማል። ምንም መደበኛ ትምህርት በሌላቸው መካከል የግርዘት መጠን 41% ሲሆን ሁለተኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ትምህርት በተከታተሉት መካከል ግን 19% ብቻ ሆኖ ተገኝቷል። ነገር ግን የሀብት መጠን መጨመር ግርዘትን እንደማይቀንስ መረጃው ያሳያል።

ምንም እንኳን በ2000 እና 2005 የEDHS መረጃና በ2011ዱ የWMS መረጃ መካከል ቀጥተኛ ንጽጽር ማድረግ ባይቻልም፤ አንድ አራተኛ ሴቶች ብቻ (በከተማ 15%፤ በአዲስ አበባ 8% ብቻ) እንደተገረዙ የሚያሳየው የ2011ዱ ሰርቬይ በመስኩ ለውጥ እየተመዘገበ ለመሆኑ አመላካች ነው። ነገር ግን የሴት ልጅ ግርዛት በአማራ (47%) እና በትግራይ (22%) አሁንም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ደቡብ (9%) እና ጋምቤላ (7%) የሴት ልጅ ግርዛት መጠን ከ10% በታች የሆነባቸው ብቸኛ ክልሎች ናቸው።

*ያንግ ላይቭስ* ከሚሠራባቸው አካባቢዎች የሴት ልጅ ግርዛት መጠንን በተመለከተ የተሠበሠበ ኢ-አኃዛዊ መረጃ ባለመኖሩና ድርጊቱ ለጥናት አስቸጋሪ ከመሆኑ አንፃር ከላይ የተተነተኑት አኃዛዊ መረጃዎች ትክክለኛነት ጥያቄ ሊቀርብባቸው ይችላል። ነገር ግን የንዑስ ቡድኑን (sub-sample data) ናሙና የሚመለከተው ኢ-አኃዛዊ መረጃችን አስተማማኝ ነው። ከ15ቱም የትልልቆች ንዑስ ቡድን አባላት ማካከል ስምንቱ ግርዘት የተካሄደባቸው ሲሆን፤ እነዚህም ከኦሮሚያ አምስቱም፣ ከአማራ አንድ፣ ከሀዋሳ አንድ (የወላይታ ብሔረሠብ አባል)[6] እንዲሁም አንድ ከአዲስ አበባ (ከሀረሪ ብሔረሠብ የሆነች ሙስሊም) ነበሩ። ከትግራይ ግን ምንም አልነበረም። በኦሮሚያ ግርዘት የሚከናወነው ከፍ ካሉ በኋላ በመሆኑ ሁሉም ሴት ልጆች በአራተኛው ዙር የጥናት ወቅት ሁሉም ግርዘቸው ማጠናቀቃቸው ታውቋል። ሴት

[6]ከአሳዳጊዎች ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት (2008) ላይ አንዲት ልጃቸውን ያላስገረዙ አሳዳጊ ባለማስገረዛቸው መጸጸታቸውን ገልጸዋል። ነገር ግን በዚህ ዕድሜዋ (ካደገች በኋላ) ለማስገረዝ አደገኛ ይሆናል ብለው ፈርተው ትተዋል።

ልጆቹ ግርዘቱን በዕድሜ እኩዮቻቸው ግፊትና ለጋብቻ ለመዘጋጀት ሲሉ በሙሉ ፈቃደኝነት ማካሄዳቸውን ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን በሌሎች የጥናት ስፍራዎች ያሉት ሴቶች በጨቅላነታቸው ወይም ገና ሙሉ በሙሉ ነብስ ሳያውቁ በመገረዛቸው ምንም አያስታውሱም፤ ወይም ትውስታቸው በጣም ጥቂት ነው፡፡

በኦሮሚያ አንዲት ሴት የልጇን ባለቤትና የልጇን ግርዘት ዝግጅትና ሂደት በሚከተለው ሁኔታ ገልፃለች፡፡

**ጉዳይ 3፡ <u>አንዲት እናት በቤትዋ የተከናወነ ግርዘት ስትገልጽ</u>**

እኔ ራሴ በሌላ አካባቢ ስኖር ስድስት ዓመት ገደማ ሲሆነኝ ነበር የተገረዝኩት፡፡ እዚህ አካባቢ ልጆች ከፍ ካሉ በኋላ ነው የሚገረዙት፡፡ ለምሳሌ ባለፈው ዓመት የልጄን ባለቤት በ17 ዓመቷ አስገርዣለሁ፡፡ ልጄ አግብቶ ወደቤት ሲያመጣት እናትዋ በመሞታቸውና ሌላ የሚረዳት ሰው ባለመኖሩ አለመገረዟን አወቅን፡፡ …… የመጀመሪያ ልጄም [16 ዓመት ገደማ የሚሆናት] በዚያው እንድትገረዝ አደረግኩኝ፡፡ ሲገረዙ እንዳያስቸግሩ (እንዲደክሙ) መጀመሪያ ፌጦ እንዲጠጡ አደረግኩኝ፡፡

በሐምሌ 2008 ሌላዋን 14 ዓመት የሚሆናት ልጄን [በጥናት ናሙና ውስጥ የተካተተች] አስገርዣለሁ፡፡ ያስገረዝኳት በራሷ ጥያቄ ነው፡፡ አንዲት ልጅ ሌላ ያልተገረዘች ልጅን ስትሰደብ ሠምታ እንደ እርሷ መሠደብ አልፈልግም ብላ እንዳስገርዛት ጠየቀችኝ፡፡ ከተገረዘች በኋላ ቁስሉ ቶሎ እንዲሸርላት እንደ ስጋ ያለ ጥሩ ጥሩ ምግብ ልሠጣት አቅም እንደሌለኝ ነገርኳት፡፡ አባትዋ አይሠጠኝም ብዩ ፈርቼ ነበር፡፡ እርሷ ግን ስለዚያ ግድ የለኝም አንቺ ብቻ አስገርዢኝ ብላ አስቸገረችኝ፡፡… እንደ ዕድል ሆኖ አባቷ እሺ ብሎ ፍየል አረደላት፡፡ በሁለት ሳምንት ውስጥ ዳነች፡፡ የአካባቢው ባለስልጣኖች ይቀጡናል ብለን በመፍራት ግርዘቱን ያደረግነው በምሽት ነበር፡፡ …. በአካባቢው ባለስልጣኖች ቢከለከልም ሁሉም ሰው ሴት ልጁን ያስገርዛል፡፡

እዚህ ላይ ልጅቷ ልጅቷ በዕድሜ ዕኩዮቿ ላለመሠደብና በግፊት ወላጆቿ እንዲያስገርዟት ማስቸገሯንና እንዳይቀጡ በመፍራትም ግርዘቱ በምሽት በድብቅ መከናወኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡

## 6 የባህላዊ ድርጊቶቹ ተቃውሞ

የሴት ልጅ ግርዛትና ያለዕድሜ ጋብቻን የመደገፍና የመቃወም ሁኔታ በተወሠነ ደረጃ በየግለሠቡ የግል ተሞክሮ የሚወሠን ይሆናል፡፡ ይህ ክፍል ግለሠቦች ከየግል ተሞክሯቸው በመነሳት በሴት ልጅ ግርዛትና ያለዕድሜ ጋብቻ ላይ ያላቸውን አመለካከት ከሚሠጡት አስተያየት መረጃ የሚሠጥ ይሆናል፡፡

## 6.1 የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ

አንዳንድ በቤተሠብ በተወጠነ ጋብቻ ያገቡ ሴቶች የድርጊቱን ትክክለኛነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባሉ። በእንደዚህ አይነት ታሪኮች ውስጥ ስለትዳር ያለ የአመለካከት ለውጥ፣ በባህላዊ ጋብቻ ውስጥ በሴትና ወንድ መካከል ስለሚኖረው የዕድሜና የስልጣን ልዩነቶች፣ ብዙ ልጆችን የመውለድ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸውን በለጋነታቸው ከፈቃዳቸው ውጭ ትዳር እንዲይዙ የማድረጋቸው ሂደት ፍትሀዊነትና ትክክለኛነት ይነሳሉ።

ሁለት ሴቶች ከራሳቸው ያለዕድሜ ጋብቻ ልምድ በመነሳት ድርጊቱ ጎጂ መሆኑን እንዳመኑበት ገልጸዋል። በኦሮሚያ ያለች አንዷ ሴት ያዕድሜዋ እንድታገባ እንደተገደደች ገልፃ ባሏን ከመጀመሪያው እንዳልወደደችውና፤ በኋላም ጠጪ በመሆኑ አባትዋ በስጦታ የሰጧቸውን የቀንድ ከብቶች ከፊሉን እንደሸጠና ከፊሎቹ ደግሞ በሚገባ ስለማይከባከባቸው በድርቅ እንዳለቁ ገልጻለች። በተመሳሳይ ሁኔታ በትግራይ በ14 ዓመቷ እንድታገባ የተገደደች ሌላዋ ሴት የመጀመሪያ ልጇን በ17 ዓመቷ መውለዷን ገልፃ፤ ያለዕድሜዋ ማግባትዋ ለትዳሯ መፍረስ ምክንያት እንደሆነ አስረድታለች።

> ያኔ ልጅ ስለነበርኩኝ ችግርና ጭቅጭቅ ምንም መታገስ አልቻልኩም። በየጊዜው እወድቅ ነበር።………. ያደግኩበት መንደርንም እናፍቅ ነበር። በጣም ሥራ የሚበዛብኝ ሲሆን አዲስ የወደቀብኝ ኃላፊት በጣም ከብዶኝ ነበር። ይህ ሁሉ በጣም ስላሳፈረኝ ወደ ፍቺ አመራሁ። በወቅቱ አብዛኛዎቹ ሴቶች ለትዳር በጣም ልጅ በመሆናቸው እንደ ውኃ መቅዳት የመሳሰለውን የህይወት ውጣ ውረድ መቋቋም ከባድ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ፍቺን ይመርጣሉ።

በሀዋሳ የአንድ ቀበሌ የሴቶች ማኅበር ሊቀመንበር ስትናገር የ10ኛ ክፍል ተማሪ የነበረች የአንድ ጓደኛዋ ልጅ ልትዳር መሆኑን ስትሰማ በመደናገጥ ከቤት ጠፍታ እንድታደጋት ወደ እርሷ ዘንድ መምጣትዋን በሚከተለው ሁኔታ ገልፃለች።

> ከፈቃድዋ ውጭ ለምን እንድታገባ እንደተገደደች ስጠይቃት እናትዋ በህይወት እንደሌለችና አክስቶቿ አንድ ሀብታም ሰው እንድታገባ እንደጠየቁት ነገረችኝ። "አንቺንም ሆነ እኛን ከድህነት ይገላግለናል" አሏት። በጣም ነው ነገሩ ያበሳጨኝ። በነገሩ ከገፉበት ወደ ቀበሌና የሕግ ክፍል እንደምወስዳት ነገርኳት። … እርሷ ከድህነት መገላገያ መንገድ አይደለችም። ምክሬን ተቀብላ አሁንም ትምህቷን በመከታተል ላይ ትገኛለች። …. ወደ ፖሊስ ወስጄ ጉዳዩን ላስመዘግብላት እንደምችልም ነግሬያታለሁ። ነገር ግን የትምህርት

> ቤት ክፍያና ሌሎች የትምህርት ወጪዎችን የሚሸፍኑላት እነዚህ ዘመዶቿ በመሆናቸው ፈራች፡፡

አንዳንዴም በሴት ልጅ ጋብቻ ላይ የቤተሠብ አባላት እርስ በርስ የማይስማሙበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በትግራይ አንድ መላሽ የሚከተለውን ብሏል፡፡

> በቤተሠብና በሴት ልጆች መካከል የአለመግባባት ዋናው ምክንያት ልጆቹ በለጋ ዕድሜያቸው ለማግባት እምቢ ሲሉ ነው፡፡ የትዳር መያዣ ዝቅተኛው ህጋዊ ዕድሜ 18 ዓመት ነው፡፡ ቤተሠብ ከዚያ ዕድሜ በፊት ትዳር ያዙ ሲላቸው ለሴቶች ማኅበር ሊቀ-መናብርት ወይም ለመምህሮቻቸው ያመለክታሉ፡፡ ልጆቹ አናገባም ሲሉ አንዳንዴ በቤተሠቦቻቸው ይደበደባሉ፡፡

ይህ ምሳሌ በትውልድ መካከል ያለውን ውጥረት ያመለክታል፡፡ የ2011 መረጃ እንደሚያመለክተው ወላጆች ሴት ልጆቻቸው ቀደም ብለው ትዳር እንዲይዙ ለማሳመን ይጥራሉ፡፡ ነገር ግን በሕግ እንዳይጠየቁ ትክክለኛ ዕድሜያቸውን ይደብቃሉ[7]፡፡ በኦሮሚያ አንዲት ልጅ በሌላ የትምህርት ቤት ጓደኛቸው ላይ የደረሰውን ስትገልጽ የ4ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው የ15 ዓመት ልጅ በወላጆቿ ለትዳር ትታጫለች፡፡ ልጅቷም ችግሯን ለትምህት ቤቷ በመናገር መምህራኖቿ እንዲያድኗት ትማጸናለች፡፡ መምህራኖቹም ለአባቷ ልጅቷ ገና ለትዳር እንዳልደረሰችና ትዳርም ትምህርቷን እንደሚያስተጓጉልባት በመግለጽ ለማሳመን ሙከራ ቢያደርጉም አባትየው አሻፈረኝ አለ፡፡ የልጅቷ የእንጀራ እናትም ጋብቻውን በመቃወም ከባልዋ ተጣላች፡፡ ወላጆቿ ለሠርጉ ሲዘጋጁ ልጅቷ ወደ አያቷ ቤት በመሄድ ተደበቀች፡፡ አባትየው እናትዋ ታማለች በማለት መምህራኖችዋን አታልሎ ወደቤት እንድትመለስ በማድረግ እርሷና አያትዋ እየተቃወሙ በግድ እንድታገባ ተደረገ ብላለች፡፡

## 6.2 የሴት ልጅ ግርዛት

የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ በኦሮሚያና ድርጊቱ በስፋት በሚካሄድባቸው ሁለት የጥናቱ የከተማ አካባቢዎች ተቃውሞዎች በአብዛኛው የሚመነጩት ከሴቶቹ ከራሳቸው ተሞክሮና ሌሎች ሴቶች በድርጊቱ ሳቢያ ከሚደርስባቸው ችግር በመነሳት ነው፡፡

ድርጊቱ የተፈጸመባቸው ሴቶች ተመሣሣይ ሁኔታ በልጆቻቸው ወይም በልጅ ልጆቻቸው ላይ እንዳይደርስ በጽኑ ይሻሉ፡፡ ለምሳሌ በሀዋሳ አንዲት ሴት እንደገለጸችው እርሷ በግርዘት ሳቢያ በወሊድ ላይ ከፍተኛ ችግር ደርሶባት ስላየች

[7] ይህ ከአሳዳጊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ ጥናት ከተገለጹት ያለዕድሜ ጋብቻዎች መካከል ሁለቱ በወላጆችና በልጆቹ ስምምነት የተፈጸሙ መሆናቸው ተመልክቷል፡፡

ልጅዋ እንዳትገረዝ እንዳደረገች ገልፃለች። በኦሮሚያ አሳዳጊዎች ሴት ልጆች ግርዘት ሲፈጸምባቸው የሚደርስባቸውን ስቃይ በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል።

> [ድርጊቱ] የጭካኔ ሥራ ሲሆን የምትገረዘው ልጅ ብዙ ደም ስለሚፈሳት ቁስሉ እስከሚድንና እስኪሻላት እስከ ሁለት ወር ድረስ ቤት ትቆያለች። ድሮ ሴት ልጆች አይናፋር ስለነበሩ ለብዙ ቀናት ከቤት ሳይወጡ ይቆዩ ነበር። የአሁን ጊዜ ሴት ልጆች ግን በጣም ፈጣን ስለሆኑ በቀላሉ ቶሎ ይሻላቸዋል። በግርዘት ጊዜ ዋናው ችግር ብዙ ደም ስለሚፈሳቸው ለመዳን ብዙ ጊዜና ጥሩ ጥሩ ምግብ ያስፈልጋቸዋል። አንዳንዴ ደሙ መፍሰስ አልቆምም ሲል አባትዋ ወይም የወደፊት ባልዋ በግ አርዶ ደሙን እንድትጠጣና የፈሰሳትን ደም እንድትተካ ይደረጋል።

የተገረዘች ልጅ የፈሰሳትን ደም ለመተካትና በቶሎ እንድታገግም ጥሩ ጥሩ ምግብ መመገብ እንደሚኖርባት አሳዳጊዎች በአጽንዖት ገልጸዋል። በኦሮሚያ አንዲት ልጅ ጓደኛዋ በአሮጌ ምላጭ ተገርዛ በዚያ ጠንቅ በመሞቷ እርሷ ግርዘቷን እንደተወች ገልጻለች። በተመሣሣይ በአዲስ አበባ አንዲት ሴት ቀደም ሲል ግርዘት የቆየ ባህል ነው በማለት በቀበሌ ባለስልጣኖች ፊት ይሟገቱ እንደነበር ገልጸው ነገር ግን የተገረዙ ወጣት ሴት ልጆች በወሊድ ላይ ምን ያህል እንደሚሠቃዩ ካዩ በኋላ ኃሳባቸውን እንደቀየሩ ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ አንዲት ያልተገረዘች ሙስሊም ልጃገረድ እናቷ እንድትገረዝ ሁሉን ነገር ካዘጋጁ በኋላ ገራኚ ወደቤታቸው ስትመጣ እርሷ ወደጎረቤት በመሄድ ተሸሽጋ ማምለጧን ተናግራለች። እዚያው የጥናት አካባቢ ያለች በ5 ዓመቷ ከፈቃድዋ ውጭ እንድትገረዝ የተደረገች ሌላ ሙስሊም ልጃገረድ በበኩሏ የተገረዘች ዕለት ብዙ ሰዎች ቤት ስለነበሩ ማምለጥ እንዳልቻለች ገልፃለች።

## 7 የለውጥ ተቃውሞ

ምንም እንኳን የሴት ልጅ ግርዛትንና ያዕድሜ ጋብቻ ተቃውሞዎች እየታዩበትና ግልጽ ለውጦችም እየተመዘበቡበት ቢሆንም አሁንም ዝቅተኛውን የትዳር መያዣ ዕድሜ በሕግ ለመወሠንና ግርዘትን በሕግ ለማገድ የሚደረጉት ጥረቶች አንዳንድ ህብረተሠባዊ ተቃውሞዎች እየደረሱበት ይገኛል። የሴት ልጅ ግርዛትንና ያዕድሜ ጋብቻን በተመለከተ ያሉት የአመለካከት ልዩነቶች አንዳንዴ በቤተሠብ አባላትና እኩያሞች መካከል ግልጽ አለመግባባቶችን እስከሚፈጥሩ ድረስ ጠንካራ ናቸው።

## 7.1 የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ

የመንግሥት አርምጃዎችና ሌሎች ተጽዕኖዎች የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻን በተመለከተ የግድ የእሴትና የአመለካከት ለውጥ አምጥተዋል ማለት አይቻልም፡፡ ብዙ መላሾች በእርግጥ ተግባራዊ ለውጥ መምጣቱን ይጠራጠራሉ፡፡ ለምሳሌ በኦሮሚያ አንድ የአገር ሽማግሌ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> መንግስት ሴት ልጆች የትዳራቸውን ሁኔታ በተመለከተ ራሳቸው እንዲወስኑ ያስተምራል፡፡ ይህ ወላጆች የወደፊት የትዳር ጓደኛን መምረጥን ጨምሮ የልጆቻቸውን የትዳር ሁኔታ የመወሠን ባህላዊ ልማድ ጋር ይቃረናል፡፡ ነገር ግን መንግሥት ልጆችን በትምህርት ቤት በማስተማርና በመሳሰለው የሚያደርገው ተፅዕኖ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ያላቸውን ቁጥጥር ቀንሶታል፡፡ ዛሬ ሴት ልጆች በትምህት ቤትና በእርሻ ቦታ ከፈለጉት ወንድ ልጅ ጋር ፍቅር መጀመር ጀምረዋል፡፡ ይህ በመጨረሻ የወደፊት ህይወታቸውንና ትምህታቸውን ያደናቀፋል፡፡

ይህ ምሳሌ የመንግሥት እርምጃና በእርሻ የቅጥር ሥራ መሰማራት በወላጆችና ልጆች መካከል ያለውን ግንኙነት እንደለወጠውና የሴት ልጆችን ጋብቻ በተመለከተ የወላጆችን የበላይነት እንደቀነሰው ያስገነዝባል፡፡ ይህ አመለካከት ወጣት ልጆች ብስለትና ብልህነት ስለሚጎድላቸው ያለታላላቆቻቸው መሪነት ችግር ላይ ይወድቃሉ በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተና በዚህ ሳቢያ ሴት ልጆች እነርሱንም ወላጆቻቸውም ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያደርሱ እንደ ጠለፋና ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም የመሳሰሉ አደጋዎች ላይ ሊወድቁ ይችላሉ በሚል ስጋት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡

በመሆኑም 18 ዓመትን እንደ ዝቅተኛውን የጋብቻ ዕድሜ በሕግ የመወሠኑ ዋና ፍራቻ ሴት ልጆችን ከጋብቻ በፊት ወሲብ እንዲፈጽሙ ሊያበረታታና ለተጓዳኝ ችግሮች ሊያጋልጥ ይችላል የሚል ነው፡፡ የEHDS 2000፣ 2005 እና 2011 ስታቲስቲክስ እንደሚሳዩት በአጠቃላይ ሲታይ የሴት ልጆች የጋብቻና የወሲብ መጀመሪያ ዕድሜዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ በከተማ ግን ወሲብ የመጀመሪያ ዕድሜ በትንሹ ይቀድማል፡፡

በትግራይ ወላጆች ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ ከፍ ማለት የሚያስከትለውን ችግር በማንሳት ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ ወደ ወደ 16 ወይም 17 እንዲወርድ ይጠይቃሉ፡፡ ለዚህም በዋናነት የሚያቀርቡት ምክንያት ሴት ልጆች በ15 እና ከዚያ በላይ ባለው ዕድሜ ለአቅመ-ሔዋን ስለሚደርሱ የጋብቻ ዕድሜን ከፍ ማድረግ ከጋብቻ ውጭ የመፀነስ እድልን ከፍ ያደርገዋል የሚል ነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ከጋብቻ ውጭ ልጅ

እንዳይወለድ በማለት የሴት ልጆቹ ወላጆች ወንዶቹ አሻረኝ ካሉ በሕግ ለመጠየቅ በማስፈራራት ጭምር ጋብቻ እንዲፈፀም ያደርጋሉ። በዚህ ሳቢያ አንዳንድ ወላጆች ሴት ልጆች አግብተው ትምህርታቸውን መቀጠላቸው ከመጠለፍ ያድናቸዋል ብለው ያስባሉ። እንዲሁም ሴት ልጆች ከቤት ርቀው ትምህርታቸውን በከተማ ሲከታተሉ የግብረ-ስጋ ግንኙነት በመፈጸም ላልተፈለገ እርግዝናና ልጅ ማሳደግ ያጋልጣቸዋል፤ እንዲሁም መልካም ጋብቻ የመመስረት ዕድላቸው ያበላሻል በማለት ሴት ልጆቻቸውን ከተማ ልከው ማስተማርን አይሹም[8]። እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸው በጊዜ አግብተው በህይወት እያሉ ልጅ ልጅ የማየት ጉጉት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ ጨዋና ታዛዥ ልጅ አሳድጎ በወግ በማዕረግ ህጓን እንደጠበቀች መዳር ትልቅ ከበሬታ ስለሚያስገኝ ቤተሠብ ልጆቻቸውን በጊዜ ለመዳራቸው ተጨማሪ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል።

በአዲስ አበባ ወላጆች የዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ ከፍ ማለት ያልተፈለግ እርግዝናንና ህገወጥ ውርጃን ያባብሳል ብለው ይሠጋሉ። እዚህም እንደሌላው ቦታ ሁሉ "ሴት ልጆች ከዚያ ዕድሜ በጣም ቀድመው ለግብረ-ስጋ ግንኙነት ይደርሳሉ" በሚለው ምክንያት ሳቢያ ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ ይሻሻላል የሚል ተስፋ ያደርጋሉ። በአዲስ አበባ ብዛት ያላቸው ሴተኛ አዳሪዎች መኖርና ሴት ልጆች በጊዜ ትዳር ከያዙ ወደዚህ ኑሮ የመግባት እድላቸው ያነሠ ነው የሚል አስተሳሰብ ከላይ ለተጠቀሰው አመለካከት መኖር ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

ጠለፋ በሠፊው በሚታይበት የኦሮሚያ ክልል ወላጆች በቤተሠብ የተወጠነ ጋብቻን ይመርጣሉ። ነገር ግን ይህ ልማዳዊ ድርጊት "የተጋቢዎቹን ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ" መልኩ ለውጥ ሊደረግበት እንደሚገባም ያምናሉ። ሴት ልጅ የማታውቀውን፣ የማትፈቅደውን ወይም በዕድሜ በጣም የሚበልጣትን ሰው እንድታገባ መገደድ የለባትም ብለው ያምናሉ። እንዲሁም ከ18 ዓመት በፊት ማግባት እንደሌለባት፣ ጋብቻዋም የወላጆቿን ፍቃድ ማግኘት እንዳለበትና በባህላዊ ሥርዓት መሠረት መፈጸም እንደሚኖርበት ይከራከራሉ። በኦሮሚያ በቤተሠብ የሚወጠን ጋብቻም ሆነ ጠለፋ እየቀነሱ መጥተዋል። በሌላ በኩል "የውዴታ ጠለፋ" (የወጣቶች ተዋድደው ተያይዘው መጥፋት) እየተስፋፋ መጥቷል። ወላጆች ጠለፋ "የሴት ልጅ የጋብቻ መብትን ሙሉ በሙሉ የሚጥስ በመሆኑ" በመቀነሱ ደስተኛ ናቸው። ቀደም ሲል አንዳንዴ ሙሽራዋ ወደ ልጁ ቤት ለመሄድ ወይም ከሙሽራው ጋር ለመተኛት አሻፈረኝ ስትል ትደበደብ የነበረበትን ድርጊት ይኮንናሉ። ነገር ግን አሁን እየተስፋፋ

[8]አንዳንድ ዓለም-አቀፍ ጥናቶች ሴት ልጆች ትምህርት ቤት መግባት ጋብቻቸውን እንደሚያዘገይ ያሳያሉ (UNICEF 2005)። አንድ ጥናት በተለይ ተማሪ ሴት ልጆች ለአቅመ-ሔዋን እንደደረሱ እንደማይቆጠሩና ለትዳር እንደማይታሰቡ ያሳይል (Malhotra and Tsui 1996: 488)። ነገር ግን ይህ ምን ያህል እውነትነት እንዳለው ምክንያቱን የሚያሳይ የረጅም ጊዜ መረጃ ባለመኖሩ ለማረጋገጥ ይከብዳል። (Mensch et al. 1998: 60).

በመጣው “የውዴታ ጠለፋ” ላይም ከፍተኛ ስጋት አላቸው፡፡ ወላጆች ብዙ ጊዜ በዚህ ዓይነት የተፈጸመ ጋብቻን የሚቃወሙ ሲሆን፤ ብዙዎቹ አግቢውንና ወላጆቹን በሕግ ቢከስሱም ፍርድ ቤት ግን በውዴታ በተፈጸመ ጋብቻ ላይ እርምጃ አይወስድም፡፡ “የውዴታ ጠለፋ” የጥሎሽ ሁኔታ ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ የአግቢው ቤተሠብ የጎሣቸውን ሥርዓት በመጣሱ ለልጅቷ ቤተሠብ 1,000 ብር፤ ለጎሣው ደግሞ 200 ብር በጠቅላላው 1,200 ብር በቅጣት መልክ ይከፍላል፡፡

በኦሮሚያ “የውዴታ ጠለፋ ” በተጋቢዎቹ በራሳቸው በምስጢር የሚወጠን ሲሆን ተዋድደው አብረው የሚጠፉት ወጣቶች ከጋብቻ በፊት የግብረ-ስጋ ግንኙነት ፈጽመው ልጅቷ ፀንሳ ይሆናል በማለት ስለሚጠረጠር “የውዴታ ጠለፋ” ጋብቻ የልጅቷንና ቤተሠቧን ክብር የሚያጎድፍ ድርጊት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ አንዳንድ ወላጆች “በውዴታ ጠለፋ” የተካሄደ ጋብቻ በፍቺ የመደምደሙ ዕድል ከፍተኛ ነው ይላሉ፡፡ ብዙ ሴት ልጆችም በዚህ አይነት ተታልለዋል፡፡ ከቤተሠብ ፈቃድ ውጭ በዚህ ዓይነት የተመሠረተ ጋብቻ ዘላቂነት የሌለውና በመጨረሻም ፍቺ ሲከተል ልጅቷ ከቤተሠቧ የመገለል ችግር ይገጥማታል ይላሉ፡፡ በቤተሠብ የተወጠነ ጋብቻ በሁሉም ወገኖች መካከል መከባበርን ይፈጥራል (በተለይ የልጁ ቤተሠብ ለልጅቷና ለቤተሠቦቿ ከበሬታ ይሰጣሉ) ተብሎ ስለሚታሰብ ይመረጣል፡፡ በተለይ ከቤተሠብ ምክር ውጭ ለመወሰን ገና አልደረሡም ተብለው የሚታሰቡትን በአሥራዎቹ መጀመሪያ ዕድሜዎቹ ላይ ያሉ ሴት ልጆችን “በውዴታ ጠለፋ” ማግባት የከፋና ክብራቸውን የሚቀንስ ድርጊት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ “በውዴታ ጠለፋ” ጋብቻ የሚጋቡ ጥንዶች እንደ መኖሪያ ቤትና ቋሚ የገቢ ምንጭ ስለማይኖራቸውና በቤተሠብ እርዳታ ስር ስለሚወድቁ ለማኅበራዊ መገለል ይጋለጣሉ፡፡

በውዴታ ጠለፋ ከሚደርሱ አቢይ ችግሮች መካከል ከልጅቷ ቤተሠብ ጋር የሚኖረው ግንኙነት መቋረጥ ሲሆን በኦሮሚያ የጥናት ስፍራ ያለች አንዷት ሴት የራስዋን ተሞክሮ እንደሚከተለው ገልጻለች፡፡

> ልጇ ባለፈው መስከረም ነው ያገባችው…. ከልጁ ጋር ተማክራ የኛን ፈቃድ ሳትጠይቅ ነው ያገባችው፡፡ በቃ፤ በራስዋ ፈቃድ ነው ቀጥሎ ያለው ከተማ ያገባችው፡፡ ካገባች ጀምሮ ቤታችን መጥታ አታውቅም፤ እኛም ቤቷ ሄደን አናውቅም፡፡ ምክንያቱም ከፍላጎታችን፣ ከፈቃዳችንና ከባህላችን ውጭ በማግባትዋ ነው፡፡ ገና ዕርቅ አላደረግንም፡፡ ስለዚህ እኛም አንሄድም፤ እሷም ወደ ቤታችን አትመጣም፡፡

በኦሮሚያ ሴት ልጆችም “በውዴታ” ጠለፋ አይስማሙም፡፡ አንድ የቡድን ውይይት ላይ ተሳታፊዎች “የውዴታ ጠለፋ” የማኅበረሠቡን ባህል የሚጻረር ጎጂ ድርጊት በመሆኑ መታገድ አለበት ብለዋል፡፡ ለዚህም የሰጧቸው ምክንያቶች ትልልቆቹ

ከሰጧቸው ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ እነርሱም በልጅቷ ትምህርት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ፣ ፍቺ የማጋጠም ዕድል ከፍተኛነት፣ በልጅነት የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸምና የልጅ እናት መሆን እና የእነዚህ ሁሉ ጥርቅም ውጤት የሚሆነው ድህነትን ያካትታል። በእነርሱ አመለካከት የልጅቷን የወደፊት የትምህርትና የኑሮ ሁኔታ ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ቋሚ ድጋፍ የሚሠጥበት በቤተሠብ የሚወጠን ጋብቻ የተሻለ ነው። በዚህ አይነት ጋብቻ የልጁ ወላጆች ልጅቷ ከጋብቻ በኋላ ትምህርቷን የምትቀጥልበትን ሁኔታ ሊያመቻቹላት ሁሉ ይችላሉ።

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ የሚታየው በወጣቱ ትውልድ በችኮላ የሚወጠነውን ጋብቻ አዝማሚያ ስጋት ሴት ልጆች በግል ምርጫ ያልሆነ ግንኙነት እንዲፈጥሩ የሚያደርግና እንደ ጥሎሽ የመሳሰሉ ባህላዊ ድርጊቶችን የማፋለስ አደጋ ያዘለ ነው በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው። የጥናቱ መላሾች ድርጊቱ ያለዕድሜ ጋብቻን ከመቀነስ ይልቅ የሚያባብስ ከመሆኑ በላይ ለፈጣን ፍቺ ወይም ትዳርን ጥሎ ለመኮብለል አደጋ ያጋልጣል ሲሉ በእርግጠኝነት ይመልሳሉ። ከዚህ በተጨማሪ ከቤተሠብ ፍቃድ ውጭ የሚመሰረት ጋብቻ በተጋቢዎቹና በቤተሠቦቻቸው መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ያሻክራል። በዚህ ሳቢያ ወላጆች ከፈቃዳቸው ውጭ ላገባች ልጃቸው የሚሰማቸው ኃላፊነት ስለሚቀንስ ተጋቢዎች የግል ኑሯቸውን ለመጀመር የሚያስችል ድጋፍና ጥበቃ ሊያጡ ይችላሉ።

## 7.2 የሴት ልጅ ግርዛት

እንደ የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ ሁሉ የመንግሥት ባለስልጣናት፣ የሴት ማኅበራት መሪዎችና እንዳንድ ወላጆች ሴት ልጅን የመግረዝ ሥርዓትን ይቃወማሉ። ነገር ግን ተግባሩ በሕግ የተከለከለ ቢሆንም የተወሰኑ የኅብረተሠብ ክፍሎች በተለያዩ ምክንያቶች የድርጊቱን አስፈላጊነት በመጥቀስ እንዲቀጥል እንደሚሹ ኃሳባቸውን ይገልፃሉ። እዚህ ላይ በኦሮሚያና አዲስ አበባ የጥናት አካባቢዎች የዚህ አይነት አስተያየት የተሠጠው በሴት ልጆች በራሳቸው መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

በኦሮሚያ የሴት ልጅን ግርዛት በተመለከተ ከፍተኛ የኃሳብ ልዩነቶች ይስተዋላሉ። ከሌሎቹ የጥናት አካባቢዎች በተለየ በኦሮሚያ የሴት ልጅ ግርዛትን ዐዋቂዎች ሳይሆኑ ወጣት ሴቶች ናቸው ለውጡን ይበልጥ የሚቃወሙት። ይህም ይበልጥ ከጓደኞቻቸው ላለመለየት በሚደርስባቸው ግፊት ሳቢያ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይታሠባል። በኦሮሚያ ክልል የወጣት ወንዶች ቡድን የሚከተለውን ምክንያት ሠጥተዋል። ትንንሽ ሴት ልጆች ህመሙን በመፍራት መገረዝን እምቢ ሲሉ ለጋብቻ የደረሱ ሴት ልጆች መካከል ግን እምቢታ እጅግም አይታይም ብለዋል። ይህም የሚሆነው እነዚህ ወጣት ልጃገረዶች በተገረዙ እኩዮቻቸው የሚደርስባቸውን ስድብና ሽሙጥ መቋቋም

ስለሚሳናቸው ነው ብለዋል። ወጣቶቹ አንዲት ሴት ልጅ ጎረቤቷ ባለመገረዟ ስላሽሟጠጠቻት ካገባች በኋላ መገረዟን አስታውሰዋል።

አንዳንድ ጊዜ ሴት ልጆች ከተለመደው ውጭ ማድረጋቸውን እያወቁ ከቤተሠቦቻቸው ፈቃድ ውጭ ራሳቸው ግርዘታቸውን በድብቅ ያዘጋጃሉ። በኦሮሚያ አንዳንዴ ሴት ልጆች በድብቅ እንደሚገረዙ ወላጆችም ገልጸዋል። ከዚሁ የጥናት ክልል አንዲት ሴት ስለሁኔታው ስትገልጽ የ12 እና 14 ዓመት ልጆቿ የግርዘታቸው ዝግጅት ካጠናቀቁ በኋላ እንደነገሯት ተናግራለች። ሌላ አንድ ትልቅ ሰው በበኩሉ የሚከተለውን ብሏል።

> ያለፈው ዓመት ብቻ በአካባቢው 17 ሴት ልጆች በራሳቸው ፈቃድ ተገርዘዋል። የአካባቢው ባለስልጣናት ገራዥዋን ፍርድ ቤት ቢያቀርቧትም ልጆቹ ሴትየዋ ሳትሆን ራሳቸውን በራሳቸው እንደገረዙ ምስክርነት ሠጥተዋል። በዚህ ሳቢያ ፍርድ ቤቱ ምስክር ባለማግኘቱ ሴትየዋን መቅጣት ሳይችል ቀርቷል። ሴትየዋም በነፃ ተለቃለች።

በዚሁ አካባቢው ድርጊቱን ለማስቆም እንዲተባበር የተጠየቀ መምህር በበኩሉ በቅርቡ በአካባቢው 35 ልጆች መገረዛቸውን አጋልጧል። ልጆቹና ቤተሠቦቻቸው ለፖሊስ ሪፖርት ሲደረጉ ልጆቹ ሌሎች የተገረዙ እኩያዎቻቸው እንዳያሽሟጥጧቸው ሲሉ ወላጆቻቸው ሳያውቁ እራሳቸው አደራጅተው እንደተገረዙ ተናግረዋል። መምህሩ በተጨማሪ “ፖሊስ ዘንድ ስንከሳቸው ማስረጃ ማቅረብ ያዳግተናል። ልጆቹ ራሳቸውን እንደገረዙ ይናገራሉ። በኋላ ለሚገርዙት ሰዎች ትምህርት መሠጠት ተጀመረ። ከዚያ በኋላ የመጣውን ለውጥ አላውቅም” ብሏል።

ሴት ልጆቹ በበኩላቸው እናቶች ለማስገረዝ አሻፈረኝ ሲሉ በድብቅ መገረዝ የማይቀር ነው ብለዋል። “ልጅቷ ገራዧ ቤት ሄዳ እንድትገርዛት ትለምናታለች። ግርዘቱ በምሽት ወይም በማለዳ ይከናወናል” ብለዋል። የሴት ልጅ ግርዛት በመንግሥት በሕግ መከልከሉ በተቃራኒው ሴት ልጆች የሚገረዙበትን ዕድሜ ዝቅ ማድረጉንና ድርጊቱን በተመለከተ በልጆችና ወላጆች መካከል ልዩነቶችን እንዳሠፋ ተጠቅሷል። ቀደም ሲል ሴት ልጆች በ15 ዓመታቸው ገደማ ይገረዙ ነበረ።

> ይህም ማለት ልጅቷ ስትታጭና ጋብቻዋ ሲቃረብ ነበር የምትገረዘው… አሁን ግን ሴት ልጆች በ10ና ከዚያም ባነሠ ዕድሜያቸው ይገረዛሉ። ድሮ ግርዘት በወላጆች፣ በተለይ በእናቶች የሚታቀድ ነበር። አሁን አሁን ግን መገረዝ በሚፈልጉት በልጆቹ በራሳቸው ሆኗል። የሴት ልጅ ግርዛት በመንግስት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተደርጎ በመወሰዱ ወላጆች ልጆቻቸውን ማስገረዝ ይፈራሉ።… ሌላው ጉዳይ ቀደም ብለው የተገረዙት ልጆች ያልተገረዙትን መስደብ ይጀምራሉ። የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት እንቅስቃሴ ከተጀመረ ወዲህ የዚህ አይነት ስድብ ተስፋፍቷል። በዚህ

ምክንያት ሴት ልጆች ከወላጆቻቸው እውቅናና እንዲሁም ከህብረተሠቡ ልማድ ውጭ በሆነ ሁኔታ ከ15 ዓመት በታች መገረዝ ጀምረዋል። …

ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌ የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት የተጀመረው ዘመቻ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትልና እንዲሁም ላለመገረዝ የሚፈልጉ ሴት ልጆች ላይ አሉታዊ ዘመቻ ሊያስከፍት የሚችል እንደሆነ ያመለክታል። ለመገረዝ የሚሹ ሁለት ልጃገረዶች እንዳመለከቱት በሌሎች ጓደኞቻቸው መዘባበቻ ከሚሆኑ ተገርዘው "ሠላም" ቢያገኙ የተሻለ መሆኑን ተናግረዋል። ሌላዋ ልጃገረድ በበኩሏ ተገርዛ የወደፊት ሕይወቷን ከምታበላሽ "ባለመገረዝዋ የሚደርስባትን ስድብ ሁሉ መቻል" እንደሚሻላት ታስብ እንደነበር፤ ነገር ግን ባለመገረዝዋ የሚደርስባት መገለል (stigmatisation) ከባድ በመሆኑ ከጥቂት አመታት በኋላ መገረዟን ተናግራለች። በ2011 ዓ.ም. በሶስተኛው ዙር የመረጃ ስብሰባ ላይ በዚህ የጥናት አካባቢ ያለው ንዑስ ቡድን አባላት የሆኑ ሴት ልጆች በሙሉ ግርዘታቸውን አጠናቀው ተገኝተዋል። በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ያሉት የኃሳብ ልዩነቶች በቤተሠብ መካከል ሳይቀር ቅራኔ ሲፈጥሩ ይታያል። በሀዋሳ ቃለ-መጠይቅ የተደረገላት አንዲት የዕድር መሪ አራት ሴት ልጆቿ የተገረዙ ቢሆንም የመጨረሻዋን አምስተኛ ልጅዋን ላለማስገረዝ መወሠንዋን ተናግራለች። ባለቤትዋ ግን በዚህ ውሳኔዋ በጣም ተናድዶ እርሷም እንደ እህቶቿ መገረዝ አለባት በማለቱ ለማቻቻል ሲባል ልጅቷ በጣም በትንሹ (ለምልክት ያህል) መገረዝዋን፤ በተገረዘች በማግስቱ ካለምንም ችግር ስትንቀሳቀስ በማየቱ ባለቤትዋ መጠራጠሩን ተናግራለች። ሴትየዋ እንደተናገረችው ይችኛዋ ልጅ እንደ እህቶቿ ሙሉ በሙሉ ባለመገረዝዋ የተሻለች ሲሆን ያልተገረዘች ልጅ ማዕድ ቤት ውስጥ ቅል ትሠብራለች ብላለች።

ለውጥ ያለመቀበል እምቢተኝነት ድርጊቱን በሚፈጽሙ ላይ የቅጣት ውሳኔ በተደነገገባቸው አካባቢዎች ሳይቀር ይታያል። ይህም በተወሰነ ደረጃ ከበላይ ድርጊቱን ለማስቆም የተወሠነ ውሳኔ ላይ እምቢተኝነት (የማመጽ ሁኔታ) ይመስላል። በዚህም ምንም እንኳን ድርጊቱ በሕግ ለማስቆም ጥረት ቢደረግም ሙስሊሞች በድብቅ ሴት ልጆቻቸውን አሁንም ያስገርዛሉ ብለዋል። በኦሮሚያ ቅጣትን በመፍራት ግርዘት በምሽት እንደሚካሄድ ተመልክተናል። መንግሥት ድርጊቱን በሕግ ከከለከለ ወዲህ በሀዋሳ ሰዎች የወንድ ልጆች ግርዘት ዝግጅትን ለሴት ልጆች ግርዘት እንደሽፋን መጠቀም ጀምረዋል። "በመጀመሪያው ዕለት [ህጋዊ የሆነውን] የወንድ ልጆች ግርዘትን ያካሂዳሉ። እንግዶችም ተጠርተው ይጋበዛሉ። በማግስቱ ግን ሴት ልጆችን ያስገርዛሉ" ብለዋል። ድርጊቱን "በቅሎን ለማኮላሸት አህያን አንከባለሉት" በሚለው የአማርኛ ብሂል ገልጸውታል። ይህ ድርጊት ውጤታማ ማታለያ መንገድ ሆኗል ምክንያቱም

ባለስልጣናት ስለድርጊቱ ሲጠይቁ እንግዶቹ የወንድ ልጆች ግርዘት መሆኑን ይመሠክራሉና።

## 8 ዘመናዊነትና የሴት ልጆች ራዕይ መጨመር

በኢትዮጵያ በመንግሥትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተደረጉት ጥረቶች ምንም እንኳን የተፈልገውን ያህልና የሴት ልጆችን ደህንነት በሁሉ መልኩ ባገናዘበ መልክ የባህሪ ለውጥ ባያመጡም በሴት ልጅ ግርዛትና ያለዕድሜ ጋብቻ ድርጊቶች ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወታቸው ቀደም ሲል ተገጿል። በዚህ ክፍል ከነዚህ እርምጃዎች በተጨማሪ በተለይ የጋብቻና የልጅ አስተዳደግ ሥርዓቶች (institutions) ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ልማዶች ቀስ በቀስ እየተቀየሩና የልጆች መብቶችና የራስን ማንነት (self-actualization) ላይ ያተኮሩ ለውጦች እየተመዘገቡ መሆናቸውን እናያለን።

ኢትዮጵያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትምህርትን በማዳረስ ረገድ አስደናቂ እመርታ አሳይታለች። ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በጋብቻ ይሰናከል የነበረው የሴት ልጆች ትምህርት ፍላጎት ተነሳሽነትና (aspiration) የሥራ ዕድል በእጅጉ ጨምሯል። በአማራ ክልል አንድ የቀበሌ ተመራጭ በዚህ ላይ አስተያየት ሲሰጡ የሚከተለውን ብለዋል።

> ..አሁን ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ልጆቻቸውን በልጅነታቸው መዳር እየተዉ ነው። አሁን ህብረተሠቡ ልጆች በራሳቸው ምርጫና ፍላጎት ማግባት እንደሚችሉም እያመነ ነው። … ጎጂ ባህላዊ ድርጎቶችን ለመከላከል የተደረገው ጥረት በሴት ልጆች ትምህርትና ጤና ላይ የነበረውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ረድቷል።

በተመሳሳይ በአማራ ወላጆች በሰጡት አስተያየት ብዙዎቹ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት በመግባታቸው ትዳር የመያዣ ዕድሜ ከፍ ብሏል። ቀደም ሲል ለሴቶችና ልጆች ብዙም ትኩረት አይሠጥም ነበር። ሀብታምና የተማረ ቤተሠብ ብቻ ነበር ልጁን ትምህርት ቤት የሚልከው። ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛትና ባህላዊ ህክምና የተለመዱና የሴት ልጆችን ትምህርት የሚያዳክሙ ልማዶች ነበሩ። "ያለዕድሜ ጋብቻና ስለትምህርት ያለው ዝቅተኛ ግንዛቤ የህዝቡ የትምህርት ደረጃ አነስተኛ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። አሁን ግን ያለዕድሜ ጋብቻ ቀርቷል" ብለዋል። ዘመናዊ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ሙሉ ፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ እንደሆነና ልጅቷ የምትፈቅደውን ሰው መርጣ ለማግባት መቻሏን በደስታ ይገልጻሉ።

የሴት ልጅ ትምህርትን በተመለከተ ትኩረቱ ልጆች ለቤተሠብ ከሚያበረክቱት ግልጋሎት ይልቅ በልጆች ደህንነት ላይ ያተኮረ ሆኖ ይታያል። ከሴት ልጆች ቤት ውስጥ የሚጠበቀው ኃላፊነትን በተመለከተ ለውጦች እየመጡ እንደሆነና ከቤተሠብ

የጋራ ፍላጎቶች ይልቅ በልጆቹ የግል ፍላጎቶቻቸው ላይ ያተኮሩ ለውጦች እንዳሉ ከተወሰኑ ቃለ-መጠይቆች መረዳት ተችሏል።

ቀደም ባሉት ክፍሎች የተጠቀሱት ስታቲስቲካላዊ መረጃዎች የትምህርት ደረጃ በጨመረ ቁጥር የሴት ልጅ ትዳር የመመስረቻ ዕድሜ እንደሚራዘምና ግርዘት የመፈጸም ዕድልም (በተለይ በወጣት ሴቶች መካከል) እንደሚቀንስ ማሳየቱ ይታወሳል። አንዳንድ መላሾች ይህ ለውጥ በሴት ልጆች በራሳቸው የዕሴት (values) እና የባህሪ ለውጥ ሳቢያ የመጣ እንደሆን ይገልፃሉ። ለዚህም አሁኑን ትውልድ ብስለትና ብልህነት በዋቢነት ይጠቅሳሉ። ለምሳሌ አንዲት ወላጅ በትግራይ የልጅ ልጇን ሁኔታ እርሷ ልጅቷን ስታክል ከነበራት ሁኔታ ጋር በማነፃፀር የዛሬ ልጆች ምን ያህል የበሠሉ እንደሆኑ በሚከተለው ሁኔታ ገልፃለች።

> እኔ በ14 ዓመቴ ነበር ያገባሁት። ያኔ ትንሽ ልጅ ነበርኩኝ። ልጆች ያለምንም ኃሳብ ለጋብቻ እንታጭ ነበር፤ ወደፊት ምን እንደሚከተል እንኳን አናውቅም ነበር። ወደ ባሎቻችን ቤት እሺ ብለን እንሄድና እዚያ ስንወድቅና ስንገረፍ እንኖራለን።

የድሮ ሴት ልጆችን ስቃይ ከዛሬ ሴት ልጆች የተሻለ የትምህርት፣ የዕውቀትና የመብት መጠበቅ ሁኔታ ጋር ታነፃፅረዋች።

> በኛ ጊዜ ባል እንድናገባ እንገደድ ነበር። ዛሬ ግን የልጅ ልጄ የ14 ዓመት ልጅ ነች። ባል አግቢ ብላት "አንቺ ራስሽ አግቢ" ነው የምትለኝ። በኛ ጊዜ በራሳችን ህይወት ላይ መወሠን አንችልም ነበር፤ ዛሬ ግን ልጆች የመወሰን መብት አላቸው። ወላጆች ከፈቃዳቸው ውጭ ሊድሯቸው ቢሞክሩ ወላጆቻቸውን ይከስሳሉ።.... የዛሬ ልጆች በጣም ብልህ ናቸው። ....[የልጅ ልጄ] ህይወቷ የተሻለ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፤ ምክንያቱም የተማረች በመሆኗ ወደፊትም የተማረ ባል ልታገባ ትችላለች። ስለዚህ ሁለቱም ጥሩ ኑሮ ይኖራሉ። ድሮ ግን ባልየው ሥራ ቢኖረው እንኳን ሚስቱን ይደበድባል፤ እርሷም ምንም አትናገርም።

በአንዳንድ የጥናቱ አካባቢዎች እንደታየው አዲስ የተፈጠረው ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ የመሠማራት ዕድል የሴት ልጆችን በራስ መተማመን ከፍ ከማድረጉ በላይ የኢኮኖሚ ነፃነት ስለፈጠረላቸው ያለዕድሜ ጋብቻንና ግርዘትን ጨምሮ በራሳቸው ጉዳይ ላይ የመወሠን አቅማቸውን ማዳበሩ ልብ ሊባል ይገባል። በአባሪ ሁለት እንደተብራራው በኦሮሚያና አማራ የጥናት አካባቢዎች በግብርና ኢንቨስትመንቶች ሥራ ላይ፤ በትግራይ ደግሞ በድንጋይ ጠረባ ኢንዱስትሪ ውስጥ ሴት ልጆች ተቀጥረው ገቢ ማግኘት መጀመራቸው የባህሪ ለውጥ እንዲያሳዩ ረድቷል። የሚቀጥለው ዙር ጥናት ደግሞ እነዚህ ዕድሎች ሴት ልጆች ያለዕድሜያቸው

በማግባትና በግርዘት ላይ የሚያደርጓቸው ውሳኔዎች ላይ በምን አይነት መንገድ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ይመለከታል፡፡

## 9 ማጠቃለያ

ይህ የጥናት ወረቀት በዓለም አቀፍ ደረጃ የህፃናት መብት ጥሠት ተድርገው የሚቆጠሩትን የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ያሉትን የተለያዩ ተፎካካሪ አመለካከቶችን ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ጥናቱ ድርጊቶቹን በተመለከተ በአገሪቱ ያሉትን እጅግ የተለያዩ ልማዶችና አፈፃፀሞችን ከመዳሠሱ ባሻገር ድርጊቶቹን ለመቀነስ የተደረገው ጥረት ያስገኘውን ለውጥ የስታቲስቲክስን ሌሎች መረጃዎችን በማጣቀስ (በከተማና በገጠር እንዲሁም በክልሎች መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም) ድርጊቶቹ እየቀነሱ መምጣታቸውን ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ልዩነቶች ቢኖሩም ድርጊቶቹን የሚፈጸምባቸው ባህላዊ መሠረቶች ተመሳሳይ መሆናቸውንም ለማየት ተችሏል፡፡ በጥናቱ የተገኙት መረጃዎች ድርጊቶቹን ከድህነት ጋር የሚያስተሳስሩትን የአዝጋሚ ለውጥ (evolutionary) እና የሐብት (materialist) ተጠይቆችን (logics) ጥያቄ ውስጥ ይከትታሉ፡፡ ከዚህ ይልቅ በመሠረቱ ድርጊቶቹ የታላላቆችና የወንዶች የበላይነት ጥምር እሴቶች (gerontocratic and patriarchal values) በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚጫኑበትን ሁኔታ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ጥናቱ ታላላቆች የሴት ልጆቻቸውን የስነ-ጾታ ባህሪ በመቆጣጠርና ማንን እንደሚያገቡ በመወሰን ቤተ-ዘመዶች በልጆቹ ስነ-ተዋልዶና (productive) የስነ-ተዋልዶ ችሎታ ላይ ያላቸውን መብት ያሳያል፡፡ እንዲሁም ይህ አመለካከት በባህል ከሴት ልጆች ደህንነት ጋር የማይጋጭና እንዲያውም የሴት ልጅ በጊዜ ትዳር መያዝና ግርዘት ማኅበራዊ ትስስራቸውን የማጥበቂያ ዘዴና የማኅበራዊና ስነ-ምግባራዊ መኮትኮቻ መንገድ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ድርጊቶቹን ለማስወገድ በመንግሥት፤ በዓለም አቀፍና አገራዊ ድርጅቶች በአድቮካሲ፣ በፖሊሲ፣ ሕግ በማውጣትና በማስከበር ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ እነዚህ ጥረቶች አመለካከትና ድርጊትን በመቀየር ረገድ ብዙ ለውጥ ማሳየታቸው በግልጽ ይታያል፡፡ መረጃዎቹ እንደሚያሳዩት በትምህርት ቤቶች የሚሠሩት ሥራዎች፣ እየጨመረ የመጣው የኢኮኖሚ ዕድልና ተያይዞ ያለው "ዘመናዊነት" በለውጡ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዘት ማኅበራዊ አቅም በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ከፍተኛ ተቃውሞዎች አጋጥመዋል፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ ድርጊቶቹን ለማስቆም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሕግ በማውጣትና በማስፈጸም በስፋት በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ተቃራኒ ውጤቶች ታይተዋል፡፡ መንግሥት በደነገገው ዝቅተኛው የትዳር መያዣ

*ዕድሜና የሴት ልጅ ግርዘትን በሚያግደው ሕግ ላይም ተቃውሞዎች ይታያሉ። የመንግሥትና የማሕበረሠብ መሪዎች በማያሻማ ሁኔታ ሁለቱንም ድርጊቶች ያወግዛሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ወላጆች፣ ወንዶችና ሴት ልጆችም በተለያዩ ምክንያቶች ድርጊቶቹን ይቃወማሉ። አንዳንድ ጊዜ ይህ አመለካከት እያደገ የመጣው ህፃናት ላይ ያተኮረ የአመለካከት መዳበር ጋር ይዛመዳል። በተለይ ሴት ልጆች የወደፊት ሕይወታቸውን በሚመለከት ውሳኔ ላይ የመሳተፍ መብትና ትምህርት የመማርና የተሻለ ሥራ የመያዝ ዕድል ሊኖራቸው ይገባል የሚለው አመለካከት እየሠፋ መጥቷል። ነገር ግን ይህ አመለካከት በተቃራኒው ሴት ልጆችን 18 ዓመት በፊት ትዳር እንዳይዙ በሕግ መከለከሉ ከትዳር በፊት የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሊጀምሩ ይችላሉ የሚል ስጋትና ጭንቀት ፈጥሯል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ልጆች በራሳቸው ጉዳይ ላይ ራሳቸው ይወስኑ የሚለው ኃሳብ ቤተሠብ ከሚያዘጋጀው ጋብቻ በተቃራኒ ሴት ልጆች ያለዕድሜያቸው ተዋድደው እንዲኮበልሉ፤ እንዲሁም የመንግሥትን ክልከላ ችላ በማለት ግርዘት እንዲፈጽሙ ሊገፋፋ ይችላል የሚል ስጋት ይደመጣል። በተመሳሳይ ሁኔታ ድርጊቶቹ እንዳይፈጸሙ ከበላይ የመጣውን ግፊትን ሕግ በመቃወም በሚመስል ሁኔታ በጠለፋ ስም ወደሚፈጸም የ”ውዴታ ጠለፋ”ና የድብቅ ግርዘት፤ ወይም ሥርዓቱ እንዳይጠፋ በማለት በትንሹ የመግረዝ ስትራቴጂዎችን አስከትሏል።*

*እነዚህን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ድርጊቶቹን ለማስቀም የሚደረጉት ይፋዊ ጥረቶች ድርጊቶቹ የሚፈጸሙበትን መሠረታዊ ምክንያት አልተረዱም ማለት ይቻላል። የተደረጉት ጥረቶች በአብዛኛው የድርጊቶቹን “ጎጂነት” ለህብረተሠቡ በማስረዳት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ለጥናቱ ያነጋገርናቸው ሰዎችም በዚህ ይስማማሉ። ነገር ግን ተጨባጭ ለውጦቹ የታሠበውን ያህል ካለመሆናቸው በላይ የሕግ ክልከላውን ለማምለጥ ሲሞክሩ ሴት ልጆች ለሌላ ያልተፈለገ አደጋ እንዲጋለጡ አድርጓል። በተለይ ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት ይሁን የሚለው በተግባር ላይ ከዋለና የደረሱ ልጆች የወሊድ መቆጣጠሪያና ያልተፈለገ እርግዝናን የማስወገድ አግልግሎት በቀላሉ የማያገኙ ከሆነ ከጋብቻ በፊት ለመውለድ አደጋ ሊጋለጡና በዚህ ሳቢያ ከቤተሠብ ሊገለሉ፤ ልጃቸውንም ያለአባት ለማሳደግ ሊገደዱ ይችላሉ። የሴት ልጅ ግርዛት በሕግ መከልከሉ ድርጊቱ በድብቅና በጨለማ እንዲደረግ በማድረግ የሚያደርሰውን የጤና አደጋ አባብሷል። ለውጡ በትውልድ መካከል እንዲያውም በቤተሠብ አባላት መካከል ግጭት እያስነሳ ለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። ወላጆችና ሴት ልጆች ግርዘትን በተመለከተ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ እሳቤዎችን ግምት ውስጥ አስገብተው በሚሠጡት ውሳኔ ላይ ለግራ መጋባትና ተቃርኖዎች ተጋልጠዋል። በተለይ ወላጆች የልጆቻቸውን ደህንነት በተመለከተ ያለዕድሜ ጋብቻ ወይም የሴት ልጅ ግርዘት በመፈጸም በሚደርሰው ጉዳትና፤ ባለመፈጸም ሊከተሉ በሚችሉትን ሌሎች አደጋዎች መካከል ሚዛን መጠበቅ ይሻሉ። ወላጆች ለልጆቻቸው በጎ በጎውን ይመኛሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙውን ጊዜ እርግጠኛ አለመሆን*

ሲታይባቸው፤ አንዳንዶም ልጆቻቸውን በጊዜ ትዳር ባለማስያዛቸው ወይም ባለማስገረዛቸው ሊከተል የሚችለውን ማኅበራዊ መዘዝ መከላከል አንችልም ብለው በማሠብ ከፍላጎታቸው ውጭ ይወስናሉ፤ ያደርጋሉም፡፡ ሴት ልጆች ከዕድሜ ጓደኞቻቸው በሚደርስባቸውን ግፊት ግምት ውስጥ ያስገባ ውሳኔ ይወስናሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ዋናው ቁም ነገር የማንኛውንም ድርጊት ዋና መሠረታዊ ምክንያትና ሊከተል የሚችለውን ያልተፈለገ አሉታዊ ውጤት በሚገባ ያላገናዘበ ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ ጥረት ውጤት የማያስገኝና እንዲያውም ተቃውሞና አሉታዊ ምላሽ የሚያመጣ መሆኑን ነው፡፡

## ዋቢ መጽሐፍት


Ahmadu, F., and R. Shweder. 2009. Disputing the myth of sexual dysfunction of circumcised women; an interview with Fumbai S. Ahmadu. Anthropology Today 25, no. 6: 14–17.

Ambatchew Abebe 1956 „Betrothal among the Säwan Amharas‟. Ethnological Society Bulletin of the Addis Ababa University College, pp. 101-8 in A. Pankhurst ed. 2002.Addis Ababa University College Ethnological Society Bulletin Reprint. Addis Ababa: Department of Sociology and Social Administration

Ambatchew Abebe et al. 1957. Fieldtrip to Nakamte. Ethnological Society Bulletin of the Addis Ababa University College, pp. 130-95 in A. Pankhurst ed. 2002.Addis Ababa University College Ethnological Society Bulletin Reprint. Addis Ababa: Department of Sociology and Social Administration.

Bauer D. 1977 Household and Society in Ethiopia. An Economic and Social Analysis of Tigray Social Principles and Household Organisation. East Lansing:Michigan State University African Studies Center.

Berhane-Selasse Tsehai. 1993. Early marriage in Ethiopia. IAC, Addis Ababa

Boddy, J. 1998. „Violence embodied? Female circumcision, gender politics, and cultural aesthetics.‟ In R.E. Dobash and R.P Dobash (Eds.), Rethinking violence against women. Thousand Oaks, CA: Sage Publications. Boyden, Pankhurst and Tafere 2012;

Braukämper, Ulrich 1983 Die Kambata. Wiesbaden: Franz Steiner Verlag

Cerulli, Ernesta 1956 Peoples of Southwest Ethiopia and its Borderland. London: International

CSAE (Central Statistical Authority Ethiopia) and ORC Macro. 2001. Ethiopia Demographic and Health Survey 2000. Addis Ababa and Calverton, MD: Central Statistical Agency and ORC Macro

CSAE and ORC Macro. 2006. Ethiopia Demographic and Health Survey 2005.Addis Ababa and Calverton, MD: Central Statistical Agency and ORC Macro.

CSAE and ORC Macro. 2012a. Ethiopia Demographic and Health Survey 2011.Draft.. Addis Ababa and Calverton, MD: Central Statistical Agency and ORC Macro

CSAE. 2012b. Ethiopia Welfare Monitoring Survey 2011.Summary Report,27 April 2012. Addis Ababa: Central Statistical Agency.

ECFE (Evangelical Churches Fellowship of Ethiopia) 2010. „Enabling Churches to address FGM and other HTPs: Declaration of Evangelical Churches against FGM", Addis Ababa, 22 January 2010.

EGLDAM 2008a. Old Beyond Imaginings: Ethiopia Harmful Traditional Practices. Second Edition. Ye Ethiopia Addis Ababa: Goji Limadawi Dirgitoch Aswogaj Mahiber (The Former National Committee for Traditional Practices in Ethiopia – NCTPE).

EGLDAM 2008b. Follow up National Survey on Harmful Traditional Practices in Ethiopia. Ye Ethiopia Addis Ababa: Goji Limadawi Dirgitoch Aswogaj Mahiber (The Former National Committee for Traditional Practices in Ethiopia – NCTPE).

EOC (Ethiopian Orthodox Church) 2010. Theological Reflection in the Teaching of the EPTC on Female Genital Mutilation. Addis Ababa: Ethiopian Orthodox Church, Norwegian Church AID Actalliance.

Hamer, J. 1987. Humane Development: Participation and Change among the Sadama of Ethiopia. Tuscaloosa: University of Alabama Press.

Hoben A. 1973 Land Tenure among the Amhara of Ethiopia: the Dynamics of Cognatic Descent. Chicago: University of Chicago Press.

Holcomb, B. 1973 „Oromo marriage in Wallaga Province Ethiopia" Journal of Ethiopian Studies 11 (1): 107-42.

Huntingford, George W. (1955) The Galla of Ethiopia. The Kingdoms of Kafa and Janjero. London: International African Institute.

Jain, S. and K. Kurz. 2007. „New Insights on Preventing Child Marriage: A Global Analysis of Factors and Programs" International Center for Research on Women. http://www.icrw.org/files/publications/New-Insights-on-Preventing-Child-Marriage.pdf

Kane, T. 1990. Amharic- English Dictionary. Wiesbaden: Otto Harrassowitz.

Malhotra, A. and A. Tsui. 1996."Marriage Timing in Sri Lanka: The Role of Modern Norms and Ideas." Journal of Marriage and Family 58(2): 476–490

Mensch, B.S., J. Bruce, and M.E. Greene. 1998. The Uncharted Passage: Girls‟ Adolescence in the Developing World. Population Council: New York http://www.popcouncil.org/pdfs/passage/passage.pdf

Morison, L., C. Scherf, G. Ekpo, K. Pain, B. West, R. Coleman, and G. Walraven. 2001. The long-term reproductive health consequences of female genital cutting in rural Gambia: A community-based survey. Tropical Medicine and International Health 6: 643–53.

Obermeyer, C. 1999. Female genital surgeries: the known, the unknown, and the unknowable. Medical Anthropology Quarterly 13: 79–106.

Obermeyer, C. 2005. Female genital surgeries: the known, the unknown, and the unknowable. MedicalvAnthropology Quarterly New Series 13 no. 17: 79–106.

Pankhurst, A 2003. „Dimensions and conceptions of marginalisation‟, in Dena Freeman and Alula Pankhurst eds. Peripheral People: Ethiopia‟s Excluded Minorities. London: Hurst.

Shack, W. 1966. The Gurage: a People of the Ensete Culture. Oxford: Oxford University Press.

Shack, W. 1974 The Central Ethiopians: Amhara, Tigriña and Related Peoples. London: International African Institute

Shell-Duncan, B. 2008.From health to human rights .American Anthropologist 1110, no. 2: 225–36.

Singh, S. and R. Samara. 1996. „Early Marriage among Women in Developing Countries.‟ International Family Planning Perspectives. Vol. 22 Issue 4: 148-158

Teferra, S. and L. Gebremedhin. 2010a. „Summary: Gender and social exclusion in Ethiopia‟ (consultancy report)

Tippet. A. 1970. Peoples of South-West Ethiopia. South Pasadena: William Carey.

UNICEF. 2005. „Early Marriage: A Harmful Traditional Practice: A Statistical Exploration.‟ http://www.unicef.org/publications/files/Early_Marriage_12.lo.pdf

Wedajo, Kifle 1953. „Wedding customs among the Amhara‟ Ethnological Society Bulletin of the Addis Ababa University College, in A. Pankhurst ed. 2002. Addis Ababa University College Ethnological Society Bulletin Reprint. Addis Ababa: Department of Sociology and Social Administration.

World Health Organisation. 2010. „Female genital mutilation. WHO Fact Sheet Number 241: February 2010‟ http://www.who.int/mediacentre/factsheets/fs241/en/

# የሥራ ፍልሠትና የሰዎች ዝውውር በኢትዮጵያ፡- ወደ ደቡብ አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ የሚደረጉ የሥራ ፍልሠቶች ምልከታ

አስናቀ ከፋለ እና ዘሪሁን መሐመድ

## 1 መግቢያ

ፍልሠት ሠዎች በቡድንም ሆነ በነጠላ በቋሚነት ከሚኖሩበት አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ በቋሚነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ ለመኖር የሚያደርጉት ጉዞ ፍልሠት ሊባል ይችላል፡፡ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ፍልሠትን በተለያዩ መስፈርቶች ይከፋፍሉታል፣ በጊዜ (የአጭር እና የረጅም ጊዜ)፣ በመዳረሻ ስፍራ (የአገር ውስጥና የውጭ)፣ በአካባቢ (የገጠር እና የከተማ)፣ በምክንያት (የፈቃደኝነትና የግዴታ)፡፡ ፍልሠት ጥንታዊ ሁነት ከመሆኑ ባሻገር ዛሬ ዓለም ለምትገኝበት ፖለቲካዊ፣ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጉልህ ሚናና አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ለምሳሌ እንደ የተ.መ.ድ የልማት ፕሮግራም መረጃ እ.ኤ.አ በ2009 ዓ.ም የዓለም የፍልሠት መጠን 3% የደረሠ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የአህጉራችን አፍሪካ ድርሻ 1.9 በመቶ ገደማ ነበር፡፡

ፍልሠት በአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ልማት ውስጥ አዎንታዊም አሉታዊም ጐኖች እንዳሉት የታመነ ነው፡፡ የሥራና የትምህርት ዕድል፣ የልምድ ልውውጥ፣ የህዝቦች መቀራረብና የባህል ልውውጥ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የውጭ የምንዛሪ ገቢ ብዙውን ጊዜ በአዎንታ የሚጠቀሱ የፍልሠት ውጤቶች ናቸው፡፡ በተቃራኒው የተማረ የሠው ኃይል መመናመን፣ የሠብዓዊ መብት ጥሠት፣ ሕገ-ወጥ የሠው አዘዋዋሪዎች መበራከት፣ በላኪና በተቀባይ ሕዝቦች መካከል የሚከሠት ግጭትና ጭፍን ጥላቻ የስደት አሉታዊ ጎኖች ተደርገው ይጠቀሳሉ፡፡

የፍልሠትን ሁኔታ በአገራችን ስንመለከት ፍልሠት በተለይም የውጭ ሀገር ፍልሠት በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዜጐች በግለሠብ ደረጃም ሆነ በቡድን ከአካባቢያቸው ወደ ሌላ ስፍራ ሲጓዙና የሌላ አገር ዜጐችም በፍልሠት ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ መኖራቸውን የታሪክ ድርሣናት ያሳያሉ፡፡ በኢትዮጵያ ታላላቅ ኃይማኖቶች በሆኑት በኦርቶዶክስ ክርስትና እና እስልምና ትውፊቶችና አስተምህሮቶዎች ውስጥ ፍልሠትን (በመፍለስም ሆነ በተቀባይነት) እናገኛለን፡፡ በኦርቶዶክስ ክርስትና ትውፊት ውስጥ የአክሱም ንግስት የነበረችው ንግስት ሳባ አያሌ ባለሟሎቿንና ተከታዮቿን አስከትላ ወደ እየሩሳሌም መጓዟን በኋላም ልጇ ቀዳማዊ

ምኒልክ የሙሴ ፅላት ከእየሩሳሌም እንዳመጣ ይተረካል። በተመሳሳይ ሁኔታ በ4ኛው ክፍለ ዘመን እስልምና በመካ አካባቢ ሲስፋፋ ከወገኖቻቸው ከፍተኛ ተቃውሞ የደረሠባቸው ሙስሊሞች በነብዩ መሀመድ ምክርና ትዕዛዝ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡና ለተወሰኑ ዓመታት እንደኖሩ ቅዱስ ቁርአን ያስተምራል። ይኸውም በኃማኖቱ ተከታዮች የመጀመሪያው ሂጅራ (ስደት) በመባል ሲታወስ ይኖራል።

በመካከለኛውና የቅርብ ጊዜ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥም የሕዝብ ፍልሠቶችና በተለያዩ አቅጣጫዎች ተካሂደዋል። ከጣልያን ወረራ (1928 ዓ.ም) ወዲህ ያለው ጊዜ ላይ ብቻ ትኩረት ብናደርግ ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገራት የተካሄደውን ፍልሠት የቅድመ-አብዮት፣ የደርግ ዘመን እና የድሕረ-ደርግ በማለት በሦስት ዋና ዋና ክፍለ-ጊዜዎች መክፈል ይቻላል።

የቅድመ-አብዮት ክፍለ ጊዜ የሚሸፍነው የአፄ ኃይለስላሴ አገዛዝ ዘመን ሲሆን በዚህ ጊዜ የባህር ማዶ ጉዞ ቀስ በቀስ እየተስፋፋ የመጣበት ወቅት ሆኖ እናገኘዋለን። በተለይም 1950ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ፍልሠት ቀስ በቀስ እየጨመረ የመጣ ሲሆን ከአገር የሚወጡት በአመዛኙ ወጣቶችና ምክንያቱም የከፍተኛ ትምህርት ቀስሞ ወደ አገር ለመመለስ ነበር። ለውጭ ትምርት የሚጓዙት ወጣት ኢትዮጵያዊያን በአብዛኛው መዳረሻቸው አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ነበሩ። ከትምህርት በተጨማሪ በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን ሙስሊምና ክርስትያኖች ለፀሎት ወደ መካ እና ወደ እየሩሳሌም ጉዞ ያደርጉ ነበር። ለፀሎት የሚጓዙት በዕድሜ ከፍ ያሉና በኢኮኖሚም ከብዙሃኑ የተሻለ አቋም የነበራቸው ነበሩ። በዚህ ወቅት የሥራ ፍልሠት በሠው አገር ሠርቶ ለመኖር ወይም ኃብት አፍርቶ ለመመለስ የሚደረግ ጉዞ እጅግ በጣም ውስን ነበረ።

ሁለተኛው ክፍለ ጊዜ የደርግ የሥልጣን ዘመናትን (1966-1983) የሚያካትት ሲሆን፣ በዚህ ወቅት የመገናኛ አውታሮች የተስፋፉበት በአገሪቱም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦች በከፍተኛ ደረጃ የተስተዋሉበት ነበር። የ1966 አብዮትና የመንግሥት ለውጥ ጋር ተያይዞ በቀጠለው ደም ያፋሰሰ የፖለቲካ ትግልና ሽኩቻ ሳቢያ ስደት እጅግ የተስፋፋበት ወቅትም ነበር። በሠፈነው የፖለቲካ አለመረጋጋትና ወታደራዊው መንግሥትም በተቃዋሚዎቹ ላይ በወሰደው እርምጃ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን ድንበር አቋርጠው ወደ ጐረቤት አገሮች ተሠድደዋል፤ የቀናቸውም ወደ ሠሜን አሜሪካ፣ አውሮፓና በተወሠነ መልኩ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች አምርተው ኑሮአቸውን መስርተዋል።

በሌላ በኩል ይህ ወቅት የሥራ ፍልሠት በተለይም ወደ አረብ አገራት በተለያዩ ሽፋኖች ብቅ ያለበት ዘመን ነው። በተለይ በዚህ ክፍል ወደኂላ በስፋት እንደምንመለከተው በሀጅና ዑምራ ፀሎት ከለላ ወደ ሳዑዲ አረቢያ የሥራ ጉዞ ከ1960ዎቹ መጨረሻ አመታት ጀምሮ መታየት ጀመረ። ነገር ግን በዚህ ወቅት

የደርግ መንግሥት የመዘዋወር መብትን (በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ) የገደበ፣ ከአገር መውጣትን በአሉታዊነት የሚመለከት ፖሊሲ ይከተል ስለነበር ከአገር መውጣት አጅግ ከባድ እንደነበር ይታወቃል።

ከደርግ መንግሥት መውደቅ ወዲህ ያሉትን ዓመታት የሚሸፍነው ሦስተኛው ክፍለ ጊዜ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት ፍልሠትን በተመለከተ ከቀደመው ጊዜ የተለዩ መሠረታዊ የሆኑ ለውጦች የታዩበት ወቅት ነው። በዋነኛነት የሚጠቀሠው ለውጥም በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) የሚመራው መንግሥት የዜጐች በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የመንቀሳቀስ መብትን የሚደነግጉ ህጎችን ያወጣበትና መብቱም የተከበረበት መሆኑ ነው። ነገር ግን የደርግ መንግሥት መውደቅና የሠራዊቱን መበተን ተከትሎ ብዛት ያለው ኢትዮጵያዊ ወደ ጐረቤት አገራት በስደት ለመጓዝ ተገድዶ ነበር። በሌላ በኩል በተለይ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ የሥራ ፍልሠት ወደተለያዩ የመካከለኛው ምሥራቅ አገራት የሚደረግ ጉዞው የተጀመረው በዚሁ ጊዜ መሆኑ ይታወቃል።

ከላይ በአጭሩ የተብራራውን የኢትዮጵያ የፍልሠት ታሪክን እንደመነሻ በመጠቀም የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ ወጣቶች በስፋት የሚሳተፉበትን የሥራ ፍልሠት መዳሰስ ነው። በዚህም በአብዛኛው ወጣቶች በሚሳተፉበትን በዋነኝነት ወደ አረብ አገራትና ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረጉ የሥራ ፍልሠቶች መንሥኤዎች፣ ጉዳቶች፣ ጥቅሞችና አስተዳደር ላይ ትኩረት ያደርጋል። በተጨማሪም መንግሥት የሥራ ፍልሠትን ለማስተዳደርና ሕገ-ወጥ ፍልሠትን ለመቆጣጠር እየወሰደ ያለውንም ዕርምጃ ጥንካሬና ድክመት ለመዳሰስ ይሞክራል። ምንም እንኳን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስደተኞችን ግልፅና ሁሉንም በሚያስማማ መልኩ በንደፈ-ኃሳብና በተግባር መለየት አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በዚህ ጽሑፍ ስደተኛ ከሚለው ቃል ይልቅ የሥራ ፈላሲ የሚለው ቃል ወደ አረብ አገራትና ደቡብ አፍሪካ የሚሄዱትን ሠዎች ይገልፃል በሚል ዕሳቤ ቃሉን ተጠቅመናል።

መረጃን በተመለከተ የዚህ ዕሁፍ አቅቢዎች የሥራ ፍልሠትን በተመለከተ ካደረጉት ሠፋ ያለ ጥናት በተለይም በደቡብና ሰሜን ወሎ፣ አርሲና ባሌ፣ ከምባታ፣ ሐዲያና ሀላባ ካደረጉት የመስክ ጥናት የተገኙ መረጃዎች ተካተዋል።

## 2 ዓለም አቀፍ የሥራ ፍልሠት በኢትዮጵያ

ከላይ በጥቂቱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከአጠቃላይ የአገሪቱ የፍልሠት ታሪክ በተቃራኒ የሥራ ፍልሠት በአገራችን ረጅም ታሪክ አለው ለማለት አይቻልም። በአጠቃላይ ስንመለከት የሥራ ፍልሠት ከሐጅና ዑምራ የጸሎት ጉዞ ጋር ተያይዞ በ1960ቹ መጨረሻና በተለይም 1970ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት እንደተጀመረ

ይነገራል። በነዚህ ጊዜያት ኢትዮጵያውያን ሴቶች በጸሎት ሠበብ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ከገቡ በኋላ የመኖሪያና የመሥሪያ ፈቃድ ሳያገኙ በአገሪቱ ውስጥ በቤት ሠራተኛነት መሥራት በጥቂቱ እንደጀመሩ ይነገራል። ነገር ግን በዚህ ወቅትም ቢሆን ወደ መካከለኛው ምስራቅ ለሥራ የሚጓዙ ሠዎች ቁጥር በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ አነስተኛ ነበር። ከነዚህም ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

የደርግ መንግሥት የመዘዋወርንና የዕምነት መብቶችን መገደብ፤

- በወቅቱ ለሐጅና ኡምራ ጸሎት ከኢትዮጵያ የሚጓዘው መዕምን ኮታ ውስን መሆን፣
- ለጸሎት ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለመጓዝ አመልካቹ በትክክል ሙስሊምና አማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ በሳውዲ ኤምባሲ ቪዛ አሰጣጥ ሂደት ላይ የነበረ የቃል ፈተናና ቁጥጥርና
- ሴቶች የሐጅና ዑምራ ጸሎት ለማድረግ ከቅርብ የቤተሠብ አባላት ማለትም ባለቤት፣ ልጅ፣ ወንድም ወይም አባት ጋር ካልሆነ ለብቻቸው መጓዝን የሚከለክለው ኃይማኖታዊ ድንጋጌና ከቤተሠብ አባላት ጋር አብሮ መሄድ የሚያስከትለው ከፍተኛ የጉዞ ወጪ ናቸው፡

በአሁኑ ጊዜ የሥራ ፍልሠት በተለይ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እጅግ ተስፋፍቶ ይገኛል። በብዙ መቶ ሺ የሚገመቱ በአብዛኛው ወጣት ሴቶች ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በሕጋዊም ሆነ ሕገ-ወጥ መንገድ ተጉዘው አብዛኛዎቹ በቤት ሠራተኛነት ተሠማርተው ይገኛሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ በአስር ሺዎቹ የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን ወደ ደቡብ አፍሪካ በአመዛኙ በሕገ-ወጥ መንገድ ገብተው ኑሯቸውን በመግፋት ላይ መሆናቸው ይታወቃል።

ከ1983 ወዲህ የሥራ ፍልሠት በኢትዮጵያ እየተስፋፋ ለመምጣቱ አስተዋፅኦ ያደረጉ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው ውስጣዊ ምክንያት ከደርግ መንግሥት መውደቅ በኋላ የተከበረው የዜጐች የመንቀሳቀስ መብት ነው። በዚህም የመብቱን መከበር ተከትሎ ዜጐች ካለምንምን ቅድመ ሁኔታ እንደ ፓስፖርት፣ የልደትና የጋብቻ ሠርተፍኬት የመሳሰሉ የማንነት ሠነዶችን በማግኘታቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በ«ሕጋዊም» ሆነ በሕገ-ወጥ መንገድ ከአገር ለመውጣት ችለዋል።

ሁለተኛውና ለሥራ ፍልሠት መስፋፋት አመቺ ሁኔታ የፈጠረው ውጫዊ ምክንያት ኢትዮጵያውያን የሥራ ፈላሲዎች በዋነኝነት በሚያመሩባቸው አገራት የተፈጠሩ የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ለውጦች ናቸው። ከነዚህ መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው በነዳጅ ዘይት በበለጸጉ አንዳንድ አረብ አገራት የተፈጠረው ከፍተኛ የሠው ኃይል (በተለይም

የቤት ሠራተኛ) ፍላጐት ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ በስፋት እንደምንመለከተው በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ ሥርዓት መደምሰስ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው አመቺ ሁኔታ አያሌ ኢትዮጵያውያን ወደ አገሪቱ እንዲፈልሱ አበረታትቷል።

## 3 የሥራ ፍልሠት/ሥምሪት በአረብ አገራት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ የሥራ ፍልሠት ታሪክ ሲዳሰስ የመካከለኛው ምሥራቅ እና የአረብ አገራት በዋና መዳረሻነት ይነሳሉ። አገሪቱ ከእነዚህ አገራት ጋር ካላት ጂኦግራፊያዊ ቅርበት፣ የታሪክና የኃይማኖት ትስስር ሳቢያ እንዲሁም በእነዚህ አገሮች በተፈጠሩት ምቹ ሁኔታዎች ምክንያት ካለፉት ጥቂት አስርተ ዓመታት ጀምሮ አያሌ ኢትዮጵያውያን እንጀራ ፍለጋ ወደ አረብ አገሮች (በተለይ ወደ ሳዑዲ አረቢያ) በብዛት መጓዝ መጀመራቸው ይታወቃል።

በሌላ በኩል ያለፉትን አራት አስርተ ዓመታት ወደኂላ ሄደን ብንመለከት ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ባሉ አገራት በተፈጠሩት የውስጥ የፖለቲካ ቀውሶችና ግጭቶች ሳቢያ በክልሉ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለስደትና ለመፈናቀል ተዳርገዋል። ከፖለቲካ ግጭትና ትርምስ በተጨማሪ ድርቅና ረሀብ፣ የአካባቢ መጎሳቀል እና ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ይኸውም የሚያስከትለው ከፍተኛ የወጣት ሥራ አጥነት ስደትን በክልሉ አባብሠውታል።

በአገራችንም በተለይ በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ ዓመታት የተፈጠሩት የፖለቲካ ብጥብጦች በአስር ሺዎች የሚገመቱ ዜጎችን ለስደት ዳርጓል። በእነዚህ ዓመታት ምንም እንኳን አያሌ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ምክንያቶች በአብዛኛው በሕገ-ወጥ መንገድ ከአገር ቢሠደዱም፤ ከአገሪቱ በሥራ ምክንያት የሚፈልሠው ሠው ብዛት ከጠቅላላው ስደተኛ ቁጥር ውስጥ ድርሻው አነስተኛ ነበር። በጊዜው ሥልጣን ላይ የነበረው የደርግ መንግሥት የሥራ ፍልሠትን ማገዱ ለሥራ ፍልሠት አነስተኛነት ዋናው ምክንያት ነበር። በ1983 ዓ.ም የደርግ መውደቅና የኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን መምጣትን ተከቶሎ ዕገዳው በመነሳቱ ከአገሪቱ የሚወጣውን የሥራ ፈላሲ ቁጥር እጅግ ሊጨምር ችሏል።

ከኢትዮጵያ ወደ አረብ አገሮች የሚደረገውን የቅርብ ዓመታት የሥራ ፍልሠት ታሪክ በሶስት ጊዜያት ከፋፍሎ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ፍልሠቱ በሚገባ መታየት ከጀመረበት 1960ዎቹ መጨረሻ ዓመታት እስከ የደርግ መውደቅ ድረስ (1983 ዓ.ም) ያለው ጊዜ ነው። ከላይ እንደተገለፀው በእነዚህ ዓመታት የሥራ ፈላሲያን ከአገር የሚወጡት የሐጅና ዑምራ ፀሎትን ሠበብ በማድረግ ሲሆን ዋና መዳረሻቸውም ሳዑዲ አረቢያ ነበረች። ሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ከደርግ መውደቅ አንስቶ

እስከ 1990/91 ዓ.ም ያሉትን ዓመታት ያካትታል:: በእነዚህ ዓመታት ሊባኖስ የአብዛኛዎቹ ወደ አረብ አገራት የሚፈልሡ ሴት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች መዳረሻ ሆና ቆይታለች:: ምንም እንኳን በእነዚህ ዓመታት ምን ያህል ኢትዮጵያዊ የሥራ ፈላሲ ወደዚያች አገር እንደፈለሰ የሚያሳይ አስተማማኝ መረጃ ባይኖርም የፍሠት መጠኑ ከዓመት ወደ ዓመት መጨመሩን የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ:: ለምሳሌ አንድ መረጃ በእ.ኤ.አ. በ1996 ዓ.ም 23 ብቻ የነበሩት ወደ ሊባኖስ ለሥራ የሄዱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በ1998/99 ወደ 413 ማደጉን ያሳያል (Yosheph, et al., 2007):: ሌሎች ጥናቶች ደግሞ እ.ኤ.አ. በ2000 ዓ.ም በሊባኖስ በሺዎቹ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በቤት ሠራተኛነት ተሰማርተው እንደነበር ይገምታሉ[1]:: በዚህ ክፍለ ጊዜ ያለው የሥራ ፍልሠት የሕግና የተቋማት ድጋፍ ባልነበረበት፣ የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች በሌሉበት የሚካሄድና፣ ቀደም ሲል በሄዱ የሥራ ፈላሲያን፣ በጉዞ ወኪሎች እንዲሁም በአስመጪና ላኪ ንግድ ዘርፍ በተሠማሩ ድርጅቶች አማካይነት ሥርዓት ባለነበረው ሁኔታ የሚካሄድ ነበር:: በዚህ ክፍለ ጊዜ የተጓዙት ሴት ፈላሲያን በአብዛኛው የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ የከተማ ልጆች ነበሩ::

የሶስተኛው ክፍለ ጊዜ ከ1990/91 እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ያሉትን ዓመታት ያካትታል:: በዚህ ክፍለ ጊዜ የተለያዩ ለውጦች የተካሄዱ ሲሆን በተለይም ሴት የቤት ሠራተኞች ዋና መዳረሻ የነበረችው ሊባኖስ በሳዑዲ አረቢያ ተተክታለች:: ለዚህ ዋናው ምክንያት በሳዑዲ አረቢያና ቀደም ሲል ለዚያች አገር የቤት ሠራተኛ በብዛት ያቀርቡ በነበሩ እንደ ኢንዶኔዢያና ፊሊፒንስ ባሉ አገራት መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ሳቢያ አገራቱ ዜጎቻቸው ወደ ሳዑዲ አረቢያ እንዳይሄዱ በማገዳቸውና ኢትዮጵያም የተፈጠረውን ክፍተት እንድትሞላ የቀረበላትን ጥያቄ በመቀበሏ ነበር::

ኢንዶኔዢያ በሠኔ 2003 ዓ.ም አሠሪዋን ገድለች የተባለች ዜጋው አንገቷ ተቀልቶ በሞት እንድትቀጣ መደረጉን ተከትሎ ዜጎቿ ወደዚያች አገር በቤት ሠራተኛነት እንደይሄዱ ከለከለች:: የፊሊፒንስ መንግሥትም በሳዑዲ አረቢያ በቤት ሠራተኛነት የሚሠሩ ዜጎቹ በሚከፈላቸው ዝቅተኛ ክፍያና በሚደርስባቸው የመብት ረገጣና ዕንግልት ሳቢያ ወደዚያች አገር የሚደረግ የሥራ ፍልሠትን አገደ:: እነዚህ ቀደም ሲል የቤት ሠራተኛ ለሳዑዲ አረቢያ በገፍ ያቀርቡ የነበሩ አገራት ውሳኔን ተከትሎ በሳዑዲ አረቢያ የተፈጠረውን የቤት ሠራተኛ ክፍተት ለመሙላት የሳዑዲ አረቢያ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄ አቀረበ::

---

[1]አል ሐያት የተባለው የሊባኖስ ጋዜጣ በእ.ኤ.አ 1999 በሊባኖስ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሴት የቤት ሠራተኞችን ብዛት በ17,000 ሲገምት፤ በ2002 በየወሩ በሺ የሚቆጠሩ ተጨማሪ ፈላሲያን በልዩ ልዩ መንገድ ወደአገሪቱ ይገባሉ ሲል አትቷል። ኢትዮጵያውያን አጥኚዎች ደግሞ በወቅቱ በአገሪቱ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ፈላሲያን ቁጥር በ25 ሺ እና በ30 ሺ መካከል ገምተውታል (Yoseph *et al.* 2007)።

የኢትዮጵያ መንግሥትም እነዚህ አገራት ዜጎቻቸው ወደዚያች አገር እንዳይሄዱ የወሠኑበትን ምክንያት በቅጡ ሳይመረምርና በሁለቱ አገራት መካከል የጋራ የሠራተኛ ልውውጥ ስምምነት (bilateral labour exchange agreement) እንኳን ሳይፈረም ለሳዑዲ አረቢያ መንግሥት ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሰጠ። በዚህም የቤት ሠራተኛ ወደ ሳዑዲ አረቢያ የመላኩ ሂደት በሳውዲና የኢትዮጵያ ግል የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች ማህበራት ስር ወደቀ። ቀድሞውንም ቢሆን የሥራ ፍልሠትን ለማስተዳደር በቂ አቅምና ዝግጅት ያልነበረው የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን ሥርዓት ያልያዘና ድንገት የፈነዳ የሥራ ፍልሠትን የመምራትና የማስተዳደር ከባድ ኃላፊነት ወደቀበት።

በሳዑዲ አረቢያ የቤት ሠራተኛነት ‹‹ዕድል›› የመምጣቱ ዜና በአገሪቱ ከዳር እስከዳር ተነዛ። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ይህ ‹‹ዕድል›› እንዳያመልጣቸው ፓስፖርት ለማውጣት በተለያዩ የአገሪቷ ክልሎች በሚገኙ የኢሚግሬሽን ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ደጅ ተኮለኮሉ። ከዚህ ‹‹በረከት›› የድርሻቸውን ለማግኘት የሚሹት የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎችም ደላሎቻቸውን እስከ ገጠር ቀበሌ ድረስ አሠማሩ። ደላሎቹም ወጣቶቹ በሳዑዲ አረቢያ ስለሚጠብቃቸው ‹‹በረከት›› በሚያማልሉ ቃላት መስበክ ቀጠሉ። ይህ የደላሎች ስብከት ቀደም ሲል ወደውጭ አገር በቤት ሠራተኛነት ሄደው ትንሽ ጥሪትና ብልጭልጭ ነገሮች ይዘው በመጡ አንዳንድ ተመላሾች ‹‹ምሳሌነት›› ታጅቦ አያሌ ወጣቶችን አነሳሳ። በዚህም ከ2001 እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት ወደ ውጭ አገር ለቤት ሠራተኛነት የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ቁጥር እጅግ አሻቀበ። ከነዚህ ተጓዦች መካከል ሴቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። ቀጥሎ የተመለከተው ሠንጠረዥ ከ2001- 2005 ዓ.ም ድረስ በሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር ተመዝግበው ወደተለያዩ የአረብ አገራት የተጓዙትን ዜጎችና ከእነርሱም መካከል የሴቶቹን ብዛት በመቶኛ ያሳያል።

**ሠንጠረዥ 1፡** ከ2001 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ በሠ/ማ/ጉ ሚኒስቴር ተመዝግበው ወደተለያዩ አገራት የተጓዙ የሥራ ፈላሲያን

| ዓ.ም | 2001 | | 2002 | | 2003 | | 2004 | | 2005* | | የ5 ዓመት ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመዳረሻ አገር | ተጓዥ ብዛት በቁጥር | የሴቶች ብዛት በመቶኛ | ተጓዥ ብዛት በቁጥር | የሴቶች ብዛት በመቶኛ | ተጓዥ ብዛት በቁጥር | የሴቶች ብዛት በመቶኛ | ተጓዥ ብዛት በቁጥር | የሴቶች ብዛት በመቶኛ | ተጓዥ ብዛት በቁጥር | የሴቶች ብዛት በመቶኛ | ተጓዥ ብዛት በቁጥር | የሴቶች ብዛት በመቶኛ |
| ሳዑዲ አረቢያ | 13,148 | 71.5 | 3,477 | 68.9 | 15,476 | 86.9 | 169,300 | 93.9 | 98,359 | 94.2 | 29,9760 | 92.4 |
| ኩዌት | 7,079 | 98.5 | 11,158 | 97.1 | 26,120 | 97.5 | 28,746 | 99.1 | 11,519 | 99.3 | 84,622 | 98.3 |
| ዱባይ | 122 | 92.6 | 143 | 99.3 | 510 | 100.0 | 430 | 74.7 | 0 | | 1,205 | 90.1 |
| ሌሎች | 919 | 98.5 | 167 | 11.4 | 127 | 90.6 | 191 | 91.6 | 70 | 84.3 | 1,474 | 86.4 |
| **ድምር** | **21,268** | **81.8** | **14,945** | **89.6** | **42,233** | **93.6** | **198,667** | **94.6** | **109,947** | **94.8** | **38,7061** | **93.6** |

(ምንጭ፡ የሠ/ማ/ጉ ሚኒስቴር)

**ሠንጠረዥ 2፡** በሠ/ማ/ጉ ሚኒስቴር ተመዝግበው ወደተለያዩ አገራት የተጓዙ የሥራ ፈላሲያን በመጡበት ክልል ዝርዝር

| ዓ.ም | 2001 | | 2002 | | 2003 | | 2004 | | 2005 | | **ጠቅላላ** | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ክልል | ድምር | ሴት | ድምር | ሴት | ድምር | ሴት | ድምር | ሴት | ድምር | ሴት | ድምር | ሴት |
| ትግራይ | 1,412 | 949 | 704 | 573 | 1,866 | 1,582 | 9,869 | 8,592 | 5624 | 4966 | 19,475 | 16,662 |
| አፋር | 183 | 35 | 84 | 31 | 165 | 139 | 919 | 611 | 436 | 375 | 1,787 | 1,191 |
| አማራ | 4,530 | 3,551 | 2,213 | 1,952 | 11,311 | 10,769 | 66,298 | 62,836 | 36,135 | 33,831 | 120,487 | 112,939 |
| ኦሮሚያ | 4,244 | 3,600 | 2,982 | 2,757 | 10,852 | 10,430 | 66,851 | 64,431 | 40,605 | 39,185 | 125,534 | 120,403 |
| ደ/ብ/ብ/ህ | 2,498 | 1,981 | 1,417 | 1,300 | 4,990 | 4,547 | 24,319 | 23,392 | 14,141 | 13,813 | 47,365 | 45,033 |
| አዲስ አበባ | 8,370 | 7,251 | 7,480 | 6,860 | 12,782 | 11,813 | 29,009 | 26,774 | 12,402 | 11,472 | 70,043 | 64,170 |
| ጋምቤላ | 0 | 0 | 0 | 0 | 14 | 12 | 52 | 50 | 20 | 17 | 86 | 79 |
| ድሬዳዋ | 10 | 8 | 38 | 34 | 171 | 162 | 825 | 764 | 276 | 272 | 1,320 | 1,240 |
| ሀረሪ | 16 | 15 | 15 | 12 | 17 | 15 | 121 | 111 | 66 | 64 | 235 | 217 |
| ሶማሌ | 5 | 5 | 12 | 10 | 18 | 16 | 48 | 41 | 27 | 27 | 110 | 99 |
| በኒሻ.ጉ. | 0 | | 1 | | 47 | 45 | 356 | 338 | 215 | 194 | 619 | 577 |
| **አገራዊ** | **21,268** | **17,395** | **14,946** | **13,529** | **42,233** | **39,530** | **198,667** | **187,940** | **109,947** | **104,216** | **387,061** | **362,610** |

*የ2005 ዓ.ም መረጃ ከሐምሌ እስከ የካቲት 12 2005 ድረስ ያለውን ብቻ የሚያካትት ነው፡፡

(ምንጭ፡- ሠ/ማ/ጉ/ሚ)

**ሠንጠረዥ 3:** <u>በሠ/ማ/ጉ ሚኒስቴር ተመዝግበው ወደተለያዩ አገራት የተጓዙ የሥራ ፈላሲያን ከጠቅላለው የክልሉ ህዝብ ጋር ሲነፃፀሩ</u>

| ዓ.ም/ | ክልል | ትግ. | አፋር | አማራ | ኦሮሚያ | ደ/ህ | አ.አበባ | ጋምቤላ | ድሬ. | ሐረሪ | ሱማሌ | ቤኒ.ሻ. | አገራዊ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2001 | የፍልሠት መጠን | 1,412 | 183 | 4,530 | 4,244 | 2,498 | 8,370 | 0 | 10 | 16 | 5 | 0 | 21,268 |
| | ከጠቅላላው ህዝብ ብዛት በ% | 0.03 | 0.012 | 0.025 | 0.015 | 0.016 | 0.290 | 0.000 | 0.003 | 0.008 | 0.000 | 0.000 | 0.027 |
| | ከ18-35 ዓመት ካለው ህዝብ ብዛት በ% | 0.21 | 0.085 | 0.161 | 0.097 | 0.097 | 1.158 | 0.000 | 0.013 | 0.042 | 0.001 | 0.000 | 0.173 |
| 2002 | የፍልሠት መጠን | 704 | 84 | 2,213 | 2,982 | 1,417 | 7,480 | 0 | 38 | 15 | 12 | 1 | 14,946 |
| | ከጠቅላላው ህዝብ ብዛት በ% | 0.015 | 0.006 | 0.012 | 0.010 | 0.009 | 0.253 | 0.000 | 0.010 | 0.008 | 0.000 | 0.000 | 0.019 |
| | ከ18-35 ዓመት ካለው ህዝብ ብዛት በ% | 0.105 | 0.038 | 0.077 | 0.066 | 0.054 | 1.008 | 0.000 | 0.050 | 0.038 | 0.002 | 0.001 | 0.118 |
| 2003 | የፍልሠት መጠን | 1,866 | 165 | 11,311 | 10,852 | 4,990 | 12,782 | 14 | 171 | 17 | 18 | 47 | 42,233 |
| | ከጠቅላላው ህዝብ ብዛት በ% | 0.039 | 0.011 | 0.059 | 0.036 | 0.030 | 0.421 | 0.004 | 0.045 | 0.008 | 0.000 | 0.006 | 0.052 |
| | ከ18-35 ዓመት ካለው ህዝብ ብዛት በ% | 0.270 | 0.072 | 0.383 | 0.234 | 0.185 | 1.679 | 0.022 | 0.218 | 0.042 | 0.003 | 0.037 | 0.326 |
| 2004 | የፍልሠት መጠን | 9,869 | 919 | 66,298 | 66,851 | 24319 | 29,009 | 52 | 825 | 121 | 48 | 356 | 198,667 |
| | ከጠቅላላው ህዝብ ብዛት በ% | 0.201 | 0.057 | 0.339 | 0.217 | 0.142 | 0.932 | 0.015 | 0.212 | 0.058 | 0.001 | 0.047 | 0.237 |
| | ከ18-35 ዓመት ካለው ህዝብ ብዛት በ% | 1.393 | 0.394 | 2.186 | 1.408 | 0.878 | 3.715 | 0.078 | 1.024 | 0.292 | 0.007 | 0.271 | 1.493 |
| 2005 | የፍልሠት መጠን | 5,624 | 436 | 36135 | 40605 | 14141 | 12,402 | 20 | 276 | 66 | 27 | 215 | 109,947 |
| | ከጠቅላላው ህዝብ ብዛት በ% | 0.112 | 0.026 | 0.180 | 0.128 | 0.081 | 0.388 | 0.006 | 0.069 | 0.031 | 0.001 | 0.027 | 0.128 |
| | ከ18-35 ዓመት ካለው ህዝብ ብዛት በ% | 0.774 | 0.182 | 1.161 | 0.833 | 0.498 | 1.548 | 0.029 | 0.334 | 0.155 | 0.004 | 0.160 | 0.805 |
| 2001-2005 | የፍልሠት መጠን | 19,475 | 1787 | 120487 | 125534 | 47365 | 70,043 | 86 | 1320 | 235 | 110 | 619 | 38,7061 |
| | በ2005 ካለው ጠቅላላው ህዝብ ብዛት በ% | 0.387 | 0.109 | 0.600 | 0.396 | 0.270 | 2.193 | 0.024 | 0.330 | 0.110 | 0.002 | 0.079 | 0.449 |
| | በ2005 ከ18-35 ዓመት ካለው ህዝብ ብዛት በ% | 2.680 | 0.746 | 3.872 | 2.576 | 1.668 | 8.742 | 0.126 | 1.597 | 0.553 | 0.015 | 0.459 | 2.834 |

(ምንጭ:- ሠ/ማ/ጉ/ሚ)

## 3.1 የፍልሠት መንገዶች

ወደ አረብ አገራት የሚደረገው ፍልሠት በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ይካሄዳል- ሕጋዊና ሕገ-ወጥ መንገዶች። ሕጋዊ የፍልሠት መንገድ የሚባለው መንግሥት ያወጣውን መስፈርት አሟልተውና በሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር ተመዝግበው የሚጓዙበት ሂደት ሲሆን፤ ሕገ-ወጥ የሚባለው ደግሞ ምዝገባ ሳያካሂዱ በተለያዩ ሠበቦችና የጉዞ መንገዶች የሚሄዱበት ሁኔታ ነው።

ሕጋዊው የሥራ ፍልሠት በራሱ በሁለት ዓይነት ሁኔታ ይካሄዳል። የመጀመሪያው በፈላሲኑ በራሳቸው የሚካሄድ ሲሆን በውጭ አገር የሥራ ዕድል ካገኙ በኋላ የሥራ ኮንትራታቸውን በመያዝ ፈቃድ እንዲሠጣቸውና እንዲመዘገቡ ለሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር ያመለክታሉ። የሚ/ር መስሪያ ቤቱ ኮንትራቱ ሕጋዊ ሁኔታዎችን ማሟላቱን በማረጋገጥ ፈቃድ ይሠጣል፤ይመዘግባል። ነገር ግን አንዳንድ ሕጋዊ የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች አንዳንድ ሠዎች በሕገ-ወጥ የሥራ አገናኞችና ደላሎች የውጭ አገር የሥራ ዕድል አግኝተው በግላቸው ያገኙ አስመስለው ከሚ/ር መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ይወስዳሉ በማለት ቅሬታቸውን ይገልፃሉ። ሁለተኛው ሕጋዊ የውጭ አገር ሥራ የማግኛ መንገድ በሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች አማካይነት የሚካሄድ ሲሆን፤ ኢጀንሲዎቹ ውጭ አገር ካለው የሥራ ሸርካቸው ጋር በመሆን የሥራ ዕድል በማምጣት ወደ ውጭ አገር ለሥራ ለመሄድ ለሚፈልግ ሠው ያመቻቻሉ። የሥራ ዕድሉና ኮንትራቱ በሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር መጽደቅና መመዝገብ ይኖርበታል።

በሌላ በኩል አያሌ ፈላሲያን መንግሥት ያወጣውን ፎርማሊቲዎች ሳያሟሉና አንዳንዶቹ ፓስፖርት እንኳን ሳይዙ በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር በማሳበር በየብስና በባህር ወደ አረብ አገራት ይጓዛሉ። ሕገ-ወጥ ፍልሠት በበኩሉ ፈላሲያን እንደሚጓጓዙበት መጓጓዣና የመውጫ በር በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው በተለያዩ ምክንያቶች (ጉብኝት፣ ህክምና፣ ትምህርት...) ሠበብ ሕጋዊ ፓስፖርትና የሚሄዱበትን አገር የመግቢያ ቪዛ በመያዝ የሚደረግ የሥራ ፍልሠት ነው። በዚህ ረገድ መንግሥት ዜጎች ለቤት ሠራተኛነት እንዳይጓዙ ወደከለከለባቸው እንደ ሊባኖስ የመሳሰሉት አገራት ሳይቀር ሠዎች በተለያዩ ሠበቦች ለቤት ሠራተኛነት ይጓዛሉ። አንዳንዴም ወደጎረቤት አገራት በሕጋዊ መንገድ በአየር በመጓዝና ትራንዚት በማድረግ ለሥራ መሄድ ወደሚፈልጉበት አገር ያመራሉ። በጋራ ስምምነት የተነሳ ኢትዮጵያውያን የመግቢያ ቪዛ የማይጠየቁባት ኬንያ ለዚህ ዓይነት ጉዞ ዋና መሸጋገሪያ እንደሆነች ይነገራል።

ሁለተኛው ሕገ-ወጥ የሥራ ፍልሠት ዓይነት ደግሞ በየብስና በባህር ላይ የሚደረገው አደገኛው የጉዞ መንገድ ነው። በዚህ ጉዞ ፈላሲያን ወደ አቅራቢያቸው የድንበር ከተማ በሕገ-ወጥ አስተላላፊዎች አማካይነት ከተጓዙ በኋላ ድንበርን በእግራቸው በማሳበር

ጎረቤት አገር ይገባሉ:: በዚህ ረገድ ጅቡቲ፣ በርበራና (ሶማሌ ላንድ) እና ቦሳሶ (ፑንት ላንድ) ዋና መሸጋገሪያ የጎረቤት አገር ወደቦች ናቸው:: ከዚያም ደህንነታቸው በማያስተማምን የተጨናነቁ አነስተኛ ጀልባዎች በባህር ላይ በመጓዝ የመን ይገባሉ:: በዚህ የጉዞ መስመር ሕገ-ወጥ አስተላላፊዎች በፈላሲኑ ላይ ከፍተኛ እንግልት እንደሚያደርሱባቸውና የባህር ላይ አደጋም በተደጋጋሚ እንደሚደርስ በስፋት ይዘገባል:: በሕገ-ወጥ አስተላላፊዎች ታግተው አገር ቤት ከሚገኙ ቤተሠቦቻቸው ገንዘብ እንዲያስልኩ ከመገደድ አንስቶ የመደብደብ፣ የመደፈርና የመገደል አሰቃቂ ዜናዎች በተደጋጋሚ በታዋቂ በዜና ማሠራጫዎች ሳይቀር ቢደመጥም በሕገ-ወጥ መንገድ የሚጓዙትን ሠዎች ቁጥር አልቀነሠውም:: ለምሳሌ የተ.መ.ድ. የሥደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) መረጃ እንደሚያሳየው በእ.ኤ.አ በ2010 በዚህ መንገድ የመን የደረሱ ኢትዮጵያውያን ብዛት 35 ሺ ያህል የነበረ ሲሆን ይህ አኃዝ በአመቱ በእጥፍ በላይ አድጓል:: ይህንን የፍልሠት መንገድ ለየት የሚያደርገው ልዩ ባህሪው በሕጋዊ መንገድም ሆነ በሕገ-ወጥ መንገድ በአየር ከሚጓዙት በተቃራኒ አብዛኛዎቹ የባህር ላይ ፈላሲያን ወንዶች መሆናቸው ነው:: ወንዶች ይበልጥ ድንበርን በሕገ-ወጥ መንገድ በመሻገር የሚፈልሱበት ዋና ምክንያት በውጭ አገር የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች አማካኝነት ለወንዶች የሚሆን ሥራ በሕጋዊ መንገድ ብዙ ጊዜ ስለማይገኝ እንደሆነ ይነገራል::

**ሠንጠረዥ 4:** <u>በሕገ-ወጥ መንገድ የመን የደረሡ ኢትዮጵያውያንና የሌላ አገር ዜጎች ብዛት (እ.ኤ.አ 2010-2013)</u>

| ዓ.ም (እ.ኤ.አ) | የመነሻ አገር (ዜግነት) | | | ድምር | የሞቱ ወይም የጠፉ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ኢትዮጵያውያን | ሶማሌያውያን | ሌሎች | | |
| 2010 | 34,422 | 18,855 | 105 | 53,382 | 15 |
| 2011 | 75,651 | 27,350 | 153 | 103,154 | 131 |
| 2012 | 84,376 | 23,086 | 70 | 107,532 | 43 |
| 2013* | 53,941 | 10,867 | 61 | 64,869 | 5 |

*እስከ እ.ኤ.አ ኖቬምበር ወር 2013 ያለውን ብቻ ያጠቃልላል::

(ምንጭ፡- UNCHR, 2013)

ሕገ-ወጥ ፈላሲያኖቹ የመን ከደረሱ በኂላ አብዛኛዎቹ ጉዟቸውን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ይቀጥላሉ:: በዚህም የመን መሸጋገሪ እንጂ ዋና መዳረሻ አለመሆኗን መረዳት ይቻላል:: በየመን በኩል አሳብረው ወደ ሳዑዲ አረቢያ የሚገቡትን ሕገ-ወጥ ፈላሲያንን ብዛት የሚያሳይ መረጃ የለም:: ነገር ግን አብዛኛዎቹ ወንድ ፈላሲያን በኮንስትራክሽን፣

በጉልበት ሥራ፣ በእርሻ፣ በግመልና ፍየል ጥበቃና ሌሎች መሠል ሥራዎች እንደሚሠማሩ ይታወቃል።

የሳዑዲ አረቢያ መንግሥት ከየመን ጋር የሚያዋስነውን የ1,800 ኪ.ሜትር የጋራ ድንበር በመስከረም 2006 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ በማጠር ከኢትዮጵያና ሌሎች አገራት በሕገ-ወጥ መንገድ በየመን በኩል ወደአገሩ የሚገቡትን ሕገ-ወጥ ፈላሲያን ለመቆጣጠር ጥረት ቢያደርግም፤ የሙከራው ውጤታማነት ጥርጣሬ ላይ የሚጥሉ ፍንጮች መታየት ጀምረዋል። አንዳንድ መረጃዎች እንደሚገልጹት ሕገ-ወጥ አስተላላፊዎች ድንበር ጠባቂዎችን በገንዘብ በመደለል ሕገ-ወጥ ፈላሲያንን ከወዲሁ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ማስገባት ጀምረዋል (BBC, 2013)።

## 3.2 የሥራ ሁኔታና የመብት ጥሠት

ዓለም አቀፍ የሥራ ፍልሠት በላኪና በተቀባይ አገራት እንዲሁም በፈላሲዎቹ ላይ የሚያደርሰው አሉታዊና አዎንታዊ ጎኖች እንዳሉት ይታወቃል። ነገር ግን በሥራ ፍልሠት በሚደርሠው ችግር ይበልጥ ተጠቂ የሚሆኑት የሥራ ፈላሲዎቹ እንደሆኑ ልዩ ልዩ ጥናቶች ያሳያሉ። ያልተመቻቸ የሥራና የኑሮ ሁኔታ፣ ከሥራ ጋር ያልተመጣጠነ አነስተኛ ክፍያ፣ ለጤና የማያመች የሥራ አካባቢ፣ የማኅበራዊ ዋስትና አለመኖር፣ የመደራጀት መብት መነፈግ፣ ጭፍን የዘረኝነት ጥላቻና ጥቃት ዋና ዋና የሥራ ፈላሲያን ችግሮች ሆነው ይጠቀሳሉ (ILO, 2010)። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሥራ ፈላሲ በሕገ-ወጥ መንገድ የሚሄድና የሚሠራ መሆኑ ደግሞ ችግሩን ዕጥፍ ድርብ ያደርገዋል።

የሥራ ፈላሲያንን መብቶች ለማስከበር የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጥረቶች ተደርገዋል። የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) በተለያዩ ጊዜያት ካወጣቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተጨማሪ የተ.መ.ድ. እ.ኤ.አ. በ1990 ዓ.ም ‹‹የዓለም አቀፍ የሥራ ፈላሲያንና ቤተሠቦቻቸውን ጥበቃ ኮንቬንሽን>>[2] አጽድቋል። ስምምነቱ ከእ.ኤ.አ. ሐምሌ 2003 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን እንደ ፊሊፒንስ፣ ሜክሲኮና ኢንዶኔዢያ የመሳሰሉ ከፍተኛ የሥራ ፈላሲ ላኪ አገራት ተቀብለው ፈርመውታል። በአንፃሩ ከፍተኛ የሥራ ፈላሲ ተቀባይ የሆኑት እንደ አሜሪካ፣ የአውሮፓ ህብረት አባል አገራትና የገልፍ አገራት ስምምነቱን ገና አልፈረሙም።

በእ.ኤ.አ. በ2011 የቤት ሠራተኞች እንደማንኛውም በሌላ የሥራ ዘርፍ የተሠማራ ሠራተኛ መብቶቻቸው ይከበሩላቸዋል የሚል ዓለም አቀፍ ስምምነት ቢፀድቅም ስምምነቱን እስካሁን 13 አገራት ብቻ (ቦሊቪያ፣ ኢኳዶች፣ ጀርመን፣ ጉያና፣

[2] Convention on the Protection of the Rights of All Migrant Workers and the Families - ICRMW)

ጣልያን፣ ሞሪሽስ፣ ኒካራጓ፣ ፊሊፒንስ፣ ደቡብ አፍሪካና ዑራጋይ) ተቀብለው ፈርመውታል። ከፍተኛ የሥራ ፈላሲ ተቀባይ የሆኑት የገልፍ አገራት ግን ገና ስምምነቱን ለመቀበል ፈቃደኝነታቸውን አላሳዩም። ነገር ግን አንዳንድ የዚህ ክልል አገራት በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደርስባቸው ግፊት ሳቢያ የውስጥ ሕጎቻቸውን ለማጤንና ለሥራ ፈላሲያን የተሻለ ጥበቃ የሚሰጥ ሁኔታ ለመፍጠር በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

ከዚህ በተጨማሪ የተመድ ሕገ-ወጥ የሠዎች ዝውውርን ለመግታት ያለመውን የፓሌርሞ ኮንቬንሽን እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን አውጥቷል። በተለይ የፓርሌሞ ኮንቬንሽን ኢትዮጵያና የገልፍ አገራትን ጨምሮ በበርካታ አገራት ተፈርሞ በመጽደቁ ሥራ ላይ ውሏል።

እነዚህ ሁሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እያሉና እነዚህ ሁሉ ጥረቶች እየተደረጉ የሥራ ፈላሲያን (በተለይ የቤት ውስጥ ሠራተኞች) ከፍተኛ በደልና መብት ረገጣ ይደርስባቸዋል። አብዛኞዎቹ የገልፍ አገራት የሥራ ፈላሲያንን መብቶች ለማስከበር የወጡትን ዓለም አቀፍ ስምነቶች ለመቀበልና በውስጥ ህጎቻቸው ውስጥ ለማካተት ፈቃደኛነታቸውን አላሳዩም (HRW, 2008)። በአብዛኛዎቹ አገራት የተዘረጋው ‹‹ከፋላ›› (ወኪል) የተባለው የሥራ ፈላሲ አስተዳደር ሥርዓት ፈላሲያን በአሠሪዎቻቸው ቁጥጥር ስር እንዲውሉ የሚያደርግ ነው። በዚህ ሥርዓት ከፍተኛ ሙያ የማይጠያቁ ሥራዎች ላይ የሚሠማሩ የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ሠራተኞች (unskilled labourers) የዚያን አገር ቪዛ ለማግኘት፣ ለመኖርና ለመስራት የአገሪቷ ዜጋ የሆነ አንድ ተያዥ (sponser) እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ሕግ ሲሆን ተያዡ ለውጭ አገር ዜጋው ሕጋዊ ተቆጣጣሪና ኃላፊ ይሆናል። በአብዛኛው ጊዜ ተያዥ የሚሆኑት አሠሪዎቹ በመሆናቸው ይህንን ‹‹የሕግ›› ድጋፍ በመመርኮዝ አሠሪዎች የሠራተኞችን ፓስፖርት ከመቀማትና እንቅስቃሴያቸውን ከመቆጣጠር አልፎ ባሻቸው ምክንያትና ጊዜ ከአገር እንዲወጡ የማድረግ ሥልጣን አላቸው[3]። በዚህ ሳቢያ በሌሎች የሥራ መስኮች ከተሠማሩት ጋር ሲነፃፀር የቤት ውስጥ ሠራተኞች (ከሌሎች በጉልበት ሥራ ላይ ከተሠማሩት ጋር በመሆን) ለበለጠ ጥቃትና መብት ረገጣ የተጋለጡ ናቸው። ይህ ሂደት የሥራ ፈላሲያን ተቀባይ የሆኑ የአረብ አገራት መንግሥታት በጉልበት ሥራ ላይ ለተሠማሩ የውጭ አገር ዜጎች የሕግ ጠለላ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ያሳያል።

---

[3] ባሕሬን እ.ኤ.አ 2009 የከፋላ ሥርዓትን ያስወገደች ብቸኛዋ የገልፍ አገር ሆናለች። በሌላ በኩል ኳታር እ.ኤ.አ. በ2022 ለሚካሄደው የዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ ሲባል በሚደረጉት ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ግንባታ ሥራዎች ውስጥ በሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች ላይ በሚፈጸሙ የመብት ረገጣዎች ምክንያት በደረሰባት ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ግፊትና ተቃውሞ ሳቢያ የከፋላ ሥርዓትን ለማሻሻል ቃል ብትገባም እስከአሁን ምንም ለውጥ አላሳየችም።

በሁለተኛ ደረጃ እነዚህ የሥራ ፈላሲያን ተቀባይ አገራት መንግሥታት ሕግ ቢያወጡና የቤት ሠራተኞችን መብቶች ለማረጋገጥ ቢፈልጉ እንኳን የቤት ሠራተኞች በግል መኖሪያ ቤቶች የሚሠሩ በመሆናቸው የግለሠቦች ቤት ዘልቆ ለመግባት የሕግና የባህል ችግርና ክልከላ ያጋጥማል። በዚህ ረገድ የግል ነፃነት መብቶች ተከብረውባቸዋል፤ የቤት ሠራተኞችን የመብት ረገጣ ለማስወገድ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ይታይባቸዋል በሚባሉት አገራት ሳይቀር ይህን መሠሉን የቤት ውስጥ መብት ረገጣ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሲሆን ይስተዋላል (Bales, 2012)።

በሶስተኛ ደረጃ በአብዛኞዎቹ የአረብ አገራት የቤት ሠራተኞችን በዜግነታቸውና በመጡበት አገር ላይ ተንተርሶ ማኅበራዊ ደረጃቸውን የሚወስን ዘረኛ ሥርት ተዘርግቷል። በዚህም ሥርዓት ኢትዮጵያውን የቤት ሠራተኞች ዝቅተኛ ክፍያ ከሚያገኙት መካከል ይመደባሉ። ከክፍያ አድሎ በተጨማሪ ከደሀ አገራት የሚመጡ የቤት ሠራተኞችን ምንም ሠብዓዊ መብትና እንክብካቤ የማያስፈልጋቸው ‹‹ባርያዎች›› አድርጎ የመቁጠር ሥሜት በህብረተሠቡ ውስጥ ሠፍኗል።

ሌላው ሴት የቤት ሠራተኞች መብታቸውን በሕግ እንዳያስከብሩ ከፍተኛ መሠናክል የሚሆነው በብዙ የአረብ አገራት (በተለይ በሳዑዲ አረቢያ) ሴቶች በኃይማኖታዊና ባህላዊ ምክንያት የሚደርስባቸው ተጽዕኖ ነው። በነዚህ ድርብርብ ምክንያቶች ሳቢያ በአረብ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የቤት ሠራተኞች ከፍተኛ የመብት ረገጣ ይደርስባቸዋል። አንዳዶቹም የከፋ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸው ቤተሠብን መርዳት ቀርቶ ወደ አገራቸው ተመልሠው ለቤተሠብ ተጨማሪ ሸክም ለመሆን ይገደዳሉ።

### 3.3 የ2006 ዓ.ም የሥራ ፈላሲያን ሠቆቃ በሳዑዲ አረቢያ

በሕጋዊ መንገድ ከአገር የወጡ የሥራ ፈላሲያን የሥራ ሁኔታና የመብት ረገጣ እንዳለ ሆኖ የሕገ-ወጥ ፈላሲን ሠቆቃና ችግር የበለጠና የተወሳሰበ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው አብዛኞዎቹ ወደ ሳዑዲ አረቢያ የሚፈልሱ ሥራ ፈላጊ ወንዶች በሕገ-ወጥ መንገድ የሚሄዱና በአገሪቱም ያለምንም ፈቃድ የሚኖሩና የሚሠሩ በመሆናቸው ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ። የሳዑዲ አረቢያ መንግሥትም በየጊዜው የሚያደርገው ሕገ-ወጥ ሠራተኞችን በጅምላ የማባረር ዕርምጃ የከፋ ሰብዓዊ ችግሮችን ሲያስከትል ይታያል። ለምሳሌም ያህል በቅርቡ የሆነውን በአጭሩ ማየት ተገቢ ነው።

የሳዑዲ መንግሥት በአገሪቱ የሚኖሩ ሕገ-ወጥ ያላቸውን ስደተኞች (ሠራተኞች) እስከ እ.ኤ.አ ህዳር 4 ቀን 2013 ድረስ ሕጋዊ የመኖሪያ/የሥራ ሠነድ እንዲይዙ ወይም ከአገር እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ ሠጠ። የተባለው ቀነ-ገደብ ከማለቁ በፊት በሳዑዲ

አረቢያ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ፈላሲዎች ያላቸው እንደ ባንግላዴሽ፣ ሕንድ፣ ፊሊፒንስ፣ ፓኪስታንና የመን የመሳሰሉ አገራት ሳዑዲ አረቢያ መንግሥትን ማስጠንቀቂያ ከባድነት በመረዳት ዜጎቻቸው ወደ አገራቸው የሚመለሱበትን መንገዶች አመቻቹ:: በዚህም ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ የሌሎች አገራት ዜጎች ከሳዑዲ አረቢያ ወጡ:: ነገር ግን ቀደም ሲል የተሠጡ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያዎችን ተከትሎ የተወሠደ ምንም እርምጃ ባለመኖሩ አሁንም ምንም አይመጣም በማለት አያሌ ሕጋዊ ፈቃድ የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ‹‹ዕድል እንዳደረገችን እንሆናለን›› በማለት ሳይወጡ ቀሩ:: ስለማስጠንቀቂያውና ስለሚያስከትለው መዘዝ ብዙም ትኩረት ያልሠጠው የኢትዮጵያ መንግሥትም እንደ ስደተኞቹ ሁሉ ይህ ነው የሚባል እርምጃ ሳይወስድ ቀረ::

በሳዑዲ አረቢያ የመገናኛ ብዙሀንም የስደተኞችን መጥፎ ጎኖች የሚጎላና በአገሪቱ ላሉት ማኅበራዊ ችግሮች ሁሉ ስደተኞች ምክንያት እንደሆኑ አድርጎ የሚያቀርብ ዘመቻ ተከፈተ:: የተባለው ቀነ-ገደብ ማለቅን ተከትሎ የሳዑዲ አረቢያ መንግሥት ሕጋዊ ፈቃድ የላቸውም ባላቸው ስደተኞች ላይ ጭካኔ የተሞላበት እርምጃዎችን መውሰድ ጀመረ:: ፖሊሶች ኢትዮጵያን ስደተኞች በብዛት ይገኙባቸዋል በሚባሉት በጂዳ፤ ሪያድና መሠል ከተሞች ከበባ አድርገው ብዛት ያላቸው ስደተኞችን በቂ መሠረታዊ አገልግሎቶች እንኳን በሌሉባቸው የማጎሪያ ስፍራዎች አጎሯቸው:: በዚህ የማሳደድ ዘመቻ ላይ ከመንግሥት በተጨማሪ ሌሎች የተደራጁ ወጣቶች ሳይቀሩ እንደተሳተፉ ይነገራል:: በዚህም አያሌ ኢትዮጵያውያን ተደበደቡ፣ ተደፈሩ፣ ተገደሉም::

ሳዑዲ አረቢያ መንግሥት ዕርምጃ ዱብ ዕዳ የሆነበት የኢትዮጵያ መንግሥት ምላሽ ዘገምተኛ ነበር:: በመጀመሪያ ደረጃ በመንግሥት በኩል የችግሩ ደረጃና መጠን በሚገባ ግንዛቤ አላገኘም ነበር:: ለምሳሌ በወቅቱ አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን በሳዑዲ አረቢያ መንግሥት እርምጃ ተጎጂ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ብዛትን በ30 ሺ ገምተው ነበር:: ይህ ቁጥር በኋላ የችግሩ ሠለባ የሆኑትንና በዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (International Organization for Migraiton - IOM) እርዳታ ወደ አገራቸው ከተመለሱት 160 ሺ ስደተኞች ጋር ሲነፃጸር ግምቱ ምን ያህል በበቂ መረጃ ላይ ያልተመሠረተ እንደነበር መገመት ይቻላል:: የተመላሾች ሁኔታን ከማመቻቸት በተጨማሪ በዲፕሎማሲው መስክ በሳዑዲ አረቢያ መንግሥት ላይ ግፊት ለማድረግ የተደረገው ጥረትም ውስን ነበር:: አዲስ አበባ የሚገኘውን የሳዑዲ አረቢያ አምባሳደር ወደ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ጠርቶ ከማነጋገር ያለፈ ኦፊሴላዊ መግለጫ እንኳን አልተሠጠም:: በዚህ ረገድ መንግሥት ከሳዑዲ አረቢያ ጋር ያለውን ግንኙነት በስደተኞች ምክንያት ችግር ላይ ለመጣል የፈለገ አይመስልም::

በሳዑዲ አረቢያ መንግሥት እርምጃ በአጠቃላይ 160,000 ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት እርዳታ ወደ አገራቸው ሲመለሱ፤ አብዛኛዎቹ ተመላሾች ያላቸውን ንብረት ተነጥቀውና ምንም ጥሪት ሳይዙ የተመለሱ በመሆናቸው ሌላ የችግር ምዕራፍ ‹‹ሀ›› ብለው ለመጀምር ተገድደዋል፡፡ እነዚህ ተመላሾች ይህንን ችግር እንዴት እንቋቋሙትና ከህብረተሠቡ ጋር በዘለቄታ እንዴት እንደሚዋሀዱ ወደፊት የሚታይ ጉዳይ ይሆናል፡፡

## 4 የሥራ ፍልሠት ወደ ደቡብ አፍሪካ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከአረብ አገራት በመቀጠል የኢትዮጵያውያን የሥራ ፈላሲያን መዳረሻ ከሆኑት አገሮች አንዷ ደቡብ አፍሪካ ሆናለች፡፡ በብዙ አስር ሺ የሚቆጠሩ ዜጐች ዛሬም ድረስ በተለያዩ መንገዶች ወደ አገሪቷ በመግባት ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያውያና የሌሎች የአፍሪካ አገራት ዜጎች በብዛት ወደ ደቡብ አፍረካ ማምራት የጀመሩት ከ1983 ወዲህ እንደሆነ ይታውቃል፡፡

በ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ወዲህ ብዛት ያለው ኢትዮጵያዊ ወደ ደቡብ አፍሪካ እንዲፈልስ ምክንያት የሆኑት በአገር (ኢትዮጵያ) ውስጥ እና በተቀባዩ ደቡብ አፍሪካ የደረሱ የፖለቲካ ለውጦች ናቸው፡፡ በአገር ውስጥ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የደርግ መንግሥት መውደቅን ተከትሎ በተወሰደው የፖሊሲ ለውጥ የዜጐች የመዘዋወር መብት መከበር ወደ ደቡብ አፍሪካና ወደሌሎች አገሮች ለሚደረገው ፍልሠት በር ከፍቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከደርግ ወድቀት በኂላ ብዛት ያለው ሠው በተለይ የሠራዊት አባላትና የደርግ ፖለቲካ ባለስልጣናት ወደ ጐረቤት አገራት ተሠድደዋል፡፡ ከነዚህ መካከል አብዛኛዎቹ ወደ ኬንያ መሄዳቸው ይታወሳል፡፡ እነዚህ ስደተኞች ኬንያን እንደመነሻ በመጠቀም ወደተለያዩ አገራት ሲሄዱ የተወሰኑት ደቡብ አፍሪካ እንደገቡ ይነገራል፡፡

በዘር መድልዎ ላይ የተመሠረተው የአፓርታይድ ስርዓት መገርሠስን ተከትሎ ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት የሚመጡ ፈላሲያን ሊደርስባቸው ይችል የነበረው መድልዎና ጭቆና ከመቅረቱ በላይ አገሪቱ ለስደተኞች ቀና የሆነ ፖሊሲ መከተሏ አያሌ እንጀራ ፈላጊ የተለያዩ አገራት ዜጎች ወደዚያች አገር እንዲሳቡ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አገሪቱ ከናይጄሪያ በመቀጠል በአፍሪካ ጠንካራ ኢኮኖሚ ያላት አገር በመሆኗ ለሥራ ፈላጊዎች ፈላሲዎች ከፍተኛ የሥራ ዕድል መፍጠር አስችሏታል፡፡

በሌላ በኩል ደቡብ አፍሪካ በሠፋፊ እርሻዎችና በማዕድን ማውጫዎች በጉልበት ሥራ ለመሠማራት ከጐረቤት አገራት የሚመጡ ፈላሲ ሠራተኞች የማስተናገድ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላትና ለፈላሲያን እንግዳ ያልሆነች አገር መሆኗ ወደዚያች አገር የሚደረገውን ፍልሠት አጠናክሮታል፡፡


ለአብዛኛዎቹ ሕገ-ወጥ ፈላሲያን ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመጓዝ የመጀመሪያ መዳረሻቸው ኬንያ ስትሆን ፓስፖርት በቀላሉ ከማውጣት ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል የሁለቱ አገር ዜጐች ቪዛ ሳያስፈልጋቸው ከአንዱ አገር ወደ ሌላው እንዲጓጓዙ የተፈራረሙት ስምምነት ወደ ደቡብ አፍሪካ ለሚደረገው ፍልሠት አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል። እነዚህ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን ፍልሠት እጅግ አስፋፍተውታል። በዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት የተደረገ አንድ ጥናት እ.ኤ.አ በ2009 በደቡብ አፍሪካ ከ45,000 እስከ 55,000 ድረስ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን እንደሚገኙ ይገምታል (Horwood, 2009)።

## 4.1 የፍልሠት መንገዶች

ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረጉ ፍልሠቶች በአብዛኛው ዓለም አቀፍ ድንበሮችን በልዩ ልዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች በሕገ-ወጥ መንገድ በማቋረጥ የሚደረጉ ናቸው። እጅግ በጣም ውሱን ቁጥር ያላቸው ልዩ ልዩ ሕጋዊ ሽፋኖችን (ጉብኝት፣ ንግድ፣ ህክምና የመሳሰሉትን) በመጠቀም በሕጋዊ መንገድ ይጓዛሉ።


በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በደቡብ አፍሪካ በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ቢገኙም አብዛኛዎቹ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ የላቸውም። ለምሳሌ ያህል በእ.ኤ.አ. 2011 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ የሥራ ፈቃድ ከተሠጣቸው 1,364 ሠዎች መካከል 110 ብቻ ኢትዮጵያውያን የነበሩ ሲሆን በተመሳሳይ ወቅት በአገሪቱ የስደተኝነት ፈቃድ ካገኙት 1,664 አመልካቾች መካከል የኢትዮጵያውያን ድርሻ 17% ሆኖ ተገኝቷል።

**ምስል1፡** <u>እ.ኤ.አ. 2011 በደቡብ አፍሪካ የንግድ ፈቃድ የተሠጣቸው ሠዎች ብዛትና የኢትዮጵያውያን ድርሻ በመቶኛ</u>




(ምንጭ፡-Documented immigrants in South Africa, 2011፡ 31)

**ምስል2፡** <u>እ.ኤ.አ. 2011 በደቡብ አፍሪካ የስደተኝነት ፈቃድ የተሠጣቸው ሠዎች ብዛትና የኢትዮጵያውያን ድርሻ በመቶኛ</u>





(ምንጭ፡-Documented immigrants in South Africa, 2011፡ 42)

ከላይ በምስሎቹ እንደተመለከተው ምንም እንኳን በደቡብ አፍሪካ ከሚገኘው ጠቅላላ ኢትዮጵያዊ መካከል ድርሻቸው እጅግ ጥቂት ቢሆንም የተወሠኑት በንግድና በስደተኝነት የመኖሪያ ፈቃድ አግኝተው በሕጋዊ መንገድ የሚኖሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

ምንም እንኳን በየጊዜው የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመጓዝ በሚሞክሩ ሠዎች ላይ የሚደርሱት አሠቃቂ አደጋዎች በስፋት ቢዘገቡም፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን (በተለይ ከደቡቡ የአገሪቱ ክፍል) ወደዚያች አገር አሁንም በመፍለስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረግ ፍልሠት ሕገ-ወጥና በስውር የሚፈፀም በመሆኑ በየዓመቱ ምን ያህል ሠው እንደሚጓዝ ለማወቅ አዳጋች ነው፡፡ ነገር ግን ፍልሠቱ ከዓመት ወደ ዓመት እጅግ እየጨመረ ለመምጣቱ አመላካች መረጃዎች አሉ፡፡ በደቡብ ብሔር ብሔረሠቦች ሕዝቦች በሀዲያ እና በከምባታ-ጠንባሮ ዞኖች በሚገኙ ወረዳዎች በሕገ-ወጥ መንገድ ከአገር የወጡ ዜጎችን ዝርዝር ለማሠባሰብ የተደረገው የመረጃ ጥናት ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ፍልሠት በአሳሳቢ ሁኔታ እየጨመረ እንደሚገኝ ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ያህል ቀጥሎ በሚገኘው ምስል እንደሚታየው በሀዲያ ዞን የግቤ ወረዳ ወደ ደቡብ አፍሪካ የተጓዙ ሠዎችን ብዛት ከተለያዩ መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት የተሠበሠበው መረጃ እንደሚያሳየው ድርጊቱ በተለይ ከ2000ዓ.ም ወዲህ እጅግ እየተስፋፋ መምጣቱን መረዳት ተችሏል፡፡

**ምስል 4፡** ከ1992-2004 ድረስ ከሀዲያ ዞን ግቤ ወረዳ ወደ ደቡብ አፍሪካ የተጓዙ ሠዎች ብዛት




(ምንጭ፡ በደ/ብ/ብ/ህ/ ክልል፣ በሀዲያ ዞን የጊቤ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ)

ከላይ የተጠቀሠው መረጃ በቀበሌ ገበሬ ማኀበራት በኩል የተሠበሠበና መረጃ ሠጪዎቹ ሕገ-ወጥ ፍልሠትን በተመለከተ ሙሉ መረጃ ሠጥተዋል ተብሎ ባይገመትም የሕገ-ወጥ ፍልሠቱ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ለመምጣቱ አመላካች ነው።


ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ሕገ-ወጥ ፍልሠት በሁለት አበይት መንገዶች ይካሄዳል። የመጀመሪያው የየብስ/የእግር መንገድ ሲሆን ፈላሲዎቹ በሕገ-ወጥ አስተላላፊዎች አማካይነት የበርካታ አገራትን ድንበሮች በእግርና በተሽከርካሪዎች አቆራርጠው ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚያመሩበት ነው። ይህ የፍልሠት መንገድ ብዙ ቀናት ብሎም ወራትን የሚፈጅ፣ አድካሚና አደገኛ ሲሆን ብዙ ተጓዦች በተለያዩ ምክንያቶች ያሰቡበት ሳይደረሱ መንገድ የሚቀሩበት አጋጣሚዎችም መከሰታቸው የተለመደ ነው። የዚህ መንገድ መነሻ በአብዛኛው የኢትዮጵያ የድንበር ከተማ ሞያሌ ሲሆን፣ ተጓዦቹ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ማላዊ/ሞዛምቢክ፣ ዚምባብዌን በየብስና በባህር (ሐይቆችን) በማቆራረጥ ደቡብ አፍሪካ ያመራሉ።

የየብስ/የእግር የፍልሠት መንገድ በጠንካራ የአስተላላፊዎች መረብ አማካይነት የሚካሄድ ሲሆን ከመነሻ ያሉት ደላሎች ፈላሲዎቹን በነጠላና በአነስተኛ ቡድን (ከ2 እስከ 6 ሠው) በማድረግ ወደ ድንበር ከተማ በማጓጓዝ እንዲከማቹ ያደርጋሉ። ከዚያም ድንበር በማሳበር ለማጓጓዝ በቂ ናቸው ብለው የሚገምቱት ሠው ያህል (ከ8-20 ሠው) እንዳገኙና ሁኔታዎች እንደተመቻቹላቸው ኬንያ ውስጥ ባሉ ተባባሪዎቻቸው አማካይነት ወደ ኬንያ (ብዙ ጊዜ ወደ ናይሮቢ) በአብዛኛው በጭነት መኪናዎች በድብቅ እንዲጓጓዙ ያደርጋሉ። በናይሮቢ ወይም መሠል ከተማ አመቺ ጊዜና ማጓጓዣ እስከሚያገኙ ሸሽገው ካቆዩዋቸው በኋላ ወደሚቀጥለው አገር እንዲያስተላፏቸው ወደሚቀጥሉት አስተላላፊዎች ያስተላልፏቸዋል። በዚህ አይነት በህገ-ወጥ አስተላላፊዎች አማካኝነት በየብስና በባህር ላይ በቅብብሎሽ በመጓዝ የደቡብ አፍሪካ ድንበር ወደሆነ አገር ይደርሳሉ። በመጨረሻም የደቡብ አፍሪካን ድንበር በአብዛኛው ጨለማን ተገን በማድረግ በእግር አሳብረው በመግባት ቀደም ሲል ጉዟቸውን የወጠኑላቸው ተቀባዮቻቸው በሚያዘጋጁላቸው መንገድ ተጉዘው ተቀባዮቻቸው ዘንድ ይደርሳሉ።

በዚህ እጅግ አድካሚና አደገኛ የጉዞ ሂደት ውስጥ ፈላሲያኑ ከተፈጥሮ አደጋና በሽታ በተጨማሪ በተለያዩ አገራት የሚገኙ ሕገ-ወጥ አስተላላፊዎች ለሚያደርሱባቸው እንግልትና በደል ይጋለጣሉ። አንዳንድ ጊዜ ሕገ-ወጥ አስተላላፊዎቹ ፖሊስ ሲደርስባቸው ወይም የሚገባንን ጥቅም ከስደተኞቹ አላገኘንም ብለው ሲያስቡ ተጓዦቹን ጫካ ውስጥ ለዱር አውሬ አጋልጠው እንደሚጠፉ ወይም ባህር ላይ ከጀልባ በመጣል እንደሚያሰጥሟቸው ጉዳቱ ደርሶባቸው በሕይወት ተርፈው

የተመለሱ ሠዎች ይናገራሉ፡፡ ተጓዦቹ ድንበር አቋርጠው ሲጓዙ በተለያዩ አገራት በፖሊስና ድንበር ጠባቂዎች በቁጥጥር ስር ሲውሉም ብዙ ጊዜ ፓስፖርትና ሌሎች የማንነት ሠነዶችን ካለመያዛቸው በላይ ብዙውን ጊዜ በቋንቋ መግባባት ስለሚያቅታቸው ለዕንግልት ይዳረጋሉ፡፡ በሚያዙባቸው አገራት ፍርድ ቤት ቀርበው የዓመታት እስር ከሚፈረድባቸው ባሻገር በእስር ወቅት በሚደርስባቸው ከባድ የጉልበት ሥራና የምግብና ህክምና እጥረት ሳቢያ ለአካልና የመንፈስ ድቀት የሚጋለጡ መሆናቸውን በጉዞ ላይ ተይዘው የእስር ጊዜያቸውን ፈጽመው የተመለሱ ሠዎች ይገልፃሉ፡፡

**ምስል5:** <u>ወደ ደቡብ አፍሪካ በሕገ-ወጥ የሚደረግ ጉዞ መንገዶች (routes)</u>




ሁለተኛው ሕገ-ወጥ የጉዞ መስመር የአየር ሲሆን ይህም በተለያዩ ሠበቦች በቀጥታ ወደ ደቡብ አፍሪካ ወይም በአብዛኛው እንደሚደረገው ወደ ደቡብ አፍሪካ አጐራባች

ወደሆኑት አገሮች (ለምሳሌ ዚምባብዌ፣ ሞዛምቢክ) በአየር በመጓዝ፣ ከእነዚህ አገራት በሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች እርዳታ በእግር ድንበር በማሳበር ወደ ደቡብ አፍሪካ በመግባት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሞዛምቢክ በሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች የምትወደድና የምትዘወተር ማስተላለፊያ እንደሆነች ከስደት ተመላሾች ይናገራሉ፡፡ ወደ ደቡብ አፍሪካ አጐራባች አገሮች በአየር ጉዞ ሂደት ውስጥ የየአገሮቹ አንዳንድ የቪዛና ኢሚግሬሽን ሠራተኞች ትብብር እንዳለ በሕገ-ወጥ መንገድ የሚሠጡ ቪዛዎችን ለማየት ተችሏል፡፡

ሕገ-ወጥ ፈላሲዎች ደቡብ አፍሪካ ከደረሱ በኋላ አብዛኛዎቹ ቀደም ሲል ወደዚያች አገር በሄዱ ዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ዘንድ ያርፋሉ፡፡ የተወሰኑት በአገሪቱ የአገር ውስጥ ሚኒስቴር የስደተኝነት ጥበቃ ለማግኘት ይመዘገባሉ፡፡ ከደቡብ አፍሪካ መንግሥት የከለላ ጥያቄያቸው የመጨረሻ መልስ ለማግኘት ብዙ ዘመን የሚፈጅ ሲሆን አመልካቾቹ ብዙውን ጊዜ በየሦስት ወሩ የሚታደስ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት እንደነዚህ ያሉት ፈላሲዎች ሁለት አይነት ማንነት አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ በአንድ በኩል የኢኮኖሚ ፈላሲ ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የከለላ ጥያቄ ስላላቸው እንደ የፖለቲካ ስደተኛ ይቆጠራሉ፡፡ አብዛኛው በደቡብ አፍሪካ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ግን ያለምንም የመኖሪያ ፈቃድ ከመኖራቸውም በላይ በአነስተኛ የንግድ ሥራ ላይ በመሠማራት ኑሯቸውን ይገፋሉ፡፡

በሕጋዊም ሆነ በሕገ-ወጥ ፍልሠት ውስጥ ማኅበራዊ ትስስር ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ገና ከመነሻው ቀድሞ የሄደ የቤተሠብ አባል፣ ዘመድ፣ ጐሣ ጉዞውን ከመወጠን ጀምሮ ወጪውን እስከመሸፈን ድረስ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመጓዝ የሚፈልግ ግለሠብ የጉዞው ዕቅድ የመጀመሪያ ተግባር በደቡብ አፍሪካ ሊቀበለው የሚችለውን ሠው መፈለግና ለጉዞ የሚያስፈልገውን ወጪ ማዘጋጀት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ተቀባይ የቤተሠብ አባል ከሆነ ብዙውን ጊዜ ለጉዞ የሚያስፈልገውን ወጪ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊሸፍን ይችላል፡፡ ቤተሠብ ያለውን ጥሪት በመሸጥና በማስያዝ፣ መዋጮ በማሰባሰብና እና በብድር (በወለድ ጭምር) የጉዞ ወጪ ከተዘጋጀ በኋላ ጉዞውን በሚመሩ አስተላላፊዎችና ደላሎች አማካይነት ጉዞው ይደረጋል፡፡

## 4.2 እነማን ይፈልሳሉ?

ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚፈልሱትን ዜጐች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባህሪያት ስንመለከት ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች በተለይ ወጣት ወንዶች ቢፈልሱም የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሠቦችና ህዝቦች ክልል ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ከዚህ ክልል ውስጥ በተለይ የከምባታ ጠንባሮ እና የሀዲያ ዞኖች ከማንኛውም ክልልና ዞን የበለጠ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለማደረገው ፍልሠት ተጋላጭ

እንደሆኑ ታውቋል:: እንዲያውም ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ፍልሠት ከእነዚህ አካባቢዎች እንደተጀመረና ቀስ በቀስ ወደ አጐራባች ወረዳዎችና ዞኖች እንደተዛመተ መረጃዎች ያመላክታሉ:: የሀላባ ልዩ ወረዳ፣ የወላይታ ዞን እና የአጐራባች ክልል ወረዳዎች ዛሬ ዛሬ ሠዎች ዕለት ተዕለት ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚፈልሱባቸው ምንጮች ሆነዋል::


የከምባታና ጠምባሮ እና ሀዲያ ብሔረሠብ አባላትና አካባቢዎች ለምንና እንዴት ወደ ደቡብ አፍሪካ ለሚደረገው ፍልሠት ግንባር ቀደም እንደሆኑ አያሌ መላ ምቶች ቢሰነዘሩም ሁኔታውን የሚገልጽ ተጨባጭ እና የማያሻማ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም:: ነገር ግን ሊሆን ይችላል ተብሎ ከሚገመትባቸው ምክንያቶች አንዱ በእነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ የህዝብ ብዛትና ጥግግት ያለ በመሆኑ ከፍተኛ የእርሻ መሬት ጥበት ይስተዋላል:: ይህንን ችግር ለማቃለል ከረጅም ዓመታት ጀምሮ የአገር ውስጥ ፍልሠት ሲተገበር የኖረ በመሆኑ አሁንም ይህ ልምድ ወደ ደቡብ አፍሪካ የተጀመረውን የሥራ ፍልሠት አበረታቷል የሚል ግምት ይሠነዘራል::

የፈላሲያን ማንነትን ከጾታ አንፃር ስንመለከት ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ፍልሠት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ከሚደረገው ፍልሠት በተቃራኒ ሙሉ በሙሉ ወንዶች ላይ ያተኮረ ሆኖ ይገኛል:: ለምሳሌ ያህል ቀደም ሲል የተጠቀሰው በሀዲያ ዞን ግቤ ወረዳ በወረዳው መስተዳድር የተሠበሠበው የፈላሲያን ዝርዝር እንደሚያመለክተው ከ1992 እስከ 2004 ከወረዳው ወደ ደቡብ አፍሪካ ከተጓዙት 926 ሠዎች መካከል ሴት አንድ ብቻ መሆኗን ያመለክታል:: ይህም ምናልባት ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ጉዞ አደገኛነት፣ መንገድ ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ አሠቃቂነት እንዲሁም ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ፈላሲያን ከሚሠማሩበት የሥራ መስክ አንፃር ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በደቡብ አፍሪካ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ኢትዮጵያውያን ከአገር ቤት ሴቶችን ለትዳር በተለያዩ መንገዶች መውሠድ በመጀመራቸው የሴት ፈላሲያን ቁጥር እየጨመረ እንደመጣ ይነገራል:: እነዚህ በሚስትነት የሚሄዱ ሴቶች ግን ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል በአየር የሚጓዙ መሆናቸው ይገለፃል::

በዕድሜ ረገድ ከፍልሠት ተመላሾች እንደሚገልፁት በደቡብ አፍሪካ ከ15 አመት ልጅ እግር እስከ 60 አመት አዛውንት ድረስ ይገኛሉ:: ነገር ግን በአመዛኙ የሚፈልሱት ከ18 እስከ 35 ዓመት ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣት ወንዶች እንደሆኑ ታውቋል:: ለዚህም ሥራ አጥነት በዋናነት የሚያጠቃው ወጣቱን የሕብረተሠብ ክፍ መሆኑ፣ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ጉዞ ለጎልማሶች አስቸጋሪ መሆኑና ወጣቶች ከጎልማሶችና አዛውንቶች ጋር ሲነፃጸሩ ከፍልሠት የሚያግዳቸው አነስተኛ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ በምክንያትነት ይጠቀሳሉ::

**ምስል 6፡-** ከ1992-2004 ድረስ በሀዲያ ዞን ግቤ ወረዳ ወደ ደቡብ አፍሪካ የተጓዙ ሠዎች የፆታና ዕድሜ ስብጥር




(ምንጭ፡- በደ/ብ/ብ/ህ/ ክልል፣ በሀዲያ ዞን የጊቤ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ)

በአጠቃላይ ሲታይ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ፍልሠት ሕገ-ወጥ፣ በሕገ-ወጥ የሠዎች አስተላላፊዎች የሚመራና ለላኪውም ሆነ ተቀባይ አገር ቀውስ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሠብዓዊ ቀውሲች የሚፈጥር ከመሆኑ ባሻገር ወደ አረብ አገራት ከሚደረገው የሥራ ፍልሠት በተቃራኒ ፍልሠቱን ወደ ሕጋዊ መንገድ ለማምጣት የሚያስችሉ የሕግ አግባቦች የሌሉት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

## 5 የሥራ ፍልሠት ምክንያቶች

እንደማንኛውም አገር ሁሉ ሠዎች ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገራት እንዲፈልሱ/እንዲሠደዱ የሚያደርጉ የግፊትና የስበት ምክንያቶች አሉ። የግፊት ምክንያቶቹ በአመዛኙ ከአገሪቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተቆራኙ ናቸው። በ1960ዎቹና 1970ዎቹ ዓመታት ከአገር ለመሠደድ ዋናው ምክንያት በጊዜው የነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋትና ተያይዞም የሠፈነው ግጭት ሲሆን፣ ከደርግ መውደቅ በኋላ ባሉት አመታት ግን ለፍልሠት ዋናው ምክንያት ኢኮኖሚዊ ሠበብ ነው ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት በዓመት በአማካኝ 2.9 በመቶ የሚያድግ ሲሆን አብዛኛው ህዝቧም በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው። የ2007 ዓ.ም የህዝብ ቆጠራ መረጃ

እንደሚያሳየው ከ15 ዓመት በታች ያለው ህዝብ ከአጠቃላዩ የህዝብ ብዛት 45 በመቶ ሲሆን፤ በሥራ ለመሰማራት በሚያስችለው የዕድሜ ክልል (15-64 ዓመት) ላይ ያለው ሕዝብ 31.9 በመቶ ድርሻ ይይዛል። በአሁኑ ጊዜ የወጣት ሥራ አጥነት በከተማም ሆነ በገጠር በሠፊው የሚስተዋል ሲሆን፤ የአጠቃላይ የሥራ አጥነት መጠን በ25 በመቶ ይገመታል (IMF 2013)።

በገጠር አካባቢዎች ወጣቶች በከፍተኛ የእርሻ መሬት እጦት የሚቸገሩ ሲሆን፤ ሌላ አማራጭ የሥራ መስክ የማግኘት ዕድላቸውም ውስን ነው። ለምሣሌ ያህል የደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች (ደ/ብ/ብ/ሕ) ክልል በክልሉ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ በ2003 ዓ.ም. በተመረጡ ዞኖች፣ ልዩ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ያካሄደው የሥራ አጥነት ገፅታ ጥናት በክልሉ ወጣቶች ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግር እንዳለባቸው ያሳያል። በጥናቱ መሠረት በሥራ አጥነት ከተፈረጁት መካከል ከ19-24 ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉት 53.2% ይይዛሉ። ይህም ወጣቱ ከአጠቃላይ የሥራ አጥ መካከል አብዛኛውን ስፍራ እንደሚይዝ ያሳያል። ይኸው ክልል በዚህ ፅሁፍ እንደሚብራራው ወደ ደቡብ አፍሪካ በሚደረገው ሕገ-ወጥ ፍልሠት ዋናው ምንጭ ነው።

በወጣት ሥራ አጥነት ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ እንደ ብቸኛ አማራጭ ሲወሰድ ቆይቷል። በቅርብ ዓመታት መንግሥት የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ማስፋፋትን እንደ ዓይነተኛ የሥራ አጥነት ማስወገጃ መንገድ አድርጎ ቢተገብርም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ አረብ አገራትና ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚጎርፉት ወጣቶች በአብዛኛው ከገጠር የሚመጡና በፕሮግራሙ ያልታቀፉ ናቸው። በከተሞችም ቢሆን በዚህ ፕሮግራም የታቀፉት ከአጠቃላይ ሥራ አጥ ወጣቶች መካከል የተወሠኑት ሲሆኑ፤ በፕሮግራሙ የተፈጠሩት አንዳንዶቹ ሥራዎችም ዘላቂ ያልሆኑ ናቸው። በመሆኑም ለሥራ ወደውጭ አገር መፍለስ ለአያሌ ወጣቶቸ እንደ ጥሩ አማራጭ ተወስዷል።

በየጊዜው ከየቦታው የሚሠማው ሠቆቃ፤ የአካልና የወሲብ ጥቃት፣ የውስጥ አካላት ዝርፊያ ግድያ ዜና እንኳን ከፍተኛ ድንበር ዘለል የፍልሠት ፍላጎትን አልበገረውም። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው ከአረብ አገራት በሙሉ የመጨረሻ ደሀ በሆነችው የመን እንኳን ኢትዮጵያውያን (ከሶማሌያውናን ጋር በመሆን) ከፍተኛው የቤት ውስጥ ሠራተኛ ቁጥር መያዛቸው ነው።

ቀደም ሲል የሴቶችን የሥራ ፍልሠት በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች (ለምሳሌ Emebet 2002; Fernandez 2010) የሴቶች የትምህርት ዕድል ውስን መሆንና ጾታዊ ጥቃትን እንደዋና የፍልሠት ግፊት ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ። ነገር ግን በቅርብ ዓመታት እጅግ እያሻቀበ በመጣው የኑሮ የውድነት ሳቢያ ብዙ ቤተሠቦች

በገቢያቸው መተዳደር እየተሳናቸው ሲመጣ አያሌ ሥራ ያላቸው ሴቶች ሳይቀሩ በቤት ሠራተኛነት ወደ አረብ አገሮች መፍለስን እንደ ጥሩ አማራጭ እያዩ ነው። አንዳንዶች በአረብ አገሮች በቤት ሠራተኛነት ለመቀጠር እንደ መምሕርነት፣ የጤናና የግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኛነት የመሳሰሉ ቋሚ የመንግሥት ሥራቸውን ይለቃሉ። እንደ የደቡብ ወሎ ዞን (አማራ ክልል) የሠ/ማ/ጉ መምሪያ ኤክስፐርቶች አስተያየት ከዞኑ በ2004 ዓ.ም ወደ አንድ መቶ የሚደርሱ ሠዎች ቋሚ የመንግሥት ሥራቸውን ለቅቀው ወደ አረብ አገራት ለቤት ሠራተኛነት ተጉዘዋል። ወደእነዚህ አገሮች የሚደረገውን ፍልሠት አጓጊ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱና ዋናው ብዙ ኢትዮጵያውያን አገር ውስጥ ሠርተው ከሚያገኙት ገቢ ጋር ሲነፃፀር በቤት ሠራተኛነት የሚከፈላቸው ክፍያ የተሻለ ሆኖ መገኘቱ ነው። በአሁኑ ጊዜ በሳዑዲ አረቢያ ለአንዲት የቤት ሠራተኛ የሚከፈለው አማካይ የ200 የአሜሪካን ዶላር የወር ክፍያ በአገር ውስጥ ብዙ የመንግሥት ሠራተኞች ከሚያገኙት የወር ደሞዝ የበለጠ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የደቡብ ወሎ የትምህርት መምሪያ መረጃ እንደሚያሳየው በ2004 ዓ.ም በዞኑ ከነበሩት 17,000 ገደማ መምህራን 800 ያህሉ ሥራቸውን የለቀቁ ሲሆን ወደ አረብ አገራት በቤት ሠራተኛነት መሄድ ሥራቸውን ከለቀቁባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ መሆኑ ተገልጿል።

ከግል ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በተጨማሪ የቤተሠብ ግፊትና ተፅዕኖ ሌላው ወደ አረብ አገራትና ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመፍለስ የሚገፋ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል። ወጣቶች ወደ ደቡብ አፍሪካ ተሠድደው ገንዘብ በማግኘት ቤተሠብን እንዲረዱ ከአንዳንድ የቤተሠቦች አባሎች ግፊት እነደሚደረግባቸው ነዋሪዎችና ከስደት ተመላሾች ይናገራሉ። በተለይ ለረጅም ዓመታት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተው ሥራ ባላገኙ ወጣቶችና ሥራ ቢሰሩም ገቢያቸው ያን ያህል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማያስገኝላቸው ወጣቶች ላይ ቤተሠብ ወደ ደቡብ አፍሪካ ተሠድደው ራሳቸው እንዲችሉና ለቤተሠባቸውም እንዲተርፉ ግፊት ያደርግባቸዋል። ይህ ግፊት በቤተሠብ ብቻ ሳይወሰን ከቤተዘመድ፣ ጓደኛና የአካባቢ ሠውም ይመጣል። በዚህ ረገድ አንዳንድ የኃይማኖት አባቶችና የአካባቢ ሽማግሌዎች ሳይቀሩ በዚህ ይወቀሳሉ[4]።

[4]በዱራሜ ከተማ (ከምባታና ጥምባሮ ዞን) በአንድ የቡድን ውይይት ላይ የተሣተፈ ወጣት ሲናገር "ቤተሠብ ትምህርት አጠናቅቆ ቤት የተቀመጠ ወጣትን እንደሸክም ይቆጥራል። 'እንደ ጓደኞችህ ወደደቡብ አፍሪካ ሄደህ እኛን እንኳን ባትረዳ ራስህን ቻል' ይሉታል። እንዲሁም 'ከአንተ እዚህ በህይወት ካለኸው ደቡብ አፍሪካ ያለ ሬሳ ይሻላል በማለት ይዘባበቱበታል፤ እንዲሠደድ ግፊት ያደርጉበታል። የደቡብ አፍሪካ ሬሳ ይሻላል የሚለው ነገር የመጣው ደቡብ አፍሪካ ሄደው በልዩ ልዩ ምክንያት ህይወታቸው የሚያልፍ ሠዎችን እዚያ ያሉ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ገንዘብ በማዋጣት አስከሬኑን ወደ አገር ቤት እንዲመጣ ያደርጋሉ። በዚህ ሂደት ከጉዞ የተረፈውን ገንዘብና ሞባይል የመሳሰሉ የሟች ጥቃቅን መገልገያዎችን ከአስከሬኑ ጋር በሳጥን ውስጥ አድርጎ ለሟች ቤተሠብ የመላክ ልምድ ዳብሮ ስለነበር ነው። በሆሳዕና ከተማ (ሀዲያ ዞን) በተደረገ ሌላ የቡድን ውይይት

በተመሳሳይ ወደ አረብ አገራት በገፍ ወጣት ሴቶች በሚሄዱባቸው አካባቢዎች (ለምሳሌ ደቡብ ወሎ) ትዳር የመሠረቱ ሴት ልጆችን ሳይቀር ቤተሠቦች ወደ አረብ አገራት በቤት ሠራተኛነት እንዲሄዱና ለባለቤቶቻቸውና ቤተሠቦቻቸው ገንዘብ እንዲልኩ ከፍተኛ ግፊት ያደርሱባቸዋል። ከኢኮኖሚው ጠቀሜታ ባሻገር በአንዳንድ አካባቢዎች ልጆችን ወደ ውጭ አገር መላክና ‹‹ውጭ አገር ልጅ አላቸው›› መባል የቤተሠብን ማኅበራዊ ክብር ማሳይ ተደርጎም ይቆጠራል። በዚህ ረገድ ብዙ ልጅ ወደ ውጭ አገር የላከ ቤተሠብ የበለጠ ከበሬታ ሲሰጠው ይታያል። በመሆኑም በአካባቢዎቹ የግል፣ የማኅበራዊና የንብረት ስኬት መለኪያ እስከመሆን የደረሰ ‹‹የፍልሠት ባሕል›› የተፈጠረ ይመስላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ አረብ አገራት ወይም ደቡብ አፍሪካ ለተወሠነ ጊዜ ቆይተው የተወሰነ ጥሪት ይዘው የሚመጡ ተመላሾች በኑሯቸው ላይ የሚሳዩት ለውጥ (ለምሳሌ የመኖሪያ ቤት መሥራት፣ የንግድ ቤት መክፈት፣ በውድ ጌጣጌጥ ማጌጥ) ወጣቶችን ለፍልሠት ሲያነሳሳና እንደእነርሱ ስኬታማ ለመሆን ፍልሠትን አቋራጭ መንገድ አድርገው ሲወስዱት ይታያል። ሠዎች ለረጅም ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አረብ አገራት ሲፈልሱ በቆዩባቸው አንዳንድ አካባቢዎችና በደቡብ ኢትዮጵያም በከምባታና ሐዲያ አካባቢዎች አያሌ ወጣቶች ህይወታቸውን በስኬት ለመምራት ወደ ውጭ አገር መፍለስን እንደ ብቸኛ አማራጭ በሚመለከቱበት ሁኔታ በመፈጠሩ ለትምህርት ያላቸው ትኩረትና አገር ውስጥ ባሉት የሥራ መስኮች ለመሠማራት ያላቸው ፍላጎት ተገድቦ ይታያል።

እጅግ እየተጠናከረ መጣው የደላሎች መረብ ወደ አረብ አገራትና ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን የሥራ ፍልሠት ከመቼውም በላይ አሳድጎታል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአረብ አገራት በሕጋዊውና ሕገ-ወጡ የፍልሠት መንገዶች መካከል ያለው የተምታታ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ ‹‹ልጆቻችሁን በቀላሉና በነፃ ወደ ውጭ አገር እንልክላችኋለን›› የሚሉ አያሌ ደላሎች በየአካባቢው በስፋት ይንቀሳቀሳሉ። አንዳንዶቹ ደላሎች በሕጋዊነት ፈቃድ አውጥተው ከሚሠሩ የግል ሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች ጋር በቅርበት ይሠራሉ፤ እንዲያውም እነርሱ የሚያሠማሯቸው ናቸው የሚል ሐሜት በስፋት ይሠማል። ደላሎቹ በውጭ አገር ስላለው መልካም ዕድልና ጥቂት ጥሪት አፍርተው የተመለሱ ተመላሾችን ‹‹ስኬት›› አጋንነው በማቅረብ ቀድሞውንም በሌሎቹ ምክንያቶች ልባቸው የተነሳሳውን ወጣቶች ይበልጥ ለፍልሠት ያበረታታሉ፤ መንገዶችንም ያመቻቻሉ።

---

ተሳታፊዎች እንደገለጹት ለጉዞ የተነሳሱ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ወጣቶች ወደሚያመልኩበት ቤተ-ክርስቲያን በመሄድ ጉዟቸው እንዲሳካ ፀሎት ማድረግ የተለመደ እንደሆነና በዚህም አንዳንድ የቤተ-ክርስቲያናት መሪዎችና ሽማግሌዎች ወጣቶችን ለስደት የሚያበረታቱ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከላይ እንደተገለጸው ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ለፍልሠት መስፋፋት ትልቅ ድርሻ ቢኖራቸውም በፍልሠትና በድህነት መካከል ቀጥተኛ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ማግኘት ያስቸግራል። በእ.ኤ.አ በ2008 የዓለም የፍልሠት ድርጅት (IOM) ባስጠናው ጥናት በፍልሠት ፍላጎትና በሕገ-ወጥ ሠዎች አዘዋዋሪዎች ዕንቅስቃሴ መካከል ጠንካራ ግንኙነት መኖሩን ያሳያል። በእርግጥም በውጭ አገር ስላለው ‹‹ሲሳይ›› የሚሰብኩ ደላሎችና ሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች በሌሉበት አካባቢ ህብረተሠቡ ስለ ውጭ አገር ፍልሠት ኢንፎርሜሽን ሊኖረውና ወጣቶችም የመፍለስ ጉጉት ሊያድርባቸው አይችልም።

ከአገር ለመውጣት የሚገፋፉ ውስጣዊ ምክንያቶች እነዚህ ሆነው ሳሉ፤ በሌላ በኩል ወጣቶች ወደ አረብ አገራትና ወደ ደቡብ አፍሪካ እንዲፈልሱ የሚስቡ ምክንያቶችም ይታያሉ። እነዚህ ሳቢ ምክንያቶች በየአገራቱ ካሉት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። በዘይት ኃብት በበለጸጉት ሳዑዲ አረቢያና ሌሎች የአረብ አገራት የሚታየው ከፍተኛ የቤት ሠራተኛ ፍላጎት በአገራቱ ገዢዎችና በዜጎቻቸው መካከል የተፈጠረው ያልተፃፈ የፖለቲካ ስምምነት ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ይኸውም ገዢዎቹ ሥልጣናቸው እንዳይነካና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች እንዳይነሱባቸው ለዜጎቻቸው የቅንጦት ኑሮ መኖር የሚያስችል ኢኮኖሚ ድጎማ ያደርጋሉ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ የቤት ሠራተኛ መኖር የኑሮ ደረጃ መለኪያ ተደርጎ እስከመወሰድ ይደርሳል። በዚህም ከፍተኛ ደሞዝ የሚከፈላትን ፊሊፒናዊ የቤት ሠራተኛን ከበላይ አድርጎ፣ ኢንዶኔዢያዊን በሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም አፍሪካውያንን በመጨረሻ ደረጃ የሚያስቀምጥ ዘረኛ የሆነ የቤት ሠራተኛን በደረጃ የሚከፋፍል ሥርዓት ተዘርግቷል። ይህም ሥርዓት የተለያዩ አገራት ዜጎች የሆኑ የቤት ሠራተኞች በሚከፈላቸው እጅግ የተለያየ የደሞዝ መጠን ይገለፃል[5]።

በዘይት ኃብት የበለጸጉት የአረብ አገራት በተለይ ሳዑዲ አረቢያ ከፍተኛ የቤት ሠራተኛ ፍላጎት አላቸው። በሳዑዲ አረቢያ ብቻ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ የቤት ሠራተኞች እንዳሉ ይገመታል። ይህ ከፍተኛ የቤት ሠራተኛ ገበያ አያሌ ወጣቶች (በተለይ ሴቶች) እንዲፈልሡ ምክንያት ሆኗል። በአገራቶቹ የሚየታው ሕገ-ወጥ ፈላሲያንን ችላ የማለት ዝንባሌ፣ ልል የድንበር ላይ ቁጥጥርና የድንበር ተቆጣጣሪዎችን በቀላሉ በመደለል ወደየአገራቱ የመግባት ዕድል ሌላው ብዙ ጊዜ የማይነሳና ፈላሲያንን እንደ ሳዑዲ አረቢያ ወደመሳሰሉ የአረብ አገራት የሚስብ ሌላው ምክንያት ነው።

---

[5] የፊሊፒንስ የውጭ አገር የሥራ ሥምሪት ኤጀንሲ ከእኤ.አ ከ2011 ጀምሮ ከአገሩ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለሚሄዱ የቤት ሠራተኞች ዝቅተኛ የወር ክፍያ 400 የአሜሪካን ዶላር እንዲሆን ሲወስን የአንዲት ኢዮጵያዊት የቤት ሠራተኛ የወር ደሞዝ ግን 200 የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው።

የደቡብ አፍሪካንም ሁኔታ ስንቃኝ የተለያዩ ሳቢ ምክንያቶች ይገኛሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ አገሪቷ ከአፍሪካ አሕጉር ጠንካራ ኢኮኖሚ ያላት በመሆኑ ከተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ለሚሄዱ ፈላሲያን ከሄዱበት አገራት ጋር ሲነፃጸር የተሻለ ሠርቶ የማግኘት ዕድል ትሰጣለች፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አብዛኛዎቹ ፈላሲ ኢትዮጵያውያን ደቡብ አፍሪካ በደረሱ አጭር ጊዜ ሥራ ከመጀመራቸውም በላይ ጥሪት ማፍራት መቻላቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ደቡብ አፍሪካ በአገሪቱ ባሉት ሠፋፊ እርሻዎችና ማዕድን ማውጫዎች ውስጥ በጉልበት ሠራተኛነት ለመሠማራት ከጎረቤት አገራት የሚመጡ ሠዎችን ለረጂም ዓመታት ስታስተናግድ የኖረች አገር በመሆኗ የሥራ ፈላሲያንን የመቀበል የቆየ ባህል አላት፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ እየቀነሰ ቢመጣም በሕብረተሠቡ መካከል የሥራ ፈላሲያንን በበጎ የመመልከት ባህል ሠዎች ወደዚያች አገር እንዲፈልሱ አበራትቷል፡፡

ከኢኮኖሚ ሳቢ ምክንያቶች በተጨማሪም በፖሊሲና ሕግ አንፃር ደቡብ አፍሪካ ለስደተኞች አመቺና ቀና ፖሊሲ አላቸው ከሚባሉት አገራት መካከል ትጠቀሳለች፡፡ አገሪቱ የሠብዓዊ መብትን የሚደነግጉ ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመቀበሏ ባሻገር፤ በመንግሥት ደረጃ ደቡብ አፍሪካ ለስደተኞች ታጋሽ ፖሊሲ ይከተላሉ ከሚባሉት አንዷ ለመሆን ችላላች፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት የአገሪቷ መሪዎች በአፓርታይድ ዘመን በትግላቸው ወቅት ከብዙ የአፍሪካ አገራት ወንድሞቻቸው የተደረገላቸው የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ እንዲሁም በስደት በብዙ የአፍሪካ አገራት በመጠላለቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን በውጭ ዜጎች ላይ በተለያዩ ጊዜያት ጥቃቶች ቢሰነዘሩም፣ አሁንም አያሌ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ወደዚያች አገር ለማምራት ከመወጠን አልታቀቡም፡፡

## 6 የሥራ ፍልሠት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ውጤቶችና ተፅዕኖዎች

ፍልሠት በጎም ጎጂም ጎኖች እንዳሉት ግልጽ ነው፡፡ ኢትዮጵያን የመሳሰሉ ታዳጊ አገራት በፍልሠት ምክንያት አያሌ ጉዳቶች ይደርሱባቸዋል፡፡ በተለይ የተማረ የሠው ኃይል ፍልሠት የታዳጊ አገራትን ዕድገት በእጅጉ የሚፈታተን ጉዳይ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ኢትዮጵያም የዚህ ችግር ሠለባ ከሆኑት አገራት አንዷ ናት፡፡ ለምሳሌ አንድ የዓለም ባንክ ጥናት እንደሚያሳየው በአገሪቱ በህክምና ሙያ ከሠለጠኑት/ከተማሩት ባለሙያዎች መካከል ከሩብ በላይ የሚሆኑት (25.6%) በሌሎች አገራት በሥራ ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ አንድ ጥናት በአሜሪካን አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል 23% ያህሉ ከአራት ዓመታት ያላነሠ የሶስተኛ ደረጃ (ዩኒቨርሲቲ) ትምህርታቸውን የተከታተሉ መሆናቸውን ያሳያል (Black et al, 2006)፡፡ ከፍተኛ የተማረ የሠው ኃይል ፍልሠትን የሚገልጸው ሌላው መረጃ ደግሞ ከ1/4ኛ እስከ 3/4ኛ የሚደርሱ በውጭ አገራት ትምህርታቸውን የሚከታተሉ

ኢትዮጵያውያን ትምህርታቸውን ሲያገባድዱ ወደ አገራቸው እንደማይመለሱ ያሳያል (Black et al, 2006)።


በሌላ በኩል በአሁኑ ጊዜ በሥራ ፍልሠት ወደ አረብ አገራት የሚሄዱት ኢትዮጵያውያን በአብዛኛው ዝቅተኛ የትምህርትና የክህሎት ደረጃ ያላቸውና ከገጠር አካባቢ የሚመጡ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ምንም እንኳን የስደት/ፍልሠት ጉዳይ ሲነሳ በአብዛኛው ጎልቶ የሚነገረው ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ተመሳሳይ ጎጂ ጎኖች ቢሆኑም፤ የሥራ ፍልሠት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት አይካድም። በዚህ ረገድ ወደአገር ውስጥ የሚገባው የውጭ ምንዛሬና ፈላሲያን የሚያዳብሩት የሥራ ክህሎትና ልምድ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። እ.ኤ.አ በ2012 በውጭ አገራት የሚኖሩ የታዳጊ አገራት ዜጎች ወደየአገራቸው የላኩት የ401 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በዓመቱ በዓለም አቀፍ ርዳታ ለአገሮቹ ከተሠጠው ገንዘብ እጅግ ልቆ መገኘቱን የዓለም ባንክ መረጃ ያሳያል (World Bank, 2013)። ነገር ግን ከዚህ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ውስጥ ከሠሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራት ድርሻ አነስተኛ ሆኖ ቢገኝም ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ በመሄድ እ.ኤ.አ. ድርሻቸው በ2014 ዓ.ም 40 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር መድረሱን መረጃው ጨምሮ ያሳያል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ከውጭ የሚመጣው ገንዘብ በኢትዮጵያ በብዙ ሺ ለሚቆጠሩ ቤተሠቦች የኑሮ መሠረት ወይም መደጎሚያ ሆኖ ይገኛል (Reinert 2006 Fransen and Kuschminder, 2009)። ለምሳሌ በ2000 ዓ.ም የበጀት ዓመት አገሪቱ ወደ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚሆን የውጭ ምንዛሬ በውጭ አገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አግኝታለች። ነገር ግን በዚህ ረገድ የብሔራዊ ባንክ መረጃ በውጭ ካሉ ኢትዮጵያውያን የሚላከውን ገንዘብ ከሚላክበት አገር አንፃር ከፋፍሎ ስለማያሳይ ከዚህ ውስጥ ምን ያህሉ በአረብ አገራት ከሚገኙ የሥራ ፈላሲያን እንደተላከ ማወቅ ያስቸግራል። ነገር ግን በእነዚህ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ብዛት ከሌሎች የዓለም አካባቢዎች የበዛ ቢሆንም፤ በሚልኩት ገንዘብ መጠን ግን ከፍተኛውን ድርሻ አለመያዛቸውን አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ። የተ.መ.ድ. የልማት ፕሮግራም መረጃ እንደሚያሳየው ምንም እንኳን አብዛኛው (37.5%) ከአገር ውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ በኤስያ (የገልፍ አገራት) የሚገኝ ቢሆንም፤ ከፍተኛው የገንዘብ መጠን የሚላከው ግን 24.1% ኢትዮጵያውያን ፈላሲያን ካሉበት የሠሜን አሜሪካ አህጉር መሆኑን ያሳያል። ይህም ሆኖ ግን ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ በመጣው ከውጭ የሚላክ የውጭ ምንዛሬ ውስጥ በአረብ አገራት ከሚገኙ የሥራ ፈላሲያ ድርሻ ቀላል አለመሆኑን መገመት ይቻላል። ይህ እንግዲህ በሕጋዊ መንገድ በባንኮች አማካይነት ወደ አገር

ውስጥ የሚገባው ሲሆን፤ በተለያዩ ሌሎች መንገዶች የሚገባውን የውጭ ምንዛሬ አይጨምርም።

**ምስል 7፡** ከ1989-2004 ዓ.ም በውጭ ካሉ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት በባንክ ቤት በኩል የተላከ የውጭ ምንዛሬ መጠን




(ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ)

ከውጭ የሚመጣው ገንዘብ የውጭ ምንዛሪን በማዳበር ረገድ ለአገር ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር የአያሌ ቤተሠቦች የሕይወት መሠረት ወይም መደጎሚያ ሆኖ ያገለግላል። ከአንድ የሥራ ፈላሲ ወደ ቤተሠብ የሚላከው የገንዘብ መጠንና ሁኔታ እንደ ፈላሲው ቤተሠብ የኢኮኖሚ አቅም ሁኔታና እንደ ፈላሲው የገቢ መጠን ይወሰናል። ነገር ግን በተለያየ መጠን ቢሆንም በውጭ አገር በሥራ ላይ ያሉ ሠዎች ወደቤተሠቦቻቸው በቋሚነት ወይም የተለያዩ ወቅቶችን ጠብቀው የሚልኩት ገንዘብ ለሁለት መሠረታዊ ግልጋሎቶች ይውላል። የመጀመሪያው ለዕለት ተዕለት ፍጆታ የሚውል ሲሆን ይህም በተለይ ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑና መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን (በተለይ የምግብ ዋስትናቸውን) ለሚሟላት የሚቸገሩ ቤተሠቦች ከውጭ ለሥራ ከፈለሰ የቤተሠብ አባል በቋሚነት የሚያገኙት ነው። የዚህ አይነት የቤተሠብ የኢኮኖሚ ችግርና ቤተሠብን የመርዳት ግዴታ የደረሡ ልጆች (በተለይ ሴት ልጆች) ወደ አረብ አገራት በቤት ሠራተኛነት እንዲፈልሱ ከሚደርጉ ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል።

ሁለተኛው ከውጭ የሚላክ ገንዘብ ግልጋሎት ደግሞ ቋሚ ንብረት ማፍራትና የመተዳደሪያ ሥራን ማጠናከር ነው። ከመስክ መረጃዎች ለማወቅ አንደተቻለው ቤት ሠርቶ ማከራየት፣ የእርሻ በሬና መሣሪያ መግዛት፣ አነስተኛ ንግድ ቤት ማቋቋም፣ የቤት እንሠሣት ማርባት ዋና ዋና የንብረት ማፍሪያ መንገዶች ናቸው። እነዚህ

ሥራዎች ለቤተሠብ ተጨማሪ ገቢ ከማስገኘታቸው ባሻገር፤ ከውጭ የሚመጣውን ገንዘብ ወደ ምርት ሥራ በማስገባት፣ ለቤተሠብ አባላት ሥራ በመፍጠርና የቤተሠብን ገቢን በማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሠጣል:: በዚህ ረገድ የመኖሪያ ቤት መሥራትና ማስፋፋት በብዙ አካባቢዎች ቅድሚያ የሚሠጠው ተግባር ሆኖ ይታያል:: ይህም ምናልባት በአሁኑ ጊዜ ከሚታየው ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት እጥረትና የተነሳ እንዲሁም ቤትን ዋጋው የማይቀንስ ቋሚ ንብረት አድርጎ ከማየት የመነጨ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ::

ከላይ የተጠቀሱት አገራዊ፣ ቤተሠባዊና ግለሠባዊ ጠቀሜታዎቹ እንዳሉ ሆነው፤ ከውጭ የሚላክ ገንዘብ አንዳንድ አሉታዊ ጎኖችም ይስተዋሉበታል:: የመጀመሪያው ዋና አሉታዊ ጎን ቤተሠቦች ከውጭ ለሚመጣ ገንዘብ በመጓጓት ልጆቻቸው፣ ባለቤቶቻቸውና ሌሎች የቤተሠብ አባላት እንዲፈልሱ በግልጽና በተዘዋዋሪ ግፊትና ጫና መሳደራቸው ነው:: ይህም በተለይ በሴት ልጆች የትምህርት ፍላጎትና ክትትል ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው እሙን ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ እናቶች ወደ አረብ አገራት ለሥራ ሲፈልሱ የቤት ውስጥ ሥራና ልጆችን የመንከባከብ ኃላፊነት በባሎችና ገና ባልደረሱ ሴት ልጆች ትከሻ ላይ ይወድቃል:: በልጆች ላይም የእናት እንክብካቤ በማጣት በትምህርት መድከምና ማቋረጥ ያስከትላል::

ከውጭ አገር በሚመጣ ገንዘብ ሳቢያ በቤተሠብ ወይም አንዳንድ የቤተሠብ አባላት ዘንድ የጥገኝነት ስሜት መዳበርና የሥራ ፍላጎት መቀነስ ሌላው የውጭ ገንዘብ አሉታዊ ጎን ሆኖ ይጠቀሳል:: ቤተሠብ የሚመጣውን ገንዘብ ንብረት ከማፍራት ይልቅ ወደ ለፍጆታ ማዋል ፈላሲዎቹ ወደ አገር ቤት በሚመለሱበት ወቅት የላኩት ጥሪት ተሟጥጦ በማለቁ ያልጠበቁትና ሊቋቋሙት የማይችሉት የኢኮኖሚና የሥነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ ይከታቸዋል::

ከዚህ ሌላ ከውጭ አገር የሚላከውን ገንዘብ ክፍፍልና አስተዳደር በተመለከተ በቤተሠብ አባላት፣ በባልና ሚስት፣ በባልና የሚስት ቤተሠቦች ወ.ዘ.ተ. መካከል ግጭት ሲፈጠር ይስተዋላል:: በአረብ አገራት ለዓመታት ለፍተው ገንዘብ በመላክ የተለያዩ ጥሪቶች በቤተሠብ አባላት ስም እንዲገዛላቸው የሚያደርጉ የሥራ ፈላሲያን ከአመታት በኋላ ወደአገራቸው ሲመለሱ ንብረቶችን የሚካዱበት ሁኔታ የተለመደ እንደሆነ ከብዙ ተመላሾች ታሪክ መረዳት ተችሏል::

## 7 የውጭ አገር የሥራ ስምሪት አስተዳደርና የመንግሥት እርምጃዎች

የውጭ አገር የሥራ ስምሪትን መምራትና መቆጣጠር የሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር ኃላፊነት እንደሆነ ቢታወቅም የፌዴራል ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ቢሮዎች ይህንን ከፍተኛና በድንገት የፈነዳ የውጭ አገር የሥራ ስምሪትን በአግባቡ ለመምራት

የሚያስችል የሠው ኃይል፣ የማቴሪልና ድርጅታዊ አቅም እንደሌላቸው በግልጽ የሚታወቅ ነው።

የግል የሥራ አገኛን ኤጀንሲዎች ፈቃድ መስጠትና መቆጣጠር እንዲሁም የውጭ አገር የሥራ ውልን ማጽደቅ ሚኒስቴሩ በሕግ ከተሠጡት ኃላፊነቶች መካከል ይገኛሉ። የሥራ ፍልሠትን ለማስተዳደር የፌደራል መንግሥት የውጭ አገር ሥራን የሚያገናኙትን የግል ኤጀንሲዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ‹‹የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ›› (ቁጥር 104/90) እና ‹‹ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት አገልግሎት አዋጅ›› (ቁጥር 632/2001) አውጥቷል። አዋጅ ቁጥር 104/90 በጊዜው በሕገ-ወጥ መንገድ አያሌ ኢትዮጵያውያንን ወደ ሊባኖስ የሚልኩ ሕገ-ወጥ የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎችን ፈር ለማስያዝ የወጣ ሲሆን፤ የ2001 ዓ.ም አዋጅ ደግሞ ሥራና ሠራተኛን በማገናኘት ሂደት ላይ የሚደረገውን የክትትልና ቁጥጥር አሠራር ሥርዓት ለማጠናከር ቀደም ሲል የወጣውን አዋጅ በማሻሻል የወጣ ነው።

እነዚህ ሁለቱም አዋጆች ኤጀንሲዎች ለሥራ ወደ ውጭ አገር ከሚሄዱ ሠዎች ላይ ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ እንዳይጠይቁ ከመከልከላቸው በላይ አዋጅ ቁጥር 632/2001 በተለይ በውጭ አገር የሚገኘው አሠሪ በኤጀንሲው በኩል የሠራተኛውን የተቀባይ አገር የመግቢያ ቪዛ፣ የደርሶ መልስ ትኬት፣ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ወጪዎች፣ የኮቴና የመድኅን ዋስትና ወጪዎችን እንዲሸፈን ያስገድዳል።

ለሥራ ወደውጭ ለመሄድ የሚፈልገው ሠው በበኩሉ የፓስፖርት፣ በአገር ውስጥ የማንነት ሠነዶች ማረጋገጫ ክፍያ፣ የጤና ምርመራና ክትባት፣ የሙያ ማረጋገጫ ፈተና ክፍያና ከወንጀል ነፃ መሆንን ማረጋገጫ ማስረጃ ማውጫ ወጪዎችን የመሸፈን ግዴታ አለበት። በአዋጁ የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎችና ፎርሚሊቲዎች ሳያሟሉ ሰዎችን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ በሕግ እንደሚያስቀጣም በአዋጁ ተደንግጓል። አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ለሥራ ወደውጭ አገር ለመሄድ የሚፈልጉ ሠዎች ለላኪዎቹ ከ5 እስከ 10 ሺ ብር ድረስ እንዲከፍሉ ይገደዱ ነበር። ኤጀንሲዎች ከሥራ ተጓዦች ክፍያ እንዳይጠይቁ በአዋጁ መከልከሉ በሥራ ፍልሠቱ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣ ሲሆን፤ ቀደም ሲል የአገልግሎት ክፍያ ለመክፈል ሲሉ በብድር፣ በአራጣና ያላቸውን ጥሪት በመሸጥ ይገቡበት የነበረውን ችግር አቃሏል። ነገር ግን አሁንም በሕገ-ወጥ መንገድ ከሥራ ፈላጊዎች ገንዘብ የሚጠይቁ ኤጀንሲዎች እንዳሉ ይነገራል።

በሌላ በኩል የሥራ ፈላሲያንን የጉዞ ወጪ አሠሪዎቻቸው እንዲሸፍኑ በሕግ መወሠኑ ሌላ ያልታሠበ ችግር በፈላሲያኑ ላይ አድርሷል። አሠሪዎች አንድ የቤት ሠራተኛ ለማስመጣት 1,300 እስከ 2,340 የአሜሪካን ዶላር ስለሚያወጡ ሠራተኞቹ እነርሱ ዘንድ ከደረሱ በኋላ እንዳይጠፉ በጥብቅ ከመቆጣጠር አልፎ ፓስፖርታቸውን

በመደበቅና ደሞዛቸውን በመያዝ እንቅስቃሴያቸውን ይቆጣጠራሉ፣ ነፃነታቸውንም ይነፍጋሉ (HRW, 2008)።

አዋጅ ቁጥር 632/2001 በተለይ የሠራተኛው ሠብዓዊና የሥራ መብቶች መከበራቸውን የሥራ አገናኝ ኤጀንሲው ኃላፊነት እንደሆነ ይደነግጋል። በተጨማሪም የሥራ አገናኝ ኤጀንሲው ወደውጭ አገር ለሥራ የሚጓዙ ሠዎች አስፈላጊው/ተፈላጊው የሙያ ክህሎች እንዳላቸው የማረጋገጥ ኃላፊነትም እንዳለበት በአዋጁ ተገልጿል። ሁለቱም አዋጆች የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች በሥራ መስኩ ለመሠማራት ለሥራ የሚልኩት ሠራተኛ ዋስትና ማስከበሪያ የሚውል ገንዘብ በዝግ ሂሳብ ማስያዝ እንዳለባቸው ይደነግጋል። በዚህ መሠረት እስከ 500 የሚደርሱ ሠራተኞችን የሚልኩ ኤጀንሲዎች 30 ሺ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር፤ ከ501 እስከ 1,000 የሚደርሱ ሠራተኞችን የሚልኩ ኤጀንሲዎች 40 ሺ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር፤ እንዲሁም ከ1,001 በላይ ሠራተኛ የሚልኩ ደግሞ 50 ሺ የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር እንዲያሲዙ አዋጁ ያዛል።

የግል የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎችን በተመለከተ በእ.ኤ.አ. በ2013 በአዲስ አበባ በሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር የተመዘገቡና ፈቃድ ያላቸው 352 የግል የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች የነበሩ ሲሆን አብዛኛዎቹ በክልል ከተሞችም ቅርንጫፍ ቢሮዎች ከፍተው ይንቀሳቀሳሉ። የአብዛኛዎቹ ኤጀንሲዎች ባለቤቶች ሠራተኞች ከሚሄዱባቸው የአረብ አገራት ጋር ግንኙነት ያላቸው ወይም በእነዚህ አገራት በሥራ የኖሩ ናቸው። ነገር ግን አንዳንድ የግል የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች ሕጋዊና ሕገ-ወጥ ሥራዎችን ቀላቅለው ይሠራሉ ተብለው በሠፊው ይታማሉ። እነዚህ ኤጀንሲዎች ጥቂት ሠራተኞችን ለሽፋን በሕጋዊ መንገድ በመላክ ብዛት ያላቸውን ሌሎች ሠዎችን የሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር ያወጣውን መስፈርት ሳያሟሉና ኮንታራታቸውን ሳያፀድቁ በሕገ-ወጥ መንገድ ይልካሉ ተብለው ይወነጀላሉ።

የውጭ አገር የሥራ ስምሪት በተመለከተ የሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር ዋና ተግባር የሥራ ኮንትራቶችን ትክክለኝነት መርምሮ መመዝገብና ማጽደቅ ነው። የሥራ ኮንትራቶች የሠራተኛውን ወርኃዊ የደሞዝ መጠን፣ አሠሪው ለሠራተኛው የመኖሪያ፣ የምግብና የህክምና አገልግሎት የማቅረብ እንዲሁም በሁለት ዓመት የአንድ ወር የዕረፍት ፈቃድ ከነደሞዙ (ወይም ተመጣጣኝ ክፍያ) ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች (አሠሪም ሆነ ሠራተኛው) የሥራ ውሉ በከፍተኛ ደረጃ ተጥሷል ብለው ካመኑ (ለምሳሌ ከፍተኛ የመብት ጥሠት ወይም ጥቃት) ውሉን የመሠረዝ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን በውሉ ይጠቀሳል።

በሌላ በኩል የሥራ ውሉ መኖር መልካም ሆኖ ሳለ አብዛኛዎቹን በውሉ ላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች ተፈጻሚነት መቆጣጠር አለመቻሉ ዋና ችግር ሆኖ ይታያል። የሠራተኞች አያያዝና መብት አጠባበቅ ሁኔታ በአመዛኙ በአሠሪዎች ባህሪ ላይ የተመሠረተ ነው። በተለይ በሁለት ዓመት የአንድ ወር የዕረፍት ፈቃድ ከደሞዝ ጋር የሚለው ግዴታ እንኳንስ ተግባራዊ ሲደረግ ቀርቶ ብዙ ሠራተኞች ደሞዝ እንኳን በወቅቱ እንደማይከፈላቸው ተመላሾች ይናገራሉ።

የሠ/ማ/ጉ/ ሚ/ር የሥራ ፈላሲያንን መብት ለማስከበር ጥረት ያደርጋል። ከሥራ ፈላሲያን፣ ከወላጆቻቸውና ከቤተሠቦቻቸው የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች እየተቀበለ የግል የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎችን በማነጋገር ለማጣራትና መፍትሔ ለመስጠት የተቻለውን ያደርጋል። በዚህ በኩል የሚቀርቡለት የቅሬታ አቤቱታዎች ከዓመት ወደ ዓመት መጨመራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ። በ2004 ዓ.ም 888 ቅሬታዎች የቀረቡለት ሲሆን፣ በ2005 ዓ.ም የቀረቡት አቤቱታዎች ወደ 2,788 ጨምሯል። የሚ/ር መ/ቤቱ ቅሬታዎች የመፍታት ደረጃም ዕድገት አሳይቷል። በ2004 73% የነበረው ቅሬታ የመፍታት ደረጃ በ 2005 ዓ.ም ወደ 87% ከፍ ብሏል። ነገር ግን አሁንም በደል የሚደርስባቸው የሥራ ፈላሲያንና ቤተሠቦቻቸው ችግራቸውን በቀላሉ ለሚ/ር መ/ቤቱ ማቅረብ እንደማይችሉ ይናገራሉ። በዚህ ረገድ እንደ ፊሊፒንስ ያሉ አገራት ዜጎቻቸው በሥራ ፈላሲያንነት በብዛት ባሉባቸው አገራት በሚገኙ ቆንስሎቻቸው ውስጥ የሥራ ፈላሲያንን ሁኔታ ብቻ የሚከታተል ክፍል በማቋቋም ችግሩን ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት ባይችሉም በከፊል ለማቃለል መቻላቸው ለእኛም ትምህርት ሠጪ ተሞክሮ ሊሆን ይችላል።

ሌላው የሥራ ፈላሲያ ጉዳይ የሚመለከተው የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መ/ቤት ሲሆን መ/ቤቱም በዋናነት ለሥራ ፈላሲያን ፓስፖርት የመስጠት አገልግሎት ይሠጣል። ዜጎች ፓስፖርት ለማውጣት በመ/ቤቱ የሚጠየቁት ዋና መስፈርት ማንነታቸውን የሚገልጽ የታደሠ የቀበሌ መታወቂያ ማቅረብ ነው። ነገር ግን በአገሪቱ አንድ ዓይነት ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ገና ሥራ ላይ ስላልዋለ ከየቀበሌው ከሚታደለው መታወቂያ ካርድ ጋር ተያይዞ ብዙ ችግሮች እንዳሉ ይሠማል። የሐሠት መታወቂያ ማቅረብ አንዱ ዋና ችግር ሲሆን፣ በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎችና አካባቢዎች ያለው የተዘበራረቀ የመታወቂያ አሠጣጥ ሥርዓት ለሐሠተኛ መታወቂያ ንግድ በር ከመክፈቱ ባሻገር የኢሚግሬሽን መ/ቤት የመታወቂያዎቹን ትክክለኛነት የመለየት ሥራውን አስቸጋሪ አድርጎበታል። ከሐሠት መታወቂያ ባሻገር በትውውቅ፣ ዝምድናና ተፅዕኖ ዕድሜያቸው አነስተኛ ለሆኑ ልጆች 18 ዓመት እንደሞላቸው ተደርጎ መታወቂያ ይሠጣቸዋል። አሁንም አስገዳጅ ብሔራዊ የልደት ሠርተፊኬት ሥርዓት ገና በአገሪቱ ስላልተዘረጋ የኢሚግሬሽን መ/ቤት 18 ዓመት እንደሞላቸው የሚገልጽ መታወቂያ ይዘው የሚመጡትን ልጆች ትክክለኛ ዕድሜ የሚያጣራበት መንገድ

የለውም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የ2001 ዓ.ም ዓዋጅ በውጭ አገር ሥራ ለመሠማራት ዝቅተኛው ዕድሜ 18 ዓመት እንደሆነ ቢደነግግም፤ ዕድሜያቸው ከዚያ በጣም ያነሠ ትንንሽ ሴት ልጆች በተጭበረበረ መታወቂያ ፓስፖርት በማውጣት ለሥራ ወደ ውጭ አገራት ይጓዛሉ፡፡

የውጭ አገር የሥራ ስምሪትን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ በሠ/ማ/ጉ ሚ/ር እና በኢሚግሬሽን መ/ቤት መካከል ያለው የሥራ ቅንጅትና ትብበር አነስተኛ ይመስላል፡፡ ቀደም ሲል ተጓዦች ወደ ውጭ አገር ለሥራ ሲጓዙ ከሠ/ማ/ጉ ሚ/ር የተፈቀደላቸው ለመሆኑ የኢሚግሬሽን መ/ቤት ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ መውጫ በር ላይ ቁጥጥር ያደርግ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ አሠራር ማንኛውም ተጓዥ ሕጋዊ ፓስፖርት፣ የሚሄድበትን አገር የመግቢያ ቪዛና የአውሮፕላን ቲኬት ከያዘ የሠ/ማ/ጉ ሚ/ር ፈቃድ የለህም ብሎ መጓጓዝ መከልከል በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጠውን የዜጎች ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት መጋፋት በመሆኑ ሕጋዊነት እንደሚጎድለው ተጠቅሶ እንዲቀር ተደርጓል፡፡ ይህ የቁጥጥር ዘዴ ከቀረ በኋላ በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በኩል ከአገር የሚወጡትን ሕገ-ወጥ የሥራ ፈላሲያ መቆጣጠሪያ ሌላ መንገድ አልተበጀም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ወደ ሊባኖስ የሚደረገው የሥራ ሥምሪት ከታገደ በኋላ ወደዚያች አገር ለሥራ ለመጓዝ የሚፈልጉ ሠዎች መጀመሪያ ወደተለያዩ አጎራባች አገሮች በልዩ ልዩ ሠበቦች በመሄድ ትራንዚት በማድረግ ወደ ሊባኖስ ያመራሉ፡፡

ኢትዮጵያ ሕገ-ወጥ ፍልሠትንና የሠዎች ዝውውርን ለመቆጣጠር የምታደርገው ጥረት ያልተቀናጀና ዓለም አቀፍ የዜና አውታሮችን የሚያጣብቡ አሠቃቂ አደጋዎች በዜጎች ላይ ሲደርሱ ብቻ የሚነሳሱ ሌላ ጊዜ የሚላሉ ሆነው ይታያሉ፡፡ የተቀናጀና ሁሉን አቀፍ የሆነ የውጭ አገር የሥራ ሥምሪት ፖሊሲ በሌለበት ሁኔታ አሠቃቂ አደጋዎች ደረሡ ሲባል ብቻ ለችግሩ ትኩረት ይሠጣል፤ ወሬው ሲረሳ ደግሞ ጥረቱም የዚያኑ ያህል ይቀንሳል፡፡ ለምሳሌ የ1991ንዱ የግል የሥራ አገናኝ ኤጀንሲዎች ዓዋጅ የወጣው ኢትዮጵያውያን የቤት ሠራተኞች በሊባኖስ የሚደርስባቸው በደልና ሠቆቃ በመገናኛ ብዙሀን በስፋት መዘገቡን ተከትሎ መሆኑ ይታወሳል፡፡ መንግሥት እንጀራ ፍለጋ የሄዱ ዜጎቹ በሊባኖስ ለሚደርስባቸው በደል ትኩረት አልሠጠም የሚለው ወቀሳ ሲበረታ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ ሕገ-ወጥ የሠዎች ዝውውርን የሚመለከት ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቋመ፡፡ ኮሚቴው ባቀረበው የመፍትሔ ኃሳብ ላይ ተመስርቶ መንግሥት በዚያች አገር የሚኖሩ ዜጎቹን ጉዳይ የሚከታተል ቆንስላ ጽ/ቤት በቤይሩት አቋቋመ፡፡

ሕገ-ወጥ የሠዎች ዘውውርን ለመግታት የመጀመሪያው እርምጃ የተወሠደው በ1999 ዓ.ም የዓለምን ትኩረት በእጅጉ የሳበ አንድ ትልቅ አሠቃቂ አደጋ ከደረሠ በኋላ ነበር፡፡

በሚያዚያ 1999 ዓ.ም 33 ኢትዮጵያውያን በሕገ-ወጥ አጓጓዦቻቸው በባህር ላይ ተጥለው ህይወታቸው ማለፉን ተከትሎ በዚያኑ ዓመት በሠኔ ወር ላይ የሠ/ማ/ጉ/ሚ/ር ሠብሳቢ፣ የፍትህ ሚ/ር ደግሞ ፀሐፊ የሆኑበት ሕገ-ወጥ የሠዎች ዝውውር መከላከያ ብሔራዊ ግብረ-ኃይል ተቋቋመ:: ነገር ግን ግብረ-ኃይሉ ለ2 ዓመታት ያህል ምንም እንቅስቃሴ ሳያደርግ እንደተቀመጠ፣ በ2001 ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመጓዝ በመሞከር ላይ በነበሩ ኢትዮጵያውያን ላይ በቅርብ ቀናት ልዩነት ሁለት ሠቅጣጭ አደጋዎች ደረሱ:: ሰኔ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በኮንቴይነር ታጭቀው ወደ ደቡብ አፍሪካ ያመሩ የነበሩ 42 ኢትዮጵያውያን ታንዛኒያ ላይ በሚጓጓዙበት ኮንቴነር (የጭነት መኪና) ታፍነው ህይወታቸው የማለፉ ወሬው ገና ሳይበርድ፣ በሳምንቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመድረስ የሚጓዙ 47 ኢትዮጵያውያን ማላዊ ላይ የሚጓዙባት አነስተኛ ጀልባ ተገልብጣ ሠጥመው መሞታቸው የዓለም ዋና ዋና የዜና አውታሮች ዋና ዜና ሆኖ ሠነበተ::

የሁለቱ አደጋዎች መድረስ የሕገ-ወጥ የሠዎች ዝውውር ብሔራዊ አጀንዳ ሆኖ እንዲነሳ አደረጉት:: በዚህም ብሔራዊ ግብረ-ኃይሉ ዳግም እንዲያንሠራራ በማድረግ በሁሉም የመንግሥት የሥልጣን እርከኖች (በወረዳና ቀበሌ ጭምር) እንዲዋቀር ተደረገ:: ለጉዳዩ ይበልጥ ትኩረት ለመስጠት ሲባል ብሔራዊ ግብረ-ኃይሉ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲመራ ሲደረግ፣ የክልል ግብረ-ኃይሎች ደግሞ በክልል ፕሬዜዳንቶች እንዲመሩ ተደረገ:: ከዚያ ቀጥሎ ባሉት ወራት ከፍተኛ የሚዲያ ቅስቀሳና ሕዝባዊ ስብሰባዎች ሲደረጉ ሠነበቱ:: የሚዲያው ዘመቻ ሁለት አበይት ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ ነበር:: የመጀመሪያው ፍልሠት የሚያስከትለውን ጉዳት የችግሩ ሠላባ የሆኑ ግለሠቦችን በማቅረብና ተሞክሯቸውን በመተረክ የድርጊቱን ጎጂነት ህብረተሠቡ እንዲረዳና ግንዛቤው እንዲዳብር ማድረግ ነው:: በዚህም ምንም እንኳን ተሞክሮዎቹ የብዙዎችን ስሜት የነካ ቢሆንም ወደ ውጭ አገር ለሥራ ልባቸው የተነሳሳውን አያሌ ወጣቶች ኃሳብ ማስቀየር መቻሉ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው:: ሁለተኛው የሚዲያ ቅስቀሳ ትኩረትና መንግሥትም አፅንዖት ሠጥቶት የሚገልጸው ወጣቶቹ ወደ ውጭ ከመመልከት ይልቅ አገር ውስጥ የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያሳስብ ነው:: ይህም የተነሳሳውን የወጣቶች ልብ በማለዘብ በኩል ያን ያህል ውጤት አስገኝቷል ለማለት አያስደፍርም:: ወጣቶች ወደ ውጭ አገር እንዲፈልሱ ከሚያነሳሷቸው ምክንያቶች አንዱ በአገር ውስጥ ያለው የሥራ ዕድልና ገቢ ማነስ መሆኑ እየታወቀ አሁን ባለው ሁኔታ ‹‹ወደ ውጭ አትውጡ፣ እዚህ ያለው ይበቃችኋል›› የሚለው ምክር ለወጣቶቹ የሚዋጥ መሆኑ ያጠራጥራል::

ግብረ-ኃይሉ ሕዝባዊ ግንዛቤ ከማዳበር በተጨማሪ በተዋረድ ያሉ አስፈፃሚ አካላትን በማስተባበር ሕገ-ወጥ የሠዎች ዝውውር መግታት ላይም ትኩረት አድርጓል::

ለምሳሌ በየካቲት 2004 የወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየው የክልል ግብረ-ኃይሎች በ6 ወራት ውስጥ 12,735 በአማራ፣ 785 በአፋር፣ 7,579 በሱማሌ እንዲሁም 400 ሠዎች በቤቢሻጉል ጉሙዝ በኩል በተደራጁ ሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች ከአገር ሊወጡ ሲሉ እንደተያዙ ይገልፃል።

ከላይ እንደተገለጸው ወደ አረብ አገራት የሚደረገውን የሥራ ፍልሠት በሕግ ማዕቀፍ ማስገባትና ሕገ-ወጡን ማስቀረት የመንግሥት ፍላጎት ሲሆን፣ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ጉዞን ግን በሕግ ማዕቀፍ ለማካተት አስቸጋሪ ነው። ከመሻው ደቡብ አፍሪካ ራሷ በሥራ አጥነት ችግር የምትፈተን በመሆኑ ከኢትዮጵያ ፈላሲ ሠራተኞች በሕጋዊ መንገድ ለማስገባት እነደማትፈቅድ ይታወቃል። ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚሄዱ ኢትዮጵያውያንም ሠብዓዊ ጥበቃ (የፖለቲካ ስደተኝነትም) ስለሚጠይቁ፣ በሕግ አንጻር ያሉበትን አቋም ለመወሰን አስቸጋሪ ነው። በዋነኝነት የመንግሥት እርምጃም የሚያጠነጥነው፡ ደላሎችንና አዘዋዋሪዎችን በመቆጣጠር ላይ ነው።

## 8 ማጠቃለያ

ምንም እንኳን ፍልሠት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ቢኖረውም፤ ኢትዮጵያውያን በአስገዳጅ ሁኔታዎች ወይም በራሳቸው ፈቃደኝነት ከአገር በመውጣት በሠፊው በውጭ አገራት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለረጂም ጊዜ መኖር የጀመሩት ከድህረ አብዮት (1966) በኋላ ነበር። የ1966ቱን የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ በተከሰተው ያለመረጋጋትና ደም አፋሳሽ ግጭት ሳቢያ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ድንበር አቋርጠው ተሠደዋል። አብዛኛዎቹ ስደተኞች ወደ ሠሜን አሜሪካና ምዕራብ አውሮፓ በማምራት ኑሯቸውን በምዕራቡ ዓለም መስረተዋል። ከእነዚህ ስደተኞች መካካል በቁጥር ትንሽ የማይባሉት የተቀባይ አገራቱን ዜግነት መውሰዳቸውም ይታወቃል። እነዚህ ኢትዮጵያውያን በማደግ ላይ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ዲያስፖራ ማህበረሠብ መስራች ተብለው ሊጠሩ ይቻላሉ።

ከ1983ቱ የደርግ መንግሥት ውድቀት በኋላ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አገር ለቀው ከመፍለሳቸውም ሌላ የኢሕአዴግ መንግሥት የመዘዋወር መብትን በመፍቀዱ በርካታ ኢትዮጵያውያን ከአገር ለመውጣት ችለዋል። ከላይ እንደተብራራው በድህረ 1983 ዓ.ም ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሠርቶ ለማግኘት ከአገር መውጣት ጀምረዋል። ምንም እንኳን በድንበር ዘለል ፍልሠት የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እያደገ ቢመጣም፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ፍልሠት ውስጥ ያላት ድርሻ ግን በጣም ውስን ነው። የአፍሪካ የፍልሸት ምጣኔ 1.9 በመቶ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ድርሻ ግን 0.6 በመቶ ይገመታል። ወደፊት ግን በትምህርት መስፋፋት፣ በሥራ አጥነት ችግር፣ በተስፋ መቁረጥ፣ ውጭ ሠርቶ የተሻለ ጥሪት የመያዝ

ፍላጎትና ሌሎች ምክንያቶች ከኢትዮጵያ የሚወጣው ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ እንደሚሄድ መገመት ይቻላል፡፡

ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገራት የሚደረገው የሥራ ፍልሠት ሕጋዊና ሕገ-ወጥ ባህርያት ይታዩበታል፡፡ ከላይ በዚህ ክፍል እንደተገለጸው ሕጋዊ የሥራ ፍልሠት የሚደረገው ወደ አረብ አገራት ሲሆን፤ ተጓዦቹም በአብዛኛው ሴት የቤት ሠራተኞች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ሠራተኞች ሕጋዊ የሥራ ውል ገብተውና ውላቸውም በሠ/ማ/ጉ ሚኒስቴር ተመዝግቦ ወደ የሚሠማሩበት አገራት ቢሄዱም በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ሳቢያ በሥራ ውላቸው የተቀሱትን መብቶችና አጠቃላይ ሠብዓዊ መብታቸውን ማስከበር አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ አንደኛው፣ በተቀባይ አገራት የሚተገበረው የውጭ ሠራተኞችን በቀጣሪዎቻቸው ቁጥጥር ስር የሚያስገባው የከፋላ (ስፖንሰርሺፕ) ሥርዓት ሲሆን ሥርዓቱ ፈላሲ ሠራተኞች በተቀባይ አገራት (የሥራ) ሕግ እንዳይታቀፉ በማድረግ ለመብት ጥሠት በር ይከፍታል፡፡ ሁለተኛው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ አገራት በርካታ ዜጎቻቸውን ለሥራ ቢልኩም የዜጎቻቸውን መብት ለማስከበር የአቅም ውስንነት ይታይባቸዋል፡፡

ወደ አረብ አገራት የሚደረገውን ሕገ-ወጥ ፍልሠት ሕጋዊውን በማጠናከርና ሥርዓት በማስያዝ መቀነስ ይቻላል የሚል ግንዛቤ ቢኖርም፤ እርሷ ራሷ ስር የሰደደ የሥራ አጥነት ችግር ያለባት ወደሆነችው ደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን ጉዞ ሕጋዊ ማድረግ የማይቻል ነው፡፡ ስለዚህም መንግሥት ያለው አማራጭ የህብረተሠቡን ግንዛቤ መጨመርና የደላሎችንና አዘዋዋሪዎችን እንቅስቃሴ በመቆጣጠር ፍልሠቱን ሙሉ ለሙሉ ማቆም እንኳን ባይቻል ለመቀነስ መሞከር ነው፡፡

ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መፍለስ የሠው ልጅ መሠረታዊ ባህርይ ከመሆኑ አንፃር፤ ፍልሠትን መግታት የማይቻል ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍን ፍልሠት በተመለከተ ሁለት ጽንፍ ኃሳቦች ይንጸባረቃሉ፡፡ በአንድ በኩል በአገሪቱ ከፍ ያለ ቁጥር ያለው ወጣት ሥራ አጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ስደት/ፍልሠት ብዙ ፈተናዎች (አሠቃቂ አደጋዎች፣ ብርቱ የመብት ጥሰቶች) የሉበት ቢሆንም፤ ከአገር መውጣት ለመለወጥ (ከድህነት ለመውጣት) ቁልፍ መሣሪያ እንደሆነ እየተቆጠረ ነው፡፡ ይህን ኃሳብ የሚያንፀባርቁ ወገኖች የፍልሠት ጎጂ ጎኑ አይታያቸውም፡፡ በሌላ በኩል ፍልሠት ያሉትን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በመዘንጋት ስለ ጉዳቱ ብቻ መመልከት የሚፈልጉ የሕብረተሠብ ክፍሎች አሉ፡፡ ዕውነታው ግን የሚያሳየው ፍልሠት በጎም ጎጂም ውጤቶች ያሉት እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የመንግሥትና የማህበራዊ ተቋማት ሚና የፍልሠትን ጎጂ ባህርያት መቀነስና የሚሰጠውን በጎ ውጤቶችን ማጎልበት መሆን ይገባዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም ፍልሠት የሚያመነጨውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም (ለምሳሌ የውጭ ምንዛሬና ኢንቨስትመንት) በመገንዘብ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን የሚያበረታቱ ዕርምጃዎች ወስዷል። የሥራ ፍልሠትን በተመለከተ ግን የመንግሥት ፖሊሲዎችና ዕርምጃዎች በአብዛኛው ለወቅታዊ ችግሮች (ቀውሶችን) መልስ ለመስጠት የዘለሉ ናቸው ለማለት አያስደፍርም። አሁንም ድረስ የሥራ ፍልሠትን ለዘለቄታው ለልማት ማዋል የሚያስችል ፖሊሲ በሥራ ላይ አልዋለም። በዚህ ክፍል እንደተብራራው መንግሥት ያወጣቸው የሠራተኛ ልውውጥ ሕጎች ሥልጠናንና ብቃት የማረጋገጥ ኃላፊነት ለግል የሥራ ኤጀንሲዎች የሚሰጡ ነበሩ። የሥራ ፍልሠትን ለማስተዳደር ኃላፊነት የተጣለበት የሠ/ማ/ጉ ሚኒስቴርም ጉዳዩ ከፍ ያለ ጫና አሳድሮበት ቆይቷል። በዚህ ክፍል እንደተቀሰው በ2006 ዓ.ም ሳዑዲ አረቢያ በኢትዮጵውያን ፈላሲ ሠራተኞች ላይ የደረሰው እንግልትና ወደ 160 ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን ከሳዑዲ አረቢያ ተባርረው መመለስ፤ መንግሥት የፍልሠት ችግሮችን ለመወጣት ያለው ዝግጁነት ውስን እንደሆነ አሳይቷል። ከ2006ቱ ቀውስ በኋላ መንግሥት የወሰደው አንዱ ዕርምጃ ወደ አረብ አገራት የሚደረግ የሥራ ፍልሠት በተቀባይ አገራትና በኢትዮጵያ መካከል ሁለትዮሽ የሠራተኛ ልውውጥ ስምምነት እስኪፈፀም ማገድ ነበር። ከልምድ እንደታየው ግን ሕጋዊው ጉዞ በሚታገድበት ጊዜ በአዘዋዋሪዎችና በደላሎች አማካይነት ኢትዮጵያውያን ሶስተኛ አገር (በአብዛኛው ኬንያንና ሱዳንን) በመጠቀም ወደታገዱት አገሮች በገፍ እንደሚጓዙ ነው።

በአጠቃላይ ሕገ-ወጥ ፍልሠትን መግታት እንኳን ባይቻል በሕጋዊ መንገድ ለሚሠማሩ ዜጎች የተሻለ ሥልጠና ዝግጅት፤ ክፍያና ጥበቃ እንዲያገኙ በማድረግ ሕገ-ወጥ ፍልሠቱን መቀነስ ይቻላል። መንግሥት ደላሎችና አዘዋዋሪዎችን ለመቆጣጠር የሚያደርገው ጥረት ተገቢ ቢሆንም፤ ዘለቄታዊ የሆነ የሥራ ፍልሠት የሚመራበትን ፖሊሲ ማውጣትና መተግበር አስፈላጊና ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ጉዳይ እንደሆነ መረዳት ያሻል።

### ዋቢ መፃህፍት

Bales, Kevin. 2012. Disposable people : new slavery in the global economy. Berkeley: University of California Press.

BBC, British Broadcasting Corporation. 2013. " 9 April 2013 Last updated at 19:06 GMT

Black, Richard, Crush, Jonathan, Peberdy, Sally. 2006. Migration and Development in Africa: An Overview. African Migration and Development Series No. 1.Southern African Migration Project.

Emebet, Kebede. 2002. "Ethiopia: An assessment of the international labour migration situation, The case of female labour migrants." in GENPROM Working Paper No. 3. Geneva: Gender Promotion Programme, International Labour Office.

Fernandez, Bina. 2010. "Cheap and disposable? The impact of the global economic crisis on the migration of Ethiopian women domestic workers to the Gulf." Gender & Development 18(2):249-62.

Fransen, Sonja, and Katie Kuschminder. 2009. "Migration in Ethiopia: History, Current Trends and Future Prospects." in Paper Series: Migration and Development Country Profiles. Maastricht Maastricht Graduate School of Governance.

Horwood, Christopher (2009) In Pursuit of the Southern Dream: Victims of Necessity - Assessment of the irregular movement of men from East Africa and the Horn to South Africa. International Organization for Migration. Geneva. Switzerland

HRW, Human Rights Watch 2008. “As If I Am Not Human” Abuses against Asian Domestic Workers in Saudi Arabia. New York: HRW.

ILO. 2010. International labour migration. A rights-based approach

IMF, Interntional Monetary Fund 2013. "The Federal Democratic Republic of Ethiopia Staff Report for the 2013 Article Iv Consultation:

Kevin Tessier (1995) The Challenge of Immigration Policy in the New South Africa.

National Bank of Ethiopia (NBE). 2009. National Bank of Ethiopia Annual Report. Addis Ababa: NBE. Available at: http://www.nbe.gov.et/publications/annualreport.htm.

Reinert, Kenneth A. 2005. Ethiopia in the World Economy: Trade, Private Capital Flows, and Migration. International Conference on African Development Archives. Paper 83. http://scholarworks. wmich.edu/africancenter_icad_archive/83

World Bank. 2013. "Migration and Development Brief 20, April 2013." Washington, DC: World Bank, available at https://blogs.worldbank.org/peoplemove/category/tags/migration-and-development-briefs.

Yoesph Endeshaw, MebratuGebeyehu and BeleteReta. 2007. Assessment of Trafficking in women and children in and from Ethiopia. International Organization for Migration.

# ወጣትና ስፖርት በኢትዮጵያ

## ገነነ መኩሪያ

### 1 መግቢያ

ስፖርት ማንኛውም ግለሠብ ዕድሜና ጾታ ሳይገድበው ጤንቱን ለመጠበቅና ለመዝናናት፣ አካሉን ለመገንባትና አዕምሮውን ለማበልጸግ እንዲሁም አቅሙንና ችሎታውን ለመመዘን በግሉ ወይንም በጋራ በተደራጀና ባልተደራጀ መልክ በማንኛውም ጊዜና ቦታ የሚያከናውነውን የተለያየ የአካል እንቅስቃሴን ያጠቃልላል።

የስፖርት እንቅስቃሴ መሠረቱ የሰው ልጅ ብሎም ህብረተሠብ ነው። በስፖርት እንቅስቃሴ መሳተፍ ጤናማ አካልና አዕምሮ ከማጎናፀፉ በተጨማሪ ማኅበራዊ ግንኙነትን በማጠናከር በኩል መተዋወቅን፣ መቀራረብን፣ አብሮ መኖርና መሥራትን እንዲሁም ቤተሠባዊ ፍቅርን ያጠናክራል። ይህ ግንኙነት እየዳበረ በመሄድ ብሔር፣ ብሔረሠቦችንና ሕዝቦችን በማቀራረብ ግንኙነታቸው እንዲዳብርና አንድነታቸው እንዲጠናከር ያደርጋል።

በስፖርት እንቅስቃሴ የተገነባ አካልና አዕምሮ በኢኮኖሚው ዘርፍ የተሻለ ለማምረት በሚደረገው ጥረት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሲያበረክት በሌላ በኩል ስፖርት ጤንነትን ለመጠበቅ ስለሚረዳ ለህክምናና ለመድኃኒት የሚወጣውን ወጪ ይቀንሳል። ሠፊ መሠረት ካለው የስፖርት እንቅስቃሴ ምርጥ ስፖርተኞችን ለማፍራት ስለሚቻል በእነርሱ አማካይነት በዓለም አቀፍ ውድድሮች በመሳተፍ አገር እንድትታወቅና ከሌሎች አገሮች ጋር የሚኖራት ግንኙነት እንዲጠናከር ያደርጋል።

የአገራችን የስፖርት ሁኔታ ሲቃኝ ዘመናዊ ስፖርት ወደ አገራችን ከገባ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ አስቆጥሯል። በዚህ የረጅም ጊዜ ታሪክ በአገራችን በመዘውተር ላይ የሚገኙት የስፖርት ዓይነቶች በርካታ ቢሆኑም ዕድገቱ ሲመዘን ግን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ለዚህም ትልቁ ችግር የአደረጃጀትና አመራር እንዲሁም የአመለካከትና የአቅጣጫ ነው። የእስከዛሬው የአገራችን የስፖርት አደረጃጀትና አመራር ሕዝባዊ መሠረት ያልነበረው በመሆኑ በየጊዜው ሲፈርስና ሲገነባ ቆይቷል። የትኩረት አቅጣጫውም ሠፊውን የህብረተሠብ ክፍል በስፖርት በማሳተፍ ምርጥ ስፖርተኞችን ማፍራት ሳይሆን በተለያየ መንገድ በራሳቸው ጥረት ብቅ ያሉትን

ምርጥ ስፖርተኞች በማሰባሰብ በውድድር ስፖርቶች ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ ማካሄድ ነበር።

ይህ በምርጥ ስፖርተኞችና በጊዜያዊ ውጤት ላይ ያተኮረ አመለካከት ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት የሚያስችል ሠፊ መሠረት ስለሌለው ውጤቱም በየጊዜው ሲዋዥቅ ይታያል። ህብረተሠቡ በስፖርት የሚያደርገው ተሣትፎ ውስን መሆን፣ የትምህርት ቤቶች ስፖርት መዳከም፣ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች፣ ትጥቅና መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖር፣ የሠለጠነ ባለሙያ እጥረት የአገራችንን የስፖርት ችግር ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል።

እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍና ስፖርትን በአዲስ አስተሳሰብና አቅጣጫ ለመምራት ህብረተሠቡን መሠረት ያደረገ የስፖርት እንቅስቃሴ ማራመድ አማራጭ የሌለው መንገድ በመሆኑ ሠፊ መሠረት ካለው የሕዝብ ተሳትፎ በመነሳትና ተጠቃሚነቱን በማጎልበት ምርጥ ስፖርተኞችን በማፍራት አገራችን በአህጉርና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ተገቢውን ደረጃ እንድታገኝ ለማድረግ በአለው ወሳኝነት የስፖርት ፖሊሲ ማውጣት አስፈልጓል። በመሆኑም መንግሥት በ1990 ዓ.ም. ስፖርቱ የሚመራበትን አቅጣጫ የሚጠቁም፣ የሚተገበርባቸውን መንገዶች የሚዘርዝርና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ሚና የሚያሳይ ብሔራዊ የስፖርት ፖሊሲ አውጥቶ ተግባራዊ አድርጓል። ከፖሊሲው እንደምንረዳው ስፖርት ለወዳጅነት፣ ለጤንነት ወዘተ. አስፈላጊ እንደሆነና የስፖርት እንቅስቃሴ ለማድረግ የማዘወተሪያ ሥፍራዎች አስፈላጊ መሆናቸውንና እንዲሁም በቂ አስተዳደራዊና ድርጅታዊ መዋቅር እንደሚያስፈልግ እንረዳለን።

ሆኖም የስፖርት ፖሊሲው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ካላቸው ሌሎች ፖሊሲዎች ጋር ካልተጣመረ ፖሊሲ መኖሩ ብቻ በራሱ በቂ አይሆንም። በመሆኑም የአገሪቱ የስፖርት ፖሊሲ ከሌሎች ተዛማች ፖሊሲዎች (የትምህርት፣ የጤና፣ የመሬት ….) ጋር የመጣጣም እና አለመጣጣም ሁኔታ ትልቁ ጥያቄ ሊሆን ይገባል።

ይህ ፅሑፍ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ሁልጊዜ እውነት መሆናቸውን ይፈትሻል። ነገር ግን በዚህ ጽሁፍ የሚነሱ ኃሳቦች የጥናት ዝርዝር ውጤቶች ሳይሆኑ በባለሙያዎች በዝርዝር እንዲጤኑና ስፖርቱን በአንድ አቅጣጫ ብቻ በመተንተን ሙሉ ምሥሉን እንዳናይ የሚያደረጉንን ሁኔታዎች ለመቅረፍ የስፖርት ምሁራን ዘርዘር ያለ ጥናት እንዲያቀርቡ ለማሳሰብ ያለሙ ናቸው።

# 2 የስፖርት ጠቀሜታ

## 2.1 ስፖርት ለወዳጅነት

ስፖርት ወንድማማችነትን ያመጣል። መቀራረብ ይፈጥራል። ብዙ አገሮችም የመቀራረብ በር የሚከፍቱት አብዛኛውን ጊዜ በስፖርት ግንኙነት ነው። የኮሌጆችና የት/ቤቶች ዓመታዊ ስፖርት ሲካሄድ ወጣቶች ከውድድር በኋላ የሚያሳዩት መቀራረብ ፍቅር ያለበትና ወዳጅነትን የሚያጠናክር ነው። በተለይ ምሽት ላይ ሁሉም የየራሱን ባህል የሚያንፀባርቅ ሙዚቃና ጭፈራ ላይ የሚያሳየው ትዕይንት እና አንዱ ከሌላው ጋር የሚያደርገው የባህል ልውውጥ ለወጣቱ ልዩ ትርጉም አለው።

በስፖርት የሚገኘው ወዳጅነት ዘላቂነት ያለውና የማይረሳ ነው። ወዳጅነቱም ተጠናክሮ አብሮ ለመዝለቅና በግንኙነት ለመተሳሰር ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ኢራቅና ኢራን በጦርነት ላይ በነበሩ ጊዜ በዓለም የጦር ሠራዊት ሻምፒዮና ላይ በቅርጫት ኳስ ውድድር ተገናኝተው ሠላማዊ ውድድር አድርገዋል። በጦርነት ቢተናነቁም በስፖርት ሠላምን አሳይተዋል። ስፖርት ሠላምን የማውረድ ኃይል አለው። በሌላ በኩል ረብሻንም ይቀሰቅሳል። በጥር 2005 ዓ.ም. በግብፅ በፖርት ሠዒድ ከተማ በተቀናቃኝ ደጋፊዎች መካከል በተነሳ ረብሻ 74 የአልሃሊ ደጋፊዎች በመሞታቸው የአገር ውስጥ ውድድር መታገዱ ይታወሳል። ይኸውም ውድድሩ ቢካሄድ ፀብ ይነሳል በሚል ነው። ይኸውም እግር ኳስ ሠላምን ማምጣት ብቻ ሳይሆን ረብሻን ይቀሰቅሳል በሚል ሁከት እንዳይነሳ ታግዷል።

በተለይ ወጣቶች በስፖርት ወዳጅነትን ለመፍጠር የሚሳዩት ተነሳሽነት በአካባቢው ህብረተሠብ ዘንድ ጥሩ ስሜትን የሚፈጥር ነው። የስፖርት ቤተሠቡም ያለምንም ልዩነት ለወጣቶች የሚሰጠው ድጋፍ ሞራላቸውን ከፍ ያደርገዋል። ወጣቶች ያለምንም እገዳ ከሚፈልጉት ጋር ለመጫወትና ወዳጅነትን ለመፍጠር ነፃ የሆነ ግንኙነት ይፈልጋሉ። በጥቅሉ ስፖርት በወጣቱ ላይ የሚያመጣው ወዳጅነት ሠፊና ጥልቅ ነው።

## 2.2 ስፖርት ለጤንነት

ስፖርት ጤንነትን ለመጠበቅ አካልን ለማዳበር በስነ-ልቦና ብቁ ዜጋ ለማፍራት አይነተኛ መሣሪያ ነው። በተለይ ጤንነትን ለመጠበቅ ስፖርት ትልቅ ድርሻ ያለው ሲሆን የህክምና ሰዎችም ስፖርትን እንደ መድኃኒት የሚያዝዙበት ጊዜ አለ። ስፖርት ለጤንነት የሚለው መርህ ጤናን ከማሻሻል ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው። ስፖርት ለጤንነት የሚለው መርህ ለጤና ከሚሰጥ ጠቀሜታ አኳያ 'ለጤንነት' የሚለው በትልቁ ይገልፀዋል።

የስፖርት አንዱ መገለጫ ውድድር ነው። በተለይ ወጣቶች በስፖርት ውድድር ብቁ ሆነው ለመገኘት፣ ብቁ ሆነው በመገኘታቸው ውስጥ በውድድር አሸናፊ በመሆን ሙገሳ ለማግኘት በገንዘብም ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት የሚያደርጉበት ነው። ስፖርት አንዱ መገለጫው ውድድር ከሆነ ለውድድር የተሻለ ለመሆን ብቁ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል። በሠፈር ህፃናቶች የሚያደርጉት የእርስ በርስ ግጥሚያ አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ፤ ሌላው ደግሞ ላለመሸነፍ የውድድር ሂደት ውስጥ ይገባሉ።

እስከትልልቆቹ ቡድኖች ድረስ በማሸነፍ ላይ የተመሠረተ ፉክክር ይደረጋል። በሩጫም አንዱ ሌላውን ለመቅደም ይሮጣል። ውድድር ማለት ይህ ነው።

## 2.3 ስፖርት ለመዝናኛ

በዓለም በአብዛኛው ተዘውታሪና ተፈቃሪ እንዲሁም የሰውን ስሜት መግዛት የቻለው እግር ኳስ ነው። አብዛኛው ወጣት የሚገኘው እዚህ እግር ኳሱ ውስጥ ነው። የሚጫወተውም የሚደግፈውም እኩል የማሸነፍ ስሜት አላቸው። እግር ኳስ ጤናን መጠበቂያ ከዚያም አልፎ መዝናኛ እንደሆነ ይታመንበታል።

እግር ኳስ መዝናኛ በመሆኑ በዓለም ተወዳጅ ነው። የጦርነት ፊልም ስናይ ያዝናናል። እንዲያውም ገቢ ያስገባል። በሆሊውድ ውስጥ የሚሠሩ የጦርነት ፊልሞች ከፍተኛ ገቢ ያስገኛሉ። እነዚህ የጦርነት ፊልሞች የጦርነትን ገፅታ እንጂ ጦርነት አይደሉም። ግን ተመልካቹን ያዝናናሉ። እግር ኳስ ግን መዝናኛ ብቻ ነው። አደጋ የለውም። አንዳንዴ ግን በስፖርት በተለይ በእግር ኳስ የሚፈጠረው ረብሻ ብዙ ችግር ሲፈጥር ይስተዋላል።

# 3 ስፖርት በኢትዮጵያ

## 3.1 የኢትዮጵያ ስፖርት አጭር ታሪክ

አንድ ጊዜ ታዋቂውን የስፖርት ሰውና ጋዜጠኛና ፍቅሩ ኪዳኔን ባወራሁት ጊዜ እንዲህ ብሎኝ ነበር። “አንድ የስፖርት ፀሐፊ ኢትዮጵያ በጥንታዊ ኦሎምፒክ ከክርስቶስ ልደት በፊት አቴና ላይ ተሳትፋ እነደነበር የሚያሳይ ፍንጭ እንዳገኘ ነግሮኛል። እንደ መነሻ የሚሆነው ጥንት ኢትዮጵያ በንግድ ከግሪክ ጋር ግንኙነት ፈጠራ ስለነበር በስፖርት መሳተፏን የሚያረጋግጡ ፍንጭ እንዳለውና በዚህም ላይ ጥናት እያደረገ መሆኑንና፤ ወደፊት መፅሐፍ እንደሚያሳትም ነግሮኛል” በማለት አጫውቶኛል።

ይህንን ለጊዜው በአፈ-ታሪክነት እንያዘውና ዘመናዊ ስፖርት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ1916 ዓ.ም ነው። ጃንሆይ አልጋ ወራሽ እያሉ እ.ኤ.አ በ1924 ዓ.ም ፓሪስ

ኦሎምፒክ ላይ በእንግድነት ተገኝተው ነበር። ከዚያ ሲመለሱ ኢትዮጵያ በኦሎምፒክ እንድትሳተፍ ዕቅድ ያዙ። አንድ ቡና ነጋዴ ወደ ቤልጂየም ሲሄድ እግረ-መንገዱን እንዲያስመዘግበን ነገሩት። ሰውዬው ሲመለስ "አንመዘግባችሁም ብለዋል" ብሎ ለንጉሡ ነገራቸው። በወቅቱ የኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዜዳንት ቤልጂየማዊ ስለነበረ በአዲስ አበባ ያለውን የቤልጅየም አምባሳደርን አስጠሩትና ጉዳዩን ጠየቁት። አምባሳደሩም ኢትዮጵያ "ዘመናዊ ስፖርት ስለማታውቅ በኦሎምፒክ መሳተፍ አትችልም። በኦሎምፒክ ለመሳተፍ ቢያንስ 5 ፌዴሬሽን መመዝገብ አለባቸው" ተብሏል ሲል አሳወቃቸው።

ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ በእግር ኳስ፣ በአትሌቲክስና በቦክስ የኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ አባል ሆንን። ይህም በኦሎምፒክ እንድንሳተፍ ረዳን። አበበ ቢቂላ በሮም ሲያሸንፍ በስፖርቱ ውስጥ ትልቅ መነቃቃት ተፈጠረ። ይህ በሆነ በዓመቱ ኢትዮጵያ የ3ኛ አፍሪካ ዋንጫን አሸነፈች። እስካሁን ኢትዮጵያ በኦሎምፒክ በቦክስ፣ በብስክሌትና በአትሌቲክስ ትሳተፋለች። ግን ውጤት ያላት በአትሌቲክሱ ብቻ ነው። ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ውድድር ውጤታማ የሆነችው በረጅም ርቀት ሩጫ ብቻ ነው። በሌሎች ልዩ ልዩ ስፖርቶች የታየው ውጤት ደካማ ነው። በአገር ውስጥ ውድድር ደረጃ የመኢሠማ፣ የተማሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲዎች፣ የከነማ፣ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊት ውድድሮች በቋሚነት ባይሆንም አንድ ጊዜ እየተቋረጡ ሌላ ጊዜ እየቀጠሉ ይካሄዳሉ።

ክለቦች በአብዛኛው እግር ኳስን ተገን አድርገው ነው የሚቋቋሙት። በ1975 ዓ.ም በወጣው ደንብ አንድ የእግር ኳስ ክለብ ሲቋቋም 5 የተለያዩ ሌሎች ስፖርቶችን መያዝ ግዴታው ስለነበረ በቅርጫት ኳስ፣ በቦክስ፣ በመረብ ኳስ፣ በቴኒስ ከ30 እስከ 50 የሚሆኑ ክለቦች በአዲስ አበባ ብቻ ይገኙ ነበር። አሁን በእነዚህ ስፖርቶች ከ5 እና 6 የበለጡ ክለቦችን ማግኘት አይቻልም። በኢትዮጵያ ውስጥ 21 የሚሆኑ ፌዴሬሽኖች አሉ። የእነዚህ ፌዴሬሽኖች ፕሬዜዳንቶች የኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል ናቸው። ሶስት ክለብ ብቻ ይዘው ፌዴሬሽን ተብለው የተቀመጡ አሉ። በአንድ ወቅት የሚያወዳድረው ክለብ ሳይኖረው ፌዴሬሽን ተቋቁሞ፤ በጀት መድቦ፤ ውድድር ሳያደርግ ጠቅላላ ጉባዔ የሚያደርግ ነበር። ብዙ ክለቦች የእግር ኳስ ብቻ በመሆናቸው ሌሎች ስፖርቶች እየተረሱ ነው።

አንጋፋውን የጊዮርጊስ ክለብን የመሠረቱት አየለ አትናሽና ጆርጅ ዱካስ የተባሉ የተፈሪ መኮንን ወጣት ተማሪዎች ነበሩ። አየለና ጆርጅ ሠፈራቸው ዶሮ ማነቂያ ነው። ጎረቤትማማቾች ናቸው። አብሮ አደግ ሲሆኑ ከልጅነታቸው ጀምሮ አፈር ፈጭተው ያደጉ የማይለያዩ ጓደኛማቾች ናቸው። እኔ በ1988 ዓ.ም ሳናግራቸው በ60 ዓመት ዕድሜያቸው ላይ እንኳን እንደልጅነታቸው ነበር የሚዋደዱትና

የሚጨዋወቱት፡፡ ጆርጅ ግሪካዊ ሲሆን የቆዳው ነጭነት በጣም የጎላ ነው፡፡ ጣሊያን እንደገባ ለልምምድ የጊዮርጊስ ተጫዋቾች ወደሜዳ ሲሄዱ አየለና ጆርጅ ኳስ ይዘው ተቃቅፈው ከሌሎቹ ገንጠል ብለው እየሄዱ ነበር፡፡ አንድ የጣሊያን አለቃ አስጠራቸውና በአስተርጓሚ ወዴት እንደሚሄዱ ጠየቃቸው፡፡ ኳስ ለመጫወት እንደሆነ ነገሩት፡፡ "ከእንግዲህ በኋላ አንተ ከእሱ ጋር መጫወት አትችልም" በማለት ነገራቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ጥቁርና የነጭ ተጫዋቾችን የሚለየውን ደንብ እየተረቀቀ መሆኑን ወጣቶቹ አልተረዱም ነበር፡፡ ወጣቶቹ እንዲለያዩ የሚደረጉት በቆዳቸው ቀለም ነበር፡፡

አየለና ጆርጅ በነገሩ በጣም ተወያዩ፡፡ ትርጉሙም ሊገባቸው አልቻለም፡፡ የጊዮርጊስ ክለብ የሚተዳደረው ተጫዋቾቹ በሚያዋጡት ገንዘብ ነው፡፡ በግቢያቸው ዶሮም በግም እያረቡ ለክለቡ ተቀማጭ ያደርጋሉ፡፡ እነ አየለ ግቢ ጥቁር በግ ነበር፡፡ የእሷ እኩያ የምትሆን ነጭ በግ አየለ አመጣና ከዚያች ጥቁር በግ ጋር አጣመራት፡፡ በጎቹ በጣም ጓደኛ ስለነበሩ አብረው ነው የሚበሉትና የሚውሉት፡፡ እነዚህ በጎች ከቆዳቸው በስተቀር ምንም ልዩነት የላቸውም፡፡ በጎቹን መለየት የሚችለው ሰው ነው፡፡ አየለና ጆርጅ አንዳንዴ በጎቹን እየነዱ ጣሊያኖች በሚበዙበት አካባቢ ይዘዋወራሉ፡፡ ይህ ኃሳብ ዘረኝነትን ለመቃወምና ለመታገል ለበኋላ መነሻ ሆኗቸዋል፡፡

## 3.2 በዓለም የስፖርት እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ሚና

### በኢትዮጵያ ሕንድ ለእንግሊዝ ጥቁር አልነበረም

ጣሊያን ከአገር ከወጣ በኋላ በስፖርት ያለውን ወዳጅነት ለማጠንከርና የቀለም ልዩነት እንዳይኖር የጊዮርጊስ ክለብ ተጫዋቾች ደንብ አረቀቁ፡፡ ፎርቱቱዲዮ ከተባለ የጣሊያን ኮሚኒቲ ጋር በመጫወት ጣሊያን አውጥቶት የነበረውን ደንብ አፍርሰው በር ከፈቱ፡፡ ህጉንም አርቅቀው በኢትዮጵያ የሚኖሩ የውጪ ዜጎች በየኮሚኒቲያቸው እንዲወያዩበት ጥሪ ተደረገ፡፡ ያለምንም ልዩነት፤ ገዢና ተገዢ በሌለበት የቀለም ልዩነት ሳይኖር መጫወት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ከብዙ ክርክር በኋላ ስምምነት ላይ ደረሱ፡፡

ቡድን ያላቸው እንዲመዘገቡ፤ ቡድን የማያሟሉ በዳኝነትና በኮሚቴነት እንዲያገለግሉ ተደረገ፡፡ የሙከራ ውድድር በ1935 ዓ.ም ሲደረግ ብዙዎቹ ተሳተፉ፡፡ ሕንድ ከእንግሊዝ ቅኝ አስተዳደር ነፃ የወጣው በ1940 ዓ.ም ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በስፖርት ሕንድ ከእንግሊዝ ጋር እኩል ድምፅ ነበረው፡፡ ገዢና ተገዢ አልነበሩም፡፡ ሕንድና እንግሊዙ እኩል ነው ሜዳውን የቆፈረው፡፡ የሕንድ ዳኛ የእንግሊዙን ተጫዋች በውሳኔ ከሜዳው የማባረር መብት ነበረው፡፡ በወቅቱ በጎረቤታችን ኬንያ ውስጥ ሕንድና ኬንያዊው ለእንግሊዙ ጥቁር ነበሩ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ሕንዱ ለእንግሊዝ

ጥቁር አልነበረም፡፡ ይህም ነፃነት የተገኘው ወጣቶች በስፖርቱ ባደረጉት ተጋድሎ ነው፡፡

**ቱርክና አርመን**

ቱርክ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ብዙ የአርመን ዜጎችን እንደጨፈጨፈና በዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠያቂ እንደሆነ በታሪክ ይነገራል፡፡ በ1935 ዓ.ም ቱርክና አርመን በኢትዮጵያ ውስጥ ተቻችለውና ተስማምተው እንዲጫወቱና አንዱ ሌላውን እንዲያከብር ተደርጎ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ፋሺስት ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰው ጭፍጨፋ ታሪክ የሚረሳ አልነበረም፡፡ ያ ደም ሳይደርቅ፣ ቂሙ ሳይበርድ፣ ጥላቻው ሳይጠፋ አበሻው ከጣሊያን ጋር ተቻችሎ እንዲጫወት ተደርጎ ነበር፡፡ ይህን ሁሉ መቀራረብ የፈጠሩት የኢትዮጵያ ወጣቶች ናቸው ፡፡ በወቅቱ በስፖርት ጥላቻን ሳይሆን መቀራረብንና ወዳጅነትን መፍጠር ትልቅ ቦታ ያለው መሆኑን ለዓለም ለማሳየት ጅማሬያቸውን የተከሉበት ጊዜ ነበር፡፡ በ1936 ዓ.ም መደበኛው የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ሲጀመር እንግሊዝን በመወከል ብሪትሽ ሚሊተሪ ሚሽን፣ ጣሊያንን በመወከል ፎርቲቲዲዩ፣ ግሪክን በመወከል ኦሎምፒያኮስ፣ አርመንን በመወከል አራራት አርመን፣ ኢትዮጵያን በመወከል ቅ/ጊዮርጊስ ተሳታፊ ነበሩ፡፡

ፌዴሬሽኑን በኮሚቴነት የሚመሩት የ18 አገር ዜጎች ነበሩ፡፡ በወቅቱ ሴኔጋል በፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ስር ስለነበረች የራሷ የሆነ ፌዴሬሽን የላትም ነበር፡፡ የፈረንሳይ ቅርንጫፍ ነው የሚባለው፤ የኬንያም የእንግሊዝም ቅርንጫፍ ነበር የሚባለው፡፡ ብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች የራሳቸው ፌዴሬሽን ስለሌላቸው በገዢዎቻቸው ነበር የሚወከሉት፡፡ ከነጮችም ጋር ተቀላቅለው መጫወትም አይችሉም ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ግን ኢትዮጵያ ነፃ የሆነ ፌዴሬሽን ነበራት፡፡ ወዳጅነትንና ፍቅርን ለማጠንከር የሁሉንም አገር ዜጎችን በፌዴሬሽኑ ውስጥ በማስገባት የቀለም ልዩነት ሳይኖር በጋራ አሰባስቦ ነበር፡፡ ይህም በስፖርት መቻቻልን በመፍጠር በሌላው አገር ያልታየ በኢትዮጵያ ብቻ በተግባር የዋለ በመሆኑ በወቅቱ ዘረኝነትን በመታገል ለዓለም ሞዴል ነን ለማለት እንችላለን፡፡ የፈረንሳይ ዜጋ ሴኔጋል ውስጥ ገዢ መሆን ይችላል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ይህንን ለማድረግ ሕጉም አይፈቅድለትም፡፡ እንግሊዛዊ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከጥቁሮች ጋር ለመጫወት ፍቃደኛ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ግን ይህን ማድረግ አይፈቀድም ነበር፡፡

**አፓርታይድን ለመጣል የተደረገ ስፖርታዊ ትግል**

በ1949 ዓ.ም የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሲቋቋም ኢትዮጵያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብፅና ሱዳን ነበር የመሠረቱት፡፡ ኢትዮጵያ የቀለም ልዩነት በስፖርት መኖር እንደሌለበት የሚገልፅበትን ደንብ ነበር ይዛ የሄደችው፡፡ ከምስረታው ጎን ለጎን

ውድድሩ ይካሄድ ስለነበር ኢትዮጵያ ከደቡብ አፍሪካ ጋር ለመጫወት ዕጣ ደረሳት። ደቡብ አፍሪካ ነጭና ጥቁርን አልቀላቅልም አለ። የደቡብ አፍሪካ ቡድን መሪ ፍሬድ ፌል የአገሩ መንግሥት በሕግ ያስቀመጠው ስለሆነ ጥቁርና ነጭ ለመቀላቀል እንደማይችል ሲገልፅ፣ የኢትዮጵያ ተወካይ ደግሞ የኤም አገር ፌዴሬሽን ዘረኝነትን ይቃወማል በማለት የደቡብ አፍሪካን ሕግ ተቃወመ። ኢትዮጵያ የዘር ልዩነትን የሚቃወመውን ደንብ በካፍ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ አስገብታው ስለነበር ደቡብ አፍሪካ በቀለም ልዩነት ከውድድር እንዲትታገድ ተደረገ።

በወቅቱ ፊፋን የሚመሩት አብዛኛዎቹ እንግሊዞች በመሆናቸውና በደቡብ አፍሪካም የንግድ ድርጅት ስለነበራቸው ኢትዮጵያ ይዛ የቀረበችውን ደንብ በመቃወም እንቅስቃሴዋን ለመግታት ጫና ማሳደር ጀመሩ። በሌላ አገር ያሉ ጥቁሮች ደግሞ ኢትዮጵያ የጀመረችውን እንድትገፋበት ድጋፍ መስጠት ጀመሩ።

ኢትዮጵያ በስፖርት የዘር ልዩነትን በመቃወም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕግ እንዲወጣ ትልቅ ጥረት አደረገች። ለ16 ዓመታት በፊፋ ጠቅላላ ጉባኤ በመከራከር ደንብ ሆኖ እንዲወጣና ጥቁሮች በየትኛውም አገር በነፃነት እንዲጫወቱ የሚያደርገውን ሕግ እንዲወጣ አስቻለች። ህጉም እንዲህ የሚል ነበር። “በኢንተርናሽናል ፉትቦል ፌዴሬሽን እንቅስቃሴ ውስጥ በአንድ አገር ወይም በአንድ ሰው ላይ በዘር፣ በኃይማኖት ወይም በጎሣ የተነሣ ልዩነት ማድረግ አይፈቀድም። የዘር፤ የኃይማኖት፣ የጎሣ ልዩነትን በሕግ በመሠረተ አገር የሚገኝ ብሔራዊ ፌዴሬሽን ከፊፋ አባልነት ጨርሶ ይሰረዛል” የሚል ነው።

ይህ ሕግ ከመውጣቱ በፊት በአውሮፓ ያሉ ፌዴሬሽኖች ጥቁሮች በአገራቸው እንዲጫወቱ አይፈቅዱም ነበር። ደንቡ ሲወጣ ግን ያለገደብ መጫወት ቻሉ። ዛሬ በአውሮፓ የምናያቸው እነ ዲዲየ ድሮግባ፣ ሳሙኤል ኤቶ እና ሌሎችም ጥቁር የአፍሪካ ተጨዋቾች ወደ አውሮፓ ሄደው መጫወት የቻሉት የኢትዮጵያ ወጣት ኳስ ተጫዋቾች የደረሰባቸው የቀለም ልዩነት አንገሽግሿቸው ራሳቸውን ነፃ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ጥቁሮች ይህ ነገር እንዳይደርስባቸው በመታገላቸው ጭምር ነው። የደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ መንግሥትም በስፖርቱ መስክ ከዓለም እንዲገለል በማድረግ የኢትዮጵያ ኃላፊነትና ድርሻ ትልቅ ነበረ።

ዛሬም በዓለም ላይ በስፖርት ያለው ዘረኝነት በአሁን ጊዜ ቅጥ ያጣ በመሆኑ መቆም አለበት። የኢትዮጵያ ወጣቶች ይህን ለማስቆም ታግለው በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕግ እንዲወጣ በማስቻል መግታት ተችሎ ነበር። ኢትዮጵያ የታገለችለትን በስፖርት ላይ የሚታየውን የዘር ልዩነትን ፈጽሞ ለማጥፋት አሁንም አፍሪካውያን በማስተባበር መንቀሳቀስ ይጠበቅባታል። ለዚህም የስፖርት ኮሚሽንና ፌዴሬሽኑ በመተባበር በፊፋና በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ማንሳትና መታገል ይጠበቅባቸዋል።

## 3.3 የዘመናዊ ስፖርት ጅማሬ

በ1927 ዓ.ም ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ኢንተርናሽናል ግጥሚያ ያደረገችበት ጊዜ ነበር፡፡ በወቅቱ ብዙ የኮሚኒቲ ቡድኖች አዲስ አበባ ውስጥ ስለነበሩ በኢትዮጵያ ስም የተጫወቱት የ14 አገር የውጪ ዜጎች ነበሩ፡፡ ጣሊያን፣ አርመን፣ ግሪክ፣ ፈረንሳይ፣ ኢትዮጵያ ወዘተ… ነበሩ፡፡ በጨዋታውም ኢትዮጵያ የፈረንሳይ መርከበኞችን 3ለ1 ስታሸንፍ ጥቁሩና ነጩ፣ አርመኑና ቱርኩ አብረው በደስታ ሲጨፍሩ በስፖርት ያለው ወዳጅነት አስደሳቹ ገፅታ ነበር፡፡

በ1928 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ክለብ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሲቋቋም ጨዋታውን መጀመሪያ ጊዜ ያደረገው አራራት አርመን ከተባለው የአርመን ኮሚኒቲ ቡድን ጋር ነበር፡፡ ከዚያም ከግሪክ፣ ከሕንድ፣ ከፈረንሳይ ኮሚኒቲ ቡድኖች ጋር በቀጣይ ጨዋታዎች ለማድረግ ፕሮግራም ይዞ ነበር፡፡ ነገር ግን በ1928 ዓ.ም ፋሺስት ጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ከላይ እንደተገለጸው ደንብ በማውጣት ጥቁርና ነጮች ለብቻቸው እንዲጫወቱ ሲደረግ ጊዮርጊስ ይህን ዕድል አጣ፡፡

### የጥቁሮች ፌዴሬሽን

በ1930 ዓ.ም በጣሊያን አስተዳደር በአዲስ አበባ የእግር ኳስ ሻምፒዮና ተጀመረ፡፡ ጥቁሮች አሁን አውቶቡስ ተራ አካባቢ ኳስ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ከነጮች ሳይቀላቀሉ ተገልለው እንዲጫወቱ ሲደረግ፤ ነጮች ደግሞ አሁን ቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤት ባለበት ቦታ በነበረው ኳስ ሜዳ እንዲጫወቱ ይደረግ ነበር፡፡ ጥቁር የሚባሉት የአገሬው ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ተጫዋቾች ናቸው፡፡ በወቅቱ ተሳታፊ የነበሩት ደጃች ውቤ፣ ቀበና፣ ጉለሌና 6 ኪሎ ነበሩ፡፡ ከነጮች ጋር በየትኛውም ቦታ ቢሆን የወዳጅነት ጨዋታ እንኳን ማድረግ አይቻልም፡፡ የቀበና ቡድን በድብቅ ጫካ ውስጥ ከሕንድ ቡድን ጋር ሲጫወት ተይዞ ተቀጥቷል፡፡ በተመሳሳይ ጉለሌም ከአርመን ጋር ሲጫወት ተይዞ ተቀጥቷል፡፡ ለጥቁሮች የወጣው ሕግ የኳስ ደንብን የያዘ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ውሳኔም ተጨዋቾች ይቀጡ ነበር፡፡ ከጨዋታው በፊት የፋሺስት ሠላምታ ያልሰጠ ቡድን ቅጣት አለበት፡፡ ጎል ያገባ ተጫዋች ለዳኛው የፋሽስት ሰላምታ ካልሰጠ ያገባው ግብ አይያዝለትም፡፡ ሌሎችም ጠበቅ ያሉ ደንቦች ነበሩባቸው፡፡ ወጣቶቹ አበሾች ጣሊያን ያወጣውን ደንብ ጥሰው ከነጮች ጋር ለመገናኘት ብዙ ታግለዋል፡፡

### በረጅም ርቀት ለምን ውጤታማ ሆንን?

በረጅም ርቀት ማዘወተሪያ ስፍራ ኖሮም ሆነ ሳይኖርም ከነ አበበ ቢቂላ ጀምሮ ውጤት ማምጣት ችለናል፡፡ በዚህ መስክ ከሌሎች የአውሮፓ አገሮች የተሻልን ነን፡፡ ለምሳሌ ጀርመን በረጅም ርቀት ሩጫ በቂ ማዘወተሪያ ስፍራ፣ የተሻለ ኢኮኖሚና

የተሻለ የስፖርት አደረጃጀት አላት። በነዚህ መስፈርቶች ሁሉ ኢትዮጵያ ከጀርመን ያነሰ ሁኔታ ላይ ነች። ነገር ግን እኛ በረጅም ርቀት ሩጫ ወርቅ ስናመጣ ጀርመን ሜዳሊያ ልታመጣ ቀርቶ በ5ሺና በ10ሺ ሜትር ሩጫ ሚኒማ ያለው ሯጭ ማፍራት እንኳን አልቻለችም።

ታዲያ እኛ ከእነሱ ተሽለን እንዴት በረጅም ርቀት ሩጫ ውጤታማ ሆንን? ብዙዎቹ አጥኚዎች እንደሚሉት ኢትዮጵያ ውጤታማ የሆነችው በአልቲቲዩድ (በአየሩ) ነው ይላሉ። ኢትዮጵያ ሲባል ሁሉም ክልል እኩል ውጤታማ አይደለም። ረጅም ርቀት ወደ አርሲ ያደላል። ከአርሲ ውስጥ ደግሞ አንዱ አውራጃ የተሻለ ነው። አንዱ ወረዳ ደግሞ ከሌላው የተለየ ነው። አንዱ መንደር ከሌላው መንደር ብቃት ያለው ይሆናል። በተመሳሳይ አልቲቲዩድ ውስጥ ሆነው የተለያየ ችሎታ ያላቸው አትሌቶችን እናገኛለን። ውጤት የተገኘው በእኔ እምነት በአልቲቲዮድ ሳይሆን በተፈጥሮ ነው። ለምሳሌ ቀነኒሳና ታናሽ ወንድሙ ታሪኩ አንድ ቤት አድገው፣ ተመሳሳይ ምግብ እየበሉ በተመሳሳይ አልቲቲዮድ ውስጥ እየተለማመዱ አንድ አይነት አሰልጣኝ እያሠለጠናቸው ውጤታቸው ግን የተለያየ ነው። ቀነኒሳ ብዙ ሜዳሊያ ሲሰበስብ፤ ታሪኩ ግን ለዚህ አልታደለም።

ኃይሌ ገ/ስላሴና ወንድምየው፣ ጥሩነሽና እህቷ በተመሳሳይ ነገር ውስጥ አልፈው በውጤት ግን ይለያያሉ። በዚህ ርቀት በዓለም አቀፍ ውድድር ውጤታማ መሆን የቻልነው ተፈጥሮን ጥገኛ ባደረግንበት ነገር እንጂ ከሌላው የተለየ ነገር ሠርተን፣ የተሻለ ድጋፍ አግኝተን ወይም በቂ ማዘወተሪያ ስፍራ ኖሮ አይደለም። ለምሳሌ በአጭር ርቀት በተለይ በ100 እና በ200 ሜትር በቂ ማዘወተሪያ ስፍራ ኖሮም ሳይኖርም፤ ለሩጫው የተሟላ ቁሳቁስና አሠልጣኝ ኖሮም ሳይኖርም ውጤት ማምጣት አልቻልንም። ብዙዎች በዚህ ርቀት በሚገባ ስላልሰራንበት ነው ቢሉም ችግሩ በእኔ እምነት ይህ አይደለም፤ የተፈጥሮ ጉዳይ እንጂ።

ይህን በምሳሌነት ለማሳየት እንደማስረጃ አንድ ነገር እንጠቁም። የጀማይካ ሯጮች 100 ሜትርና 200 ሜትር በዓለም ውጤታማ ናቸው። በረጅም ሩጫ ግን ሚኒማ እንኳን ያለው ሯጭ የላቸውም። በረጅም ርቀት ስላልሰሩ፤ በአጭር ርቀት ስለሰሩ ሳይሆን በዚያ ርቀት በተፈጥሮ በንፅፅር ከሌላው የተሻሉ በመሆናቸው በተፈጥሮ ላይ ስለሰሩበት ውጤታማ ለመሆን ችለዋል።

እኔ የተማርኩት ሻሸመኔ ነው። በርካታ ጃማይካዊያን መኖሪያቸው ያደረጉት እዚያው ነው። እዚያው የተወለዱ ጃማይካዊያን እኔ ባለሁበት ት/ቤት አብረውኝ ይማሩ ነበር። በት/ቤት የስፖርት ውድድር በ100 ሜትር ሩጫ አንችላቸውም ነበር። ረጅም ርቀት ሩጫ ደግሞ እነሱ አይችሉንም። እዚያው ከተማ ውስጥ ተመሳሳይ ምግብ በልተን፣ በአንድ አሰልጣኝ እየሰለጠንን፣ በተመሳሳይ አልቲቲዩድ ውስጥ ሆነን እነሱ ከእኛ

በ100 ሜትር የተሻሉበት እኛ ደግሞ ከእነሱ በረጅም ርቀት የተሻልንበት 'ተፈጥሮ' መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው በዓለም አቀፍ ውድድር እኛ ት/ቤት የተመዘገበው ውጤት በአጭሩ ጃማይካውያን በረጅሙ ኢትጵያውያን ውጤታማ የሆኑት፡፡ ኢትጵያዊያን በ1948ቱ የሜልቦርን ኦሎምፒክ ጀምሮ በ100 ሜትር ብዙ ሞክረን እስካሁን ድረስ አልተሳካልንም፡፡ ስላልሰራን ነው እያልን ተፈጥሮን ረስተነው እየለፋን ነው፡፡ አሣ ጥገኛ የሆነው ባሕሩን እንደመሆኑ፤ እኛም ውጤታማ የሆንነው ጥገኛ የሆንበትን የረጅም ርቀት ውድድር ላይ ነው፡፡

# 4 የስፖርቱ ችግር ምንድነው?

## 4.1 ለድክመቱ የሚነሱ ችግሮች

በስፖርት በተለይም በእግር ኳሱ ውጤታማ ላለመሆናችን ብዙ ምክንያቶች ይነሳሉ፡፡ በእኔ እምነት አንዳዶቹ ምክንያቶች መሠረታዊ ችግሮች ሳይሆኑ ዋናውን ችግር የሸፈኑ ሠበቦች ናቸው፡፡ እግር ኳስን በምሳሌነት ያነሳሁት በአብዛኛው ወጣቱ የሚሳተፍበትና የህዝቡም ስሜት ያለው እዚህ ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ችግሮች ተብለው ከሚነሱት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል የአደረጃጀት፣ የአስተዳደር፣ የማዘወተሪያ ሥፍራ እጥረት፣ የአሠልጣኞ እርስ በርስ አለመፋቀር፣ የኢንተርናሽናል ጌም ልምድ ማጣት፣ የፕሮጀክት ያለመኖርና ለአሠልጣኞች በቂ ጊዜን አለመስጠት ይጠቀሳሉ፡፡

### የክለቦች ዝምታ

በአዲስ አበባ የሚገኙ ትልልቅ ክለቦች የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራ ችግርን ለመቅረፍ የመስሪያ ቦታ ጥያቄ አቅርበው መንግሥት መሬት በነፃ ሰጥቷቸዋል፡፡ ባገኙት ቦታ መጠነኛ ስታዲየም ገንብተው የመዝናኛና የንግድ ሱቆችን አብረው ለመክፈት መሬት ተረክበዋል፡፡ በዚህ ረገድ ቡና፣ ባንክ፣ መብራት እንደዚሁ ሌሎቹ ይጠቀሳሉ፡፡ ነገር ግን እስካሁን አንዳቸውም ግንባታ አልጀመሩም፤ ቦታውን ብቻ አጥረው ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህ ክለቦች መሬት ሲጠይቁ ገንዘብ እንዳላቸው ገልጸው ነው፡፡ ክለቦቹ በርካታ ደጋፊ አላቸው፡፡ ከደጋፊዎቻቸው 90 ከመቶው ወጣቱ ነው፡፡ እነዚህን ማዘወተሪያ ስፍራዎች ቢሰሯቸው ወጣቶቹ በክለባቸው ማዘወተሪያ ሥፍራ ውስጥ ስፖርት በመስራትና ውድድር በማካሄድ ተጠቃሚ መሆን ይችሉ ነበር፡፡

በሌላ በኩል 95 በመቶ የሚሆኑ በፌዴሬሽኑ የተመዘገቡ ክለቦች በመንግሥት ድጎማ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ አንድ ክለብ በዓመት ከአምስት እስከ አስራ አምስት ሚሊዮን ብር ለስፖርት ውድድር ወጪ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ባንኮች በ2005 ዓ.ም ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ ለተጫዋቾች ግዢ አውጥቷል፡፡ ነገር ግን በአገር ውስጥም ሆነ በኢንተርናሽናል ውድድር ያለው ውጤት ደካማ ነው፡፡ በፊት እንደሚያደርገው ወጣት ተጫዋቾችን

ከታች በማሳደግ ለተጫዋች ግዢ የሚያወጣውን በዓመት ከ3 እስከ 4 ሚሊዮን ብር መቆጠብ ይችላል። የግዢው ዋጋ ለወደፊት በጣም እያደገ ስለሚሄድ በ10 ዓመት ውስጥ እስከ 60 ሚሊዮን ብር ሊያወጣ ይችላል። ክለቡ 60 ሚሊዮን ብር ከድርጅቱ ተበድሮ ዘመናዊ ስታዲየም ሊሰራ ይችላል። ይህ አንዱ አማራጭ ነው። ሌላው አማራጭ ስታዲየሙን በብድር ሠርቶ ከሱቅና ከሜዳ ኪራይ አገልግሎት ክፍያ በመሰብሰብ እዳውን ሊያቃልል ይችላል። ባንኮች በከፍተኛ ዲቪዚዮን ውድድር የጀመረው በ1981 ዓ.ም ነው። እስካሁን 23 ዓመት ቆይቷል። የ2005 ዓ.ም በጀቱ ከ8 ሚሊዮን ብር በላይ እንደሆነ ይነገራል። ከዚህ ውስጥ 80 ከመቶ ወጪውን የሚበላው እግር ኳሱ ነው። በ23 ዓመት ቆይታው በዓመት በትንሹ ቢያንስ 2 ሚሊዮን ብር ቢያወጣ በአጠቃላይ በእነዚህ ዓመታት 46 ሚሊዮን ብር ያህል አውጥቷል ማለት ነው። ድርጅቱ ይህንን ያህል ገንዘብ ሲያወጣ ምንም ያገኘው ትርፍ የለም። ድርጅቱ የማይመልሰው ገንዘብ ለስፖርት የሚያወጣ ከሆነ በተረከበው መሬት ላይ ስታዲየም ቢሰራ በገቢው ተጠቃሚ ይሆናል። ለብዙ ወጣቶችም መዝናኛና ማዘወተሪያ ያዘጋጃል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ የመወዳደሪያ እጥረት ስላለ ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጣል።

ቀደም ሲል የስፖርቱ በተለይም የእግር ኳሱ ችግሮች ናቸው ያልኳቸውን አንዳንዶቹን ልጠቃቅስ።

**ሀ) አደረጃጀት፡-**

የስፖርት አደረጃጀታችን ችገር እንዳለበት ግልጽ ነው። የስፖርት ፖሊሲው ከወጣባቸው ምክንያቶች አንዱ የስፖርት አደረጃጀቱን በማሻሻል ሕዝባዊ መሠረት ለማስያዝ እንደሆነ ይታወቃል። ነገር ግን የስፖርት ድክመታችን በሙሉ አደረጃጀት ውጤት ነው ለማለት ግን ይከብዳል።

የስፖርት አደረጃጀታችን ችግር ስላለበት ዓለም አቀፍ ውጤታችን ደካማ እንደሆነም ይነገራል። በሲድኒ ኦሎምፒክ ታላቋ ብሪታኒያ (ስኮትላንድ፣ ዌልስ፣ እንግሊዝ ተጣምረው) አንድ የወርቅ ሜዳያ ብቻ ስታገኝ፤ ኢትጵያ 4 የወርቅ ሜዳያ አግኝታለች። ኢትዮጵያ ከብሪታኒያ በአደረጃጀት ተሽላ ነው ይህን ውጤት ያመጣቸው ለማለት ይከብዳል። ለምሳሌ ቀደም ሲል ያነሳነው የባንኮች ስፖርት ክለብ እግር ኳሱ እና አትሌቲክሱ በአንድ አደረጃጀት ሥር ነው ያለው። በ1992 ዓ.ም በሰበሰብኩት መረጃ የባንክ ክለብ ለአትሌት የሚከፍለው ከፍተኛ ደመወዝ 700 ብር ነው። ለእግር ኳሱ ከፍተኛው 2,500 ብር ሲሆን የመጨረሻ ዝቅተኛው 1,000 ብር ነው። የአትሌቶቹ ከፍተኛው ደሞዝ የእግር ኳሱን የመጨረሻውን አይደርስበትም። አትሌቶቹ በሳምንት 2 ጊዜ ይለማመዳሉ፤ እግር ኳስ ተጫዋቾቹ ደግሞ በየዕለቱ ይለማመዳሉ። አትሌቶቹ በሳምንት ሁለቴ ከልምምድ በኋላ ብቻ ይመገባሉ፤ እግር ኳስ ተጫዋቾቹ

በካምፑ ተቀምጠው ቀኑን ሙሉ ይመገባሉ:: አትሌቶቹ በኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ሲያገኙ፤ የእግር ኳስ ቡድኑ በኢራቅ ወታደሮች ቡድን 13ለ0 ተሸንፎ የተመለሰበት ሁኔታ ነበር::

በአንድ አደረጃጀት ሥር ሆኖ የተሻለ እንክብካቤ ያለው ደካማ ውጤት ሲያገኝ፤ በቂ እንክብካቤ የሌለው የተሻለ ውጤት እያስመዘገበ ነው:: ስፖርቱ በአንድ አደረጃጀት ሥር ሆኖ የተለያየ ውጤት ካገኘ ችግሩ ሙሉ በሙሉ አደረጃጀት ነው ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል::

**ወጣቶችን የሚያቅፉ ህዝባዊ ክለቦች ለምን አይኖሩም?**

በፌዴሬሽን ተመዝግበው ከሚገኙ 70 የሚሆኑ ክለቦች ውስጥ 95 በመቶው በመንግሥት የሚደጎሙ ናቸው:: መንግሥት የሚመድብላቸውን ገንዘብ ይወዳድሩበትና ዓመቱን ያጠናቅቃሉ:: ደጋፊዎቻቸውም ተጠቅመው፤ ፈጠራ አክለው ወጣቱን በማሳተፍ ወደ ህዝባዊነት መቀየር አልቻሉም:: ቀደም ሲል በ1950ዎቹ እነ አንድነት፣ በራሪ ኮከብ፣ ሀማሴን፣ እምባሶሪያ፣ ቅዱስ ሚካኤልና ሌሎችም በርካታ ክለቦች ህዝቡ አቋቁሟቸው ለትልቅ ደረጃ የደረሱ ነበሩ:: ሠፈር ውስጥ ህፃናቶች ገንዘብ አዋጥተው ቡድን ይመሠርታሉ:: እነዚህን የህፃናት ቡድኖች የአካባቢው ሰው ይደግፋቸዋል:: በውጤታቸውም ጥሩ ከሆኑ ወደ ከፍተኛ ውድድር ይገባሉ፤ የደጋፊያቸውም ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል፤ በአካባቢያቸውም የማዘወተሪያ ስፍራ ይገነባሉ:: እንዲህ እንዲህ እያሉ ህዝባዊ ቡድኖች ተጠናክረውና ጎልተው ይወጣሉ:: አሁን ግን ትልቅ ቦታ አሉ ከሚባሉ ክለቦች ውስጥ ህዝባዊ የሚባሉት ውስን ናቸው::

አሁን ያሉት አብዛኛዎቹ ክለቦች የመንግሥትን እጅ ጠብቀው የሚተዳደሩ ናቸው:: ባለፉት ረጅም ዓመታት በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ተመዝግበው ይወዳደሩ የነበሩ በመንግሥት የሚደገፉ እንደነ ድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ፣ ምድር ባቡር፣ ህንፃ ኮንስትራክሽን፣ አውራ ጎዳና፣ ቴሌ፣ ሲሚንቶ፣ በርታ ኮንስትራክሽን፣ ፔፕሲ፣ ባህር ትራንዚት፣ ኪራይ ቤቶች አስተዳደር፣ ጨርቃ ጨርቅ (አርባ ምንጭ፣ ኮንቦልቻ፣ አዋሳ፣ አቃቂ)፣ አየር መንገድ፣ ጭማድ፣ አግሮ፣ ብርሃንና ሠላም፣ እርሻ ጣቢያ የመሳሰሉት ክለቦች ፈርሰዋል:: ብዙዎቹ በርካታ ተጫዋቾችን ለብሔራዊ ቡድን ያበረከቱና በአፍሪካ የክለብ ሻምፒዮና ኢትዮጵያን ወክለው የተሳተፉ ነበሩ:: ለምሳሌ የድሬዳዋ ጥጥ ማኅበር ሶስተኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ኢትዮጵያ ስታገኝ ብዙ ተጫዋቾች በማሰለፍ ግንባር ቀደም የነበረ ሲሆን፤ በአፍሪካ የክለብ ሻምፒዮና ኢትዮጵያን ለመጀመሪያ ጊዜ የወከለ ክለብ ነበር:: ድርጅቱ ወደግል ሲዛወር ክለቡ ፈረሰ:: ህንፃ ኮንስትራክሽንም እንዲሁ ድርጅቱ ሲፈርስ ክለቡም ተበተነ:: አንዳንዶቹ ክለቦች ደግሞ በድርጅቶቹ ስራ አስኪያጆች በጎ ፈቃድ የተቋቋሙ በመሆናቸው ሥራ አስኪያጆቹ ሲቀየሩ ክለቦቹም ይፈርሳሉ::

ክለቦቻችን በህዝብ ተሳትፎና መዋጮ የተመሠረቱ ባለመሆናቸው መንግሥት የሚሠጣቸውን ገንዘብና ቦታ እንደ መነሻ ይዘው ተከታዮቻቸውን አሳትፈው በስፖርት ልማት ውስጥ መግባት አልቻሉም። እነዚህ የመንግስት ክለቦች ቅድሚያ የሚሰጡት ለማዘወተሪያ ስፍራ ሳይሆን ለውድድር ነው። በውድድር ተሳትፎ የኢትዮጵያን እግር ኳስ መለወጥ አልቻሉም ወይም ከበጀቱ ቀንሰው ማዘወተሪ ስፍራ ሠርተው ይህን ችግር ቀርፈው ወጣቱን ተጠቃሚ ማድረግ አልቻሉም።

ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ፌዴሬሽን ተመዝግበው የሚዋዳደሩ ከ60 እስከ 70 የሚሆኑ የህፃናት እግር ኳስ ቡድኖች ነበሩ። ከ50 በላይ ደግሞ የወጣት ቡድኖች አሉ። እነዚህ ታዳጊዎች በቅብብሎሽ ዋና ቡድን ይገባሉ። አሁን ግን ክለቦች የተጫዋች ግዢ በመጀመራቸው ከታች ለሚያድጉ ታዳጊዎችና ወጣቶች ትኩረት መስጠት ትተዋል። ብዙዎቹም የህፃናትና የወጣቶች ቡድኖቻቸውን አፍርሰዋል። ዘንድሮ 10 የሚያህሉ ቡድኖች ናቸው በወጣቶች ውድድር ክለብ አቋቁመው የተወዳደሩት። እነርሱም ቢሆኑ ወደዋናው ቡድን ታዳጊዎችን አያሳድጉም። ብዙዎቹም ክለቦች በግዢ እየተጠቀሙ ነው። ዕድገት ከሌለው ቢያንስ እንደቀድሞ ህፃናትና ወጣቶችን መያዝ ነበረባቸው። ክለቦች ለተተኪዎች ትኩረት ስለማይሰጡ ወጣትና ታዳጊዎች ወደ ክለቦች መሄድ ትተዋል፤ አቅጣጫቸውን ቀይረዋል።

## ለ) የውጭ አሠልጣኞች

ደካማ የሆነውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ በዓለም አቀፍ ውድድር ውጤታማ ለማድረግ ፌዴሬሽንና ክለቦች በአገር ውስጥ አሰልጣኝ እምነት ስላጡ ከአውሮፓ የውጭ አሠልጣኞችን ሲቀጥሩ ቆይተዋል። በጥቅምት 2004 ዓ.ም ከብሔራዊ ቡድን የተሰናበተው ቤልጂየማዊ አሠልጣኝ ለብሔራዊ ቡድኑ 38ተኛው አውሮፓዊ አሠልጣኝ ነው። ባለፉት 52 ዓመታት ፌዴሬሽኑ 38 የውጭ አሰልጣኞች ቀጥሮ እግር ኳሱን መለወጥና በዓለም አቀፍ ውድድር ውጤታማ ሊያደርገን አልቻለም። ፒተር ሺተንገር የተባለ ጀርመናዊ የአይቮሪኮስት አሠልጣኝ ሆኖ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን 6ለ1 አሸነፈ (ይህ እስካሁን በአፍሪካ ዋንጫ ያልተሰበረ በብዙ ጎል የመሸነፍ ሪከርድ ነው)። ፒተር የአይቨሪኮስትን ቡድን በመለወጡ የተሻለ አሠልጣኝ ነው በሚል የኢትየጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ለ2 ዓመት ቀጠረውና ለ10ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ቡድኑን ተረከበ። በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች እየተዟዟረ የወዳጅነት ግጥሚያ ከማድረጉ በተጨማሪ በቀድሞው ምዕራብ ጀርመን ቡድኑ ለ2 ወር ተዘጋጅቶ 10 የአቋም መለኪያ ግጥሚያ አደረገ። ቡድኑ 2 ዓመት ተዘጋጅቶ አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የአፍሪካ ዋንጫ ከምድቡ ማለፍ አልቻለም። ፒተርም ችሎታ የለውም ተብሎ ተባረረ። ከ20 ዓመት በኃላ በ1989 ዓ.ም ፒተር የሴኔጋልን ቡድን ይዞ አዲስ አበባ መጣ። የእኛን ቡድን 2ለ1 አሸነፈ። ሴኔጋል ጠንካራ ነበር። ፌዴሬሽኑም ፒተርን

እንደገና ለመቅጠር ፈለገ፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ፒተር ችሎታ የለውም ወይስ ለእርሱ (ለስልጠናው) የሚሆን ተጫዋች ኢትዮጵያ ውስጥ የለም የሚለው ነው፡፡ እኛ አገር ችግር የሆነው አውሮፓውያኖች ለሚከተሉት ስልጠና የሚሆን ሰው (ተጫዋች) ሳይኖር አሠልጣኝ ከአውሮፓ ማምጣታችን ነው፡፡ ከአውሮፓ አሠልጣኝ የምናመጣው እግር ኳሳቸው ያደገ በመሆኑ የእኛንም እንዲለውጡልን ነው፡፡ ይህ እውነታ ነው፡፡ ለስልጠናው የሚሆን ሰው ግን ያስፈልጋል፡፡

ጀርመን በእግር ኳሷ ያደገ አገር ስለሆነ ከጀርመን አሠልጣኝ እናመጣለን፡፡ በረጅም ርቀት ሩጫ ኢትዮጵያ በዓለም ውጤታማ ናት፡፡ ጀርመን ደግሞ በረጅም ርቀት ሩጫ ውጤት ልታመጣ ቀርቶ ሚኒማ የሚያሟላ ሯጭ የላትም፡፡ ታዲያ ለምንድነው ጀርመን ከእኛ የረጅም ርቀት አሠልጣኝ የማትወስደው? መልሱ ቀላል ነው፡፡ ለረጅም ርቀት ሩጫ የሚሆን አትሌት ከሌላት ውጤታማ አሠልጣኝ ከኢትዮጵያ መቅጠሩ ምን ያደርግላታል? እኛም አውሮፓ ለሚከተለው ሥልጠና መነሻ የሚሆን ተጫዋች ከሌለን ለምን ከጀርመን አሠልጣኝ እናመጣለን?

እስካሁን 38 አሰልጣኝ ከአውሮፓ ቀጥረን እነርሱ በሚከተሉት ሥልጠና ውጤት ካጣን ለምን ስልጠናው ውስጥ ያለውን ነገር አንመረምርም? እስከዛሬ የተሠጠው መፍትሔ ግን አንዱ የአውሮፓ አሰልጣኝ በድክመት ሲባረር ሌላውን መተካት ነው፡፡ ስህተቱ የቱ ጋር ነው? የተሳሳተው ሰውየው ነው ወይስ ስልጠና"? የሚሉትን ጥያቄዎች አናነሳም፡፡ የተሳሳተው ሰውየው (አሰልጣኙ) ከሆነ ሰውየው ተባሯል፤ ነገር ግን መፍትሔ የለም፡፡ ስለዚህ ችግሩ ሥልጠናው ላይ ነው ማለት ነው፡፡ ፌዴሬሽኑ ለአለፉት 52 ዓመታት ሥልጠናውን ሳይሆን አሠልጣኙን ነው የቀየረው፡፡ ስለዚህ በእግር ኳሱ ወጣቱ ያለውን የተፈጥሮ ችሎታ በስልጠና ቀይሮ ወደ ውጤት በማሸጋገር ወጣቱንና ስፖርቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነገር አልታየም፡፡

**ሐ) ማዘወተሪያ ስፍራ**

ስፖርት ሲታሰብ ማዘወተሪያ ስፍራ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ ወጣቱ ሁሉንም ነገር የሚያከናውነው በማዘወተሪያ ስፍራ ላይ ነው፡፡ ለመጫወት፣ ለመሮጥ፣ ጥሩ ነገር ለማሠብ፣ ኃሳቡንና ዕውቀቱን ለማሳረፍ የሆነ ነገር መኖር አለበት፡፡ እሱም የማዘወተሪያ ስፍራ ነው፡፡ ትምህርት ለመማር ጠረጴዛ፣ ወንበርና ሌላም ቁሳቁስ እንደሚያስፈልግ ሁሉ በስፖርት ጥበብና ፈጠራን ለማሳየት፣ ለማዳበርና ለመተግበር፣ ወደ ውጤት ለመቀየርና ብሎም ድል ለማምጣት መነሻ ቦታ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የማዘወተሪያ ስፍራ ነው፡፡ ከማዘወተሪያ ስፍራ ልምምድ፣ ሙከራ፣ ለውጥ እነዚህን ተከትሎ ደግሞ ውጤት ይገኛል፡፡ ማዘወተሪያ ስፍራ ሲኖር ወጣቱ ጤንነቱን ከመጠበቅ ባሻገር በአዕምሮ ፣ በአካልና በስነ-ልቦና የተሻለ ዜጋ ይሆናል፡፡ በስፖርት

የተገነባ አካልና የታነጸ አዕምሮ ያለው ወጣት በልማቱ መስክ ፈጣሪ፤ የአገር አንድነትና ድንበር በጠመቅ ረገድ ዝግጁ ዜጋ ይሆናል።

እነዚህን ሁሉ ለማሳካት ማዘወተሪያ ስፍራ ያስፈልጋል። በውድድር ስፖርቶችም በስፖርት የተገነባ ወጣት ድል ለማግኘት በድሉ የአገሩን ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስጠራት ህዝቡን በማስደሰት ትውልድን ለቀጣይ ድል ማነሳሳት ይቻላል። ስፖርት ለወዳጅነት የሚለው ጥቅም ሲሆን፤ ማዘወተሪያ ደግሞ ስፖርት የሚሠጠውን ጥቅም ማስፈፀሚያ ነው።

አለማየሁ ኃይለስላሴ የተባለ የቀድሞ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ሲነግረኝ ተማሪ በነበረበት ሠዓት በእነርሱ ትምህርት ቤት ብቻ አራት ሜዳዎች እንደነበሩና ዛሬ የተጫወቱበትን ሜዳ በማግስቱ እንደማይደግሙበትና ሌላኛው ሜዳ ላይ ሄደው እንደሚጫወቱ አጫውቶኝ ነበር። ይህ እንግዲህ በ1950ዎቹ መሆኑ ነው። በዚያን ጊዜ ትምህርት ቤቶች የሚይዙት ጥቂት ተማሪዎችን ብቻ ነበር። አሁን ግን የተማሪው ቁጥር በመጨመሩ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ክፍሎች ግንባታ ስለሚያስፈልጋቸው ይህን ግንባታ ከግቢው ውጪ ማድረግ አልቻሉም። ክፍት ቦታ ሲፈልጉ ያገኙት የስፖርት ሜዳውን ነው። ስለዚህ በአብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ክፍሎች የተገነቡት ቀደም ሲል የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራ በነበሩት ቦታዎች ላይ ነው። ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች መሠራቱ ለትምህርት አገልግሎት ስለሚውል ጥሩ ነው። በእነዚያ ክፍሎች ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል ሳይንቲስት ወይም የሂሳብ ሊቅ ማፍራት ይቻላል። ነገር ግን ክፍሉ የተሠራው የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራ ላይ በመሆኑ በስፖርት የተገነባ ጤነኛ ወጣት ተማሪ ለማግኘት ያስቸግራል። አስገራሚው ነገር ደግሞ ብዙዎቹ ትምህርት ቤቶች የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራውን ለሌላ ግንባታ ካዋሉት በኋላ ሜዳ እንደሌላቸው እየታወቀ በትምህርት ቤት ውድድር ላይ ይሳተፋሉ። ወጣቱ የት ስፖርት ሠርቶ፤ የትስ ተለማምዶ ነው ለውድድር የሚቀርበው?

በኮሌጆችም ተመሳሳይ ነገር ነው የሚታየው። በ2005 ዓ.ም በአዳማ በተካሄደው የግል ኮሌጆች የስፖርት ውድድር ላይ አብዛኛዎቹ ኮሌጆች እግር ኳስን ጨምሮ በአትሌቲክስ፣ በቅርጫት ኳስ፣ በመረብ ኳስ በሌሎችም የስፖርት ዓይነቶች ተሳታፊ ነበሩ። እንደሚታወቀው አዲስ አበባ ውስጥ በርካታ የግል ኮሌጆች ፎቅ ላይ ተከራይተው ነው የሚያስተምሩት። ማዘወተሪያ ስፍራ ሊኖራቸው ቀርቶ ጥቂት የመኪና ማቆሚያ ስፍራ እንኳን የላቸውም። እነዚህ ኮሌጆች በእግር ኳስ፣ በመረብ ኳስ፣ በቅርጫት ኳስና በአትሌቲክስ ሲወዳደሩ ትምህርት ቤቱን የሚወክሉ ተጫዋቾችን ለመምረጥ የውስጥ ውድድር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ኮሌጁ ፎቅ ላይ ተንጠልጥሎ፤ ሜዳ ሳይኖረው በኮሌጆች ውድድር ላይ መሳተፉ በጣም የሚገርም

ነው፡፡ እነዚህ ኮሌጆችና ት/ቤቶች አብዛኛው ወጣቱን ነው የያዙት፡፡ ማዘወተሪያ ስፍራ ስለሌላቸው ይህንን ወጣት ክፍል ውስጥ አጉረውት ይውላሉ፡፡

ልጆች በአፀደ-ህፃናት ሲማሩ አብዛኞቹ በመኪና ወደ ት/ቤት ይሄዳሉ፡፡ አብዛኛው አፀደ-ህፃናት ሜዳ የለውም፡፡ ታዳጊው ከአፀደ-ህፃናት ሲወጣ ወደ ትልልቅ ት/ቤቶች ይገባል፡፡ እዚያም ለተጨማሪ ክፍሎች ሲባል የስፖርት ማዘውተሪያ የነበሩት ቦታዎች ግንባታ ስለተካሄደባቸው የማዘወተሪያ ስፍራ ስለሌለ መንቀሳቀስ አይችሉም፡፡ ከመደበኛ ት/ቤቶች አልፎ ወደ ኮሌጅ ሲገባም ፎቅ ነው የሚጠብቀው፡፡ ከልጅነቱ ኮሌጅ እስኪገባ የማዘወተሪያ ስፍራ ችግር ስላለበት ጤነኛ የሆነ ዜጋ ለማፍራት ያስቸግራል፡፡ ጤነኛ ዜጋ ማፍራት ካልተቻለ በፈጠራው፣ በልማቱና ዳር ድንበር በማስከበር አገሩን የሚጠቀም ሰው ማፍራት የማይታሰብ ይሆናል፡፡

ከትምህርት ቤቶች ወጣ ብለን በስፋት ስንመለከት በአዲስ አበባ ባለፉት 20 ዓመታት ወጣቱ ለስፖርት ማዘወተሪያነት ይጠቀምባቸው የነበሩ ቦታዎች ለሌላ አገልግሎት እየዋሉ ነው፡፡ በአውቶቡስ ተራ አካባቢ ኳስ ሜዳ ተብሎ የሚጠራው ሜዳ ባለፉት 30 ዓመታት እነ ኤፍሬም፣ ጌቱ፣ ኃይሌ፣ ሳምሶን፣ አስፐሪላ፣ አሲን ጨምሮ ከ50 በላይ ተጫዋቾችን ለብሔራዊ ቡድን ያፈራ ነው፡፡ በፒያሳ ማዘጋጃ ቤት አጠገብ የነበረው ሜዳም እንደዚሁ በርካታ ተጫዋቾችን ያፈራና ታላላቅ ውድድሮችም የሚካሄዱበት ነበር፡፡ እነዚህን ሜዳዎች ጨምሮ ወጣቶች ውድድር የሚያደርጉባቸው በርካታ ሜዳዎች ለሌላ አገልግሎት ውለዋል፡፡

ከእነዚህ ሜዳዎች የተወሰኑት ቀደም ሲል ለስፖርት ማዘውተሪያነት ታስበው ሳይሆን ክፍት ቦታ ስለተገኘ ብቻ ወጣቱ በማዘወተሪያ ስፍራነት ይጠቀምባቸው ነበር፡፡ እነዚህ ቦታዎች በስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራነት ተመዝግበውና ተከብረው ወጣቱ እንዲጠቀምባቸው በተደጋጋሚ ስፖርቱን ለሚመራው የመንግሥት አካልና ለየአካባቢው ቀበሌዎች ጥያቄ ቢቀርብም ምላሽ ሳያገኙ ቀርተው ለሌላ አገልግሎት ውለዋል፡፡

በተለያየ ጊዜ በስልጣን ላይ የቆዩት የስፖርት ኮሚሽን ኃላፊዎች የማዘወተሪያ ስፍራዎችን ለስፖርቱ አገልግሎት በማስተር ፕላን ውስጥ አስገብተን እናስከብራለን ቢሉም ብዙዎቹ የማዘወተሪያ ስፍራዎች ከወጣቱ እጅ ተነጥቀዋል፡፡ በቅርቡ እንደሰማሁት የክልል ኮሚሽነሮች በየአካባቢያቸው የሚገኘውን የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራ መዝግበው ለፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ሊያቀርቡና እነዚህን ሜዳዎች ከመንግሥት ጋር ተነጋግረው በባለቤትነት ለማስከበር እንዲችሉ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሆነ ተረድቻሁ፡፡ እነዚህ እንዴት ተግባራዊ ይሆናሉ የሚለው ወደፊት የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

ልጆችና ወጣቶች የመጫወቻና የስፖርት መስሪያ ቦታ ሲያጡስ ምን ያደርጋሉ? የሚለው ሌላው ዋና ጥያቄ ነው። መልሱ በየመንደሩ መጫወቻ ቦታ ያጡ ታዳጊዎችና ወጣቶች የስልክ እንጨት ላይ ኳስ በገመድ አስረው ከግድግዳ ጋር እያጋጩ ይጫወታሉ፤ ምትትሮሽ ይጫወታሉ፤ በእግር ጢብ ጢብ ይጫወታሉ፤ የኳስ ስሜታቸውን መቆጣጠር ያቃታቸው ወጣቶች ደግሞ ማዘውተሪያ ስፍራ ስለሌላቸው መኪና በሚመላለስበት አስፋልት ላይ ይጫወታሉ። አስፓልት ላይ በመጫወታቸው መንገደኛውም በኳስ ይመታል፣ የትራፊክ ችግር ይፈጥራሉ፤ ቤተሠባቸውንም ያስጨንቃሉ፤ አልፎም የሞት አደጋ ይደርሳል።

ቀደም ሲል በአዲስ አበባ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ቤቶች ፎቅ አልነበሩም። የመኖሪያ ግቢዎች ትንሽም ቢሆን ሠፋ ይሉ ነበር። የቤቱ ልጆች እዚያው ግቢያቸው ውስጥ ይጫወታሉ። ከግቢ ውጪም ክፍት ቦታ ስለሚኖር ከሠፈር ልጆች ጋር ይጋጠማሉ። አሁን በአብዛኛው ሰው ፎቅ ውስጥ ነው የሚኖረው። በዚያ አካባቢ ደግሞ በርካታ ሰው ይኖራል። ፎቅ አካባቢ በአብዛኛው ቢኖር 'ግሪን ኤርያ' እንጂ ለስፖርት መጫወቻ ተብሎ የተዘጋጀ ቦታ የለም። በዚህ የተነሳ የማዘውተሪያ ሥፍራ በመታጣቱ ወጣቱ ፎቁ ላይ ቁጭ ብሎ ቀርቷል።

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ያጣው ታዳጊና ወጣት የት ነው ያለው? ምንስ እየሠራ ነው? የሚሉ ጥያቄዎችንም መጠየቅ ይገባል። ወጣቱ ከስፖርት በመነጠሉ ደረሠበት የምላቸውን አንዳንድ ነገሮች ላንሳ፤

### ኢንተርኔት መጠቀም

ታዳጊዎች ማዘወተሪያ ስፍራ ስላጡ ክለቦችም ታዳጊዎችን ስለማይዙ ተተኪዎቹ መሄጃ አጡ። ገና በልጅነታቸው ኢንተርኔት ተጠቃሚ ሆኑ። ይህም እየጨመረ ሲሄድ የቴክኖሎጂው ሱሰኛ ሆኑ። ትኩረታቸው በስፖርት ጤናቸውን መጠበቅ ሳይሆን ኢንተርኔት ላይ በሚያገኙት መረጃ ላይ ሆነ። ቴክኖሎጂው ከስፖርቱ ነጥሎ ወሰዳቸው። እናም ኢንተርኔቱ የወጣቱ ማዘወተሪያ ሆነ። ይህ አካሄድ ደግሞ ወጣቱን ከማህበረሠቡ አገለለውና ግለኛ አደረገው። በአካባቢው ያለውን ነገር ለማወቅ አይፈልግም። ቀደም ሲል ለስፖርቱ ሲወጣ ከጓደኞቹና ከአካባቢው ሰዎች ጋር ስለሚቀላቀል በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ብዙ ነገር ያውቃል። አሁን ግን ኢንተርኔት ላይ ስለተተከለ ከአካባቢውም ከባህሉም አፈነገጠ፤ በሀሳቡም አገሩን ጥሎ ወጣ።

### ኳስ ማሳያ ቤቶች

ወጣቱ ማዘወተሪያ ሲያጣ የስፖርት ስሜቱን ለመወጣት ሲል የኳስ ማሳያ ቤቶች ይውላል። በዚህም አካባቢ ስፖርትን በማዘወተር ሳይሆን በመመልከት ተክቶታል።

በግሉም ቤት ውስጥ ቴሌቪዥን ሲያይ፤ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሲያስስ ይውላል። አካሉ እዚህ ሆኖ አዕምሮው ሌላ ቦታ ሄዷል።

### ታክሲ ግፊያ

ወጣቱ በተለያየ መንገድ ከስፖርት እየራቀ በመምጣቱ አድካሚ ነገሮች ውስጥ መግባት አይፈልግም። የአፀደ ህፃናትና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች 4 እና 5 ፎቅ ያለው ሕንፃ ውስጥ ይማራሉ። ደረጃውን መውጣት አይችሉም። መጀመሪያም በስፖርት ሰውነታቸውን ማደርጀት ባለመቻላቸው ደረጃውን መውጣት አሰልቺና አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። እኔ ወደ ቤቴ ለመሄድ አብዛኛውን ጊዜ ታክሲ የምይዘው ሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ ነው። ከሜክሲኮ አደባባይ እስከ ባልቻ ሆስፒታል ድረስ ያለው ርቀት 300 ሜትር ቢሆን ነው። ይህንን ርቀት ለመጓዝ ታክሲ ተጋፍተው የሚይዙ ብዙ ወጣቶች ያጋጥሙኛል። ወጣቱ 300 ሜትር በእግሩ መጓዝ ካልቻለ ምን አይነት ጤነኛ ዜጋ ነው የሚኖረን? የቸኮሉትን እንቀበልና ሌላው ግን ተጋፍቶ ታክሲ ይዞ በየካፍቴሪያው ቁጭ ብሎ ይታያል።

### ሲጋራ

በአሁን ሠዓት ወጣቱ ትምባሆ በጣም እንደሚጠቀም ይነገራል። ትምባሆ ሞኖፖል ከሚያመርታቸው ሲጋራዎች መካከል ኒያላ የተባለውን ምርት ብቻ በቀን 10 ሚሊዮን ሲጋራ በቁጥር አምርቶ ወደ ገበያ ያወጣል። ሲጋራው ሲመረት ከቅጠሉ ሌላ ውስጡ ውስኪ፣ ብራንዲ፣ ቀረፋ ይጨመርበታል ይባላል። አልኮል መጠጦችን ለማይጠቀሙ ሰዎች ከተማ ውስጥ በጪስ መልኩ ቀርቦላቸዋል። አንድ ሲጋራ ተለኩሶ በአማካኝ 16 ጊዜ ይሳባል። ከዚህ ውስጥ ስምንቱ ወደ አጫሹ ውስጥ ሲገባ የተቀረው ስምንቱ አየር ውስጥ ገብቶ አካባቢን ይበክላል። በቀን ውስጥ የ10 ሚሊየን ኒያላ ጪስ አየሩን ይበክላል። የማያጨሰውም በዚህ መልኩ ያገኘዋል። ይህም ወጣቱ ከስፖርት በመነጠሉ የገባበት ሌላው ችግር ነው።

### አልኮል መጠጥ

ቢ.ጂ.አይ. የተባለው የቢራ አምራች ድርጅት በወር 20 ሚሊዮን ሊትር ቢራ ወደ ገበያ ያቀርባል። ከዚህ ውስጥ 48 በመቶ ድራፍት ሲሆን፤ 52 በመቶ ደግሞ የጠርሙስ ቢራ ነው። ወጣቱ በአብዛኛው የድራፍት ተጠቃሚ ነው። በተለይ የማዘወተሪያስፍራ ችግር ስላለ ወጣቱ ጊዜውን የሚያጠፋው መጠጥ ቤት ሆኗል። ቀደም ሲል መጠጥ መጠጣት የሚጀመረው ከሠዓት በኋላ አመሻሽ ላይ ነበር። አሁን ግን በጠዋት የመጠጥ ቤቶች ሙሉ ሆነው ማየት የተለመደ ሆኗል።

## ጤና ጥበቃ

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል በአብዛኛው ሰው ስፖርት እንዲሠራ የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ። ነገር ግን ህብረተሠቡ ማዘወተሪያ ስፍራ ስለሌለ ጤናውን በአግባቡ መጠበቅ አልቻለም። ጤና ጥበቃ 3,900 ጤና ጣቢያዎችን ገንብቷል። ጤና ጣቢያዎቹን ለመገንባት ለሕንፃዎቹ፣ ለህክምና መሣሪያዎች፣ ለመድኃኒት፣ ለባለሙያ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን አንድም ጤና ጣቢያ በውስጡ የማዘወተሪያ ስፍራ የለውም።

ጤና ጥበቃ የጤና ጣቢያ ወይንም ሆስፒታል ሲገነባ በውስጡ የአካል እንቅስቃሴ መስሪያ ስፍራ አብሮ ቢሰራ ከህክምናው ጎን ለጎን ህመምተኞች በስፖርት ጤናቸውን እንዲጠብቁ ማድረግ ይችላል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አላማው በቅድሚያ በሽታን መከላከል በመሆኑ በስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራ ችግሮችን ማቃለል ይችላል። ትምባሆ ሞኖፖልም ከሲጋራ ከሚያገኘው ገቢ አምስት በመቶ ለማዘውተሪያ ስፍራ ግንባታ ቢያውል ቢያንስ ሲጋራ ተጠቃሚ ደንበኛው ስፖርት እየሠራ ጤናውን እንዲያሻሽል ይረዳዋል። በተመሳሳይ የቢራ አምራቹም የተወሰነ ፐርሰንት ለማዘወተሪያ ስፍራ ግንባታ ድጎማ ቢያደርግ በጤና ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ነገር ግን ይህን ተግባር ላይ ለማዋል የሚያስገድድ ሕግ ያስፈልጋል።

## ኳስ ወደቤት

ቀደም ሲል መንደር ውስጥም ሆነ ሜዳ ላይ ህፃናትና ወጣቶች በክፍት ቦታ እግር ኳስ ይጫወቱ ነበር። አሁን የመጫወቻ ሜዳ እጥረት ስላለ እግር ኳስ ወደ ቤት ውስጥ እየገባ ነው። ከአለፉት 5 ዓመታት ጀምሮ የአምስትዮሽ ጨዋታ በሚል (አንድ ቡድን 5 ተጫዋች ይይዛል) በኮተቤና በወወክማ ጅምናዚየሞች ወጣቶች ቡድን እያቋቋሙ በአምስትዮሽ ግጥሚያ ላይ ይሳተፋሉ። ጅምናዚየሞቹ የተለያየ ስፖርት የሚካሄድባቸው በመሆኑ የአምስትዮሽ እግር ኳስ ለመጫወት አመቺ ናቸው። ይህ አምስትዮሽ ጨዋታ የሚመራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ውድድር ቢያካሄድም፤ በጅምናዚየም እጥረት ሳቢያ የፈለገው ያህል መግፋት አልቻለም።

## 5 መደምደሚያ

ከላይ እንደተብራራው በኢትዮጵያ ስፖርትን በወጣቱ ዘንድ ለማስፋፋት በጎ ጅምሮች ይታያሉ። ከነሱም መካከል፤

- ብሔራዊ የስፖርት ፖሊሲ በአገራችን መቀረፁና መተግበር መጀመሩ፤
- ስፖርቱ ህዝባዊ አደረጃጀት እንዲኖረው ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤
- የት/ቤቶችና የኮሌጆች ውድድሮች ዳግም መጀመራቸው፤

- የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በተወሠነ መልኩም ቢሆን በአንዳንድ ስፍራዎች መገንባትና መስፋፋት መጀመራቸው በመልካም ጅምርነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በተቃራኒው ስፖርቱ የሚፈለግበት ደረጃ እንዳይደርስ በተለይም ወጣቱ ከስፖርት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ያላስቻሉት ማነቆዎችም አሉ፡፡ ከእነሱም መካከል ዋና ዋናዎቹ፤

- የስፖርቱ አደረጃጀት የታሰበውን ያህል አሳታፊ አለመሆን፤
- የህዝባዊ ስፖርት (ማስ ስፖርት) የተፈለገውን ያህል አለመስፋፋት፤
- በከተሞች መስፋፋትና ግንባታ ሳቢያ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና መጫወቻ ቦታዎች መጥፋት፤
- በግል ት/ቤቶችና የህክምና ተቋማት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አለመኖር፣
- ስፖርትን በተመለከተ የጉዳዩ ባለቤት በሆነው የሚኒስቴር መ/ቤት፣ ሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶች፣ የንግዱ ህብረተሠብ፣ የሲቪል ማኅበረሠብ መካከል እኩል ግንዛቤና ትኩረት አለመኖር ይጠቀሳሉ፡፡

በመሆኑም ስፖርቱን የሚመሩት ክፍሎች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስፖርት ምሁራንና ሌሎች አካላት በእነዚህ የወጣቱን የስፖርት ተሣትፎ በገደቡ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ስፖርት ከሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች ጋር ተጣጥሞ ወጣቱ በአካል፣ በአዕምሮና ስነ-ልቦና የታነጸ ዜጋ እንዲሆን የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

# የአደገኛ ዕፅ ተጠቃሚነት እና ባህሪያዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የጤና ጠንቆቹ

ጌጤ ፀጋዬ

## 1 መግቢያ

በዓለም ወደ አራት ሺህ የሚደርሱ አዕምሮን የሚያነቃቁ ንጥረ-ነገሮች የያዙ ዕፅዋት መኖራቸውንና ከነዚህም መካከል ወደ 60 የሚሆኑት በዓለም ዙሪያ በሰው ልጆች የሚዘወትሩ መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ (Malcom,1972 cited in Austin, 1979)፡፡ በተጨማሪም የሰው ልጆች እነዚህን አነቃቂ ነገር ያላቸውን መድኃኒቶች ከጥንት ጀምሮ ይጠቀሙ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ (Hales, 1999 Cited in Santrocte, 2000)፡፡ ለምሳሌ አገራችን ኢትዮጵያ የጫት የመጀመሪያ አብቃይ መሆኗ ይነገራል፡፡ እንዲያውም ጫት ከኢትዮጵያ ወደ አካባቢው የአፍሪካና የአረብ አገሮች በተለይም ወደ ኬንያ፣ ማላዊ፣ ዑጋንዳ፣ ታንዛንያ፣ የመን፣ ኮንጎ፣ ዚምባብዌ፣ ዛምቢያ፣ ማዳጋስካር እና ወደ ደቡብ አፍሪካ መስፋፋቱ ይነገራል፡፡ በተጨማሪም መረጃዎች በኢትዮጵያ አገራችንም ሀረርጌ የጫት የመጀመሪያ መገኛ ስፍራ እንደሆነች ያሳያሉ፡፡ በአንጻሩ የጫት መጀመሪያ መገኛ አገር የመን መሆኗን ሌላ አፈ-ታሪክ ያስረዳል (Lemessa, 2001)፡፡

በኢትዮጵያ፣ የመን እንዲሁም ሶማሊያ ጫት ለመዝናኛነት በተለይም ሰዎች ሠብሠብ ብለው በሚቀመጡበት ጊዜ ሲቃም አያሌ ዘመናት ያስቆጠረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ጫት ለመዝናኛነት ጥቅም ላይ የዋለው ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በደቡብ ቀይ ባህር አካባቢ እንደሆነ ነው (Weir, Shelagh,1985)፡፡ በጥንት ጊዜ ኃይማኖተኛ ሰዎች በለሊት ለረጅም ጊዜ ነቅተው ለመጸለይ ያስችላቸው ዘንድ ጫትን ይጠቀሙ እንደነበር ታውቋል፡፡ አንድ ጥናት እንዳመለከተው በሐረርጌ አካባቢ ጫት መደኃኒትነት ያለው ዕፅ እንደሆነ ይታመናል (Alem, 2001)፡፡ ለምሳሌ ያህል የተቀመመ የጫት ቅጠልና ስር ኢንፋሉዌንዛን እንዲሁም ሳል፣ ጨብጥ፣ የአስም ህመምና ሌሎች የመተንፈሻ አካል በሽታዎችን ለማከም ጥቅም ላይ ይውል ነበር፡፡ በተጨማሪም የጫት ስር ለሆድ ቁርጠትና ለእባጭ በሽታ ይወሰዳል፡፡ ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ ጫት ወደተለያዩ አገሮች ኤክስፖርት በማድረግ ከፍተኛ ገቢ ታገኛለች (Lemessa, 2001)፡፡

ቀደምት ከሆኑት ጥናቶች መካከል የአንደኛው ውጤት እንደሚያሳየው የጫት ተጠቃሚዎች በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውንና እንዲያውም

ጸታ፣ ዕድሜና ኃይማኖትን ባልለየ መልኩ ተጠቃሚነቱ በመስፋፋት ላይ መሆኑ ተገልጿል (Gebreselassie & Gebre, 1995)። በተመሳሳይ የቅርብ ጊዜ ጥናቶችም ይህንኑ አረጋግጠዋል። የጫት ተጠቃሚነትን ስናነሳ በአገራችን ጫትን በተመለከተ ምንም አይነት ሕጋዊ ክልከላ ባለመኖሩ የተጠቃሚነት ስርጭቱ በመላው አገሪቱ በመስፋፋት ላይ ይገኛል። የጫት ተጠቃሚነት ጉዳይ በአገራችን ብቻ ሳይሆን በሌሎች አፍሪካ አገሮችንም ትኩረት የሳበ ማኅበራዊ ችግር እየሆነ መምጣቱ ይታያል (Lemessa, 2001)።

በሌላ በኩል ደግሞ ስለጫት ያለው ሁኔታና አመለካከት ከቦታ ወደቦታ ይለያያል። ለምሳሌ በአሜሪካና ካናዳ እንዲሁም በአንዳንድ የአውሮፓ አገሮች ጫት ሄሮይንና ኮኬይን ከተባሉት አደገኛ መድኃኒቶች ተርታ ይፈረጃል። የሚታይበትም የሕግ አግባብ ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ነው (The Guardian, 2004)።

ለረጅም ጊዜ አልኮል ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የአፍሪካውያን ማኅበራዊ ህይወት አካል ሆኖ ቆይቷል። በአብዛኛው ጊዜ አልኮል የሚዘጋጀው ከዳጉሳና በቆሎ ከመሳሰሉ የእህል ዘሮች ሲሆን፤ ለምሳሌ ከገብስ የሚዘጋጅ ቢራ በግብጽ ጥቅም ላይ የዋለው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ4241 ዓመተ-ዓለም እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ (Obot, 1993 Cited in Dimah & Gire, 2004)።

ቀደም ሲል በመስኩ የተጠና አንድ ጥናት አልኮል በስፋት ተጠቃሚዎች ያሉት መሆኑን አመላክቷል። ይህ ጥናት በተጨማሪ ካናቢስ የተሠኘው ዕፅ በሺህ ለሚቆጠሩ ዓመታት ሰዎች የሚጠቀሙበት የኖሩ መሆኑንና ለመድኃኒትነትም ሲወሰድ መቆየቱን ያሳያል (Losken, *et. al*, 1996)። አንዳንድ ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ደግሞ ለአፍሪካዊያን ካናቢስ የሚባለውን ዕፅ ያስተዋወቁት ሙስሊም የባሕር ላይ ነጋዴዎች እንደሆኑና ጊዜውም 12ኛው ክፍለ-ዘመን እንደሆነ ይነገራል (Du Toit,1980)።

በኢትዮጵያ ካናቢስ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ መዋል የጀመረው ወፍ-ዘራሽ ሆኖ በሚበቅልባቸው ገዳማት እንደሆነ ቢታወቅም፤ ወደቀረው ህብረተሠብና የአገሪቱ ክፍል የተስፋፋበት ሁኔታ በውል አይታወቅም። ነገር ግን አንዳንድ መላ ምቶች የካናቢስን መስፋፋት ከቱሪስቶች ጋር ያገናኙታል።

በኢትዮጵያ የሻሸመኔ ከተማ ካናቢስ በስፋት ከሚመረትባቸው ሰፍራዎች መካከል መሆኗ ይታወቃል። እንዲያውም ካናቢስ ከአርባ ዓመት በላይ በሻሸመኔና በአካባቢዋ ሲመረት እንደቆየ አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ (Kassaye, *et. al*, 1999)። ካናቢስ በኢትዮጵያ ስራ አጥ በሆኑ ሰዎችና በጎዳና ተዳዳሪዎች እንዲሁም የወንጀል ድርጊት በሚፈጽሙ ሰዎች በስፋት የሚወሰድ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ (Ethiopian Federal Police Drug Control Dept 2003, UNODC, 2007)። ከኦሺኒያ አካባቢ

ቀጥሎ የማሪዋና ተጠቃሚነት ስርጭት የተመዘገበው በአፍሪካ አህጉር ነው (UNODC/World Drug Report, 2006)።

በሌላ በኩል ደግሞ በምስራቅ ሜድትሬንያን የሺሻ ተጠቃሚነት የሚዘወተረው በተለይም ከዝቅተኛው የኢኮኖሚ ክፍል በሆኑት ወንድ አረጋውያን ነው። ሆኖም ግን በአሁኑ ጊዜ የዕድሜም ሆነ የጾታ እንዲሁም የኢኮኖሚ ደረጃን ሳይለይ ሺሻ ማጨስ በኅብረተሠቡ ዘንድ በስፋት እየተስፋፋ መሆኑ ታውቋል (Center for Tobacco Control Research, 2006)። በኢትዮጵያ ሺሻ ማጨስ ያልተለመደና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወጣቶች ዘንድ እየታየ ያለ ጉዳይ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአሁኑ ወቅት በተለይም በትልልቆቹ የኢትዮጵያ ከተሞች ሺሻ ማጨስ እየተስፋፋ መሆኑ ይታወቃል (Tsegaye and Bharwaj, 2010) ።

ቀደም ባሉት ዓመታት የአደገኛ መድኃኒቶች እና አደንዛዥ ዕፆች ተጠቃሚነት በኢትዮጵያ ተስፋፍቶ የጎላ ማኅበራዊ ችግር ሆኖ የሚታይ አልነበረም። በአንጻሩ በአሁኑ ወቅት የችግሩ ስርጭት የት/ቤቶችን፣ የመምህራንን፣ የወላጆችን፣ የህብረተሠቡንና የመንግሥትንም ትኩረት ሁሉ የያዘ ማኅበራዊ ችግር ወደመሆን ደረጃ ያደገ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኗል (Gete, 2013)።

ይህ ጥናትም የተካሄደው የችግሩ አሳሳቢነት በአገሪቱ በስፋት በሚታይባቸው በሻሸመኔ እና በሀዋሳ ከተሞች በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ አተኩሮ ነው። የጥናቱ ዋና ዋና አላማዎችም፤

- የአልኮል፣ አደገኛ መደኃኒቶችና አደንዛዥ ዕፆች ተጨቃሚነት ስርጭት በሻሸመኔና ሀዋሳ የመንግሥትና የግል ት/ቤቶች ምን ያህል እንደሆነ ማየት፤
- የተሳታፊዎቹ የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒቶች ተጠቃሚነት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ፤
- የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፆችና አደገኛ መድኃኒቶች ስርጭት በጾታ፣ በከተማና በኃይማኖት ለይቶ ማየት፤
- ወጣት ተማሪዎችን ለዕፅና መድኃኒት ተጠቃሚነት የሚያጋልጡ ዋና ዋና ምክንያቶችን ማወቅ፤
- የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒቶች ተጠቃሚነት በባህሪ፣ በጤና በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መረዳት ናቸው።

# 2 ምርምሩ የተካሄደበት ዘዴ

## 2.1 ጥናቱ የተካሄደበት ስፍራ

ይህ ጥናት የተካሄደው ከአዲስ አበባ 250 ኪ.ሜትር ርቀት ባላት በሻሸመኔ ከተማ እና የደቡብ ክልል ዋና ከተማ በሆነችውና ከአዲስ አበባ ከተማ 275 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው የሀዋሳ ከተማ ነበር። ሁለቱ ከተሞች የተመረጡበትም ዋና ምክንያት አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መደኃኒቶችን በተመለከተ ካላቸው ስትራቴጂያዊ ቦታነት የተነሳ ነው።

## 2.2 የናሙና አወሳሰድ

በምርምሩ ተሳታፊ የሆኑት ተማሪዎች ቁጥር የተወሰነው የናሙና አወሳሰድን በሚያመለክት ቀመር (Sample size determining formula) መሠረት ነበር። በዚሁ መሠረት 'የተከፋፈለ አቦሠጥ የናሙና አመራረጥ' (Stratified Random Sampling) ዘዴን በመጠቀም በሻሸመኔና ሀዋሳ የመንግሥትና የግል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከ9-12ኛ ተማሪዎች ከሆኑ ተማሪዎች ከሻሸመኔ 828 ከሀዋሳ 918 በድምሩ 1,746 ተማሪዎች ለጥናቱ በናሙናነት ተመርጠው ነበር። ከነዚህ መካከል በጥናቱ ለመሳተፍ በመጀመሪያ ፈቃደኛነታቸው ገልጸው የነበሩ 26 ተማሪዎች ኃሳባቸውን በመቀየራቸው የጥናቱ ናሙና ብዛት ወደ 1,726 እንዲወርድ ተደርጓል። በተጨማሪም ከ48 ሰዎች ጋር የቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) የተካሄደ ሲሆን፤ በውይይቶቹም የትምህርት ቤት ርዕሳነ-መምህራን፣ የመምህራን ተወካዮች፣ የተማሪ ካውንስል አባላት እንዲሁም የኃይማኖትና የማህበረሠብ መሪዎች ተሳትፈውባቸዋል።

በጥናቱ ወቅት ትክክለኛ የምርምር ስነ-ምግባሮች ለመከተል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። የጥናቱ መሠረታዊ ዓላማዎች ለጥናቱ በናሙናነት ለተመረጡ ተማሪዎች በሙሉ ተገልጾላቸዋል። በተጨማሪም በዚህ ጥናት መሳተፍ በበጎ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆኑንም እንዲያውቁት ከመደረጉ በላይ በማንኛውም ጊዜ ተሳታፊዎች ኃሳባቸውን ለመቀየር ቢፈልጉ ተሳትፎአቸውን ያለምንም ተጠያቂነት ማቋረጥ እንደሚችሉ በግልፅ ተነግሯቸዋል።

የመረጃ ስብሰባ ሂደቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ መረጃው ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ተሰብስቧል። በተጨማሪም ማንኛውም ተሳታፊ የሚሞላው መጠይቅ የመረጃ ሰጪውን ስም ወይንም ሌላ መለያ ስላልተጠየቀበት የመረጃው ምስጢራዊነት በቀጣይም አስተማማኝ መሆኑን ለተሳታፊዎች ተገልጿል።

## 2.3 የመረጃ አሠባሠብ ቴክኒክና ሂደት

ይህ ጥናት አኃዛዊ (Quantitative) እና ኢ-አኃዛዊ (Qualitative) መረጃዎች በመጠቀም የተካሄደ ነው። አኃዛዊ መረጃው የተሰበሰበው መጠይቅ (survey) በማዘጋጀት ሲሆን ኢ-አኃዛዊ መረጃው የተሰበሰበው ደግሞ በቡድን ውይይቶች ነው። መጠይቁ በመጀመሪያ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከተዘጋጀ በኋላ ወደ አማርኛ ተተርጉሟል። የተተረጎመው መጠይቅ ትክለኛነት ከተረጋገጠ በኋላ ሙከራ ተደርጎበታል። ከሙከራው በተገኘው አስተያየት መሠረት የማስተካከል ሥራ ከተሠራ በኋላ መጠይቁ በመጨረሻ ለምርምሩ መረጃ አሰባሰብ ውሏል።

የዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው ጥናቱ ከተካሄደባቸው ት/ቤቶች በተመለመሉና በተመራማሪዎቹ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በሚደረግላቸው 46 ሥልጠና በተሰጣቸው መምህራን ነው።

# 3 የመረጃው ስታትስቲካዊ ትንተና

የመረጃው ስታትስቲካዊ ትንታኔ የተካሄደው (SPSS Version 11) በተባለ ሶፍት ዌር ነው። የመረጃው ትንታኔ ከመካሄዱ በፊት የመረጃ ማጽዳት ስራ ተካሄዷል። በዚህም 39 መጠይቆች የተሟላ መረጃ ስላልነበራቸው እንዲወጡ ተደርጓል። በመቀጠልም ከቀሩት መጠይቆች በተሰበሰበው መረጃ ትንታኔ ተሠርቷል።

## 3.1 የጥናቱ ውጤትና ማብራሪያ

በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች እንደ የመኖሪያ ከተማ፣ ጾታ፣ የትምህርት ክፍል፣ የሚማሩበት ት/ቤት ሁኔታና የወላጆቻቸው የትምህት ደረጃ የመሳሰሉት ልዩ ልዩ ማኅበራዊና 'ዲሞግራፊያዊ' (socio-demographic characterstics) ባህሪያት ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ ተዘርዝረዋል።

**ሠንጠረዥ 1፡-** የናሙናው ማኅበራዊና ሥነ-ህዝባዊ (demographic) ባሕሪያት

| Variable | | ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ከተማ | ሻሸመኔ | 774 | 46.0 |
| | ሀዋሳ | 907 | 54.0 |
| ጾታ | ሴት | 604 | 35.9 |
| | ወንድ | 1,077 | 64.1 |
| ት/ቤት | የግል | 185 | 11.0 |
| | የመንግስት | 1,496 | 89.0 |
| ክፍል | 9tኛ እና 10ኛ | 1,197 | 71.2 |
| | 11ኛ እና 12tኛ | 484 | 28.8 |
| ዕድሜ | ከ14 ዓመት በታች | 67 | 4.0 |
| | 14-17 ዓመት | 859 | 51.1 |
| | 18-21 ዓመት | 704 | 41.9 |
| | ከ21ዓመት በላይ | 51 | 3.0 |
| ኃይማኖት | ኦርቶዶክስ | 631 | 37.5 |
| | ካቶሊክ | 128 | 7.6 |
| | ፕሮቴስታንት | 428 | 25.5 |
| | ሙስሊም | 331 | 19.7 |
| | ሌላ | 163 | 9.7 |
| የእናትየትምህርት ደረጃ | ማንበብና መፃፍ የማይችል | 533 | 31.7 |
| | ማንበብና መፃፍ የሚችል | 408 | 24.3 |
| | አንደኛ ደረጃ | 234 | 13.9 |
| | ሁለተኛ ደረጃ | 282 | 16.8 |
| | የሙያ(ቮኬሽናል) | 33 | 2.0 |
| | ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ | 191 | 11.4 |
| የአባት የትምህርት ደረጃ | ማንበብና መፃፍ የማይችል | 321 | 19.1 |
| | ማንበብና መፃፍ የሚችል | 374 | 22.2 |
| | አንደኛ ደረጃ | 240 | 14.3 |
| | ሁለተኛ ደረጃ | 329 | 19.6 |
| | የሙያ (ቮኬሽናል) | 90 | 5.4 |
| | ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ | 327 | 19.5 |

**ሠንጠረዥ 2፡-** ባለፉት አንድ ዓመትና 30 ቀናት ዕፅ ተጠቃሚዎች ብዛት በቁጥርና በመቶኛ

| ባለፉት 12 ወራት | | | | ባለፉት 30 ቀናት | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዕፅ የተጠቀሙ | | ዕፅ ያልተጠቀሙ | | ዕፅ የተጠቀሙ | | ዕፅ ያልተጠቀሙ | | | |
| በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 713 | 42.4% | 968 | 57.6% | 702 | 41.7% | 979 | 58.2% | 1,681 | 100% |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው ከ1,681 በጥናቱ ከተሳተፉት ተማሪዎች መካከል ከ40% በላይ የሚሆኑት ባለፉት 12 ወራት በጥናቱ ከተጠየቁት አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፆችና አደገኛ መደኃኒቶች አንዱን ወይንም ከአንድ በላይ መጠቀማቸውን ሪፖርት አድርገዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡-** *ጥናቱ ካካተታቸው አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፆችና መድኃኒቶች መካከል ባለፉት 30 ቀናት የተጠቀሙ ብዛት በመቶኛ*

| ተ.ቁ | የዕፅ አይነት | የተጠቃሚ ብዛት (በመቶኛ) |
|---|---|---|
| 1 | አልኮል | 31.2 |
| 2 | ጫት | 15.0 |
| 3 | በአፍንጫ የሚሸተቱ (ቤንዚን ሙጫ የንፋስ (Spray) ቀለም) | 8.9 |
| 4 | ሲጋራ | 6.8 |
| 5 | ሺሻ | 4.7 |
| 6 | ማሪዋና | 4.3 |
| 7 | ኮኬይን | - |
| 8 | ሄሮይን | - |
| 9 | ሌሎች | 2.3 |

ከላይ ያለው ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው በቅደም ተከተል አልኮል፣ ጫትና በአፍንጫ የሚሳቡት/የሚሸተቱ ነገሮች ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸሩ ከፍ ያለ የተጠቃሚ ቁጥር እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ቀደም ባሉ ተመሳሳይ ጥናቶች በዋነኛነት ተጠቃሚ ካላቸው መካከል ሲጋራ አንዱ እንደነበረ መረጃዎች ይጠቁማሉ (G/selassie & Gebre, 1995)፡፡ ይሁንና በዚህ ጥናት በአፍንጫ የሚሳቡ (እንደ ቤንዚን ያሉ) ነገሮች ሲጋራን እንደተኩት ይታያል፡፡ ይህም አዲስ ክስተት መሆኑ ተዘግቧል፡፡

በዚህ ጥናት እንደታየው ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል አልኮል የ31.2% ተጠቃሚ እንዳለው ታውቋል። በሌሎች የአፍሪካ አገሮችም በተሠሩ ተመሳሳይ ጥናቶች የአልኮል ተጠቃሚነት ተቀዳሚውን ስፍራ ይዞ ይገኛል። ለዚህም አልኮል በቤት ውስጥ መዘጋጀት የመቻሉና በዚህም ልጆች በቀላሉ ሊያገኙት የሚችሉበት ዕድል መኖሩ ዋነኛ ምክንያት ሳይሆን እንዳልቀረ ጥናቶች ያመላክታሉ (Nazarius & Rogers, 2005)። በተመሳሳይም ቡድን ውይይቶች ላይ የተገኙ መረጃዎች እንዳሳዩት በየበዓላቱና አውዳመቱ በቤት ውስጥ ጠላን የመሳሰሉ የአልኮል መጠጦች ስለሚዘጋጁ ልጆች አልኮልን በቀላል የሚያገኙትና መጀመሪያ የሚሞክሩት እንደሆነ ገልጸዋል። በተለይም አንዳንድ ወላጆች እና ዐዋቂ የቤተሠብ አባላት ህፃናት የዐዋቂዎችን ትራፊ እያነሱ ሲጨልጡ ከመገሰፅ ይልቅ የሚስቁ፣ የሚያበረታቱና እና እንዲያውም አልኮል ለህፃናት የሚያቀምሱ መኖራቸውን ተናግረዋል።

ይህም ተግባር ህፃናትን ገና ከወዲሁ በጨቅላነታቸው ከአልኮል መጠጥ ጋር የሚያስተዋውቅ አጉል ተግባር በመሆኑ ትምህርት የሚያስፈልገው እንደሆነም ጨምረው ገልፀዋል። የዚህ ጥናት ውጤት በተለይም የአልኮል ተጠቃሚነትን በተመለከተ ሲታይ ቀድሞ ከተመዘገቡ አንዳንድ ጥናቶች (ለምሳሌ Kassaye *et al*, 1999) ጋር ሲነጻጸር የአልኮል ተጠቃሚ ተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ መሄዱን ያሳያል።

ከአልኮል በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ (15%) ተጠቃሚ ያለው ጫት መሆኑን ጥናቱ በግልጽ ያሳያል። የጫት ተጠቃሚ ተማሪዎች ቁጥር በከተማ ንጽጽር ሲደረግ በሀዋሳና በሻሸመኔ ከተሞች መካከል የተጠቃሚዎቹ ቁጥር ተመሳሳይነት አሳይቷል። ቀደም ሲል ከተካሄደና የ8.5% የጫት ተጠቃሚነትን ከሚያሳይ አንድ ጥናት (Kebede *et. al*, 2002) ውጤት ጋር ሲነጻጸር ግን ይህ ጥናት የጫት ተጠቃሚ ቁጥር ከፍ ማለቱን አሳይቷል።

በተመሳሳይ በሀዋሳና በሻሸመኔ የተካሄዱት የቡድን ውይይቶች እንዳመለከቱት ጫት በርካታ ተጠቃሚዎች ያሉት ዕፅ ሲሆን፤ በተለይም በወጣት ተማሪዎች መካከል ጫት የመቃም መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ተገልጿል። የጫት ተጠቃሚነት የሚጀምረው ገና በወጣትነት ወቅት ነው። ለዚህም ደግሞ ህጋዊ ክልከላ ያለመደረጉ አስተዋጽኦ እንዳለው ተገልጿል። በአንጻሩ በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ ጫት በሕግ የተከለከለ ነው።

ኢትዮጵያ ወደጎረቤት ጅቡቲ፣ ሱማሊያ እንዲሁም ሌሎች አገሮች የምትልከው የጫት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። በዚያው ልክ ደግሞ የአገር ውስጥ የጫት ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመር ግምት ውስጥ ሲገባ በአገር ውስጥ ያለውንም የጫት ተጠቃሚ ቁጥር የዋጋው ንረት አንኳን ያልበገረው መሆኑን አሳይቷል።

በአፍንጫ የሚሳቡ ወይንም የሚሸተቱት ቤንዚንና የመሳሰሉት ደግሞ የ8.9% ተጠቃሚ ያላቸውና በሶስተኛ ደረጃ የሚታዩ ናቸው፡፡ በአንጻሩ በቡድን ውይይቱ የተሳተፉ ተሳታፊዎች በአፍንጫ የሚሸተቱት እንደቤንዚን የመሳሰሉትን ይበልጥ አዘወትረው የሚጠቀሙ የጎዳና ተዳዳሪ የሆኑ ልጆች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ የሆነ ሆኖ ከጥናቱ ውጤት የታየው በቤት ውስጥ ከወላጆቻቸው ጋር የሚኖሩም ልጆችም የችግሩ ተጠቂ መሆናቸውን ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ አገር አቀፍ የሆነ ጥናት ከት/ቤት ውስጥ ካሉ ተማሪዎች 0.2% ብቻ ቤንዚን የመሳብ ልምድ እንዳላቸው ገልጿል፡፡ (Mitike, *et al*, 2002)፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት ከላይ የተጠቀሰው አገር አቀፍ ጥናት ከተሰራ ከዓመታት በኋላ የተጠና በመሆኑ በእነዚህ ዓመታት የተጠቃሚዎቹ ቁጥር መጨመሩን ያሳያል፡፡ ከዚህም በላይ ይህኛው ጥናት በቤንዚን ብቻ ላይ ያተኮረ ሳይሆን ሌሎች በተመሳሳይ የሚሸተቱ እንደ ሙጫ እና የሚነፉ ቀለሞችንም (spray paints) ማሸተት የጨመረ በመሆኑ ቁጥሩ ጨምሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከአነስተኛና ጥቃቅን የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ጋር ተያይዞ ጥናቱ በተካሄደባቸው ከተሞች ከምንግዜውም በላይ የእንጨት ሥራ ንግድ ቤቶች ተስፋፍተዋል፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል ብስክሌት ይጠቀሙ የነበሩ ብዙ ወላጆች በአካባቢው ብስክሌታቸውን በሞተር ሳይክል ስለለወጡ ልጆች በቀላሉ ቤንዚንና የመሳሰሉ ነገሮችን የማግኘት ዕድላቸው ጨምሯል፡፡ ስለዚህም ይህ ሁኔታ የራሱ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል፡፡

ሺሻ ጋያ መሠል በሆነ ዕቃ በቱቦ የሚጨስ በተለያየ ፍራፍሬ ጠረን የተቀመመ ትንባሆ ቅልቅል ነው፡፡ ሺሻ ማጨስ በአገራችን ከተወሠኑ ዓመታት ወዲህ የመጣ ቢሆንም፤ በአሁኑ ጊዜ በትልልቅ የአገራችን ከተሞች በመስፋፋት ላይ ያለ ነው፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ የተጠና አንድ ጥናት የሺሻ ተጠቃሚዎች ብዛት 0.9% መሆኑን ያመለክታል (Mitike *et al*, 2002)፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት በጥናቱ ከተሳተፉት ተማሪዎች መካከል የሺሻ ተጠቃሚዎች ብዛት 4.7% መሆኑን አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ የቡድን ውይይቱ ተሳታፊዎች በሻሸመኔና በሀዋሳ የሺሻ ቤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፉ መምጣታቸውንና ወጣቶችም ሺሻ ማጨስን እንደዘመነኛነት እየቆጠሩት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ሺሻ ማጨስ በአገራችን የቅርብ ጊዜ ጅማሬ ይኑረው እንጂ በወጣቶች ዘንድ ያለው አመለካከት ሺሻ አጫሽነትን በከፍተኛ ፍጥነት ሊያሳድግ የሚችል አይነት መሆኑን ይህ ጥናት አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ በዚህ ጥናት የምርምር መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ተመራማሪዎቹ ያነጋገሯቸው አንዳንድ አጫሾች ሺሻን የሚያጨሱበት ዋነኛው ምክንያት ለመዝናናት ቢሆንም፤ ሺሻ ከማዝናናት በዘለለ ቆዳን የሚያጠራና ውበትን

የሚጨምር ንጥረ ነገር በውስጡ እንዳለ የሚያውቁ መሆኑን አስረድተዋል:: ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ በብዙዎች ዘንድ ሲስፋፋ ብዙዎችን ለጉዳት መዳረጉ አይቀሬ ይሆናል::

በዚህ ጥናት ከተካተቱት አደገኛ መድኃኒቶች አንዱ የሆነው ማሪዋና ነው:: ማሪዋና ሀሺሽ ተብሎም ይታወቃል:: ይህ አደገኛ መድኃኒት 4.3% ተጠቃሚዎች እንዳሉት መረጃው ያሳያል:: ይሁንና ማሪዋና ከጫትና አልኮል በተለየ ሕጋዊ ክልከላ ስላለበትና ምንም እንኳን መጠይቁ የተሳታፊዎቹን ማንነት የማይጠይቅ ቢሆንም አንዳንድ ተጠቃሚዎች እውነቱን ሪፖርት ለማድረግ ሊጠራጠሩ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል:: ስለዚህም የተጠቃሚዎቹ ቁጥር ሪፖርት ከተደረገው የሚበልጥበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ይታሠባል::

**ሠንጠረዥ 4፡-** ባለፉት 30 ቀናት የአልኮል፣ ዕፅና መድኃኒት ተጠቃሚ በከተሞች ተለይቶ ሲታይ

| የአልኮል/ዕፅ/ መድኃኒት | ከተማ | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሻሸመኔ | | ሀዋሳ | | | |
| | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| አልኮል | 244 | 14.4 | 282 | 16.8 | 526 | 31.2 |
| ጫት | 120 | 7.1 | 134 | 8.0 | 254 | 15.1 |
| በአፍንጫ የሚሳቡ ነገሮች | 83 | 4.9 | 67 | 4.0 | 150 | 8.9 |
| ሲጋራ | 55 | 3.3 | 55 | 3.3 | 110 | 6.5 |
| ሺሻ | 42 | 2.5 | 37 | 2.2 | 79 | 4.7 |
| ማሪዋና/ሀሺሽ | 43 | 2.6 | 30 | 1.8 | 73 | 4.3 |
| ኮኬይን | - | - | - | - | - | - |
| ሄሮይን | - | - | - | - | - | - |
| ሌሎች | 23 | 1.4 | 16 | 1.0 | 39 | 2.3 |
| **አጠቃላይ ድምር** | **774** | | **907** | | **1681** | |

በሀዋሳና ሻሸመኔ ከተሞች የማሪዋና ተጠቃሚዎች በንጽጽር ሲታይ በሻሸመኔ ይበልጥ የተጠቃሚዎች ቁጥር እንዳለ ታይቷል:: ሻሸመኔ በአገራችን ዋነኛዋ ሀሺሽ የሚመረትበት ከተማ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ከሐዋሳ ይልቅ በሻሸመኔ የሀሺሽ ተደራሽነት ስለሚጨምር የበለጠ ተጠቃሚዎች መኖራቸው ከዚህ ጋር የተያያዘ እንደሚሆን ይታሠባል::

**ሠንጠረዥ 5፡-** *<u>የአልኮል ዕፅና መድሀኒት ተጠቃሚዎች የተጠቃሚነት ደረጃ (ባለፉት 30ቀናት)</u>*

| ተማሪዎቹ የሚጠቀሚቸው ዕፆችና መድኃኒቶች ብዛት | የተጠቃሚዎች ቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| አንድ አይነት | 419 | 58.8 |
| ሁለት አይነት | 168 | 23.6 |
| ሶስት አይነት | 66 | 9.2 |
| አራት አይነት | 37 | 5.2 |
| ከአራት አይነት በላይ | 23 | 3.2 |

ከላይ እንደተጠቀሰው ከአልኮል ዕፅና መድኃኒት ተጠቃሚዎቹ መካከል 17.6% የሆኑት ሶስትና ከዚያ በላይ የሆኑ የተለያዩ ዕፆችና መድኃኒቶች ተጠቃሚ እንደሆኑ ታውቋል፡፡

## 3.2 የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒቶች ተጠቃሚነት በማኅበራዊና ዲሞግራፊያዊ ፋክተሮች ሲታይ

### *ሀ. በጾታ*

በዚህ ጥናት ከተሳተፉት 604 ሴት ተማሪዎች መካከል 216 (35.8%) ተማሪዎች ባለፉት 12 ወራት፣ እንዲሁም 212 (35.0%) ተማሪዎች ደግሞ ባለፉት 30 ቀናት የአንድ ወይንም የሌላ አደንዛዥ ዕፅ፣ አደገኛ መድኃኒት ወይም አልኮል ተጠቃሚ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በአንጻሩ በጥናቱ ከተካተቱት ወንድ ተማሪዎች መካከል 497 (46.2%) ባለፉት 12 ወራት፤ እንዲሁ 490 (45.5%) ባለፉት 30 ቀናት አደንዛዥ ዕፅ ወይንም አደገኛ መደኃኒት ወይም አልኮል ተጠቃሚ ነበሩ፡፡ ይህም ወንዶቹ ተማሪዎች ከሴቶቹ ይበልጥ ተጠቃሚ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

ይህን ውጤት ስንመለከት በርካታ ወንድ ተማሪዎች የዕፅ ወይንም መድኃኒት ተጠቃሚ ይሁኑ እንጂ የሴት ተጠቃሚ ተማሪዎችም ቁጥር በቀላሉ ሊታይ የሚችል ያለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተካሄዱት ቡድን ውይይቶችም ከዚህ ቀደም ባልተለመደ መልኩ በርካታ ሴት ተማሪዎችም የዕፅ ተጠቃሚዎች እየሆኑ መምጣታቸው ተረጋግጧል፡፡

### *ለ. በኃይማኖት (ቤተ-እምነት)*

የአደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነት ብዛት በኃይማኖት (ቤተ እምነት) የተወሠነ ልዩነት ያሳይል፡፡

**ሠንጠረዥ 6፡-** አልኮል የአደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነት በኃይማኖት


| እምነት | ተጠቃሚዎች | | የማይጠቀሙ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ኦርቶዶክስ | 352 | 55.8 | 279 | 44.2 | 631 | 100 |
| ካቶሊክ | 58 | 45.3 | 70 | 54.7 | 128 | 100 |
| ሙስሊም | 132 | 39.9 | 199 | 60.1 | 331 | 100 |
| ፕሮቴስታንት | 107 | 25.0 | 321 | 75.0 | 428 | 100 |
| ሌላ | 53 | 32.5 | 110 | 67.5 | 163 | 100 |
| **ድምር** | **702** | **41.8** | **979** | **58.2** | **1681** | **100** |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደሚታየው የአልኮል፣ የአደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነት በኃይማኖት ልዩነት አሳይቷል፡፡ የሆነው ሆኖ የየትኛውም ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ ተማሪዎች ከአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነት ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዳልሆኑ በግልጽ ማየት ተችሏል፡፡ በአንጻሩ በቡድን ውይይቱ የተሳተፉ የእምነት አባቶች ግን የትኛውም እምነት የዕፅ ተጠቃሚነትን የሚደግፍ ያለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ ስለዚህም ጥናቱ የቤተ እምነት መሪዎች ወይንም ኃይማኖት አባቶች ለምዕመናኖቻቸው ትምህርትን በመስጠት ይህንን እንደ ሠደድ እሣት በወጣቱ ዘንድ እየተስፋፋ ያለውን ችግር ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን ሚና መጫወት እንዳለባቸው ያሳያል፡፡

### *ሐ. በወላጆች ወይም የአሳዳጊዎች የትምህርት ደረጃ*

የአደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነት በወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች የትምህርት ደረጃ ሲታይ ከተማሩ ቤተሠብ መሆን ወይንም ካልተማሩ ቤተሠብ መምጣት ጉልህ ስታቲስቲካዊ ልዩነት የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**ምስል 1፡-**<u>የወላጆች/አሳዳጊዎች የትምህርት ደረጃና የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ እንዲሁም የአደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነት በመቶኛ</u>




በሌላ በኩል ጥናቱ ለአደንዛዥ ዕፅ የሚያጋልጡ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉና እነዚህ ምክንያቶችም እንደየሰው የተለያዩ እንደሆኑ አሳይቷል፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ዋነኞቹ የአቻ ወይንም ጓደኛ ግፊት ሲሆን በመቀጠል የዕጾቹና መድኃኒቶቹ በአካባቢው መኖርም እንደ ምክንያት ተጠቅሷል፡፡ በሌላ በኩል ቁጥራቸው ቀላል የማይባል (24.2%) ተማሪዎች ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውጭ ሌላ ምክንያቶች ለችግሩ እንዳጋለጣቸው አስታውቀዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 8፡-** <u>ለአደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነት የሚያጋልጡ ምክንያቶች</u>

| ምክንያቶች | ብዛት | |
|---|---|---|
| | **በቁጥር** | **በመቶኛ** |
| የጓደኛ (አቻ ግፊት) | 238 | 34.5 |
| የአልኮል ዕፆችና አደገኛ መደኃኒቶች በአካባቢው መገኘት | 74 | 40.1 |
| ከአንድ በላይ የሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች | 67 | 9.7 |
| የቤተሠብ ግጭት | 42 | 6.1 |
| የቤተሠብ ዕፅ/መደኃኒት ተጠቃሚነት | 38 | 5.5 |
| የትምህርት ችግር | 67 | 9.7 |
| ምንም | 168 | 24.3 |
| **ድምር** | **690** | **(100)** |


በቡድን ውይይቶቹ ላይ የተሳተፉት ተሳታፊዎች ደግሞ ለወጣቶች ወደ አልኮል፣ ዕፅና መድኃኒት መገፋት በምክንያትነት ያቀረቡዋቸው በርካታ ምክንያቶች ነበሩ። ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ፤

- የአቻ ግፊት፤
- በት/ቤት የክትትል ማነስ፤
- በዕፆች ላይ ህጋዊ ክልከላ ያለመኖር፤
- ዕፅ ተጠቃሚነትን እንደዘመናዊነት ማየት፤
- የአልኮል፣ ዕፅ ወይንም አደገኛ መድኃኒቶች ተጠቃሚነት ጉዳትን ያለማወቅ፤
- ጤናማ የሆነ መዝናኛ ስፍራ በተለይ በረጅሙ የክረምት እረፍት ወራት ወጣቶቹ ማጣታቸው፤
- አዲስ ነገር የመፈተሽ (የመሞከር) ፍላጎት፤
- ከቤተሠብ ርቆ በሌላ ከተማ መማርና የዐዋቂ ቁጥጥር በቅርብ አለመኖር፤
- በፈተና ግዜ አምሽቶ ለማጥናት መፈለግ፤
- የወላጆች የተጣበበ የሥራ ፕሮግራም ልጆችን በተገቢው መንገድ ለመምራትና ለማገዝ ያለማስቻሉ፤
- የወላጆች የዕፅ ወይንም መድኃኒት ተጠቃሚነት ናቸው።


## 4 የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነትና በባሕሪ ላይ ያለው ተፅዕኖ

አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒቶችን መጠቀም ከፍተኛ የሆነ የባሕሪ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ጥናቶች ያሳያሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ ሁኔታ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል። የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው አልኮል፣ ዕፅ ወይንም አደገኛ መድኃኒት የሚወስዱት ተሳታፊዎች ከማይወስዱት ይበልጥ በጭንቀትና በድብርት ስሜቶች የሚጠቁ መሆኑ ታይቷል። ሌላ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው ከሌላው ሰው ይልቅ ዕፅ ወይም አደገኛ መድኃኒት የሚጠቀሙ ሰዎች ከማይወስዱት ሰዎች ይልቅ ለአዕምሮ ችግር የበለጠ የተጋለጡ መሆናቸውን ነው (WEB MD, 2007)። የሆኖ ሆኖ እነዚህን ነገሮች መጠቀም በቀጥታ የድብርት እና የጭንቀት ምክንያት እንደሆነ መውሰድ አያስችልም። በተጨማሪም የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች እንደገለፁት ቁጡነት፣ ብቸኝነት፣ ዝቅተኛ የትምህርት ውጤትና የባህሪ ችግር አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ ወይንም አደገኛ መድኃኒት በሚወስዱ ተማሪዎች ላይ አዘውትሮ የሚታዩባቸው ባህሪያት መሆናቸውን ገልፀዋል።

**ምስል 11፡-** <u>የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚ በሆኑና ተጠቃሚ ባልሆኑ መካከል ያለ የጭንቀት መጠን</u>




**ምስል 12፡-** <u>የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚ በሆኑና ተጠቃሚ ባልሆኑ መካከል ያለ የድብርት መጠን</u>




ቀደም ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትም የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፆችና አደገኛ መድኃኒቶች ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ለወንጀል ድርጊትም የሚገፋፉ መሆኑን ያሳያሉ (AHSDA, 1999)፡፡

**ሠንጠረዥ 7፡-** ባለፉት 30 ቀናት የአልኮል አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚዎች ወጪ በብር

| የገንዘብ ወጭ | መጠን | |
|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ |
| ከ50 ብር በላይ በሳምንት | 42 | 11.6 |
| 40-49 ብር በሳምንት | 30 | 8.3 |
| 20-39 ብር በሳምንት | 31 | 8.5 |
| 10-19 ብር በሳምንት | 67 | 18.5 |
| 5-9 ብር በሳምንት | 84 | 23.1 |
| ከ5 ብር ያነሰ በሳምንት | 109 | 30.0 |
| **ድምር** | **363** | **100%** |

አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ከሚወስዱ ተማሪዎች መካከል ለዚህ ጉዳይ በሳምንት የሚያወጡት ወጪ ሲጠየቁ ምላሽ የሰጡት ግማሽ ያህሉ ብቻ ናቸው:: ከእነዚህ መካከል ደግሞ ወደ 30% የሚጠጉት በሳምንት 20 ብር ወይንም ከዚያ በላይ (በወር ደግሞ 80 ብር ወይንም ከዚያ በላይ) እንደሚያወጡ ሪፖርት አድርገዋል:: በአንጻሩ ደግሞ በሳምንት ከ50 ብር በላይ (በወር ከ200 ብር በላይ) ወጪ የሚያደርጉ መኖራቸውን መረጃው ያሳያል:: በተጨማሪም አልኮል ፣ዕፅ ወይም አደገኛ መድኃኒት መጠቀም ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የሚፈልጉትን የእርካታ ስሜት ለማግኘት መጠቀም ያለባቸው የዕፅ መጠን እየጨመረ መሄዱንም ተጠቃሚዎቹ ገልፀዋል:: በሌላ በኩል የገንዘብ ምንጫቸው ከየት እንደሆነ ሲጠየቁ 149 (21.8%) ከወላጆቻቸውና ከቤተ-ዘመድ፣ 139 (19.8%) ከጓደኞቻቸው፣ 85 (12.4%) ከቤት ወይንም ከውጪ በማጭበርበርና በመስረቅ፣ 71 (10.4%) በትርፍ ሠዓታቸው ሥራ በመሥራት፣ 9 (1.3%) ከተለያየ ምንጭ እንዲሁም 231 (33.7%) ከሌላ ምንጭ ገንዘብ እንደሚያገኙ ገልፀዋል::

## 5 የአልኮል አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚነትና የጤና ሁኔታ

የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚ ከሆኑት ተማሪዎች መካከል 30.6% ተማሪዎች የግብረ-ስጋ ግንኙነት መጀመራቸውን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን በአንጻሩ ተጠቃሚ ካልሆኑት ተማሪዎች ግብረ-ስጋ ግንኙነት የፈጸሙት 12.7% ብቻ ሆነው ተገኝተዋል:: ከአልኮል፣ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚዎቹ መካከል 18.7% ከተለያዩ ሠዎች ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንደሚፈጽሙ ሲታወቅ፤ በአንጻሩ የአልኮል፣ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚ ካልሆኑት ተማሪዎች መካከል ተመሳሳይ ድርጊት የሚፈጽሙት 4.9% ብቻ መሆናቸው ታውቋል::

በተጨማሪም በምን አይነት በሽታ እንደሆነ ባይገለጽም ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ከአልኮል፣ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ተጠቃሚ ተማሪዎቹ መካከል 32.6% በጤና ችግር ምክንያት ወደ ህክምና ድርጅት የሄዱና 14.1% ያህሉ ደግሞ ህመማቸው ሆስፒታል የሚያስተኛ ሆኖ በመገኘቱ ተኝተው የታከሙ መሆኑ ታውቋል። በሌላ በኩል ደግሞ አልኮል፣ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ከማይወስዱት ተማሪዎች መካከል 26.3% በጤና ችግር ወደ ህክምና ድርጅት ባለፉት ጥቂት ሳምንታት የሄዱ ሲሆን 7.5% ደግሞ በሆስፒታል ተኝተው የታከሙ ናቸው።

ይህ መረጃ የተማሪዎች የጤና ችግር በቀጥታ ከሚወስዱት የአልኮል መጠጥ፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒቶች የተነሳ የተከሰተ እንደሆነ ባያመለክትም በጤናቸው ላይ ግን ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል የሚያሳስብ ይሆናል። በተጨማሪም በቡድን ውይይቱ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒት የሚወስዱ ተማሪዎቸ የምግብ ፍላጎት እንደሌላቸውና በበሽታ በቀላሉ የሚጠቁ፤ እንዲሁም ግብረ-ስጋ ግንኙነትን በተመለከተ ራሳቸውን መግዛት የማይችሉ እንደሆኑ ያሳያል።

## 6 ማጠቃለያና የመፍትሔ ኃሳብ

የዚህ ጥናት ግኝት አንደሚያመለክተው በሻሸመኔ እና ሀዋሳ ከተሞች በጥቅሉ የታየው የ42.4% የአደገኛ ዕፅ ተጠቃሚነት የችግሩን በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መስፋፋት ያመለክታል። በከተሞችም በንጽጽር የተገኘው ውጤት በሻሸመኔ 44.1% በሀዋሳ 39.8% በመሆኑ ችግሩ በሻሸመኔ ከተማ የሠፋ መሆኑን ያሳያል። ጥናቱ ቁጥራቸው ከሌላው ይነስ እንጂ በሁለቱም ከተሞች ት/ቤቶች የማሪዋና ተጠቃሚ ወጣቶች መኖራቸውንም አመልክቷል።

ነገር ግን ሄሮይንና ኮኬይን የተባሉት አደገኛ መድኃኒቶች በሁለቱም ከተሞቸ ተጠቃሚ እንደሌላቸው ጥናቱ አሳይቷል። በጥናቱ ከተካተቱት መካከል አልኮል፣ ጫትና በአፍንጫ የሚሳቡ እንደ ቤንዚን ያሉ ነገሮች በቅደም ተከተል ከሌሎቹ ይልቅ በተማሪዎች መካከል በርካታ ተጠቃሚዎች ያሏቸው መሆኑም ታይቷል።

ተማሪዎችን ለአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃኒቶች ተጠቃሚነት ከሚያጋልጧቸው ምክንያቶች ዋነኞቹ የአቻ ግፊትና የዕፆቹ በአካባቢዎቹ በቀላሉ መገኘት መሆኑም ታውቋል። ስለሆነም የችግሩ ስፋት በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ ወላጆች፣ ት/ቤቶች፣ ህብረተሠቡና መንግሥት በቅንጅት የአልኮልና አደንዛዥ ዕፅ እንዲሁም የአደገኛ መድኃኒቶችን ስርጭት ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ተግተው መስራት እንደሚኖርባቸው ጥናቱ ያሳስባል። ከዚህ አንጻር የሚከተሉት ሊተገበሩ እንደሚያስፈልግ ጥናቱ ይጠቁማል፡-

- ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሄደውን የተማሪዎች ቁጥር መምህራን ተማሪዎቻቸውን በሚገባ እንዲከታተሉ የማያስችል በመሆኑ የተማሪ-መምህር ጥምርታ ለክትትል የሚያመች ቢሆን፤

- በት/ቤት ሚኒ-ሚዲያዎች የአልኮልም ሆነ የአደንዛዥ ዕፅና የአደገኛ መድኃኒቶችን ጉዳት ትምህርት ቢሰጥ፤

- ፀረ-ዕፅና አደገኛ መድኃኒት ክበቦች በየት/ቤቱ ቢቋቋሙና በችግሩ ውስጥ ላሉ ተማሪዎችም የምክር አገልግሎት እገዛ የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች፤

- ወላጆችና ልጆቻቸው የራስ መተማመን ስሜት ያዳበሩና ለአቻ ግፊት የማይበገሩ እንዲሆኑ የሚያስችል አስተዳደግ ቢከተሉ፤

- መንግሥት የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ እንደ አልኮልና ጫት ያሉት ላይ ሕጋዊ ቁጥጥሮችን ቢያደርግ፤

- ለወጣት ልጆች በተለይም በትልቁ የክረምት የእረፍት ወራቶች ጊዜያቸውን የሚያስልፉባቸው ጤናማ የመዝናኛ ስፍራዎች (ለምሳሌ የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት፣ ጂምናዝየሞችና የስፖርት ማዕከላት) ቢገነቡ፤

- ሚዲያዎች ለወጣቱም ሆነ ለአጠቃላይ ህብረተሠቡ አልኮል፣ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፅ ተጠቃሚነት ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳቶች ቢያስተምሩ፤

- ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች እየተተገበሩ በየጊዜው የችግሩን ስርጭት በተመለከተ ጥናቶች እየተደረጉ እንደመፍትሔ የሚወሰዱት እርምጃዎችም በጥናት ላይ የተደገፉ ቢሆን፤

- ጥናቱ እንደሚያሳየው እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ቀደም ሲል የተደረጉ ጥናቶች እንዳመለከቱት ችግሩ አገር አቀፋዊ ይዘት ስላለው ለችግሩ ተጠቂዎች በየክልሉ ቢያንስ አንድ የማገገሚያ ማዕከል (Rehabilitation Center) ቢቋቋም ዛሬ እጅግ በፈጣን ሁኔታ በተለይ በወጣቱ ዘንድ እየተስፋፋ የመጣውን የአልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅና አደገኛ መድኃቶችን መጠቀም ቢያንስ መቀነስና መቆጣጠር ያስችላል።

## ዋቢ መፃህፍት


Alem, A., Kebed, D. & Kullgren, G.(1999). The prevalence and Socio-demographic correlates of khat Chewing in Butajira, Ethiopia. *Acta psychiatricaScandinavia*, 100; 84-91.

Austin, G. (1979). *Perspectives on the History of Psychoactive Substances use*. Available on http: // www. taima. org/ en/ psychoactive.htm

Center for Tobacco Control Research and Education. (2006). *Tobacco Use in Shisha Studies on Water pipe Smoking in Egypt.* Available from http://repositories.cdlib.org/tc/whotcp/SHISHA

Dimah, A., & Gire, J. T. (2004). *The* Health and Economic Consequences of Alcohol Use in Central Nigeria. *African Journal of Drug & alcohol Studies* 3(1&2):44-53.

Ethiopian Federal Police Drug Control Department Report. Addis Ababa. 2004. Ethiopian Federal Police Drug Control Department. *Drug Use in Ethiopia.* Drug use in Ethiopia. Addis Ababa. 2003.

Gebresellassie, S. & Gebre, A. (1995). *Report on The Rapid Assessment of the Situation of Drug and Substance Abuse in Selected Urban Areas in Ethiopia.* Prepared for The Ministry of Health of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and The United Nations International Drug Control Program.

Gete, G. (2013). Proceeding of The Annual Research Review Workshop, Volume 1 ,Hawassa University, Research & Development Directorate.

Gete, T. (2013) Drug |Use and Its Psycho-socialand Health Impacts:The Case of Halaba Secondary School sStudents,Proceeding of The Annual Research Review Workshop,Vol.I

Kassaye, M., Taha Sherief, H., Fissehaye. G., & Teklu, T., (1999). *Drug Use among -High School Students in Addis Ababa & Butajira*. Ethiop. J. Health Dev.13 (2):101-106.

Lemessa, D. (2001). *Khat (Catha edulis): Botany, Distribution, Cultivation, Usage and Economics in Ethiopia*. Ethiopia, Addis Ababa.

Mitike, G., Lemma, W., Berhane, F., Ayele, R., Assefa, T., G/Michael, T., Enquoselassie, F., Alem, A., Abebe, Y., & Kebede, D. (2002). *HIV/AIDS Behavioral Surveillance Survey* (BSS), Ethiopia.

Nazarius, T.M. & Rogers, K. (2005). Alcohol and its Association with Sexual Abstinence, Condom Use and Risky Behavior among Unmarried Young People Aged 18-24 Years in Uganda. African *Journal of Drug and Alcohol Studies*. 4 (1&2) 19-31.

Santrock, J.W. (2000).*Psychology*. McGraw-Hill Co. New York. U.S.A.

The Guardian5/2/2004Chew on this. Availab http://www.Biopsychiatry.com /methacathinone/qat.Html

United Nations Office of Drug Control/HONLAF. Thirteenth Meeting of Heads of National Drug Enforcement Agencies, Africa. Port Louis,8-12 Sep.2003.

United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC). *Overview of Illicit Drugs*. Regional Office, Kenya. 2007.

United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC). *World Drug Report. 2006.*

WEB M.D. (2007). *Fact about Teen Drug and Alcohol Abuse*.

# ወጣቶችና ጫት በኢትዮጵያ

## ግርማ ነጋሽ

በተማራማሪዎች ዘንድ ካታ ኢዱሊስ (*catha edulis*) እየተባለ የሚጠራው ጫት፤ ዓመቱን ሙሉ አረንጓዴ ሆኖ መቆየት የሚችል ተክል ነው፡፡ ኢትዮጵያ፣ የመን፣ ኬንያ፣ ዑጋንዳ፣ ማላዊና ደቡብ አፍሪካ በስፋት ከሚመርትባቸውና ጥቅም ላይ ከሚውልባቸው አገራት ጥቂቱ ናቸው፡፡ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ስዊድናዊው የአዝዕርትና የአትክልት ተመራማሪ ፒተር ፎርስካል የጫትን ዝርዝር ባህሪያት ተንትኖ ለማስቀመጥ ፈር ቀዳጅ እርምጃ እንደወሰደ ይታወቃል፡፡ እስከ ዛሬ የተደረጉ የጫትን ኬሚካላዊ ባህርያት የሚዳስሱ ጥናቶች ተክሉ የሰው ልጅን የነርቭ ሥርዓት የማነሳሳት ብቃት ያላቸው አነቃቂ ንጥረ ነገሮችን (alkaloids) የያዘ እንደሆነ የሚስማሙበት ነው፡፡ ከነዚህ አነቃቂ ንጥር ነገሮች ውስጥ ካቲኖን (cathinone)፣ ካቲን (cathine) እና ኖርፊድሪን (norephedrine) ዋና ዋናዎቹ የሚባሉ ናቸው (Keneedy, 1987pp.176-177; Anderson and Beckerleg, 2007, pp.3-5) ፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ማዕከል የሆነው የሲዳማ ዞን፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሠቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ሥር ከሚገኙት ጫት አብቃይ አካባቢዎች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በ1998[1] በዞኑ በተዘረጋው አዲስ አስተዳደራዊ መዋቅር መሠረት የሲዳማ ዞን በ19 ወረዳዎች እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡ በ1999 በተደረገው የህዝብ ቆጠራ መሠረት የዞኑ የህዝብ ብዛት 2,956,652 ሲሆን፣ በ2005 ይህ አኃዝ ወደ 3,232,308 እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ የዞኑ የህዝብ ጥግግት 425 ሰው በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ደርሷል (የሲዳማ ዞን ባህል ቱሪዝምና የመ/ኮ/ጉ/መ፣ ገጽ 2)፡፡ በዚህም ነው በአጠቃላይ በመላው ደቡብ ሕዝቦች ከሚገኙ ዞኖች ውስጥ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ የህዝብ ጥግግት አለው የሚባለው ይህንን አኃዝ በመመልከት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በከፍተኛ ፍጥነት በአገሪቱ እያደገ የመጣውን የጫት ምርት መጠንና የጫት ቃሚዎች ቁጥር፤ በተለይ ከአገሪቱ ጠቅላላ የህዝብ ቁጥር 43% ከሚሆነው ከወጣቱ አኳያ፤ ጥቅምና ጉዳቱን በሚዛናዊነት ማሳየትና፤ በዚሁ አንጻር፤ በተለይ ከዚህ በፊት ያልተዳሰሱ ጉዳዮች ካሉ ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ ላይ ወጣት እየተባለ የሚጠቀሰው በ1996 በወጣው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ" መሠረት

---

[1] በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የተጠቀሱት ዘመኖቸ ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ናቸው፡፡

ዕድሜያቸው ከ15-29 የሆኑትን የህብረተሠብ ክፍሎች ነው (Ministry of Youth, Sports & Culture: 2004, 4)። የጫትን ክፉና ደግ በተለይ ከወጣቱ አኳያ የመቃኘትን አስፈላጊነት ትኩረት እንድሰጠው ያነሳሳኝ፤ ከላይ እንደተገለፀው፤ ወደ ግማሽ የሚጠጋው የአገሪቱ ህዝብ ወጣት በመሆኑ ምክንያትና፤ እንድያም ሲል በተለያዩ አጋጣሚዎች "ኢትዮጵያ ወጣቷ አገር" እያሉ መጥራት እየተለመደ መምጣቱ አንዱ ሲሆን\ ሁለተኛው ደግሞ ጫትን በመቃም ብቻ ሳይሆን በምርቱና በንግዱም ላይ ወጣቱ ቁልፍ ሚና የሚጫወትና እንዲያውም ዋና "አንቀሳቃሽ ሞተር" ሆኖ በማግኘቴ ነው። በእርግጥ ጫት በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ እያደረሰ ያለው የጤና፣ የኢኮኖሚ የማኅበራዊና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጉዳቶች በተለያዩ ጥናቶች ተዳሰዋል። ነገር ግን ይኸው የህብረተሠብ ክፍል በተለይ በጫት ንግድና ዝውውር ሂደት ላይ ያለው የመሪነት ሚናና ግንባር ቀደም ተጠቃሚነት ትኩረት ተሰጥቶት አልተጠናም፤ እዚህ ግባ የሚባል ዝርዝር ዘገባም አልታየም። ይህ የኔ ጥናት አሥምሮበት የሚነሣውና በማስረጃ እያንተራሰ የሚሞግተው ኃሳብ ከማንኛውም የህብረተሠብ ክፍልና የዕድሜ ክልል እጅግ በጐላ ሁኔታ የጫት ንግድ በወጣት የሚመራ የወጣቶች ሥራ ነው የሚል ነው።

የጫት ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙዎች ከሚገምቱት በላይ ረጅም ታሪክ እንዳለው አንዳንድ ድርሳናት ያሳያሉ። ለምሳሌ በ14ኛው ክፍለ ዘመን የተፃፈው የንጉሥ አምደጽዮን (1314 - 44) ዜና መዋል፤ እና አል ኡማሪ (1301 - 478) የተባለው የዘመኑ የአረብ ተጓዥ በወቅቱ ጫት በኢትዮጵያ ስለመቃሙና አንዳንድ የማህብረሠብ ክፍሎች እንደሚያበቅሉት ተገልጾ ተጽፏል (Ezekiel: 2004, 3)። ስለሆነም የጫት ጉዳይ እንደ እንግዳ ሊታይ የሚችል አይደለም። አሁን ግር ሊል የሚችለው ጉዳይ ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከባድ ፍጥነት እያደገ የመጣው የጫት የገበያ ፍላጐትና በዚህም ምክንያት ይህ ተክል እንደ ቀድሞ በሀረርጌ አካባቢ ከመወሰን አልፎ በብዙ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የእህል ማሳዎችን የራሱ ማድረጉና አቢይ የሸያጭ ዕቃ የመሆኑ ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ወቅት እጅግ በርካታ በሆኑ የህብረተሠብ ክፍሎች መሀል ጫትን አዘውትሮ የመቃም ባህሪ ተስፋፍቶና ተንሰራፍቶ ይገኛል። እኒህ ቃሚዎች ስለምን በዚህ ተክል ፍቅር እንደወደቁ የሚሰጡት ምላሽ የተለያየ ነው። አንዳንዶች እንቅልፍና ድብርትን በማባረር ነቃ የማለት ስሜት ይፈጥርልናል ይላሉ። ይህ ደግሞ ጫት በውስጡ ከያዛቸው ካቲኖንና ካቲን ከተባሉ አነቃቂ ንጥሮች የመነጨ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። አንዳንዶቹ ደግሞ ለመዝናናት፣ ጊዜ ለማሳለፍና መቃሙ የሚፈጥረውን የጨረፍታ የደስታ ስሜት ለማጣጣም ነው ይላሉ። ከዚህ አልፎም ጫት ጉንፋንን፣ ተቅማጥንና ሌሎችም የህመም ስሜቶችን ለመዋጋት እንደሚጠቅም የሚያምኑ አሉ። አንዳንድ በተለይ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ደግሞ ጫት

መቃም ከአልኮል እንድንታቀብና የሚፈጥረው የንቃትና የአትኩሮት መጨመር ደግሞ ለሌሊት ፀሎት ያተጋናል ብለው ያምናሉ (Eshetu & H/Mariam, 96; Sebsebe, 7; Varisco, 103; and Anderson and Beckerleg, 5)።

ከእነዚህ የጫት ተጠቃሚዎች የተለያዩ አስተያየቶች በተጨማሪ ጫት መቃም የሚፈጥረው የመጨረሻ ስሜት ('ምርቃና' ይሉታል)፤ ብዙውን ጊዜ በጫት መቃሙ ሂደት ከነበረው የተጠቃሚው ስሜታዊ ሁኔታና የዘወትር ልምድ ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ እንደ ሀረርጌ ባሉ አካባቢዎች የሚገኙ ጫት አብቃይ ገበሬዎች ጫት እየቃሙ ወይንም ከቃሙ በኋላ በግብርና ሥራ መሠማራት ሥራ ከማሳለጡም በላይ የግብርና ሥራውን አሠልቺነትና ድካም ይቀንሳል ተብሎ ይወሰዳል። መቃም የሚያዘወትሩ የጭነት መኪና አሽከርካሪዎች፣ የኮሌጅ ተማሪዎችና በጥበቃ ሥራ የተሠማሩ ግለሠቦች ደግሞ ጫት መቃምን እንቅልፍ የማባረሪያ አይነተኛ መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል። ሌላው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጫትን ዝና ያናኘው ሁኔታ ደግሞ በጋራ ጫት መቃም ለብዙ ሰዎች የመግባቢያና የመቀራረቢያ ምቹ መድረክ እየሆነ የመምጣቱ ጉዳይ ነው። ሳይንሳዊ ምክንያቱን ማብራራት ባይቻልም ጫት መቃም/ምርቃና በአብዛኛው የአጥቂነት ስሜትን (aggressive behavior) በመጫን ወዳጃዊና ፍቅራዊ ስሜትን ያበዛል። ስለሆነም ሰብሰብ ብለው በሚቅሙ ጓደኛሞች መሀከል ወዳጅነትና ትስስርን የማጐልበት ማኅበራዊ ፋይዳ አለው የሚሉ አጥኝዎችም አሉ።

ይህም ሆኖ ግን በጫት ላይ በቀረቡ በርካታ ጥናቶችና ዘገባዎች ላይ ብዙ ቦታና ትኩረት የሚሠጣቸው ጭብጦች በተለይ ጫት በአፍቃሪዎቹ ላይ ያስከትላል ተብለው የሚታመኑ ሥነ-አካላዊና ሥነ-አእምሮአዊ ጉዳቶች ናቸው። ዝቅ ብዬ በዝርዝር ለማሳየት እንደምሞክረው ጫት በብዙ አወዛጋቢ፤ አንዳንዴም እርስ በእርሳቸው በሚጣረሱ፤ ትንታኔዎችና የጥናት ውጤቶች የታጀበ ዕፅ እንደሆነ መደበቅ የሚቻል አይደለም። እነዚሁ ጥናቶች በአመዛኙ የጫትን የጤና ጠንቅነት ለማስረገጥ የሚሞክሩና በተለይ በወጣቱ ላይ የሚያደርሰውን አዕምሮአዊ፤ አካላዊና ማኅበራዊ ሳንካዎች አጉልተው የሚያሳዩና የሚያስጠነቅቁ ናቸው። በተለይ በህክምናው ዘርፍ የተሠማሩ ተመራማሪዎች፤ ከሙያ ግዴታም አንፃር ሊሆን ይችላል፣ ትኩረቶቻቸውም ሆነ ግኝቶቻቸው የጫትን የጤና ጠንቅነት በማጋለጥ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ኛቸው። ጫት መቃም እንደመንስኤ ከሚታማባቸው የጤና ችግሮች መካከል ጥቂቶቹን እንኳን ብንጠቅስ\ የጨጓራ ህመም፣ የበዛ የደም ግፊት፣ የመተንፈሻ አካሎች ችግር፣ የሆድ ድርቀት፣ የአፍ ውስጥና የሆድ ካንሰር\ የጥርስ ደዌዎችና ማለቅ\ ስንፈተ-ወሲብና የእንቅልፍ ማጣት ይገኙበታል (Dechassa, 96; Varisco, 104; and Amare & Krikorian, 375) ።

ጫት መቃም የስነ-አካላዊ (physiological) ብቻ ሳይሆን የስነ-አዕምሮአዊ (psychological) ችግሮች መንስኤም እንደሆነ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ ባይደርስም አንዳንድ ጠቋሚ ናቸው የተባሉ ግኝቶች ግን አልጠፉም:: አንዳንድ ዓለም አቀፍ የጤና ተቋማትም ጫት መቃም ስነ-አዕምሮአዊ ተፅእኖ ያስከትላል መባሉን በከፊልም ቢሆን ይጋራሉ:: ለምሳሌ በ1980 (እ.ኤ.አ) የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) ጫትን መለስተኛ አደንዛዥነት ካላቸው እጾች ጐራ/ተርታ መድቦታል (Ezekiel, 2008፡ 796; Ward & Gatter, 40):: በዚህ ዘርፍ ባሉ አጥኚዎች መካከል ያለው ልዩነት የጫትን የሱስ አስያዥነት ደረጃ ቁርጥ ባለ መልኩ ማስቀመጥ አለመቻል ከመሆኑ በስተቀር ለረጅም ጊዜ በተከታታይ የጫት ተጠቃሚ መሆን ለአንዳንድ የአዕምሮ ችግሮች ሊያጋልጥ እንደሚችል አጠቃላይ እምነት አለ:: ለምሣሌ የስሜት መዋዠቅ፣ የመረበሽ ስሜት (ቅዠት) የድብርት ችግርና ምክንያት አልባ ጠርጣራነት የመሳሰሉ የአዕምሮ ቀውሶች ከበርካታ መንስኤዎቻቸው አንዱ ጫት አዘውታሪነት ሊሆን እንደሚችል የሚጠቅሱ ጥናቶች ይገኛሉ (Anderson and Beckerleg, 2007፡ 6-7)::

ከጤናው ዘርፍ ስንወጣ፤ ጫት የአንዳንድ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መንስኤ ተደርጐ የሚጠቀስበትንም ሁኔታም እናገኛለን:: በእርግጥ በኢትዮጵያ በተመረጡ ቤተሠቦች (household) በተሰበሰቡ ናሙናዎች ላይ ተመሥርቶ የተጠና የጫት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ትንተና እስከአሁን ባይኖርም፣ በየመንና በሶማሊያ የተደረጉ ጥናቶች፤ ጫት በቤተሠብ ደረጃ ሳይቀር የሚከሠቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን እንደሚያስከትል ያሳያሉ:: ከነዚህ ችግሮች በጣም ተጨባጭ የሆኑትና ጐልተው የሚታዩት የጫት ወጪ የቤተሠብን ኢኮኖሚያዊ አቅም በማሚጠጡ ምክንያት የሚፈጠረው ቀውስ ነው:: ከዚህም በላይ ጫትን በማኘክ የሚጠፋው ጊዜ በምርት ሥራ ላይ እንዳይውል ስለሚያደርግ የቤተሠብን ገቢ ያዳክማል:: አንድ ታዛቢ "ጫት ከህፃናት አፍ ምግብን ይነጥቃል፤ ከሴቶቻችን ጀርባ ደግሞ አልባሳትን ያራቁታል" (Green, 1999: 41) ሲሉ ይገልፁታል:: ከነዚህ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች በተጨማሪ አብዛኞቹ ጫት አዘውታሪዎች የቤተሠብ ኃላፊነታቸውን ችላ የማለትና በቂ ጊዜ ያለመስጠት ችግር እንዳለባቸው ይጠቀሳል:: በተለይ በቤተሠባዊ ፍቅርና መረጋጋት ላይ ጉልህ አንድምታ ያለው ጉዳይ፤ በርካታ ጫት ቃሚዎች ብዙ ጊዜአቸውን\ ልጆቻቸው ፍቅራቸውንና አብሮነታቸውን በሚሹ ሠዓት እንኳ ቢሆን፤ ከቤታቸውና ከቤተሠባቸው ርቀው ለጫት መቃም መሥጠታቸው ነው (Varisco, 115; Cassanelli, 251; and Anderson *et al.*, 177)::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ነበር በ20ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ የጫት በገበያ ላይ ተፈላጊነት እየጨመረ የመጣው:: በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ በኢትዮጵያ የጫት ምርትና ዝውውር ከወትሮው እየጨመረ የመጣበት ሁኔታ ቢታይ እንኳን ይህን ያህል የጐላ አልነበረም:: አንዳንድ ፀሐፍት በተለይ የደርግ ዘመን (1967 — 1983)

የጫት መቃም ባህል በእጅጉ የተስፋፋበትና የጫት የገበያ ተፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ያሻቀበበት ነው ይላሉ። ለምሳሌ እዝቅኤል ገቢሣ የተባሉ ተመራማሪ የጫት መቃም ባህል ከፍተኛ እመርታ ያሳየው የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻን (1967—1969) ተከትለው በመጡት አሥርት ዓመታት ነው ይላሉ። ዋናው መከራከሪያ ነጥባቸውም፤ ይህ ዘመቻ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና የኮሌጅ ተማሪዎችን ያለምንም የቤተሠብ ቁጥጥር በየገጠሩና በዳር አገሩ በማሠማራቱ ወጣቶችን የመማረክ ኃይል ያላቸው ጫት፣ ሲጋራና\ አልኮል በሠፊው እንዲለመዱ አድርጓል የሚል ነው። ከዘመቻው ቀጥሎ በተከተሉት አሥርት ዓመታት የሆነውም ይኸው ነው። ብዙ ወጣቶች የተለያዩ ሱሶችን አፍርተው ተመለሱ (Ezekiel, 2004: 13)። በየከተማው በግላጭ ጫት መቃም እንደወግ የተለመደ ነገር ሆነ። በርካታ የጫት ኪዎስኮች በየጓጡና በየስርጉጥጓጡ ተቋቋሙ። በትንንሽ ፒከ አፕ (pickup ) መኪናዎች ይጓጓዝ የነበረው ጫት በአይሱዙና በከባድ መኪናዎች ይጫን ጀመር። በተለያዩ የጫት አምራች አካባቢዎች ያሉ ገበሬዎችም ይህንን እየናረ የመጣ የገበያ ፍላጐት ለማሟላት ሌሎች ተክሎችን እየነቀሉ በጫት መተካቱን ተያያዙት። ይህን ሂደት ካፋጠኑት ዋና ዋና ምክንያቶች መሀል ቀደም ሲል ሰዎች ለጫት ያላቸው የንቀት ስሜት እየቀነሰ መምጣትና ጫት በአደባባይ መቃም የማያሳፍር ተግባር ሆኖ መታየት መጀመሩ ሳይጠቀስ አይታለፍም።

እንደሚታወቀው ሁሉ በአዲሱ ሚሊንየም መግቢያ ላይ የኢትዮጵያ ወጣት ቁጥር ከአጠቃላዩ ህዝብ ቁጥር 30% እንደሚደርስ ተገምቷል (Ministry of Youth & Culture, 2006: 1)። የዚህ ጽሁፍም ዋና ትኩረት በዚህ የማህበረሠባዊ የለውጥ ሂደት የወጣቱ ሚና እንዴት ይታያል? ከጫት ጋር ያለው የቀጥታም ሆነ ተዘዋዋሪ ግንኙነት ምን ይመስላል? የሚሉትን ጉዳዮች መዳሰስ ነው። ከጫት መቃም ባህል መስፋፋት ጋር ተያይዘው ለሚመጡ ችግሮች ደግሞ ከየትኛውም የኅብረተሠብ ክፍል በላይ ተጋላጭ የሆነው ወጣቱ እንደሆነ እስካሁን የተደረጉ የጫት ጉዳይ ጥናቶች በደምሳሳው የሚስማሙበት ነው። ስለሆነም ይህ የጫት ባህል እንደማዕበል መስፋፋት በወጣቱ ላይ በተለይ እንደ አንድ የማኅበረሠብ ክፍል ያስከተለውን እንድምታ መመልከት ጠቃሚ ይሆናል።

ምንም እንኳን የጫት መቃም ባህል ያላንዳች የጾታ፣ የዕድሜ፣ የኃይማኖት፣ የዘር ገደብ ወደ ሁሉም የኅብረተሠብ ክፍል የተስፋፋ ቢሆንም፤ በአመዛኙ የዚህ ወጀብ ሠለባ የሆነው ግን ወጣቱ መሆኑ የብዙ ጥናቶችን ይሁንታ ያገኘና አሌ የማይባል ሐቅ ነው። ከዚህም የህብረተሠብ ክፍል በርካታ ቁጥር ያለው የችግሩ ሠለባ ሥራ አጡ ወጣት መሆኑ ደግሞ የአደጋውን አሳሳቢነት ያጐላዋል። ይኸውም በተለይ ስራ አጡ ወጣት ጫት መቃምን እንደ ተመራጭ የጊዜ ማሳለፊያ በመውሰዱና በሱስም በመጠመዱ ምክንያት ጫትን በመደበኛነት ለማግኘት ሳይችል የቀረ እንደሆነ በቀላሉ

ወደ ወንጀልና ወደ ሁከት ተግባራት የሚሰማራ በመሆኑ ነው (Dechassa, 2001፡ 3; Taye & Aune, 2003፡ 189; Eshetu & H/Mariam, 2001፡ 104)፡፡ የቅርብ ጊዜ የአዕምሮ ጤና ምርምር ውጤቶች ደግሞ የወጣቶች ውስጣዊ የአዕምሮ ክፍል ከጐልማሦች ይልቅ ሱስ በሚያሲዙ ዕፆች ለከፍተኛ ጉዳት እንደሚዳረግ ይጠቁማሉ (Lubman *et al.*, 792)፡፡ ይህ ደግሞ በተለይ እንደ አገርና እንደ ማኅበረሠብ ስናስብ ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡

በተለይ በኮሌጆችና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ከአጠቃላይ የተማሪ ቁጥር ብዙው እጅ በጫት ሱስ የተጠመደ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአጋሮ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ2002 ላይ የተደረገ ጥናት ከሦስት እጅ ሁለቱ አዘውትረው ጫት የሚቅሙ መሆኑን አሳይቷል፡፡ በገለምሶ ሁለተኛ ደረጃ፣ በአንዳንድ የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ በጅማ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም በቡታጅራ ከተማ የተደረጉ የናሙና ጥናቶችም የሚያሳዩት ጫት ቃሚነት በወጣቱ መካከል በፍጥነት እያደገ መምጣቱን ነው (Ezekiel, 2008፡ 785) ፡፡ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በኦገስት 2002 የቀረበ አንድ የቢቢሲ ዘጋቢ ሪፖርት ጫት በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ የተጋረጠ አዲስ አደጋ ነው ይላል፡፡ አክሎም አብዛኞቹ ጫት ቃሚዎች ወጣቶች ናቸው .... በርካታ የሁለተኛ ደረጃና የኮሌጅ ተማሪዎች እንዲሁም አስተማሪዎች ጫት ቃሚዎች ናቸው፡፡ ትኩረታችንን ይጨምርልናል ብለው ያምናሉ (Bhalla, June 2010) ሲል ያትታል ፡፡

አንዳንድ የአገር ውስጥ ጋዜጦችም የጫትን ጥቋቁር ገጽታዎች የበለጠ በማድመቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በነሐሴ 11, 1999 ዕትሙ "ዩኒቨርሲቲ አንድ ጥለው አንድ አንጠልጥለው ... " በሚል ርዕስ ባቀረበው ሀተታ፤ የአገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች፤ ወጣቶች ትምህርትና ዲግሪ ብቻ አግኝተው የሚወጡባቸው ቦታዎች ሳይሆኑ የጫት ወይም የሌላ ሱስ ሠለባ የሚሆኑበት አጋጣሚ እየጨመረ መምጣቱን ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በተመሳሳይ፣ የኢትዮጵያ ሄራልድ (Ethiopian Herald) የተባለው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚታተም ዕለታዊ ጋዜጣ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በአፕሪል 29/ 2010 ባወጣው ዕትሙ "የዕፅ ተጠቃሚነት በኢትዮጵያ" ("Substance Abuse in Ethiopia") የሚል የዜና ሀተታ አቅርቦ ነበር፡፡ የዜናው አብይ ጭብጥ የዕፅ ተጠቃሚነትን በተመለከተ ለአዲስ አበባ ወጣቶች ስለቀረበ አንድ የግንዛቤ ማዳበሪያ ጥናታዊ ጉባዔ የሚያወሳ ነው፡፡ ነገር ግን ዘገባው እንደሚያሳየው በጉባዔውም ላይ ሆነ በሃተታው ላይ ሙሉ ሽፋን የተሰጠው ከሌሎች በከተማው በድብቅ ከሚቸበቸቡ ካናቢስ፤ ኮኬይንና፤ ሄሮይን ከመሳሰሉ እጅግ አደገኛ ዕፆች ይልቅ እስካሁንም በኢ-ህጋዊነት ያልተፈረጀው ጫት ነበር፡፡ ለማንኛውም ከዚህና ከሌሎች እዚህ ካልተጠቀሱ የጋዜጣ ዘገባዎችም ሆነ የዜና ሽፋኖች

የምንወስደው ነገር ቢኖር፣ጫት በብብት ከመወሸቅና በጀርባ ከመሸጎጥ አልፎ ህዝባዊ ትኩረትና ውይይትን የሚጋብዝ ተክል እየሆነ መምጣቱን ነው።

እስካሁን በዝርዝር ከተመለከትናቸው የጫት መጥፎ ጎኖች፣ ፀረ-ጫት ውግዘቶች እና የ"ይውደም" ጥሪዎች ይብዛም ይነስም ጫት በጎ ጎኖችና ጥቅሞች እንዳሉት አለማንሳት ሚዛናዊነትን ከመጋፋቱም በላይ 'ግመል ሰርቆ አጎንብሶ' እንደሚባለው የአገራችን ብሂል ይሆናል። አንዳንድ ጥናቶች የጫትን ክፉና በጎ ገጽታዎች በንጽጽር ለማሳየት ሞክረዋል[2]።

በርካታ ፀሀፍት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ የጫትን ጎጂነት አበክረው የሚሠብኩ ጽሁፎችን አቅርበዋል። ሌሎች ጥቂቶች ደግሞ ጫት 501 ለሚደርሱ በሽታዎች ፍቱን መድኃኒት እንደሆነና አይነተኛ የቪታሚን ሲ (C) ምንጭ እንደሆነ ከመግለጻቸውም በላይ፣ እንዲያውም ጫትን ጎጂ ዕፅ (harmful drug) ብሎ ለመፈረጅ በቂ መነሻ የለም ሲሉ ይከራከራከሉ (Anderson and Beckerleg, 177; Green, 38; Fitzgerald, 2; Varisco, 113)። ራልፍ ኪንግሌ የተባለ ፀሀፊ ደግሞ ሚዛናዊ መፍትሄ ነው ያለውን እንዲህ ሲል ይጠቁማል። "ጫት በሰዎች ጤናና ማኀበራዊ ህይወት ላይ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች መለስተኛ ሊባሉ የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ በሁሉም ሳይሆን በጥቂቶች ላይ ብቻ የሚያጋጥም ነው። ይህም ቢሆን እንኳ ሊደርሱ የሚችሉ ማኀበራዊ ጉዳቶችን በማስተማርና፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን የሚጠብቅ ሕግ በማውጣት መከላከል ይቻላል" (Kingele, 18) ይላል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት የጫት ንግድ ዋና ከሚባሉ የአገሪቱ የውጪ ምንዛሪ ምንጮች ተርታ መግባቱ[3]፣ በተለያዩ የጫት አምራች ዞኖችና ክልሎች ከጫት ንግድና ዝውውር የሚገኘው ወርሃዊና ዓመታዊ ገቢ ከፍተኛ የመሆኑ ጉዳይና በአጠቃላይ የጫት ምርትና ንግድ የፈጠረው የሥራ ዕድል፣ ጫትን አምርረው የሚያወግዙትም ክፍሎች እንኳን ቢሆኑ አሌ ሊሉት የሚሳናቸው እውነት ሆኖባቸዋል። ባለፉት አራት አሥርታት በጫት አምራች ገበሬዎች ህይወት ላይ የሚታየው ተጨባጭ የኑሮ ለውጥና መሻሻሎችን አኮስሦ ለማየት የሚቻል አይደለም። ለምሳሌ የሐረርጌ ገበሬዎች ከጫት በሚያገኙት ዳጐስ ያለ ገቢ ምክንያት አልፎ አልፎም ቢሆን የታሸጉ የቆርቆሮ ምግቦች እስከመመገብ የደረሰ፣ የተሻለና ዘና ያለ ህይወት እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። የብዙ የገጠር መንደሮች በኤሌክትሪክ ብርሃን መንቆጥቆጥ፣ ቴሌቪዥንና

---

[2] ለምሳሌ የEzekiel Gebissaን "Scourge of Life or an Economic Lifeline? Public Discourse on Khat (*Catha edulis*) in Ethiopia" *Subsistence Use and Misuse.* Vol. 43 ይመልከቱ።

[3] መንግስት በ2006 ዓ.ም ብቻ ከጫት ያገኘው ገቢ 260 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መድረሱን የንግድ ሚኒስትሩ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረቡት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ገልጸዋል (ሪፖርተር ጋዜጣ ግንቦት 24/2006 ዓ.ም. ይመልከቱ)።

ቴኘሪከርደሮችን የመሳሰሉ ዘመናዊ የቤት መገልገያዎች በእያንዳንዱ ገበሬ ቤት እንደ ብርቅ ሳይሆን እንደተራ መገልገያዎች መገኘትና፣ አልፎም በርካታ ጠንካራ ገበሬዎች የንግድ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ተጓዳኝ የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ ማድረግ መቻል (Ezekiel: 2004,180; Eshetu & H/Mariam, 101; Anderson and Beckerleg, 85) በማያወላዳ ሁኔታ የጫት አምራች አካባቢዎችና ገበሬዎች ህይወት ለመለወጡ አመላካች ነው፡፡

ይህ በእጅጉ እየተስፋፋ የመጣው የጫት ምርትና ንግድ በጫት አምራች አካባቢዎች በሚኖሩ ወጣቶች ላይ ያለው እንድምታ እስከምን ድረስ ነው ብዬ ስመረምር፤ በተለይ በኔ የጥናት አካባቢ የሚገኘው የኅብረተሠብ ክፍል ጫትን በክፉ ጐኑ የማይመለከትና የጫት ጥቅሙ እንጂ ጉዳቱ የማያሣሥበው እንደሆነ ማየት ችያለሁ፡፡ ከላይ በዝርዝር ለማስቀመጥ የሞከርኩት በብዙ የኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶች በጫት አዘውታሪነት ለሚከሠቱ አካላዊ፣ ስነ-ባህሪያዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች ተጋላጭ የመሆናቸውን ጉዳይ ነው፡፡ አሁን ላሰምርበት የፈለኩት ሌላው እውነት ግን በተለይ በጫት አምራች አካባቢዎች የሚኖሩና፤ ሕይወታቸው በንግዱም ሆነ በማምረቱ ሂደት ከጫት ጋር የተቆራኘ ወጣቶች ከዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ መስፋፋት በተጨባጭ ተጠቃሚ መሆናቸውን ነው፡፡ ስለዚህ፤ የቱንም ያህል አወዛጋቢ ጉዳይ ቢመስልም፣ የአብዛኞቹ በጫት ምክንያትነት የሚመጡ ጉዳቶች ዋና ገፈት ቀማሽ ወጣቱ ነው ብንልም፤ በዚሁ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ሌሎች ወጣቶች ደግሞ በጫት ኢንዱስትሪው መስፋፋት ተጠቃሚ መሆናቸውን ይህ ጥናት ያሳያል፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት የጫት ንግድ የወጣት ሥራ ነው የሚል መንደርደሪያ ኃሳብ ይዞ ይነሳል፡፡ የዚህ መሠረቱ ደግሞ በተለይ በአምራች አካባቢዎች የማንኛውም የጫት ንግድና ዝውውር ዋና አንቀሳቃሽ ሞተሮች ወጣቶች ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡ ይህንን ለማስረገጥ ደግሞ ብዙም ሳንርቅ በጫት ላይ ከተሠሩ ጥናቶች አንዳንድ ኃሳቦችን በመምዘዝ እንጀምር፡፡ አንዱ ቁልፍ ጉዳይ ጫት ከተቆረጠ በኂላ እጅግ ቢዘገይ ከ48 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ጥቅም ላይ ካልዋለ የሚጠወልግና የሚበላሽ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስለሆነም በማንኛውም ምክንያት ከተቆረጠ በኂላ ለተጠቃሚው በአስቸኳይ ካልደረሰ ይጠወልጋል፣ ይደርቃል፣ ዕጣ ፋንታውም መቃም ሳይሆን መጣል ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በቀላል ቋንቋ ኪሣራ ማለት ነው፡፡ ይህ የጫት ተፈጥሮአዊ ባህሪ ታዲያ የጫት ንግድ አንዳችም ወለም ዘለም የማያውቅ ጠንቃቃ የጊዜ አጠቃቀም የሚጠይቅ የንግድ ዘርፍ እንዲሆን ያስገድደዋል፡፡ የሚገርመው ነገር የከተማው ጫት ቃሚም ቢሆን፤ከሱስነቱ ጋር ተያይዞም ሊሆን ይችላል፣ እሱ በፈቀደው ሰዓት የሚፈልገውን ጫት በአንዱ ኪዎስክ ጉራ ብሎ ብድግ አድርጐ መሄድ እንጂ፤ እንኳን ጨርሶ መቅረትን፤ መዘግየትን እንኳን አይታገስም፡፡ ታዲያ ይህ በየቀኑ በምሳ ሠዓት አንዳችም ቀንና ሰዓት ሳያዛንፍ በየከተማው የጫት

ኪዎስኮች እንደለመለመና በትኩስነቱ የሚቀርበው ጫት የሺዎች ትጉህ ነጋዴዎች እንቅልፍና ድካም ያልበገረው የዕለት ተዕለት የሥራ ውጤት መሆኑ መታወቅ አለበት። የጫት ንግድ በጥድፊያ አነዳድና በአስከፊ የመኪና አደጋዎች የተሞላ አደገኛ የንግድ ዘርፍ እንዲሆን ያደረገውም ይኸው ነው።

ለጫት ንግድ ስኬታማነት ከልፋትና ውጣ ውረድ በተጨማሪ ጽናትና ቅልጥፍና አስፈላጊ ግብዓቶች ናቸው። የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ በሰሜን ሲዳማ በነበረው የመስክ ዝውውርና ጥናት ያገኘው ግንዛቤም ይህንን የሚያረጋግጥ ነው። በአንዳንድ የቀውስና የግርግር ወቅቶች ስንኳ ቢሆን የጫት ንግድና ዝውውር በአስገራሚ ሁኔታ ይቀጥላል። በዚያ ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታ ከተሜ የጫት ደንበኞች እንዴትም ይምጣ፤ የጫት አቅርቦት አይቋረጥባቸውም። ማኅበራዊ ቀውሶች ተፈጥረው ተኩስና የጉዳና ግርግር በሚያጋጥሙበት ወቅቶች እንኳን የጫት ኪዎስኮች የጫት መቸርቸር ስራቸውን "በቶሎ በል" ታጅበው ሲያጧጡፉት መመልከት አስገራሚ ትዕይንት ነው። የዚህ እንድምታ ደግሞ የጫት ንግድ፤ በአጨናናቂና አድካሚ ሁኔታዎች የሚሠራ ሥራ ብቻ ሳይሆን ድፍረትና ቆራጥነትን የሚጠይቁ አሥፈሪ ሁኔታዎችንም እየተጋፈጡ መሥራትን የግድ እንደሚል ነው። ለዚህም ነው የጫት ንግድን በብቃትና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመከወን የወጣት ትኩስ ጉልበትና የወጣት ድፍረት በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ግብዓት ነው የምለው።

ምንም እንኳ በጫት እርሻና ማምረት ሥራ ላይም ከተሠማሩት ገበሬዎች ውስጥ በርካታዎቹ ወጣቶች ቢሆኑም (Dechassa, 3, 11) እንደ ጫት ንግዱ ሥራ በከፍተኛ ደረጃ በወጣቶች ቁጥጥር ሥር የዋለ የለም። ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ጫትን በከፍተኛ ደረጃ የሚያወግዙ ፀሐፍትም ሳይቀሩ የጫት "ኢንዱስትሪው" የፈጠረውን የሥራ ዕድሎች ሙሉ ለሙሉ ማጣጣል የማይደፍሩት። የጫት ንግድ ሥራ ራሳቸውን በአጣዳፊና ጫና በበዛበት ሁኔታዎች መሥራትን ያለማመዱ በርካታ ሰዎችን ያቀፈ ነው። ይህ ጥናት እንደሚያሳየው ከነዚህ ሠራተኞች ውስጥ የመግዛት-የመሸጡን፣ የመከርከም - የመጠቅለሉ፣ የመጫን - የማውረዱን፣ የመደለሉን፣ ከእርሻ ቦታ እስከ ገበያ የማመላለሱን ሥራ ሁሉ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የሚያከናውኑት ወጣቶች ናቸው።

ከዚህ በላይ ደጋግሜ ያነሳሁትን የዚህን ጥናት ዓላማዎች ለማሳካት፤ በተለይ በጫት ንግድ ሥራ የወጣቶች ሚና ምን ይመስላል የሚለውን፤ ያሳይ ዘንድ ከዋና ዋና የአገሪቱ ጫት አብቃይ አካባቢዎች አንዱ በሆነው የሰሜን ሲዳማ አካባቢ በንግዱ እንቅስቃሴ የወጣቶች ሚና እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመተንተን እሞክራለሁ። መረጃዎችን የሰበሰብኩት ላለፉት ከሦስት አስርት ለበለጡ ዓመታት ለአዳማ፣ ለሞጆ፣ ለቢሾፍቱ፣ ለአዲስ አበባና ለሌሎች የአርሲና የባሌ ከተሞች ሁለት የታወቁ የጫት

ዓይነቶችን (በለጨና ወንዶ የሚባሉትን) በየዕለቱ ሲያቀርቡ ከከረሙት ሁለት ዋና የጫት ገበያዎች ነው። አንዱ ባሻ በተባለው የወንዶ ገነት ወረዳ ዋና ከተማ የሚገኘው ጠፈራ የሚባለው ገበያ ሲሆን፣ ሌላው ከሀዋሳ ከተማ በስተደቡብ 11 ኪ/ሜ ርቀት ላይ የሚገኘው የቱላ ገበያ ነው።

የወጣቶቹን ሚናና የተሳትፎ ደረጃ በደንብ ለመገንዘብ እንዲረዳ በቅድሚያ በጫት ንግዱ ፍሠት ላይ በየደረጃው ያሉ የሥራ ዘርፎችን በፈረጅ በፈርጃቸው መለየትና የሚያከናውኑትን ተግባር ከነኃላፊነቱ ማወቅ ያስፈገልገናል። በቅድሚያ በአካባቢው አጠራር "የገበሬ ነጋዴዎች" የሚባሉ ከተለያዩ የጫት ማሳዎች ምርቱን የማሰባሰብ ቀዳሚ ተግባር የሚያከናወኑ ሰዎች ያሉበት የሥራ ሂደት ይገኛል። በዚህ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል፣ ገበሬ የነበሩና ከገበሬው መካከል የወጡ ናቸው። ስለዚህም ይመስላል የገበሬ ነጋዴ የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው። ዋና የሥራ ተግባራቸውም ጫቱን ገና በማሳ ላይ እንዳለ አስፈላጊውን የዋጋ ድርድር በማድረግ መግዛት ነው። ይህ ደግሞ በየቀኑ ከአንዱ የገጠር አካባቢ ወደ ሌላው፣ አንዱ ማሳ ወደ ሌላ ማሳ መሯሯጥ ከመጠየቁም በላይ በቂ የገንዘብ አቅም፣ የማያቋርጥ የመረጃ ፍሠትን የሚያግዝ የሰው - ለሰው ግንኙነት እንዲሁም በቂ የመደራደር ችሎታን ይጠይቃል።

የነዚህን ነጋዴዎች ህይወት ቀረብ ብዬ ከማየት የተረዳሁት ነገር ቢኖር “ምን ትንፋሽ አለው” በሚባል ደረጃ ሲባትሉ የሚውሉ እንቅልፍ አልባ ሰዎች መሆናቸውን ነው። የሥራቸው ፀባይ በማያቋርጥ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የተሞላ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ የምግብ ሠዓት እንኳን የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ለልጆቻቸውንና ለአጠቃላይ ቤተሠባቸውም ቢሆን ጊዜ የላቸውም። ከነዚህ ነጋዴዎች ጋር የፈቀድኩትን ያህል ለመጨዋወትም ሆነ ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ የሚሞከር ሆኖ አላገኘሁትም። በዚሁ ምክንያት ለዚህ ጥናት የኃሳብ ግብዓት አድርጌ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችን ያገኘሁት እንደ ዮሴፍ ኤቢሦ (የ28 ዓመት ወጣት)፤ እንደ ረጋሣ ናኮ (ዕድሜው 24) እና እንደ ማቴዎስ ያቀብ (ዕድሜው 24) የመሳሰሉ ለሰው አሳቢ ደጋግ የገበሬ ነጋዴዎች ባገኟሃት የጊዜ ቀዳዳ ሁሉ ከኔ ጋር ለመጨዋወት በመፍቀዳቸው ነው። ዮሴፍ ከተለያዩ ማሳዎች ለቱላ ገበያ ጫት አቅራቢ ሲሆን ረጋሣና ማቴዎስ ደግሞ ለጠፈራ ገበያ ጫት የሚያቀርቡ ናቸው። ምንም እንኳ በቁጥርና በፐርሰንት ሊቀርብ የሚችል መረጃ ባይኖረኝም ከላይ ከጠቀስኳቸው ወጣቶች ስለግል ህይወታቸውና ስለ ሥራ ጓደኞቻቸው ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመላክተው፤ ይህ የሥራ ሂደት በአመዛኙ ዕድሜያቸው ከ29 ዓመት በታች በሆኑ ወጣቶች የሚካሄድ መሆኑን ነው።

በጠቀስኳቸው የጫት ገበያዎች ላይ ሌላው ዋና የጫት ንግዱ አካል የሆነው እንቅስቃሴ "ወኪል ነጋዴዎች" የሚባሉት የሚያከናውኑት ነው። እነዚህ ነጋዴዎች

እንደስማቸው ሁሉ ሁለትና ሦስት ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ፤ በከተሞች የሚኖሩ ጫት አከፋፋዮችንና ቸርቻሪ ነጋዴዎችን ወክለው የሚሠሩ፤ ወይንም በነሱ ጥሪት የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ብዙዎቹ "ወኪል ነጋዴዎች" የጫት ገበያዎቹ በሚገኙባቸው በባሻና በቱላ ከተሞች ከነቤተሠባቸው ወይም ለብቻቸው ቤት ተከራይተው የሚኖሩና የሚሠሩ ናቸው። በእርግጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቱላ ገበያ ላይ ከሚንቀሳቀሱት ውስጥ አኩሌታዎቹ ኑሮአቸውን በሀዋሳ ከተማ አድርገው በሥራ ሠዓታቸው ወደ ቱላ በመብረር ሥራቸውን ሲጨርሱ ደግሞ ለአዳር ወደ ሀዋሳ የሚመለሱ ሆነዋል። የ"ወኪል ነጋዴዎች" ዋና የሥራ ድርሻ በገበያዎቹ በተለመደው ሠዓት የሚቀርቡትን የጫት ጆምቦች (እስሮች) ከአምጪ "የገበሬ ነጋዴዎች" ጋር በመደራደር መግዛት፣ በተለያዩ ትንንሽ መጠኖች (ዙርባዎች) ማስጠቅለልና ለትራንስፖርት አዘጋጅቶ ማስረከብ ነው።

አብዛኛዎቹ በጠፈራ ገበያ ላይ የሚንቀሳቀሱት፤ እንዲሁም በተወሰነ ቁጥርም ቢሆን በቱላ ገበያ ላይ የሚንቀሳቀሱት ወኪል ነጋዴዎች፤ የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ የሲዳማ ወጣቶች ናቸው። የጥናቴ አካባቢ የሆነው ሰሜን ሲዳማ በእርሻ መሬት እጥረት ችግር የታወቀ ከመሆኑ አንፃር በርካታ ወጣቶች ይህን ሥራ እንደዋና ሙያቸው አጠናክረው መያዛቸው ብዙም አያስገርምም። ነገር ግን በየትውልድ ቀያቸው ይዞታ ያላቸው ደግሞ ያቺንም በተጨማሪነት እንደያዙ መቀጠል የተለመደው አኗኗር ነው። ቀደም ሲል ያነሳሁትን አንኳር ነጥብ ያጠናከረልኝ ነገር ቢኖር በጠፈራ ገበያ ላይ ከሚንቀሳቀሱት የገበሬ ነጋዴዎች ውስጥ 48 የሚሆኑትን እድሜያቸውን መዝግቤ ሁሉም ከ30 ዓመት በታች መሆናቸውን ማረጋገጤ ነው። እነዚህ 48 ነጋዴዎች በሙሉ ከ20 እስከ 30 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ይህ ደግሞ ከላይ ወጣት ማለት በየትኛው የዕድሜ ክልል የሚገኝ ነው ለሚለው ጥያቄ ከሰጠነው መልስ ጋር የሚሰማማ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በዚህ ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች አማካይ ዕድሜ ሲሰላ ደግሞ 25.8 ዓመት መሆኑን እናያለን። ስለዚህም በተለይ "ወኪል ነጋዴዎች" የተሰማሩበት የንግድ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ በወጣቶች የተሞላ ነው ማለት ይቻላል። በተጨማሪም ከነዚህ ከ48ቱ ውስጥ 39 የሚሆኑት ያገቡ፣ ልጆች የሚያሳድጉና በዚያ የሥራ ጫናቸው ላይ ከፍተኛ ተጨማሪ ማኅበራዊ ኃላፊነትንም የተሸከሙ ናቸው።

እነዚህ ወኪል ነጋዴዎች በሥራቸው የሚንቀሳቀሱ ረዳት ሠራተኞች አሏቸው። የሥራ ኃላፊነታቸው ዓይነት ብዙ እንደመሆኑ መጠን እነዚህ ረዳቶች ሁለ-ገብ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በገበያ ላይ በሚደረገው የግዢ ሂደት ለወኪል ነጋዴው ከፍተኛ እገዛ

የሚያደረጉ ከመሆኑም በላይ በአካባቢው አጠራር "ጫቲ ጠንጣሚኔ"[4] ተብለው በሚጠሩ ብዙ ቁጥር ባላቸው የጫት መከርከሚያና መጠቅለያ ቤቶች የሚከናወነውን ሥራ በከፍተኛ ኃላፊነት የሚወጡ ናቸው። በገበያ ቦታ የግብይት መጀመርን የሚያበስረው ፊሽካ ሲነፋ[5] የተሻለ ጥራት ያለውን ጫት የያዙ ነጋዴዎችን ተሻምቶ መያዝ ብቻ ሳይሆን የመደራደሪያ ዋጋ በማቅረብም ከሌሎች ተፎካካሪዎች ቅድሚያ ለመውሰድም ይሯሯጣሉ። "ወኪል ነጋዴዎች" በሥራቸው የሚያሠሯቸው ረዳቶች ቁጥር እንደ መግዛትና መላክ አቅማቸው የተለያየ ቢሆንም፤ እያንዳንዳቸው በአማካይ ከ5 - 8 ወይም ከዚያ በላይ ረዳቶችን ማሠማራት ያስፈልጋቸዋል።

እዚህ ላይ ከዋናው አርዕስተ ጉዳይ ጋር ቀጥታ ተዛማጅነት ያለው ነጥብ ቢኖር፤ በእነዚህ ትንንሽ የጫት መጠቅለያ ክፍሎች ውስጥ ሥራቸውን በፍጥነት ለማከወን ሲዋከቡ የሚያመሹት ሰዎች በሙሉ ወጣት ብቻ ሳይሆኑ ዕድሜያቸው በአሥራዎች ውስጥ የሚገኙ ልጆች መሆናቸው ነው። በየዕለቱ አመሻሻ ላይ በአሠሪያቸው "ወኪል ነጋዴ" መሪነት ከተለያዩ የጫት ማሣዎች የተሰበሰቡ የጫት ዓይነቶችን እየደባለቁ ያላንዳች ሚዛን በተመጣጣኝ ይዘትና ጥራት የመጠቅለልን ሙያ የተካኑት እነዚህ ልጆች ናቸው። እነዚህ ወጣቶች በዕድሜያቸው ለጋ ሊባሉ የሚችሉ ቢሆንም ሥራቸውን የሚያከናውኑት በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ነው። ከዚያም በላይ በየቀኑ ያለው ከሠዓት ጋር መሯሯጥና መዋከብ ጉልበትና ትዕግሥትን የሚያሚጥጥ መሆኑ እነዚህ ወጣቶች ለምን ለዚህ ሥራ እንደተመረጡ የሚያመላክት ነው።

በኔ የጥናት አካባቢ በሚካሄደው የጫት ንግድ ሌላው ወሳኝ የሥራ ሂደት ደላላ ወይም በአካበቢው አጠራር "ባለመደብ ደላላ" የሚባሉት የሚከውኑት ነው። የባለመደብ ደላሎች ዋና ሥራ ለየገበያዎቹ ጫት የሚያቀርቡ "የገበሬ ነጋዴዎችን"ና ጫት ተረካቢ "ወኪል ነጋዴዎችን" ማገናኘትና የዋጋ ድርድሩን ማሳለጥ ነው። በድርድር ሂደትም የገበሬ ነጋዴዎቹን በማሣመንና አልፎ አልፎም በመጫን ሽያጩ እንዲከናወን ይለፋሉ። የልፋታቸውን ዋጋ የሚያገኙትም ሻጭ ከሚከፍላቸው ኮሚሽን ነው። የሲዳሚኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች መሆናቸው ለሥራቸው አስፈላጊ የሆነ ጠቃሚ ማሣሪያቸው ነው። ባለመደብ የሚለው ከደላላ በፊት የተጨመረው ቅጥያ እኒህ ሰዎች በሁለቱ ዋና ዋና የጫት ገበያዎች ላይ በስማቸው የተመዘገቡና የጫት ሽያጭ ዝውውሩ የሚካሄድባቸው መደቦች እንዳሏቸው ገላጭ ነው። ለነዚህም መደቦች ዕለታዊ ኪራይ ይከፍሉባቸዋል።

---

[4]ጠፈራ ገበያና በቱላ ገበያ ዙሪያውን የተሠሩ ቁጥራቸው ከ250 - 300 የሚደርሱ ባለአንድ ክፍል ዛኒጋባ ቤቶች ይገኛሉ። በዚህ መጠሪያ የሚታወቁት እነዚህ ቤቶች ናቸው። ነጋዴዎቹ እነዚህን ቤቶች በግልም ሆነ በጋራ በመከራየት ትልልቅ ጀምቦችን በመቀነስ ትንንሽ ዙርባዎች በመከርከምና በመደበላለቅ እያዘጋጁ ይጠቀልላሉ።

[5]በጠፈራ ገበያ በፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ1990ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ጀምሮ የጫት ግብይት እንቅስቃሴው የሚጀመረው ፊሽካ ሲነፋ ብቻ ነው።

በሰሜን ሲዳማ በሚገኙ ሁለት ዋና የጫት ገበያዎች የሚሠሩ ደላሎች በማኀበር የተደራጁ ናቸው። "አክስዮን" እየተባለ የሚጠራው የጠፈራ ገበያ የደላሎች ማኀበር አራት መቶ የሚደርሱ አባላት ሲኖሩት፣ የቱላው የደላሎች ማኀበር ደግሞ አንድ መቶ የሚደርሱ አባላት አሉት። ከ400ዎቹ የጠፈራ አክስዮን አባላት 360ዎቹ በገበያው ላይ የሚገኙ መደቦች የተሰጣቸው ናቸው። የ"አክስዮኑ" መስራች አባላት ከመነሻው ለመመዝገቢያ በሚል 1,100 ብር የከፈሉ ከመሆናቸውም በላይ በየቀኑ 3 ብር (በሳምንት 21 ብር) ለሚጠቀሙበት የመደብ ኪራይ ይከፍላሉ። ወደ ቱላ ስንመጣ ደግሞ የደላላው ማኀበር አባለት በጫት ገበያው ለሚጠቀሙበት መደብ የቀን ኪራይ 10 ብር ለከተማው አስተዳደር ይከፍላሉ። ይህ ተመን አኔ ለመስክ ጥናት ቱላ በነበርኩበት በ2005 ዓ.ም. የነበረ ነው። በአጠቃላይ ማየት የሚቻለው ግን እነዚህ ማኀበራት የአካባቢው ወጣቶች ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱባቸው መሆናቸውንና በእነዚህ ማኀበራት ካልተደራጁ መደብ ማግኘት የማይቻል የመሆኑ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ ሥራውን ከሌሎች የውጪ ወገኖች (intruders) የመጠበቂያ ስትራቴጂ መስሎ ይታየኛል። ዋናው መደምደሚያዬ የሚሆነው ግን ምንም እንኳ እንደሌሎቹ ከላይ እንዳየናቸው የሥራ መስኮች በቁጥር የታጀበ መረጃ ማቅረብ ባይቻለኝም እንደ ራሴ የመስክ ምልከታ ግን በዚህኛውም የጫት ንግዱ ክፍል ቢሆን የወጣቶች የአንቀሳቃሽነት ሚና ከሌሎች የንግዱ ዘርፎች ባልተናነሰ ጐልቶ ይታያል።

በጫት ፅሑፎችም ላይ በሰፊው እንደሚታየው የጫት ንግድ የታክስ ገቢ ለአካባቢና ለክልል መንግሥታት የሚያስገኘው ወፍራም ገቢ በየጊዜው እየጨመረ እንደሆነ ይታወቃል[6]። የአካባቢው ወጣቶች በማኀበር ተደራጅተው እዚህ ሥራ ውስጥ መንቀሳቀሳቸውን በተለይ ከፀጥታ አንፃርና የገበያውንም ሠላማዊነት ከማስጠበቅ አኳያ የአካባቢው የአስተዳደር አካላትም በበጐ ጐኑ የሚያዩት ነው። ከሁሉም በላይ ግን አካባቢው ከፍተኛ የሆነ የእርሻ መሬት እጥረት ያለበት ከመሆኑ አንፃር እነዚህ ጫት ያስገኛቸው የሥራ እድሎች በመሬት እጦትና በሥራ እጦት ምክንያት በአካባቢው ወጣቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን አስከፊ ችግር መቅረፉን መካድ አይቻልም። አንድ ስማቸውን የማልጠቅሰው የወረዳ ባለሥልጣን "ጫት የኛ ኮብል ስቶን" ነው በማለት ገልፀውታል። በአሁኑ ሠዓት በብዙ የኢትዮጵያ ከተሞች በሚከናወኑ የኮብል ስቶን (የድንጋይ መንገድ ማንጠፍ) ሥራዎች በርካታ የቀድሞ ሥራ አጥ ወጣቶች መታቀፋቸው ካበረከተው ማኀበራዊ አስተዋጽኦ ጋር ማወዳደራቸው ነው።

በጫት ንግዱ ሠንሠለት ላይ ሌላው ቁልፍ የሥራ ክፍል የጫት ነጋዴው ማኀበረሠብ "ኮንትራክተር" እያለ የሚጠራው ነጋዴ ግለሠብ የሚመራው ነው። የኮንትራክተሩ ዋና

---

[6]ምን ያህል ወፍራም? የሚለውን ጥያቄ ሊመልሱ የሚችሉ የአንዳንድ የጫት አምራች ወረዳዎች የቀናትና የወራት የገቢ መረጃዎች በጄ የሚገኙ ቢሆንም በዚህ ጥናት ላይ ለማቀነቅነው ዋና ኃሳብ ብዙም አስፈላጊ ስላልሆኑ ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልገኝም።

ሥራ ግዢያቸው ተፈጽሞ በአግባቡ ተጠቅልለው የተዘጋጁ የጫት ጀምቦችን ያላንዳች መስተጓጎል በመደበኛነት ወደ ተለያዩ ተቀባይ ከተሞች ማጓጓዝ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ላኪ ነጋዴዎችን በመወከል የሁሉንም በመኪናው ላይ የተጫኑ የጫት ጀምቦችን የቀረጥ ክፍያ (ነጋዴዎቹ ጫቱን መላክ እንጂ አብረው የማይጓጓዙ በመሆኑ) በየቀረጥ ኬላው ሁሉ በተመኑ መሠረት ይከፍላል፡፡ ይህንንም ወጪውን በኋላ ከሌላው የአገልግሎት ክፍያ ጋር በመደመር ከተረካቢ ነጋዴዎቹ የሚቀበል ይሆናል፡፡ ስለሌሎቹ የጫት ንግዱ አብይ የሥራ ክፍሎች ዝርዝር ማብራሪያ ሰጥቼ "የኮንትራክተሩን" ቁልፍ ሚና ሳልጠቅስ ማለፍ ስለሌለብኝ እንጂ የኮንትራክተርነት ሥራም በአብዛኛው በወጣቶች የተያዘ ነው ለማለት ፈልጌ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ፡፡ በእርግጥ ስለዚህ የሥራ ክፍል ምንም ሳይሰስት ጥልቅ መረጃ የሰጠኝ ዋናው አስረጂዬ ዘርፉ ሰቀሎ በአጋጣሚ በወጣትነት ዕድሜ ክልል የሚገኝ ቢሆንም ብዙዎቹ ኮንትራክተሮች እንደእርሱ ወጣት እንዳልሆኑ አረጋግጫለሁ፡፡ ሥራው የሚጠይቃቸው የጥሪት አቅምና ሌሎች መጋዘንና ማጓጓዣ መኪናን የመሳሰሉ አስፈላጊ ንብረቶች ለአንድ ወጣት በቀላሉ የማይገኙ ከመሆናቸው አንፃር ኮንትራክተርነት ለወጣቶች የማይደፈር መስክ መሆኑ አያስገርምም፡፡

ሌላኛው ቁልፍ ሥራ ደግሞ የጢሾ እና የሆኪቶ አቅርቦት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች፤ የጫት ጀምቦቹ ከገበያ ከተገዙ በኋላ ለጉዞ መኪና ላይ ከመጫናቸው በፊት ለሚካሄዱ የመደበላለቅ፣ የእንደገና ጥቅለላና የዙርባዎች ዝግጅት ሥራ እጅግ አስፈላጊ ግብዓቶች ናቸው፡፡ ጢሾ የሚባለው ከላይ ለተጠቀሰው የሥራ ክንውን በማሠሪያ ገመድነት የሚያገለግል የእንሠት የግንዱን የላይኛውን ሽፋን በመተልተል የሚገኝ ቃጫ መሳይ ድር ነው፡፡ ሆኪቶ ደግሞ የእንሠት ቅጠሉ ሲሆን በጫት ጥቅለላው ሥራ ላይ ለመሸፈኛነት/መጠቅለያነት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ከሁሉም የጫት ገበያዎች በጣም ትልቁ ግብይት በሚደረግበት በጠፈራ ገበያ የእነዚህ አስፈላጊ ቁሦች አቅርቦት መቶ በመቶ የሚካሄደው በሴቶች ብቻ ነው፡፡ በገበያው ሠሜናዊ ምዕራብ ጠርዝ ላይ በሚደረገው ግብይት እኒህን ቁሦች ወደ ሚፈለጉበት መጠቅለያ ቦታዎች ገዝቶ ለመውሠድ ከሚመጡ ወጣት ልጆች በስተቀር ወንዶች አይታዩም፡፡

ከአርዕስተ ጉዳያችን ጋር ተዛማጅነት ያለውና እዚህ ጋ መነሳት ያለበት ሌላው ዋናው ጉዳይ፤ በዚህ የጢሾ ገበያ ላይ ካየኋቸው ሴቶች ውስጥ የሦስቱ ብቻ ዕድሜያቸው ከ30 ዘለል ከማለቱ በስተቀር ሌሎቹ ዕድሜያቸው በሃያዎቹ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ከኋለኞቹ ውስጥ ዕድሜያቸው በአሥራዎቹ ውስጥ የሚገኝ ወጣት ልጃገረዶችም አሉባቸው፡፡ በ2005 ዓ.ም. አጋማሽ በአካባቢው የመስክ ጥናት በማደርግበት በአንዱ ቀን በገበያው የተገኙትን የጢሾና የሆኪቶ ሻጭ ሴቶችን ዕድሜ መዝግቤ መያዝ በመቻሌ ከዚህ በታች ላቀረብኩት ትንተና ተጠቅሜበታለሁ፡፡ በዕለቱ በማስታወሻ ደብተሬ ከመዘገብኳቸው 33 ሴቶች ውስጥ 17ቱ ጢሾ ሻጮች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 16ቱ

ደግሞ ሆኪቶ አቅራቢያዎች ናቸው። ከነዚህ ሁሉ ሴቶች የአንደኛዋ ብቻ ዕድሜያቸው 40 የደረሰ ሲሆን፤ የሌሎቹ ተሳታፊዎች ዕድሜ ግን በ14 እና በ35 መካከል የሚገኝ ነው። በዚህኛው ዘርፍ የተሠማሩት ሴቶች መካከለኛ ዕድሜ ሲሰላ 19.21 ዓመት በመሆኑ ምክንያት የጫት ንግድ ሥራው በተለይ ለወጣቶች (ይሄኛው እንዲያውም ለሴቶች መሆኑን ያሰምሯል) ከፍተኛ የሥራ ዕድል ፈጥሯል የሚለውን ኃሳብ የሚያዳብር ነው እላለሁ[7]።

በጫት ንግዱ ሠንሠለት ላይ ወጣቶች መሪ ተሳትፎ የሚያደርጉባቸው ሌሎች የሥራ ዘርፎች የጫት ጫኝ አይሱዙ አሽከርካሪነትና ረዳትነት፤ እንዲሁም ጫት ጫኝነትና አውራጅነት ናቸው። የጫት መኪና አሽከርካሪዎች "ከኮንትራክተሩ" ጋር በመሆን በየቀኑ በቋሚነት ከየገበያዎቹ ላይ የሚነሳውን የጫት ጭነት ወደ ተለያዩ ተቀባይ ከተሞች የሚያመላልሱ ናቸው። በተለይ የአዲስ አበባ - ሻሸመኔ መንገድ በተሻሻለ ዘመናዊ አስፋልት መንገድነት ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ከ1994 ዓ.ም. በፊት በነበሩት ዓመታት የአሽከርካሪው ሚና እጅግ በጣም ወሳኝ ነበር። በጫት ንግድ ሥራ ሠዓት ወይም ጊዜ ቁልፍ ቦታ አለው። በተፈለገው ሠዓት ያልደረሰ ጫት ካልመጣ ይቆጠራል። ነጋዴውንም ከባድ ዋጋ ያስከፍላል። ሁሉም ነጋዴዎች፤ እንደከተሞቹ ርቀት ሠዓቱ ይለያይ እንጂ ከምሳ በፊት መድረስ ይፈልጋሉ። ከምሳ በኋላማ የመቃሚያው ሰዓት ነው! ስለዚህም ነበር በወቅቱ በፍጥነት አሽከርክረው በፍጥነት የሚደርሱ አሽከርካሪዎች እንደ ጀግና ይወደሱ የነበረው። አሁን ያ ቀርቷል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም መንገዱም ተሻሽሏል፤ ንግዱም የተሻለ ሥርዓት በመያዙ የመነሻና የመድረሻ ሠዓቱ ለሁሉም ተመሳሳይ ነው።

ለማንኛውም ከጠፈራ ገበያ አዲስ አበባን ጨምሮ ወደተለያዩ ከተሞች ጫት የሚጭኑ 8 የአይሱዙ መኪናዎች ሹፌሮችን ከነ ረዳቶቻቸው ጭምር ስምና ዕድሜያቸውን መዝግቤ ለማየት ሞክሬአለሁ። ታዲያ ይህ ዝርዝር ያሳየኝ ነገር ቢኖር በነዚህ ከጫት ንግዱ ጋር በተያያዙ የሥራ ዘርፎችም ቢሆን ወጣቶች አንቀሳቃሽ ሞተር መሆናቸውን ነው። ለአብነትም የአሽከርካሪዎቹ እድሜ ከ24 - 35 ባለው ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን አማካይ ዕድሜያቸው ሲሰላ ደግሞ 28.13 ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የረዳቶቻቸው ዕድሜ ደግሞ በ20 እና በ27 ዓመት መካከል የሚገኝ ሲሆን አማካዩ ዕድሜ ደግሞ 23.38 ነው።

[7] በቱላ ገበያ ደግሞ ጢሾና ሆኪቶ ለጫት ነጋዴዎች የሚያቀርቡት በዕድሜያቸው ወጣት የሆኑ ወንዶች ናቸው። ስድስት የሚሆኑትን ስምና ዕድሜያቸውን መዝግቤ ሳየው የሁሉም እድሜ ከ23 ዓመት በታች መሆኑን ተመልክቻለሁ። በእርግጥ እንሠቱ ከሚበቅልበት ቦታ በመሰብሰብ ወደ ከተማ ተሸክመው የሚያመጡት ሴቶች ናቸው። ነገር ግን እነዚህ አቅራቢዎች ተሸክመው ያመጡትን ጢሾና ሆኪቶ፤ በቀጥታ ከጫት ነጋዴዎቹ ጋር ላይገናኙ፤ ለከተሜዎቹ ጢሾና ሆኪቶ ነጋዴዎች አስረክበው ይመለሳሉ።

**ማጠቃለያ**

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2007 ዓ.ም. የወጣው የተባበሩት መንግሥታት ዘገባ እንደሚያሳየው፤ ከሰው ልጆች ሁሉ እንደ ወጣቶች ሥራ አጥነት ለሚያስከትላቸው ችግሮች የተጋለጠ የለም:: ይኸው ሪፖርት እንደሚገልጸው "ሥራ አለማግኘትና ሥራ-ፈት መሆን የዓለም ወጣቶች ችግር እየሆነ መጥቷል:: በመላው ዓለም የሚገኙ ወጣቶች የሥራ ገበያውን ሠብሮ መግባት ተስኗቸዋል:: በዓለም ላይ ለሥራ ዝግጁ ከሆነው ኃይል ውስጥ 25 ከመቶው ወጣት ቢሆንም፤ ከዓለም ሥራ አጦች ውስጥ ግን 43.7 በመቶ የሚደርሱት ወጣቶች ናቸው:: ይህም ማለት ከሁለት ሥራ አጥ ሰዎች አንዱ ዕድሜው ከ15 - 24 የሚገኝ ወጣት ነው ማለት ነው" (UN World Youth Report, 2007፡ 238):: የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያ ራፐብሊክ የወጣቶች ፖሊሲ ሠነድ 44 በመቶ የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ በመጨረሻ ድህነት እንደሚኖር አስቀምጦ፤ በወጣቶች መሀከል ተንሠራፍቶ የሚታየው ሥራ አጥነት ደግሞ ዋናው የዚህ ድህነት ተጠቂ ወጣቱ መሆኑን የሚያመላክት ነው:: ይኸው ዶኩሜንት ብዙ ቁጥር ያላቸው ወጣቶችን በማንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ (informal economy) በገጠር ወጣቶች ላይ ሊገን የሚችለውን ሥራ አጥነት በመቀነስ ከገጠር ወደ ከተማ የመፍለስን ችግር እንደሚገታ ይጠቁማል (Ministry of Youth, Sports & Culture, 2004: 11-12) :: ይህ አጠቃላይ ሁኔታ ደግሞ ከዚህ በቀደሙት ገጾች ላይ ካነሳሁት የእርሻ መሬት እጥረት ችግርና፤ ይኸውም ችግር ከዓመት ዓመት እየተባባሰ የሚሄድ ከመሆኑ ጋር አያይዘን ማየቱ የተሻለ ግንዛቤ እንድንጨብጥ ይረዳል::

በአገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሠፍኖ የሚገኘውን አስፈሪ የሥራ አጥነት ችግርና፤ ጫት ለሲዳማ ወጣቶች የፈጠረውን የሥራ እድል (በሌሎችም ጫት አብቃይ አካባቢዎች ሁኔታው ተመሳሳይ እንደሚሆን መገመት ይቻላል) ስናስተያየውና ጫት ነክ አገራዊ ፖሊሲን ስናስብ አሁን በሠፊው ከሚካሄደው ፀረ-ጫት ነቀፋና ዘመቻ በዘለለ ማየት የሚገቡን ነገሮች እንዳሉ ያነቃናል:: በዚህ ጥናት በዝርዝር እንደተብራራው በአንድ በኩል የጫት ንግድ በአምራች አካባቢዎች ለሚገኙ በርካታ ወጣቶች የህልውናቸው ዋና መሠረት ሲሆን፣ በሌላ በኩል በከተሞች የሚገኙ ወጣቶች ደግሞ የተለያዩ ጫት የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ሠለባ የመሆናቸው ጉዳይ እንዲህ በዋዛ የሚታረቅ አይመስልም:: በዛ ላይ እንደ አገርና እንደ መንግሥት በጫት ላይ ጥርት ያለ አቋምና ፖሊሲ የለንም:: ከጥቂት ወራት በፊት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የንግድ ሚኒስትር ከተወካዮች ምክር ቤት አባል ጫትን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ ሪፖርተር ጋዜጣ በግንቦት 24/2006 ዓ.ም ዕትሙ እንደሚከተለው አስፍሮታል፤

> ጫትን ለማበረታት የምንሠራው የለም። ለግብርና ምርታችን የኤክስቴንሽን ሠራተኞች መድበን እናበረታታለን። የማዳበሪያና ሌሎች ግብዓቶችንም እናቀርባለን። ምርጥ ዘርም እናቀርባለን። በጫት ላይ ግን የምንሠራው ምንም ድጋፍ የለም። ግን በራሱ ጉልበት እራሱ እየቀጠለ ነው። በራሱ ጉልበት ሲቀጥል እኛ እንደ ንግድ ሚኒስቴር እየሸጥን ተጠቃሚ መሆን አለብን። እየሸጥንም ነው። ስለዚህ መንግስት አያበረታታም አያዳክምም። ለማዳከምም ብሎ አትሽጡ ብሎ ነቅሎ ከማሳ ያቃጠለበትም አጋጣሚ የለም ስለዚህ በዚህ ጉዳይ <u>ለጊዜው ዝም ነው</u> (መስመር የተጨመረ)። አናበረታታም። የጫት ተጠቃሚ የህብረሰብ ክፍል ስላለ ሸጠን መጠቀም ስላለብን እየሸጥን ነው። ገቢው ቀላል አይደለም። በዓመት እስከ 260 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይገኛል። ትልቅ አቅም ነው እንሸጣለን።

ይኸው የነጠረ ፖሊሲ አለመኖር ከላይ ብቻ ሳይሆን በወረዳ ደረጃም የሚንፀባረቅ ነው። ለምሳሌ የወንዶ ገነት ወረዳ የግብርና ገጠር ልማት ጽ/ቤት በ2002 ያወጣው የ5 ዓመት ተሳትፎዊ የልማት እቅድ "ዓላማ" በሚል አርዕስት ስር የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል። "… በአርሦ አደሩ ተቀባይነት ያላቸውን የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማሰራጨት ለአርሶ አደሩና ለግብርና ኢንቨስተሮች የሙያ፤ የምክርና ሥልጠና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት አርሦ አደሩን በኅብረት ሥራና በሌሎች ማኀበራት እንዲደራጅ በማድረግ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶች ላይ በማተኮርና (መስመር የተጨመረ) ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር።" ምንም እንኳ ጫት በገበያ ተፈላጊ የሆነ የግብርና ምርት ቢሆንም፤ ከላይ ሚኒስትሩም እንደገለጹት፤ ገበሬዎች የብድርና የኤክስቴንሽን ድጋፍም ሆነ ሙያዊ ምክርና ሥልጠና አያገኙም። ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ! እስከመቼ "የዝም ፖሊሲው" ይቀጥላል? አንደእኔ ችግሩ ካለ በዝምታ መቀጠል የሚያዛልቅ አይመስለኝም። "በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም" እንደሚባለው የሀገራችን ብሂል! ታዲያ ምን ይሻላል? የሚሻለውማ አንድ ነጥሮ የወጣ ፖሊሲ ላይ እስክንደርስ ችግሩን በመጋፈጥ ከጫት ተጉጂዎች የሆኑትንም ከጫት ተጠቃሚዎች የሆኑትንም ኃሳብ ባስተናገደ መልኩ ጠንከር ያሉ ክርክሮችንና ውይይቶችን ማድረግ መቀጠል ይመስለኛል።

## ዋቢ መጽሃፍት

Amare Getahun and Krikorian A.D. (1973) "*Chat: Coffee's Rival From Hara, Ethiopia I. Botany, Cultivation and Use*." In **Economic Botany**. 27, no.4 : 353-389.

Anderson, David and Beckerleg (2007). *The khat Controversy: Stimulating the Debate on Drugs*. Oxford: Berg.

Bhalla, Nita. "Awaday Eastern Ethiopia." Accessed 12 June 2010, from available at http://news.bbc.co.uk/1/hi.html .

Cassanelli, Lee. "Qat: Changes in the Production and Consumption of a Quasi Legal Commodity in North East Africa." In The social life of Things: Commodities in Cultural Perespective, edited by Appanduria, Arjun, 236-257. Cambridge: Cambridge University Press, 1986,

Dechassa Lemessa (2001) "Khat (Catha Edulis): Botany, Distribution, Cultivation Usage and Economics." UN- Emergency Unit for Ethiopia. (Addis Ababa, June 2001).

Eshetu Mulatu and Habtemariam Kassa. "Evolution of Small Holder Mixed Farming Systems in the Harar Highlands of Ethiopia: The Shift Towards Trees and Shrubs." Journal of Sustainable Agriculture. 18, no. 4 (2001): 81-109.

Fitzgerald, John. "Khat: a Literature Review." A Report of Center for Ethnicity, Culture and Health, 5 March 2009,

Ezekiel Gebissa. Leaf of Allah :Khat and Agricultural Transformation in Hararge Ethiopia !875-1991. London: James Currey, 2004.

Ezekiel Gebissa." Scourge of Life or an Economic Lifeline? Public Discourse on Khat (Catha edulis) in Ethiopia." Subsistence Use and Misuse. Vol. 43 (2008): 784- 802.

Green, Reginald Herbold. "Khat and the Realities of Somalis: Historic, Social, Household, Political and Economic." Review of African Political Economy No. 79 (1999) : 33-49.

Goldsmith, Paul. "The Production and Marketing of Miraa in Kenya." In Satisfying Africa‟s Food Needs: Food Production and Commercialization in African Agriculture, edited by Ronald Cohen, 121-152. London: Lynne Rienner Publishers, 1988.

Kennedy, John G. The Flower of Paradise: The Institutionalized Use of the Drug Qat in North Yemen. Dordrecht: D.Reidel Publishing, 1987.

Kingele, Ralph. "Hararghe‟s Farmers on the Cross-roads Between Subsistence and Cash Economy" Unpublished UN document by UN Emergency Unit for Ethiopia (September, 1998).

## ጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢዎች

**አቶ አበራ ደገፋ፡-** አቶ አበራ ደገፋ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምሕርት ቤት የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በማስተማርና ምርምር ሥራ ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ። አቶ አበራ በአሁኑ ጊዜ በሶሻል ወርክ የትምህርት ዘርፍ የዶክተሬት ትምርታቸውን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

**ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት፡-** ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት የማስተርስና ዶክተሬት ትምህርታቸውን እንግሊዝ አገር ከሚገኘው የማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ያገኙ ሲሆን ፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለ16 ዓመታት በመምህርነት አገልግለዋል። በረጂም የአገልግሎት ዘመናቸው አያሌ የምርምር ሥራዎችን ያሳተሙ ሲሆን ሠፈራና የሰዎች ፍልሠት፣ የተፈጥሮ ኃብት እንክብካቤ፣ ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች፣ ዕድሮችና ሌሎች ማኅበራዊ ድርጅቶች ከጥናቶቻቸው ርዕሶች ማካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ያንግ ላይቭስ በተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ ኃላፊና ተመራማሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

**ዶ/ር አስናቀ ከፋለ፡-** ዶ/ር አስናቀ ከፋለ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪያቸው እንዲሁም ጃፓን አገር ከሚገኘው ኢንተርናሽናል ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ጃፓን በዓለም አቀፍ ግንኙነት የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በመቀጠል ኔዘርላንድ ከሚገኘው የላይደን ኒቨርሲቲ የዶክተሬት ዲግሪቸው ተቀብለዋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምህርት ዘርፍ መምህር በመሆን በማገልገል ላይ ከመሆናቸው በተጨማሪ የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የጥናትና ሕትመት ዳይሬክተር ሆነው በመስራት ላይ ይገኛሉ።

**ጋዜጠኛ ገነነ መኩሪያ፡-** ጋዜጠኛ ገነነ መኩሪያ ከ1978 ጀምሮ በአዲስ ዘመንና በቀድሞው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦችና በኢትዮጵያ ሬድዮ በፍሪላንስ ጋዜጠኝነት ያገለገሉ ሲሆን፤ ከ1985 ጀምሮ ‹‹ሊብሮ የተሠኘው የስፖርት ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበሩ። አሁንም በሬድዮ ጋዜጠኝነትና በግላቸው የኢትዮጵያን ስፖርት በሚመለከት ጥናትና ምርምር በማድረግ ሥራ ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ።

**ዶ/ር ጌጤ ፀጋዬ፡-** ዶ/ር ጌጤ ፀጋዬ ሕንድ አገር ከሚገኘው የደልሂ ዩኒቨርሲቲ በስነ-ልቦና (Psychology) የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ካገኙ በኂላ በዚሁ የትምህርት ዘርፍ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከግላስኮ ዩኒቨርስቲ (ስኮትላንድ) ተቀብለዋል። ከዚያም ወደ ደልሂ ዩኒቨርሲቲ በመመለስ የዶክተሬት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ደ/ር ጌጤ በአዋሳ ኒቨርሲቲ

በመማርና ምርምር ሥራ ላይ የተሠማሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የዩኒቨርሲቲው የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤ/ት ዲን ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

**ዶ/ር ግርማ ነጋሽ፡-** ዶ/ር ግርማ ነጋሽ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ የመጀመሪያ፣ የማስተርስና የዶክተሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ ዶ/ር ግርማ በዲላ ኒቨርሲቲ በመምሕርነትና በተመራማሪነት ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ኒቨርሲቲ የታሪክ የትምህርት ክፍል በመምህርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ የሕብረተሠብ ግንኙነት (social relations)፣ የገጠር የእርሻ ምርት ለውጥ፣ ጫትና ተጓዳኝ ተጽዕኖዎቹ ከዋና ዋና የምርምር ዘርፎቻቸው ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

**ወ/ት ማርታ ክብሩ፡-** ወ/ት ማርታ ክብሩ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1998 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ያገኙ ሲሆን፣ በመቀጠልም ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ በ2000 ዓ.ም በኢኮኖሚክስ ትምህርት በተለይ በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና (Economic Policy Analysis) የማስተርስ ዲግሪ ተቀብለዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል በአስተማሪነትና ተመራማሪነት በመስራታቸው ላይ ከመሆናቸው በተጨማሪ የዶክተሬት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

**ዶ/ር ዘሪሁን መሐመድ፡-** ዶ/ር ዘሪሁን መሐመድ በታሪክ መጀመሪያ ዲግሪያቸውን፤ በሶሻል አንትሮፖሎጂ የማስተርስ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያገኙ ሲሆን ከዚያም እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የዶክተሬት ዲግሪያቸውን በሂዩማን ጂኦግራፊ ወስደዋል፡፡ ዶ/ር ዘሪሁን ባለፉት ሶስት አስርተ-ዓመታት መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች፤ እንዲሁም በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ኃብት ኮሌጅ መምህርነት ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ተመራማሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

ወጣቱ ለውጥን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ብሩህ አዕምሮ ባለቤት በመሆኑ አገር ገንቢ፣ ፈጣሪና ለውጥ አምጪ ኃይል እንደሆነ ይታመናል። ወጣቱ የማይሳተፍበት የኢኮኖሚ መስክ፣ የማኅበራዊ ኑሮ ዘርፍና የፖለቲካ እንቅስቃሴ የለም ማለት ይቻላል። ባለፉት አያሌ አስርተ ዓመታት በአገራችን የተካሄዱት ለውጦች ውስጥ ወጣቱ ደማቅ አሻራውን አሳርፎ አልፏል። በአሁኑ ጊዜ ወጣቱ ከጠቅላላው በአገራችን ህዝብ የ30 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን ምንም እንኳን ይህ የህብረተሠብ ክፍል የወጣበትን ማኅበረሠብ ዕሴት፤ አመለካከት፣ ራዕይ፣ መልካም አጋጣሚዎችና ችግሮች ከሌሎች የህብረተሠብ ክፍሎች ጋር የሚጋራ ቢሆንም በሚገኝበት የዕድሜ ክልል ሳቢያ የተለዩ ተግዳሮቶችና ችግሮች ይጋረጡበታል።

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ይህንን ዕሳቤ ግምት ውስጥ በማስገባት ወጣቱ በአገር ልማትና ግንባታ ሂደት ውስጥ የሚኖረውን ተሳትፎ ለማሳደግና ከሚገኘው ውጤትም የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ወጣትና ልማት በኢትዮጵያ በሚል መሪ ርዕስ ሥር በተለያዩ ርዕሠ-ጉዳዮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ ሕዝባዊ ውይይት ሲያካሂድ ቆይቷል። በሕዝባዊ ውይይቶቹ ላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች ዳብረውና አርትዖት ተደርጎባቸው እነሆ ቀርበዋል። ሕዝባዊ ውይይቶቹና ጥናታዊ ጽሁፎቹ መረጃ ከመስጠታቸው ባሻገር በመስኩ ቀጣይ ጥናቶችና በመረጃ ላይ የተመሠረቱ ውይይቶችን ያበረታታሉ የሚል ዕምነት አለን።